# እጅግ በጣም ጥሩ ትምህርት ቤት

የቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤቶች






**ጁላይ 1, 2024**

# የተማሪ ምግባር እና ተግሣጽ፣ መብቶች እና ኃላፊነቶች

**www.cherrycreekschools.org**

**የቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤቶች ድስትሪክት፡ ተልዕኮ የእያንዳንዱ ተማሪ እንዲያስብ/እንዲታስብ፣ እንዲማር/እንዲትማር፣ እንዲከናወንለት/እንዲከናወንላትና ለሌላው ደንታ ያለው/ያላት ዜጋ እንዲሆን/እንዲትሆን ማበረታታት ነው።**

ይህ ተልዕኮ ሊሳካ የሚችለው ደኅንነታቸው የተጠበቀና ሥርዓት ባላቸው ትምህርት ቤቶችና የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ ብቻ ነው።ውጤታማ የሆኑ ትምህርት ቤቶች አሳማኝ፤ለሁሉም ግልጽና ጽኑ የሆኑ የምግባር ደንቦችና መመዘኛዎች አሏቸው። የእንደነዚህ ያሉ ደንቦች ጠቀሜታ ለጠቅላላ የመማሪያ አከባቢ ብቻ ሳይሆን ተማሪዎች ኀላፊነት እንዲሰማቸው ለማስተማርም ጭምር ይረዳሉ። የቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤቶች ድስትሪክት የትምህርት ቦርድ በድስትሪክቱ ውስጥ ላሉት ለሁሉም ተማሪዎች ደኅንነት ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል። ያንን ደኅንነት ለማረጋገጥ የትምህርት ቦርድ ደኅንነትንና ሥርዓትን አስመልክቶ ፖሊሲዎችን አውጥቷል። የዚህ ህትመት ዓላማ ወላጆችና ተማሪዎች እነዚያን የትምህርት ቦርድ ፖሊሲዎችንና የተማሪ ኀላፊነቶችን ግልባጭ በቀላሉ እንዲያገኙ ነው።

**ማስታወሻ፡ የዲስትሪክት ፖሊሲዎች በተሰጠው የትምህርት ዘመን ውስጥ ሊቀየሩ ይችላሉ። የማንኛውም የመተዳደሪያ ደንብ ሙሉ ህትመት ከትምህርት ቤቱ ኃላፊ ወይም ቀጥሎ የተሰጠውን የድስትሪክቱ የአስተዳደር ቢሮ በመጠየቅ ማግኘት ይቻላል፤**

የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት ቁ. 5
**<u>አድራሻ፤</u>** Cherry Creek School District No.5
4700 South Yosemite Street
Greenwood Village, Colorado 80111

የድስትሪክቱን ፖሊሲዎች ግልባጭ ድረ ገጹ ከሆነው ከ'www.cherrycreekschools.org' ማግኘት ይቻላል።

**ቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት ቁ. 5 በጎሳ፣ በቀለም፣ በብሄር፣ በጾታ፣በጾታዊ አመለካከት፣ በእድሜ ወይም በአካል ጉዳተኝነት ምክንያት ባሉት ፕሮግራሞች መግቢያና መገልገያ ውስጥና በማንኛውም ዓይነት ተግባራቶች ውስጥ አያዳላም። የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃት ማነስም በድስትሪክቱ ተግባራትና ፕሮግራሞች ውስጥ ከመሳተፍ አያስተጓጉልም። የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት ቁ. 5 በሰራተኞች ቅጥር ሂደት ውስጥም አያዳላም።**

ይህ መመሪያ የተዘጋጀው የ1964ቱ 'Title VI' የሚባል የዜጎች መብቶች አዋጅ፣ የ1973ቱ የመልሶ መቋቋም አዋጅ ክፍል 504፣ የ1972ቱ 'Title VX' የሚባል የትምህርት መሻሻሎች፣ የ1975ቱ የእድሜ አድልዎ አዋጅ፣ እንደዚሁም የ1990 የአሜሪካ አካል ጉዳተኛ ዜጎች አዋጅ መስፈርት መሰረት ነው። ጥያቄዎች ወይም አቤቱታዎች ካለዎት፣ እንደዚሁም እነዚህን የተሰጡት ህጎች በተመለከተ ለበለጠ የድስትሪክቱ የአቤቱታ ቢሮ ተጠሪ የሆነችውን መረጃ **እስቴፈኒ ዴቭስን(Stephanie Davies)ያነጋግሩ። የትምህርት ቢሮ አድራሻና የስልክ ቁጥር እንደሚከተለው ነው፤ 'Educational Services Center, 4700 S. Yosemite Street, Greenwood Village, Co 80111 (303)773-1184'፣ ወይም ደግሞ በአሜሪካን አገር አቀፍ ትምህርት ቢሮ፣ የዜጎች መብቶች ክፍል፣ ክልል VIII፣ የፌዴራል ቢሮ ህንጻ 1244 የሆነውን በሚከተለው አድራሻ በቀጥታ ማነጋገር ይቻላል፤ 'U.S. Department of Education, Office for Civil Rights, Region VIII, Federal Office Building 1244 North Speer Blvd., Suite # 310, Denver, Co 80204' ።**

**እስቴፈኒ ዴቭስ (Stephanie Davies)**፣ የድስትሪክት የአቤቱታ ተጠሪ (District Compliance Officer)
<u>አድራሻ፤</u> 4700 South Yosemite Street
Greenwood Village, Colorado 80111
<u>ስልክ፤</u> 720-554-4471

Megan Lonergan,የድስትሪክት የአቤቱታ ተጠሪ (District Compliance Officer)
አድራሻ፤ 4700 South Yosemite Street
Greenwood Village, Colorado 80111
ስልክ፤ 720-554-4415

ዲስትሪክቱ ለወላጆች እና ቤተሰቦች የቋንቋ እርዳታ አገልግሎቶች አሉት። እንደዚህ አይነት አገልግሎቶችን ለመጠየቅ የትርጓሜ እና የትርጉም ቢሮ ድጋፍ በ 720-554-5046 ጋ ይደውሉ

## ማውጫ

**መብቶችንና ኀላፊነቶችን ለወላጅ ማሳወቅ (Parent Notification of Rights & Responsibilities)**


FERPA በየቤተሰብ የትምህርት መብትና የግል ምስጢር መጠበቅ አዋጅ ሥር ያሉትን መብቶች ማሳወቅ ....6
PPRA የተሻሻለውን የተማሪ መብቶች መጠበቅ ሥር ያሉትን መብቶች ማሳወቅ....7
C.R.S.21-1-124 የወሲብ ጥቃት መረጃን አስመልክቶ ለወላጆች የተሰጠ ማስገነዘቢያ....8
JICA-E የተማሪን ምግባር ለመቆጣጠር የቪዲዮ ካሜራን መጠቀም አስመልክቶ ለወላጆችና ለተማሪዎች የተሰጠ ማስገነዘቢያ....8
JLDAC የተማሪዎች የማጣሪያ ፈተና አስመልክቶ ለወላጆችና ለተማሪዎች የተሰጠ ማስገንዘቢያ....9


**የተማሪ መብቶችና ኀላፊነቶች(Student Rights and Responsibilities)**


ACC ማስፈራራት/ማዋከብ/ማዋረድ....12
ACC-R ማስፈራራት/ማዋከብ/ማዋረድ....13
ADC ከአደንዛዥ እፅና ከትንባሆ ነፃ የሆኑ ትምህርት ቤቶች....13
JICC በአውቶቡሶች ውስጥ የተማሪ ምግባር....14
JH የሚታለፉ (ይቅርታ የሚደረግላቸው) የተማሪ ቀሪዎች....15
JHB የማይታለፉ (ይቅርታ የማይደረግላቸው) የተማሪ ቀሪዎች/ያለ ፈቃድ ከትምህርት ቤት መቅረት....17
JIC የተማሪ ምግባር....17
JICA የተማሪ ምግባርን ለመቆጣጠር የቪዲዮ ካሜራዎችን መጠቀም....19
JICA-R የተማሪ ምግባርን ለመቆጣጠር የቪዲዮ ካሜራዎችን መጠቀም....19
JICAB የተማሪ የአለባበስ ሥርዓት....20
JICDA የምግባርና የሥርዓትደንብ....21
JICDB ኃይለኛና ጥለኛ ምግባር....24
JICDE ማስፈራራትን መከላከልና ማስተማር ....25
JICEA ትምህርት-ነክ የሆኑ የተማሪ ህትመቶች....26
JICEA-R ትምህርት-ነክ የሆኑ የተማሪ ህትመቶች/የትምህርት ቤት የህትመት ሕግ....27
JICEC ተማሪዎች የሚያሰራጩት ሥርዓተ ትምህርት ነክ ያልሆኑ ጉዳዮች/ጽሁፎች....28
JICED የተማሪ የሐሳብ መግለጽ መብቶች....28
JICF አደገኛ በዘኔዎች/የሽብር ድርጊቶች....29
JICH የተማሪዎች ትንባሆና አደንዛዥ እፅ መጠቀም ....30
JICH-R የተማሪዎች ትንባሆና አደንዛዥ እፅ መጠቀም....31
JICHA የተማሪዎች ትምባሆ መጠቀም....37
JICI በትምህርት ቤቶች ውስጥ ትጥቆች መያዝ....38
JICJ የተማሪ የኤሌክትሮንክ መገልገያ ዕቃዎችን መጠቀም....40
JIH ለተማሪ ቃለ መጠይቅ ማድረግ፣ ማሰስና ማሰር....41
JJI የ ት ም ህ ር ት ቤ ት አትሌትክስ....44
JJI-R የ ት ም ህ ር ት ቤ ት አትሌትክስ (የአትሌትክስ ሕግ)....45
JK የተማሪ ምግባር....47
JKBA ተማሪን ለቅጣት ከመማሪያ ክፍል ማስወጣት....48
JKBA-R ተማሪን ለቅጣት ከመማሪያ ክፍል ማስወጣት....49
JKD-1 ተማሪዎችንለተወሰነጊዜከትምህርትቤትማስወጣትእና ሌሎችጠልቃገንነቶች.... .52
JKD-1-R ተማሪዎችን ለተወሰነ ጊዜ ከትምህርት ቤት ማስወጣት....53
JKD-1-E ተማሪን ለተወሰነ ጊዜ ከትምህርት ቤት የሚያስወጡ ወይም ምዝገባን የሚያስከለክሉ ምክንያቶች....57
JKD-2 የአካለ ስንኩላን ተማሪዎች ሥርዓት....58
JKD-4 ከመደበኛ ትምህርት ቤት ለታገዱ ተማሪዎች የሚሰጡ አማራጭ የመማር ዕድሎች....60
JKG ተማሪንበትምህርትቤት ውስጥ ማገድ
JLCA የተማሪየጤናአገልግሎቶችናመስፍርት ....61
JLCB የተማሪዎች ክትባት.
JLCB-R ክትባት .... .61
JLCD የመጀመሪያ እርዳታና ድንገተኛ የህክምና አገልግሎት....62
JQ የተማሪ የመመዝገቢያ ክፊያ፣ የገንዘብ መቀጮና ሌሎች ወጪዎች....62
JRC የተማሪ ሰነዶች/የተማሪን መረጃ ለሌላ ወገን መስጠት....63


**የእኩልነት የመተዳደሪያ ደንቦች (Non-Discrimination Policies)**


AC አለማዳላት/እኩል ዕድል/ከሰዎች ጋር ያሉ ግንኙነቶ....70
AC-E-1 ያለማዳላት/የእኩልነት ማስታወቂያ/ማስገነዘቢያ....73
AC-R-4 የተማሪዎች የወሲብ ጥቃት(ወሲባዊ ውከቢያ)....73
AC-R-5 የተማሪዎች የወሲብ ጥቃት(ወሲባዊ ውከቢያ) የአቤቱታ አቀራረብ ሂደት ....74
AC-R-6 በጎሳ እናበዘር በተመሰረተ አድልዎ አለማድረግ....75
AC-R-7 በአካል ስንኩልነት/በሰውነት ጉድለነት ላይ በተመሰረተ አድልዎ አለማድረግ....76
የዜጎች መብትና የጎሳኝነት ማስፈራራት የአቤቱታ ማቅረቢያ ሂደት....76


**የብዙኃን መገናኛዎች የአጠቃቀም ፖሊሲዎች (Network Resources Policies)**


EHC የብዙኃን መገናኛ የኤሌክትሮኒክ መረጃ ሰጪ መስመሮች ....79
JS የተማሪዎች የእንቴርኔትና የኤሌክትሮኒክ መገናኛ መስመሮች አጠቃቀም....84


**ተጨማሪ ፖሊሲዎች (Additional Policies)**


KI የድስትርክት ጎብኝዎች .... 87
KI-R የድስትርክት ጎብኝዎች ....88
IKA የተማሪ የትምህርት ክንውን መሻሻል/ተለውጦ ሚዘናና ግምገማ ....89
JLCDA ሥር የሰደደ ወይም ከባድ የጤና ሁኔታ ያላቸው ተማሪዎች....91

## በአንደኛ ደረጃና በሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ተቋማት የቤተሰብ የትምህርት መብትና የግል ምስጢር የመጠበቅ አዋጅ (‘FERPA’፣ 20USC’ 1232 (‘g’) ሥር የተሰጡ መብቶችን ማሳወቅ

የቤተሰብ የትምህርት መብትና የግል ምስጢር የመጠበቅ አዋጅ ‘FERPA’ ለወላጆችና እድሜያቸው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆኑ (መስፈርቱን ለሚያሟሉ ተማሪዎች)የተማሪን የትምህርት ሠነዶች አስመልክቶ የተወሰኑ መብቶችን ይሰጣል። እነዚህ መብቶች፤
(1) የተማሪን የትምህርት ሠነድ ለመመርመርና ለመከለስ ለድስትሪክቱ ጥያቄ ካቀረቡለት ጊዜ ጀምሮ በአርባ አምሳት (45) የሥራ ቀናት ውስጥ ጉዳዩን የማስፈጸም መብት:;

ወላጆች ወይም መስፈርቱን የሚያሟሉ ተማሪዎች ለመመርመር የሚፈልጉትን ሠነድ(ሠነዶች) የሚገልጽ የጽሁፍ ማመልከቻ ለትምህርት ቤቱ ኃላፊ ወይም ለተወካይ ያቀርባሉ። የትምህርት ቤቱ ኃላፊም የተጠየቀውን ሠነድ ለመስጠት በማቀድ ሠነዱ የሚመረመርበት ጊዜና ቦታ ለወላጅ ወይም ለተማሪው ያሳውቃል/ታሳውቃለች።

(2) ወላጅ ወይም መስፈርቱን የሚያሟላ ተማሪ  የተማሪ  የትምህርት ሠነድ ትክክል አይደለም ወይም ስህተት አለበት፣ ወይም ደግሞ የቤተሰብ የትምህርት መብትና የግል ምስጢር የመጠበቅ አዋጅ ‘FERPA’ ሥር የተቀመጠውን የተማሪ የግል ምስጢር መጠበቅ መብት ይጥሳል ብሎ ካመነበት ሠነዱ እንዲሻሻል የመጠየቅ መብት አላቸው።

ሠነዱ እንዲሻሻል ትምህርት ቤቱን የሚጠይቁ ወላጆች ወይም መስፈርቱን የሚያሟሉ ተማሪዎች ለትምህርት ቤቱ ኃላፊ (ወይም ለተወካይ) ከሰነዱ እንዲሻሻል የሚፈልጉትን ክፍል ከነምክንያቱ ጋር በግልጽ በጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል። ትምህርት ቤቱ የሚቀርብለትን አቤቱታ ውድቅ ካደረገ ውሳኔውን በጽሑፍ ለወላጅ ወይም ለተማሪ በማሳወቅ፣ ጉዳዩን አስመልክቶ ቅሬታ ካላቸው ቅሬታቸውን ለችሎት የማቅረብ መብት እንዳላቸው ይመክራል፤ በተጨማሪም የችሎት የቅሬታ አቀራረብ ሂደት አስመልክቶ ለወላጅ ወይም ለተማሪ አስፈላጊውን መረጃ ከውሳኔው ጋር ይሰጣል።

(3) በቤተሰብ የትምህርት መብትና የግል ምስጢር የመጠበቅ አዋጅ መሰረት የተማሪ የግል መረጃ ያለፈቃድ የሚገለጽበት ልዩ ሁኔታ በስተቀር፣ ሌላው የተማሪ የግል መረጃ ከመገለጹ በፊት የሚመለከተውን ግለሰብ ማስፈቀድ ያስፈልጋል።

ያለፈቃድ የተማሪን የግል መረጃ ማየት የሚችሉ የትምህርት ቤቱ ባለሥልጣናት ሲሆኑ፣ ይህም የሚሆነው ለህጋዊ የትምህርት ጉዳይ ብቻ ሲሆን ነው። የትምህርት ቤቱ ባለሥልጣናት ሲባል የትምህርት ቤቱ ሕጋዊ ሠራተኛ የሆኑና የአስተዳደር (የአመራር) ሥራን የሚሰሩ፣ የትምህርት ቤቱ ኃላፊ (አለቃ)፣ አስተማሪ፣ የድጋፊ ሰጪ ሠራተኞች (የትምህርት ቤቱ ክሊኒክ የጤና ባለሙያዎችና የህግ ክፍል ይጨምራል)፣ ትምህርታዊ አገልግሎቶችን ለማስተላለፍ ያገለገሉ የኦንላይን  ላይ አገልግሎት ሰጭዎች  የትምህርት ቤቱ የቦርድ አባል፣ ትምህርት ቤቱ በራሱ ሠራተኞችና አለቃ ፈንታ ለአንዳንድ ጉዳዮች ሕጋዊ ውክልና የሰጣቸው ግለሰቦች ወይም ኩባንያ (አቃቤ ሕግ፣ ኦዲተር፣ የሕክምና ባለሙያ፣ ወይም የጤና ምክር ሰጪ)፤ እንደ የሥርዓት ወይም የአቤቱታ/ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ያሉ የትምህርት ቤቱ ሕጋዊ ኮሚቴ ውስጥ ያለ/ች ተማሪ ወይም ወላጅ፣ ወይም የትምህርት ቤቱን አለቃ በትምህርት ቤት ተግባራት የሚረዳ/የሚትረዳ ተማሪ ወይም ወላጅ ናቸው።በኦፊሴላዊ ኮሚቴ ውስጥ የሚያገለግል ወላጅ ወይም ተማሪ፣ እንደ የዲሲፕሊን ወይም የቅሬታ ኮሚቴ፣ ወይም ሌላ የትምህርት ቤት ባለስልጣን ተግባራቱን እንዲፈጽም መርዳት፣ እና የስቴት ኤጀንሲዎች ጥናትን ማካሄድ (እንደ የኮሎራዶ የህዝብ ጤና እና የአካባቢ ጥበቃ መምሪያዲስትሪክቱ የትምህርት መዝገቦችን ወደ ሌሎች መዝገቦቹን ለጠየቁ ትምህርት ቤቶች ያስተላልፋል ምክንያቱም ተማሪው ለመመዝገብ ወይም ለመመዝገብ ስላሰበ እና ይፋ ማድረጉ ከተማሪው ምዝገባ ወይም ዝውውር ጋር የተያያዘ ነው።

ሙያዊ ተጠያቂነቱን/ተጠያቂነቷን ለመወጣት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የትምህርት ቤቱ አለቃ የትምህርት ሠነዶችን ለሕጋዊ የትምህርት-ነክ ጉዳዮች ማየት ይችላል/ትችላለች።

- በቤተሰብ የትምህርት መብትና የግል ምስጢር የመጠበቅ አዋጅ (‘FERPA’) መሰረት የትምህርት ድስትሪክቱ ከወላጅ/ከአሳዳጊ ወይም አግባብ ካለው ተማሪ የጽሑፍ ፈቃድ ሳያገኝ የተማሪን መረጃ ግልጽ ማድረግ ይችላል። በቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት እነዚህ መረጃዎች የሚከተሉ ናቸው፡ የተማሪ ስም፤ የትውልድ ቦታና ዘመን፤ የወላጅ እና የተማሪ ኢሜይል አድራሻዎች  ተማሪው/ዋ የሚያጠና/የሚታጠና ዋና የትምህርት ዓይነት፤ የክፍል ደረጃ፤  የክፍል ደረጃ  ስም ዝርዝሮች እውቅና ባላቸው የትምህርት ቤቱ ተግባራትና እስፖርቶች (አካላዊ እንቅስቃሴዎች)፤ የአትሌትክስ ቡድን አባላት ክብደትና ቁመት፤ የተከታተሉባቸው ቀናት የምዝገባ ቀናት ፤ ያገኙት ድግሪዎችና ሽልማቶች፤ ተማሪው በቅርብና ድሮ የተከታተላቸው የትምህርት ድርጅት ወይም ተቋማትን ያጠቃልላሉ። በአሁኑ ጊዜ ትምህርት ላይ ያሉ ተማሪዎች የስልክ ቁጥርና አድራሻ እና የእሜይል አድራሻ  በኮሎራዶ ሕግ መሰረት ግልጽ አይደረጉም።

  - ወላጅ/አሳዳጊ ወይም አግባብ ያለው/ያላት ተማሪ ማንኛውንም ወይም ሁሉንም ዓይነት መረጃዎች እንዳይወጣ የመቃወም መብት አለው/አላት። ይህም የሚቻለው ተቃውሞ**ውን/ዋን** ለትምህርት ቤቱ ኃላፊ እስከ መስከረም 7፤ ቀኑ ቅዳሜ ወይም እሑድ ላይ ከዋለ በቀጣዩ ሰኞ በጽሑፍ ሲያቀርብ/ሲታቀርብ ነው።

  - የሌላ የትምህርት ድስትርክት የተማርዎችን መረጃ ለትምህርት ፤ለዝውውር፤ ወይም ለምዝገባ ምክንያት ከፈለገ ድስትረክታችን  ያለ ፍቃድ መረጃው ልሰጥ ይችላል ነገር ግን  በህጉ መሰረት መሆን አለበት። በተጠየቀ ጊዜ፣ የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት የዲሲፕሊን መረጃን እና የዛቻ ግምገማዎችን ጨምሮ የትምህርት መዝገቦችን ያለቅድመ የጽሁፍ ፈቃድ ለሌላ የትምህርት ቤት ዲስትሪክት ወይም ትምህርት ቤት ኃላፊዎች ይሰጣል፡፤  ወይም ተማሪው ለመመዝገብ ያሰበ ወይም አስቀድሞ የተመዘገበው ለእዚህ ዓላማ ከሆነ  ከFERPA ጥበቃ በስተቀር እንደተፈቀደው የተማሪው ምዝገባ ወይም ማስተላለፍ።

(4) የቤተሰብ የትምህርት መብትና የግል ምስጢር የመጠበቅ አዋጅ (‘FERPA’) በድስትሪክቱ ሲጣስ፣  **‘U.S. Department of Education’** ለሚባለው ዩናይተድ ስቴትስ የትምህርት ቢሮ አቤቱታ የማቅረብ መብት። ‘FERPA’ የሚባለውን የቤተሰብ የትምህርት መብትና የግል ምስጢር የመጠበቅ አዋጅ  የሚያስተዳድር የቢሮ ስምና አድራሻ የሚከተለው ነው፡ **‘Family Policy Compliance Office, U.S. Department of Education, 400 Maryland Ave. SW, Washington, DC 20202-4605’** የሚባለው ነው።

JRC’ የሚባለው የተማሪ ሠነዶች/የተማሪን መረጃ መስጠት የሚመለከት የድስትሪክት ፖሊሲ ፣ የተማሪን ሠነድ መስጠት አስመልክቶ መብቶችንና ኃላፊነቶችን ይገልጻል። የዚህ ፖሊሲ ግልባጭ በእያንዳንዱ ትምህርት ቤቶች፣ የድስትሪክቱ ድረ ገጽ የሆነው ‘www.ccsd.k12.co.us’ ላይ ወይም በ ‘4700 S. Yosemite St., Greenwood Village, CO 80111’ በሚገኘው የቼሪ ክሪክ ድስትሪክት የትምህርት ቢሮ ይገኛል።

## በተሻሻለው የሕዝብ መብቶች ጥበቃ ሥር ያለውን መብቶች ማሳወቅ (PPRA)

‘PPRA’ የሚባለው የተሻሻለው የሕዝብ መብቶች ጥበቃ ለወላጆችና ዕድሜያቸው 18 ዓመት ለሆናቸው ወይም ራሳቸውን ለቻሉ ተማሪዎች(“ መስፈርቱን ለሚያሟሉ ተማሪዎች”) የሚናካሂደው የዳሰሳ ጥናት፣ ለግብይት ዓላማ የመረጃዎችን አሰባሰብና አጠቃቀም እና የተወሰኑ የአካል ምርመራ አስመልክቶ የተወሰኑ መብቶችን ይሰጣል። እነዚህ መብቶች ቀጥሎ ያሉትን ያጠቃልላሉ፤

- ተማሪዎች በዳሰሳ ጥናት እንዲሳተፉ ከመጠየቃቸው በፊት ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ነጥቦች አንድ ወይም ከዚያ በላይ ጉዳይ የሚመለከት (“ የግል መረጃ የዳሰሳ ጥናት”) የማስፈቀድ መብት፤ የዳሰሳ ጥናቱ በሙሉ ወይም በከፊል **‘U.S. Department of Education’** በሚባለው የዩናይቲድ ስቴትስ የትምህርት ቢሮ መርሃግብር የሚደጎም ከሆነ ነው።

    1. የተማሪው ወይም የተማሪው ወላጅ የፖለቲካ ወይም የሃይማኖት አመለካከት፤
    2. የተማሪው ወይም የተማሪው ወላጅ የአይምሮ ወይም የሥነ ልቦና ችግሮች፤
    3. የወሲብ ምግባር ወይም ባህሪያት;
    4. ሕገ ወጥ፣ ጸረ ማኅበረሰባዊ፣ የራስ ከሳሽነት፣ ወይም የራስ ወቃሽነት ምግባር፤
    5. ከተማሪው/ዋ ጋር ቅርብ ቤተሰባዊ ግንኙነት ላላቸው ለሌሎች ሰዎች የነቀፋ አስተያየት ማቅረብ፣
    6. ሕጋዊ እውቅና ያለው ልዩ መብት፣ ለምሳሌ ከጠበቃ፣ ከሐኪሞች ወይም ከሚኒስቴሮች ጋር ያለው/ያላት ግንኙነቶች፤
    7. የተማሪው ወይም የወላጅ የሃይማኖት ልምምዶች፣ ቁርኝቶች፣ ወይም እምነቶች፤ ወይም
    8. በመርሃ ግብር (በፕሮግራም) ለመሳተፍ መስፈርት ማሟላትን ለመወሰን በሕግ አስፈላጊ ከሆነ ሌላ ገቢ፣ ፤
- የሚከተሉትን ጉዳዮች ማሳወቅና ተማሪ በጉዳዮቹ እንዳይሳተፍባቸው ዕድል መስጠት፡
    1. በማናቸውም ሌሎች የግል መረጃ የዳሰሳ ጥናት፤ ለጥናቱ የሚከፈለው ገንዘብ ግድ የለም፣
    2. ማናቸውም ድንገተኛ ያልሆኑ፣ በትምህርት ቤት ወይም በተወካዩ የሚካሄዱ የአካል የክትትል ምርመራ፣ ይህም የመስማት፣ የማየት፣ ወይም የጀርባ አጥንት ምርመራዎች ካልሆኑ በስተቀር፣ የግድ የተማሪን ጤናና ደህንነት ለመጠበቅ የሚደረጉ ምርመራዎች አይደሉም፣ እና
    3. ለግብይት ወይም ለሽያጭ ወይም ደግሞ መረጃዎቹን ለሌሎች ለማሰራጨት ሲባል ከተማሪዎች የግል መረጃዎችን የመሰብሰብ፣ የመግለጽ፣ ወይም የመጠቀም ድርጊቶች።
- ጥያቄው ሲቀርብና የሚከተሉትን ከማካሄድና ከመጠቀም በፊት መፈተሽ፣ ፡
    1. የተማሪዎች የግል መረጃ የዳሰሳ ጥናቶች፤
    2. ከላይ ለተጠቀሱት ለማናቸውም ለግብይት፣ ለሽያጭ፣ ወይም ለሌሎች ስርጭት ዓላማዎች ከተማሪዎች የግል መረጃ የመሰብሰቢያ ዘዴዎች፤ እና
    3. እንደ ሥርዓተ ትምህርት የሚያገለግል የማስተማሪያ መጻህፍትና ሌሎች ነገሮች።

- ልጆች 18 አመት ስሆናቸው ይህ ሁሉ መብት የልጆች ይሆናል
- እነዚህን መብቶች አስመልክቶና ለግብይት፣ ለሽያጭ፣ ወይም ለሌሎች ለስርጭት ዓላማዎች ሲባል የተማሪን የግል መረጃ መሰብሰብ፣ መግለጽ፣ ወይም መጠቀም በተመለከተ የተማሪን የግል ምስጢር መጠበቅ አስመልክቶ የቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት ቁጥር 5 ከተማሪ ቤተሰቦች ጋር በመመካከር ፖሊሲዎችን አውጥቶ ሥራ ላይ አውሏል። የትምህርት ድስትሪክቱ ወላጆችንና መስፈርቱን የሚያሟሉ ተማሪዎች ስለ ፖሊሲዎቹ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በዓመቱ መጀመሪያ ትምህርት ሲጀመርና ማናቸውም መጠነ ሰፊ ለውጥ ሲደረጉ በቀጥታ ያሳውቃቸዋል። የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት እነዚህን መብቶችና ኃላፊነቶች ‘JLCA’ በሚባል፣ የተማሪ የጤና አገልግሎቶችና መስፈርቶች እና ‘JLDAC’ በሚባል የተማሪዎች ማጣሪያና ምርመራ ፖሊሲዎች ውስጥ ዘርዝሯል። የነዚህን ፖሊሲዎች ግልባጭ ከኮምፒዩተር ድረ ገጽ ላይ ወይም ድስትሪክቱን ወይም ትምህርት ቤቶችን በመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። በተጨማሪም የቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት በተወሰኑ ድርጊቶች ወይም በዳሰሳ ጥናቶች እንዲሳተፉ የተመደቡ የተማሪዎች ወላጆችን በቀጥታ በደብዳቤ ወይም በኢሜል ያሳውቃቸዋል፣ እንደዚሁም ወላጅ ልጁ/ጇ በተወሰኑ ድርጊቶች ወይም በዳሰሳ ጥናቶች እንዳይሳተፍ/እንዳትሳተፍ የማድረግ ዕድል ያገኛል/ታገኛለች። ድስትሪክቱ በወቅቱ የድርጊቱን ወይም የዳሰሳ ጥናቱን ቀናት በትክክል ወይም በግምት ካወቀ በዓመቱ የትምህርት መጀመሪያ ላይ ወላጅን ያሳውቃቸዋል። የዓመቱ ትምህርት ከተጀመረ በኃላ ለሚደረጉ ድርጊቶችና የዳሰሳ ጥናቶች አስመልክቶ የታቀዱ ድርጊቶችና የዳሰሳ ጥናቶች ዝርዝር፣ እንደዚሁም ልጃቸው በነዚህ ድርጊቶችና የዳሰሳ ጥናቶች እንዳይሳተፍ/እንዳትሳተፍ የመምረጥ ዕድል ለወላጆች ይሰጣቸዋል። በተጨማሪም ወላጆች የተያያዙ የዳሰሳ ጥናቶችን እንዲከልሱ ዕድል ይሰጣቸዋል።

መብታቸው እንደተጣሰ የሚያምኑ ወላጆች/መስፈርት የሚያሟሉ ተማሪዎች ለሚከተለው **የቤተሰብ ፖሊሲ አቤቱታ ማቅረቢያ ቢሮ** አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ፡ **The Family Policy Compliance Office, U.S. Department of Education, 400 Maryland Avenue, SW, Washington, D.C. 20202-4605**

**ቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤቶች ቁ.5**

**የጾታዊ ትንኮሳ መረጃን አስመልክቶ ለወላጆች የተሰጠ ማስገነዘቢያ**

በኮሎራዶ የሚገኙ የድስትሪክት ትምህርት ቤቶች ለወላጆችና መስፈርቱን ለሚያሟሉ ተማሪዎች (18 ዓመት ለሆናቸው ወይም ከዚያም በላይ ለሆኑ ተማሪዎች) ፣ እንደዚሁም የማኅበረሰቡ አባላት በወሲባዊ ትንኮሳ ምክንያት የተመዘገቡትን ሰዎች አስመልክቶ በህግ አስከባሪ ድርጅቶች የተሰበሰቡትን መረጃዎች ማግኘት የሚችሉትን ቦታና እንዴት ማግኘት እንደሚችሉም ጭምር የሚገልጽ መረጃ እንዲሰጡ የሚያስገድድ ህግ የኮሎራዶ አጠቃላይ ጉባኤ አስተላልፏል። ለዚህ ሕገ ደንብና መመሪያ በመታዘዝ፣ የቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤቶች ድስትሪክት ቁ. 5 በድስትሪክቱ ሥራውን የሚያከናውኑ የተለያዩ የህግ አስከባሪ ባለሥልጣናትን አድራሻዎች ሰጥቷል። የሚፈልጉት ወላጆች፣ መስፈርቱን የሚያሟሉ ተማሪዎች እና የማኅበረሰቡ አባላት በአካባቢያቸው የሚገኘውን የህግ አስከባሪ ድርጅቶችን በመጠየቅ በዚያ አከባቢ ውስጥ የሚኖሩትና በወሲባዊ ትንኮሳ ምክንያት የተመዘገቡትን ሰዎች አስመልክቶ የበለጠ መረጃ ማግኘት ይችላሉ።

ቀጥሎ የተዘረዘሩት የህግ አስከባሪ ድርጅቶች ወሲባዊ ትንኮሳን አስመልክቶ መረጃን በስልክ አይሰጡም፤ ስለዚህ ይህንን መረጃ ለማግኘት በሚኖሩበት ከተማ ውስጥ የሚገኘውን የህግ አስከባሪ ድርጅት በአካል በመቅረብ መረጃውን ከመጠየቃቸው በፊት ማንነታቸውን የሚያረጋግጥ ህጋዊ መታወቂያ ማሳየት ይኖርባቸዋል። ማንነታቸው ከተረጋገጠ በኋላ መረጃውን የሚፈልግ ግለሰብ የሚፈልገውን መረጃ ለመጠየቅ የወሲባዊ ትንኮሳ ቅጽ እንዲሞላ/እንዲትሞላ ይጠየቃል/ትጠየቃለች። ለዚህ አገልግሎት ክፊያ ሊኖር ይችላል፤የአገልግሎቱ ክፍያ ለተለያዩ የህግ አስከባሪ ድርጅቶች የተለያየ ሊሆን ይችላል።

ቀጥሎ የተሰጡት የቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤት ድስትሪክትን የሚያገለግሉ የህግ አስከባሪ ድርጅቶች ናቸው፤

የግሪንውድ ቪሌጅ ፖሊስ ክፍል አድራሻ፤ 
6060 S. Quebec St.
Greenwood Village, CO 80111
303-773-0252
The village@greenwoodvillage.com

የአውሮራ ፖሊስ ክፍል አድራሻ፤
15001 E. Alameda Pkwy.
Aurora, CO 80012
303-739-6000
access@auroragov.org

የአራፓሆ ካውንቲ ሸሪፍ ክፍል አድራሻ፤
13101 E. Broncos Pkwy.
Centennial, CO 80112
dwalcher@.arapahoegov.com
303-795-4711

የቼሪ ሂልስ ቪሌጅ ፖሊስ ክፍል አድራሻ፤
2450 E. Quincy Ave.
Cherry Hills Village, CO 80113
303-789 -2541
village@cherryhillsvillage.com

የግለንደል ፖሊስ ክፍል አድራሻ፤
950 S. Birch St.
Glendale, CO 80246
303-759-1513
info@glendale.co.us

የወሲባዊ ጥቃት ምዝገባ ክፍል፤
Colorado Bureau of Investigation
690 Kipling Street, Suite 3000
Lakewood, CO 80215
303-239-5732
cbi.denver@.state.co.us

ይህንን መረጃ በተመለከተ ጥያቄ ወይም ጉዳይ ካለዎት፣ የቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤት ድስትሪክት ደህንነትና ጥበቃ ኃላፊ የሆኑትን አቶ Ian Lopez የሚባሉትን በስልክ ቁጥር 720-554-4489 ያነጋግሩ።

## የተማሪን ምግባር ለመቆጣጠር የቭዲዮ ካሜራን መጠቀም አስመልክቶ ተማሪዎችንና ወላጆችን ማሳወቅ (JICA-E)

የትምህርት ቤቶችን ማጓጓዣ ለመቆጣጠር ድስትሪክቱ በትምህርት ቤቶች አውቶቡሶች ላይ ምሥልን የሚቀርጹ ካሜራዎችን አስገብቷል፣ በተሰጠው የትምህርት ዘመን ውስጥ ካሜራው በነሲብ የአውቶቡስ መስመሮች/ተግባራት ምሥሎችን ይቀርጻል። አውቶቡሶች ምሥሎችን የሚቀርጽ እና ካሜራን የሚያነቃቃ የምሥል መቆጣጠሪያ ሳጥን አላቸው። በአውቶቡሳቸው ላይ ምሥል የሚቀርጽ ካሜራ የሚሰራበትን ጊዜ ለተማሪዎች ማሳወቅ አያስፈልግም። በተጨማሪም፣ ምሥል የሚቀርጹ ካሜራዎች በድስትሪክቱ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ህንጻዎችና ምናልባትም በሌሎች ድስትሪክት ትምህርት ቤቶችና ህንጻዎች ውስጥም ያለማቋረጥ ሥራቸውን ይሰራሉ።

የተቀረጹ ምሥሎች ታይተው በተገኘው መረጃ መሰረተ ምግባረ ብልሹ የሆኑ ተማሪዎች ጉዳይ በሰነድ ይያዛሉ። የድስትሪክቱን የምግባር ደንብ ጥሰው የተገኙ ተማሪዎች ጉዳዩ ተገልጾላቸው በቦርዱ ደንቦችና የተማሪ ምግባርና ሥርዓት መቅጫ ሕግ መሰረት የቅጣት እርምጃ ይወሰድባቸዋል።

በቤተሰብ የትምህርት መብትና የግል ምስጢር የመጠበቅ አዋጅ ሥር የቪድዮ ምሥሎች እንደ የተጠበቁ የተማሪ ሰነዶች ይታያሉ። የሚከተሉ መመሪያዎች ሥራ ላይ ይውላሉ፡

1. የተቀረጹት የቪድዮ ምስሎች የትምህርት ድስትሪክት ንብረት በመሆን አግባብ ባለው ትምህርት ቤት ወይም ድስትሪክት ውስጥ ይያዛል።
2. በምግባረ ብልሹ ተማሪዎች ላይ የተወሰደውን የቅጣት እርምጃ ተከትሎ ወላጆች ወይም ተማሪዎች የቭድዮ ምስሉን ማየት ከፈለጉ ጥያቄያቸውን 'JICA-R' በሚባለው የተማሪን ምግባር ለመቆጣጠር የቭድዮ ካሜራን መጠቀም ሥር በተሰጠው አካሄድ መሰረት ያቀርባሉ ።
3. የቅጣት እርምጃው የማይመለከታቸው ሰዎች የአውቶቡስ የቭድዮ ምሥሎችን እንዲያዩ አይፈቀድላቸውም።

በትምህርት ቤቶች የበላይ አለቃ Robert D. Tschirki የጸደቀ፣ የካተት 8፣ 1999

## ሀ. የተማሪዎች የዳሰሳ ጥናት፣ ትንተና ወይም ግምገማ

### ፍቃድ የሚያስፈልገው የዳሰሳ ጥናት፣ ትንተና ወይም ግምገማ

መረጃው ይፋ የሚሆን፣ በግል የሚያጋልጥ ሊሆን ወይም ላይሆንም ይችላል፣ ስለ ተማሪው/ዋ ወይም ስለ ተማሪው/ዋ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ ያለ ወላጅ ፈቃድ፣ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን መረጃዎችን ይፋ የሚያደርግና ከሥርዓተ ትምህርት ወይም ከሌሎች የትምህርት ቤት ድርጊቶች/ተግባራት ጋር የተያያዘ የዳሰሳ ጥናት፣ ትንተና ወይም ግምገማ ውስጥ በሕግ ካልተገደዱ በስተቀር መሳተፍ የለባቸውም።

1. የፖለቲካ አመላካከት/ረዕዮተ ዓለም

2. ለተማሪው/ዋ ወይም ለቤተሰቡ/ቧ አስጨናቂና አሳፋሪ የሆነ የአይምሮ ወይም የሥነ ልቦና ችግሮች

3. የወሲብ ምግባር ወይም ባህሪያት

4. ሕገ ወጥ፣ ፀረ ማኅበራዊ፣ የራስ ወቃሽነት እና የራስ ማንኳሰስ ምግባር

5. ከተማሪው/ዋ ጋር ቅርብ ቤተሰባዊ ግንኙነት ላላቸው ለሌሎች ሰዎች የነቀፋ አስተያየት ማቅረብ

6. ሕጋዊ እውቅና ያለው ልዩ መብት ወይም ግንኙነት፣ ለምሳሌ ከጠበቃ፣ ከሐኪሞች ወይም ከሚኒስቴሮች ጋር ያለው/ያላት ግንኙነቶች

7. (በመርሃ ግብር (በፕሮግራም) ውስጥ ለመሳተፍ ወይም በመርሃ ግብሩ(በፕሮግራሙ) ውስጥ የገንዘብ ድግፍ ለማግኘት መስፈርት ማሟላትን ለማረጋገጥ በሕግ በሕግ አስፈላጊ ከሆነ ሌላ) ገቢ

8. የተማሪው/ዋ ወይም የተማሪው/ዋ ወላጆች/አሳዳጊዎች የሃይማኖት ልምምዶች፣ አመለካከቶች ወይም ሃይማኖቶች
9. የሶሻል ሰኩሪቲ ቁጥር

ይህንን የዳሰሳ ጥናት፣ ትንተና ወይም ግምገማ የማካሄድ ኃላፊነት ያለው/ያላት የትምህርት ቤት ሠራተኛ ቢያንስ ከሁለት ሣምንታት በፊት ለተማሪው/ዋ ወላጅ/አሳዳጊ ወይም መስፈርቱን ለሚያሟላ ተማሪ (እድሜው/ዋ 18 ዓመት የሆነ/የሆነች ተማሪ) በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት። የጽሁፍ ማስታወቂያው በሚጠየቁበት ጊዜ የሚከተሉትና መረጃዎች እንዲያቀርቡ መግለጽ አለበት፡

1. ለምርመራና ለዳሰሳ ጥናቱ፣ ለትንተናው እና ለግምገማው የሚያስፈልጉ ሠነዶች ወይም መረጃዎች

2. ሠነዶቹ ወይም መረጃዎቹ የሚገኙበት ዘዴ

3. ሠነዶቹ ወይም መረጃዎቹ የሚያስፈልጉበት ዓላማ

4. መረጃውን ሊያገኙ የሚችሉ ተቋማት ወይም ሰዎች፣ የተቋማቱ ወይም የሰዎቹ የአባልነት ሁኔታ ግድ የለም

5. ሠነዶቹን ወይም መረጃዎቹን ለማግኘት ወይም ለመመርመር ወላጅ/አሳዳጊ ፈቃድ የሚሰጥበት ወይም የሚከለክልበት ዘዴ

እነዚህን የጽሁፍ ማስታወቂያዎች አስቀድሞ መስጠት በማናቸውም 'U.S. Department of Education' በሚባለው የዩናይቲድ ስቴትስ የትምህርት ቢሮ የሚደጎም የዳሰሳ ጥናት፣ ትንተና ወይም ግምገማ ሥራ ላይ ይውላል።
አስቀድሞ የጽሁፍ ማስታወቂያ መስጠት እና "ያለ መሳተፍ" መብትን ማሳወቅ ለግብይት ዓላማዎች ሲባል በዳሰሳ ጥናት፣ በትንተና እና በግምገማ ውስጥ ሥራ ላይ ይዉላል።

**ዳሰሳ ጥናት፣ ትንተና እና ግምገማ ለግብይት ዓላማዎች**

ወላጆች/አሰዳጊዎች እና መስፈርቱን የሚያሟሉ ተማሪዎች (ዕድሜያቸው 18 ዓመት የሆኑ ተማሪዎች) የጽሁፍ ማስታወቂያ ማግኘትና ለመረጃ ግብይት ወይም ለሽያጭ ዓላማ ሲባል ወይም ደግሞ መረጃውን ለሌሎች ለማቅረብ ዓላማ ከተማሪ የሚሰበሰበውን የግል መረጃን ይፋ ማድረግ ወይም መጠቀም ተግባራት ውስጥ ያለመሳተፍ መብት ሊሰጣቸው ይገባል።

**የመከለስ መብት**

ወላጆች/አሳዳጊዎች እና መስፈርቱን የሚያሟሉ ተማሪዎች (እድሜያቸው 18 ዓመት የሆኑ ተማሪዎች) የሚካሄዱትን ወይም ትምህርት ቤት ለተማሪዎች የሚያሰራጫቸውን ማንኛውንም የዳሰሳ ጥናት፣ ትንተና ወይም ግምገማ በድስትሪክቱ ወይም በሦስተኛ ወገን መካሄዳቸውን ጠይቆ የመከለስ መብት አለው።

**የፖሊሲ ልዩ ሁኔታዎች**

በዚህ የፖሊሲ ክፍል ውስጥ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ነጥቦች የሚከለክል ምንም ነገር የለም፡

1. በፌደራል ህግ ካልተከለከለ በስተቀር በየጋዜጠኝነት ሙያ መምህር ወይም አማካኝ/እስፖንሰር ቁጥጥር ሥር የሚሰራን ተማሪ ያለ ፈቃድ የዳሰሳ ጥናት፣ ትንተና ወይም ግምገማ ከማዘጋጀት ወይም በተግባሩ ከመሳተፍ የሚያግደው/የሚያግዳት ነገር የለም።

2. የክፍለ ግዛት(የስቴት) ህግ እንደሚያዘው የድስትሪክቱ ሰራተኛ የታወቀውን ወይም የሚጠረጠረውን የልጅ በደል ከመጠቆም የሚያግድ ነገር በፖሊሲው ውስጥ አልተገለጸም።

3. የድስትሪክቱ ትምህርት ቤት የጤና ባለሙያ የልጅን ግላዊ የጤና ሁኔታ የማየት(የመገምገም) መብት የሚገድብ ጉዳይ በፖሊሲው ውስጥ አልተገለጸም።

4. ለተማሪዎች ወይም ለትምህርት ተቋማት የሚውል ትምህርት ነክ የዳሰሳ ጥናት፣ ትንተና ወይም ግምገማ ለማካሄድ የወላጅ ፈቃድ እንደሚያስፈልግ የሚገልጽ ሃሳብ በፖሊሲው ውስጥ አልተገለጸም። እነዚህ አገልግሎቶች የሚከተሉትን ነጥቦች ያካትታሉ፣ ነገር ግን ቀጥሎ በተዘረዘሩት ነጥቦች ብቻ አይወሰንም።

- ለኮሌጅ ወይም ከሁለተኛ ደረጃ በኃላ የትምህርት ምደባ ወይም ለውትድርና የምደባ ተግባራት
- የመጻሕፍት ከለብ፣ መጽሔቶች እና ዝቅተኛ ዋጋ ያላቸውን ለመጻፍና ለማንበብ የሚረዱ መጻሕፍትና ጽሁፎች የሚያቀርቡ መርሃ ግብሮች
- በድስትሪክት ትምህርት ቤቶች የሚገለገሉ የሥርዓተ ትምህርትና የማስተማሪያ መጻሕፍት
- የተማሪዎችን እውቀት፣ ግምገማ፣ ምርመራ፣ ችሎታ/ተሰጥኦ ሁኔታ፣ ወይም የክንውን መረጃ ለማቅረብ የሚረዱ በድስትሪክት ትምህርት ቤቶች የሚሰጡ ቴስቶች እና ግምገማዎች
- ትምህርት ቤት ነክ ወይም ትምህርት ነክ የሆኑና ለገቢ ማሰባሰቢያ የሚውሉ በተማሪዎች የሚሸጡ የተለያዩ ምርቶች ወይም በተማሪዎች የሚሰጡ አገልግሎቶች
- የተማሪ የማበረታቻ ሽልማቶች መርሃ ግብሮች (ፕሮግራሞች)

5. ተማሪ ምን እንደሚያውቅና ምን መተግበር እንደሚችል ለማወቅ፣ እንደዚሁም ተማሪ የተሰጠውን የትምህርት ይዘት ደረጃ ላይ እንደደረሰ ለመገምገም ወላጅን ማሳወቅና የወላጅ ፈቃድ ማግኘት
6. የራስን ማጥፋት ሙከራ ወይም የዛቻ ግምገማን በተመለከተ የድስትሪክቱን ሥልጣን መገደብ

**በሚስጥር የመያዝ ሁኔታ**
ትምህርት ቤት ለተማሪዎች የሚሰጣቸውን ወይም የሚያሰራጫቸውን ማንኛውም የዳሰሳ ጥናት፣ ትንተና ወይም ግምገማ አስመልክቶ የተማሪ ሠነዶችን በምስጥር ስለ መያዝ የሚመለከተው ግዛት (ስቴት) እና የፌደራል ህግ በሚያዘው መሰረት መሆን ይገባል።

***መስፈርቱን የሚያሟሉ ተማሪዎች***
ዕድሜው/ዋ 18 ዓመት ወይም ከዚያም በላይ የሆነ/የሆናት ተማሪ እነዚህን መረጃዎች ያለ ወላጅ ፈቃድ በራሱ/ሷ ፈቃድ እንደነዚህ ያሉትን መረጃዎች መስጠት ይችላል/ትችላለች።

***የፖሊሲ የዚህ ክፍል ማሳሰቢያ***
ዲስትሪክቱ በዚህ የፖሊሲ ክፍል ሥር ያሉትን መብቶች ለወላጆች/ለአሳዳጊዎች እና መስፈርቱን ለሚያሟሉ ተማሪዎች ያሳውቃቸዋል።
1. የግል መረጃን ለግብይት ዓላማ መሰብሰብ፣ ለሌላ ወገን መስጠት፣ ወይም መጠቀም፤
2. ጥብቅ የሆኑ የመረጃ ዳሰሳ ማካሄድ
3. ማንኛቸውም ድንገተኛ ያልሆኑ፣ የሰውነት ፍተሻ ወይም ምርመራ (የጆሮ፣ የአይን፣ ወይም የጀርባ አጥንት ምርመራ በስተቀር)
   - ለትምህርት ክትትል አስፈላጊ የሆነ
   - በትምህርት ቤት ቀደም ብሎ ፕሮግራም የተያዘበትና በትምህርት ቤት የሚካሄድ፣ እንደዚሁም
   - የተማሪውን ወይም የሌሎች ተማሪዎችን ጤንነትና ደህንነት ለማረጋገጥ አስፈላጊ ያልሆነ

***ለ. የሥነ አእምሮ /የሥነ ልቦና የምርመራ ) አሰጣጥ ዘዴዎች ወይም ሂደቶች***

***ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው የሥነ አእምሮ /የሥነ ልቦና የምርመራ ዘዴዎች ወይም ሂደቶች***

እንደ የመማርያ ክፍል ወይም በማስተማር ተግባር አካል ተወስዶ ለምርመራ፣ ለግምገማ ወይም ማንኛውንም የስሜታዊነት፣ የምግባር፣ ወይም የአይምሮ መዛባት ወይም ስንኩልነትን ለማከም (ለመንከባከብ) ዓላማ ሲባል ያለ ወላጅ እውቅና እና ፈቃድ ተማሪዎች ለማንኛውም የሥነ አእምሮ/የሥነ ልቦና የምርመራ ዘዴዎች/ሂደቶች እንዲቀርቡ አይጠየቁም። ነገር ግን፣ ወላጆች የፕሮግራም (የመርሃ ግብር) ገምጋሚ ቢሮን በጽሑፍ ሲጠይቁ የግል ምርመራ ይደረግላቸዋል። ዕድሜው/ዋ 15 ዓመት የሆነው/የሆናት ተማሪ የአእምሮ ጤንነት አገልግሎት እንዲሰጠው/እንዲሰጣት ያለ ወላጅ ፈቃድ በራሱ/ሷ ፈቃድ መጠየቅ ይችላል/ትችላለች። ይህም የሚሆነው እነዚህን አገልግሎቶች በፋሲሊቲ ሲሰጡ ናቸው (ለምሳሌ ይህንን እንክብካቤ (ህክምና) የሚሰጡ ክሊኒክ ወይም የማኅበረሰብ የአይምሮ ጤና ማዕከል) ወይም በዚህ ግዛት (ስቴት) ውስጥ በህክምናው የሙያ ፈቃድ ባለው/ባላት ሐኪም ወይም በዚህ ግዛት (ስቴት) ውስጥ በሙያው ፈቃድ ባለው/ባላት የሥነ ልቦና ባለሙያ ሊሆን ይችላል። 18 ዓመት የሆነው/የሆናት ወይም ከዚያም በላይ የሆነ/ች ተማሪ ያለ ወላጅ ፈቃድ በሥነ አእምሮ ወይም በሥነ ልቦና የምርመራ ዘዴዎች ወይም ሂደቶች በራሳቸው ፈቃድ ሊሳተፉ ይችላሉ።

ፈቃድ ያላቸው የትምህርት ቤት ሰራተኞች ስለ ሥነ- አእምሮ ወይም ስለ ሥነ ልቦና የምርመራ ዘዴዎችና ሂደቶች እውቀት እንዲኖራቸው ይበረታታሉ። ሆኖም ግን ተገቢውን ፈቃድ ከለላቸው በማናቸውም የአእምሮ መዛባት ወይም ስንኩልነት ምርመራ ወይም ህክምና (እንክባካቤ) መሳተፍ የለባቸውም። በግዛት (ስቴት) ህግ መሰረት በሙያው ፈቃድ ያላቸው የትምህርት ቤት የሥነ ልቦና ባለሙያዎችን ጨምሮ የትምህርት ቤት ሰራተኞች የሥነ አእምሮ/ልቦና ህክምና (እንክብካቤ) እንዲሰጡ ወይም ካላቸው ስልጠና፣ ልምድ ወይም ችሎታ ውጪ ወይም በላይ የሆኑትን ማናቸውንም የሥነ አእምሮ ወይም የሥነ ልቦና ሂደቶችን እንዲያካሄዱ አይፈቀድላቸውም።

የሥነ ልቦና ቴስቶች (ፈተናዎች) ለተማሪዎች መሰጠት ያለባቸው ተገቢውን የሙያው ፈቃድ ባላቸውና ለዚሁ ዓላማ በተቀጠሩ የትምህርት ቤት ሰራተኞች ወይም በሙያው ፈቃድ ባላቸው ባለሙያዎች ተጠባባቂነት ወይም ቁጥጥር ሥር ሆኖ በሙያው እየሰለጠኑ ባሉ ተማሮዎች ብቻ መሆን አለበት ። ይህንን ፖሊሲ መከተል ወይም መደገፍ ጥራት ያለውን የሥነ ልቦና አገልግሎቶች ለመስጠት እና የተማሪዎችንና የወላጆችን የትምህርት መብቶች፣ ክብር እና የግል ምስጥር መጠበቅን ያረጋግጣል።

ተማሪው/ዋ በራሱ/ሷ ግልጽ የሆነ የጽሁፍ ፈቃድ ለመስጠት ሕጋዊ ዕድሜ ላይ ካልደረሰ/ካልደረሰች በስተቀር፣ የሥነ ልቦና ምርመራ ሊደረግ የሚችለው ከተማሪው/ዋ ወላጆች ወይም አሳዳጊ ግልጽ የሆነ የጽሁፍ ፈቃድ ሲገኝ ብቻ ነው። የሥነ ልቦና መረጃ በተማሪው የትምህርት ፕሮግራም ውስጥ የሚከሰቱትን ማናቸውም ለውጦች ለመወሰን ከሚረዱ መስፈርቶች ውስጥ አንዱ መሆን አለበት። ከሦስት ዓመት በላይ የቆዩ የስነ ልቦና መረጃዎች ለማስተማር ወይም ተማሪን ለመመደብ መሰረት ሊሆኑ አይችሉም።

መደበኛ ትምህርት፣ የትምህርት ተግባራትና ስልቶች የሆኑና በሥርዓት-ትምህርት ውስጥ የተካተቱ የሥነ ልቦና ወይም የሥነ አእምሮ ትምህርቶች በዚህ ፖሊሲ ውስጥ የማይካተቱና የተፈቀዱ ናቸው።ስለ ስነ ልቦናዊ ወይም ስነ አእምሮአዊ ዘዴዎች ወይም አካሄዶች የሚያስተምር የጸደቀውን ስርአተ ትምህርት የሚያካትቱ መደበኛ የመማሪያ ክፍል መመሪያዎች፣ እንቅስቃሴዎች እና ቴክኒኮች ተፈቅደው ከዚህ ፖሊሲ ወሰን ውጭ የሚወሰዱ ናቸው። ህክምናን በመለማመድ እና በተፈጥሮ ህክምና ሊሆኑ የሚችሉ ተግባራትን በማቅረብ መካከል

ከፍተኛ ልዩነት እንዳለ እንረዳለን ። ማንኛውም የታቀደ እንቅስቃሴ የስነ አእምሮ ወይም የስነ-ልቦና ዘዴዎችን ወይም መምህሩ በትክክል በዝያ ሙያ ያልሰለጠና ከሆነ ወይም ፍቃድ ያልተሰጣቸው ሂደቶችን የሚያካትት መሆኑን የሚጠይቅ መምህር ከትምህርት ቤቱ ርእሰመምህር ጋር መማከር አለበት።

**ሐ. ልዩ ትምህርት (ስፔሻል ኤጁኬሽን)ግምገማ**

ልዩ ትኩረት ያለውን ትምህርት አስመልክቶ ግምገማ ለማካሄድና ለስንኩላን ተማሪዎች ተገቢውን አገልግሎት ለመስጠት እና ተመሳሳይ አገልግሎቶችን ለተማሪዎቹ ለመስጠት የወላጆችን ፈቃድ የማግኘት ሁኔታ በግዛት(በስቴት) እና በፌዴራል ህግ ይገዛል። ይህ ፖሊሲ ተጨማሪ ነው እንጂ ማናቸውንም የወላጆችና የተማሪዎች ህጋዊ መብቶችና ግዴታዎችን አይተካም።

**በአእምሮና ፤ስሜት ላይ ተጽህኖ የሚያደርሱና ፤ በህርይ ለዉጥ የሚያመጡ መድሃንቶች**

የትምህርት ቤት ሰራተኞች ለማንኛውም ተማሪ በአእምሮና ፤ስሜት ላይ ተጽህኖ የምያደርሱና ፤ በህርይ ለዉጥ ልያመጡ የምችሉትን መድሃንቶች ማዘዝ ወይም እንዲጠቀም/እንዲትጠቀም ማስገደድ/መጠየቅ/መምከር አይችሉም።

ኖቨምበር 12፣ 2012 ተሻሻለ
ፈቡራሪ 13፣ 2006 ሥራ ላይ ዋለ

ህጋዊ ዋቢዎች፤ C.R.S. 22-32-109(i)(ee) (ሰራተኞች ያለ ወላጅ ፈቃድ የምግባር ምርመራዎችን እንዳያካሂዱ የሚከለክል ፖሊሲን ሥራ ላይ ማዋል) (የትምህርት ቤት ሰራተኞች ለማንኛውም ተማሪ አደንዛዥ እፅን ማዘዝ ወይም አደንዛዥ እፅ እንዲጠቀም/እንዲትጠቀም ማስገደድን/መጠየቅን/መምከርን የሚከለክል ፖሊሲ ሥራ ላይ ማዋል)
C.R.S. 22-1-123 (የተማሪ መብቶችን መጠበቅ አስመልክቶ ድስትሪክት ለፌዴራል ህግ መታዘዝ አለበት፤ የተማሪዎችን የዳሰሳ ጥናት፣ ትንተና እና ግምገማ አስመልክቶ ኮሎራዶ የሚሰጣቸው ህጎች)
C.R.S. 22-32-109.2 (የስሜታዊነት/የአእምሮ መዛባት ወይም ስንኩልነትን መመርመርና ማከም ወይም አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ)
C.R.S.27.10.103 (ለአእምሮ ጤና አገልግሎቶች በፈቃደኝነት ማመልከት)
C.R.S. 13-22-101 (18 ለተወሰኑ ሂደቶች ብቁ እድሜ ነው)
20 U.S.C. 1232(h) (የትምህርት መርጃ መሳሪዎችን መገምገም የሚመለከትና ለዳሰሳ፣ ለጥናትና ለግምገማ አስቀድሞ ማስፈቀድን የሚመለከት የተማሪዎችና የወላጆች መብቶች)
20 U.S.C. 1232(g) (የቤተሰብ የትምህርት መብቶችና የግል ምስጥር መጠበቅ አዋጅ)

ጥምር ዋቢዎች፤ GCS፣ በባለሙያ የሚካሄዱ ጥናትና መርመርና ማሳተም
JID፣ ህጋዊ እድሜ ላይ የደረሱ ተማሪዎች
JLCA፣ የተማሪ የጤና አገልግሎቶች እና መስፈርቶች
JRC፣ የተማሪ ሠነዶች/ የተማሪዎችን መረጃ ለሌላ መስጠት
LC፣ ከየትምህርት ጥናትና ምርምር ድርጅቶች ጋር ያሉ ግንኙነቶች

## ሰውን ማስፈራራት፣ ማዋከብ እና ማዋረድ (ACC)

የትምህርት ቦርድ የሁሉም ሰዎች ደህንነት የተጠበቀና ሌላውን ከማስፈራራት፣ ከማዋከብና ከማዋረድ ወይም አካላዊ ጉዳት ከሚያመጡ ሁኔታዎች ነጻ የሆነ አከባቢ ውስጥ የመኖር መብት እንዲኖራቸው ያረጋግጣል።

ማንኛውም ተማሪ ወይም ሰራተኛ ማንኛውንም ተማሪ፣ ሰራተኛ ወይም ሌላ ሰው በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ወይም በትምህርት ቤት በሚደገፉ ድርጊቶች/ተግባራት ላይ አካላዊና ስሜታዊ ጉዳቶችን በሚያስከትሉ መንገዶች የማዋከብ ወይም የማዋረድ ተግባር ውስጥ መሳተፍ የቦርድ ፖሊሲን መጣስ ነው። በግድየለሽነት ወይም ሆን ብሎ የሌላውን ሰው ስሜት ወይም አካላዊ ጤንነት ወይም ደኅንነት አደጋ ላይ የሚጥል በማንኛውም አስገዳጅ ተግባር የሚያካትት ሌላውን ሰው የማዋረድ ተግባር ውስጥ መሳተፍ በዚህ ህግ የተከለከለውን ሌላውን ሰው ማስፈራራት እና ማዋከብ ተግባራት ውስጥ እንደመሳተፍ ይቆጠራል።

በሥራ ላይ የዋለው፤ ህዳር 8፣ 1999

ህጋዊ ዋቢዎች፤ C.R.S. 18-9-111 (ማዋከብ)
C.R.S. 18-9-124(2)(a) (ማዋከብን መከልከል)

ጥምር ዋቢዎች፤ AC ያለማዳላት/እኩል ዕድል መስጠት ከሌሎች ሰዎች ጋር ያለ ግንኙነቶች
JK የተማሪ ሥርዓት
JKD ተማሪዎችን ከትምህርት ቤት ለጊዜው ማገድ ወይም ማስወጣት

# ሰውን ማስፈራራት፣ ማዋከብ እና ማዋረድ
# (ACC-R)

በትምህርት ቤት አከባቢ የሁሉንም ተማሪዎችና ሰራተኞች ደህንነትና ሰላም ለመጠበቅ በሚደረግ ጥረት፣ የትምህርት ቤቱ ኃላፍ ወይም ተወካይ ከድስትሪክት አስተዳደር ጋር በመሆን ለሁሉም ተማሪዎችና ሰራተኞች ይህንን ፖሊሲ ያሳውቃል፣ በተጨማሪም ተማሪዎችና ሰራተኞች የዚህ ዓይነት ምግባር ይዘትና ውጤት ለማሳወቅ አስፈላጊው ጥረት እንደተደረገም ያረጋግጣል።

ቀጥሎ በተዘረዘሩት በማናቸውም ምግባሮች የተሳተፈ ሰው የማስፈራራት፣ የማዋከብ ወይም የማዋረድ ተግባራትን ይፈጽማል፡

1. አካላዊ ጉዳትን (ጥቃትን) በሚያስከትል ልፊያና አካላዊ ንክኪ ውስጥ መሳተፍ፤ ወይም
2. ከሌላ ሰው ጋር መላፋት፣ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ቢያካትትም በእነዚህ ብቻ አይወሰንም፡ መማታት፣ መጋፋት፣ ለጨወታ ወይም ሆን ብሎ የሌላውን ሰው አካል ወይም ስሜት ሊጎዳ በሚችል መልኩ መራገጥ፣
3. በሌላው ሰው ላይ ትችታዊ አስተያየትን ማቅረብ ወይም አላስፈላጊ የሆኑ አካላዊ እንቅስቃሴዎችን ማሳየት፤ ወይም መሳደብ፣ ማፌዝ (የአሽሙር ቃላትን መጠቀም ) ወይም ሌላውን ሰው መገዳደር፤ ወይም
4. በሚያስፈራ፣ በሚያሳስብ ወይም በሚያስደነግጥ አካሄድ ሌላውን ሰው መከታተል
5. በሰው ላይ አካላዊ ጉዳትን ለማድረስ መዛት
6. ሰውን የማዋረድ ተግባራት ውስጥ መሳተፍ፣ማለትም ረዘም ያለ አካላዊ እንቅስቃሴን ማስገደድ ፣ ማንኛውንም ንጥረ ነገር ከልክ በላይ ፍጆታ ማስገደድ፤ ለብዙ ጊዜ በግዳጅ እንቅልፍ፣ ምግብ፣ ወይም መጠጥ መከልከል፣ ወይም በግድየለሽነት የግለሰብን ጤንነት ወይም ደህንነት አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል፣ በዚህ ባይወሰንም በተማሪዎች መሃል ቡድን ለመፍጥር ዓላማ ሊሆን ይችላል፣ ሌላ ማንኛውም ምግባር መፈጸም

ሰውን ከማስፈራራት፣ ከማዋከብ ወይም ከማዋረድ ጋር የተያያዘ ማንኛውም ዓይነት ክስተት በጊዜ ለትምህርት ቤቱ ኃላፊ ወይም ተወካይ፣ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ለምርመራና ለተጨማሪ  እርምጃ እንዲረዳ ለድስትሪክት አስተዳደርም መጠቆም ያስፈልጋል። የተጣሰው ህግ የትምህርት ቦታን በአሳሳቢ ሁኔታ፣ የህዝብን ሰላምና ጸጥታ፣ ወይም የተማሪዎችና የሰራተኞች ደህንነትና ሰላምን የሚያቃውስና አደጋ ላይ የሚጥል ከሆነ የትምህርት ቤት ኃላፊዎች ተማሪን ከትምህርት ቤት ለጊዜው እንዲያግዱ እና/ወይም እንዲያስወጡ/እንዲያባርሩ መመሪያ ይሰጣቸዋል።

በትምህርት ቤቶች የበላይ አለቃ  Monte C. Moses የተረጋገጠ፣ ህዳር 11፣ 1999።

## ከትንባሆ ነፃ የሆኑ ትምህርት ቤቶች
## (ADC)

የትምህርት ቤቶች ድስትሪክት፣ እንደ የትምህርት ተቋም፣ የትምህርትና ለመልካም ጤንነት ምቹ የሆነ የሥራ ቦታ የመፍጠር ኃላፍነት እንዳለበት፣ እንደዚሁም ትምባሆን መጠቀም በተመለከተ ያለውን እውኔታና ተያያዥ ችግሮችን አስመልክቶ ለተማሪዎች ውጤታማ የሆኑ መርሃ ግብሮችን የማቅረብና መልካም አርያነትን የማሳየት ኃላፊነት እንዳለበት የትምህርት ቦርድ ይገነዘባል።

አጠቃላይ የተማሪዎችና የሠራተኞች ጤንነት፣ ሠላም፣ እና ብልጽግና ለመጠበቅና ለማሻሻል፣ ማጤስ፣ መቃም፣ ወይም ሌላ ማንኛውንም ዓይነት የትምባሆ ምርት በሠራተኞች፣ በተማሪዎች እና በማኅበረሰቡ አባላት መጠቀም በሁሉም ትምህርት ቤቶች ቅጥር ግቢ/ንብረት ውስጥ የተከለከለ ነው።
የሚከተሉት ትርጉሞች ለዚህ ፖሊሲ ዓላማ ይውላሉ።

1. “የትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ/ንብረት”ማለት የድስትሪክቱ ትምህርት ቤት ንብረት የሆነ ነገር ሁሉ፣ በድስትሪክቱ ትምህርት ቤት የተከራየ ወይም ደግሞ በኮንትራት መልክ የሚያገለግል ነገር ሁሉ ሲሆን በእነዚህ ባይወሰንም ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ነገሮች ያጠቃልላል፡

   ሀ. የትምህርት ቤቱ ህንጻዎች በሙሉ እና ማንኛውም በዚያ ውስጥ ያሉ ነገሮች ወይም ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች ለሆኑ ልጆች ለማስተማሪያ ወይም ለቤተ መጻህፍት፣ ለመደበኛ የጤና እንክብካቤ፣ ለመዋእለ-ህጻናት ወይም ለህጻናት ማስተማሪያና ማሳደጊያ አገልግሎቶች፣ እንደዚሁም ለአስተዳደር፣ ለድጋፍ ሰጪ፣ ለጥገና ወይም ለዕቃ ማከማቻ አገልግሎቶች የሚውሉ ቦታዎችን ሁሉ ያጠቃልላል።
   ለ. የድስትሪክቱ ትምህርት ቤት የሚቆጣጠራቸው የትምህርት ቤቱ ይዞታዎች ሲሆን ይህም የትምህርት ቤቱን ቅጥር ግቢ፣ የመጫወቻ ቦታዎች፣ የአትሌትክስ ሜዳዎች፣ የመዝናኛ እና የመኪና ማቆሚያ ሥፍራዎችን ያጠቃልላል።
   ሐ. ተማሪዎችን፣ ሠራተኞችን፣ ጎብኚዎችን ወይም ሌሎች ሰዎችን ለማጓጓዝ ድስትሪክቱ የሚጠቀምባቸው ሁሉም መኪናዎችን ያጠቃልላል።
   መ. በትምህርት ቤት ተግባራትና ዝግጅቶች ላይ።

2. “የትንባሆ ምርቶች” ማለት፤
   ሀ. ክኖቲን ወይም ቶባኮ ያለው ማንኛውም ምርት ሆኖ የሚጨስ፣ የሚዋጥ፣ የሚታኘክ፣ የሚቀባና ወይም በማንኛውም መልኩ የሚጠቀሙት ሲጋራ፣ ሺሻ፣ እና የሲጋራ ዘሮችን ሁሉ የሚያካትት ነው።
   ለ. በእሌክትሮኒክ መልኩ ወደ ሌላ ሰው የሚተላለፍ የእሌክትሮኒክ ሲጋራና ሲጋራ ነክ የሆኑ ምርቶች
   ሐ. “የትንባሆ ምርት” ከትንባሆ ሱስ ለመላቀቅና ሲጋራን ለማቆም የሚረዱና በፌዴራል የተፈቀዱ ምርቶችን አያጠቃልልም።

3. “መጠቀም” ማለት ሥጋራን መለኮስ፣ ማንኛውንም የትምባሆ ምርት መቃም፣ መሳብ ወይም ማጤስ ማለት ነው።

ሥጋራን ማጤስና ማንኛውንም ዓይነት የትምባሆ ምርት በማንኛውም መንገድ መጠቀም በክፍለ ግዛትህግ እና በድስትሪክት ፖሊሲ መሰረት ክልክል እንደሆነ ለማኅበረሰቡ ለማሳወቅ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢና በይዞታዎቹ በሙሉ ውስጥ ምልክቶች ይደረጋሉ። ይህ ፖሊሲ በሰራተኞችና በተማሪ መመሪያ ውስጥ ይታተማል።

ከሥራ ሰዓት በኃላ ትምህርት ቤቱንና ቅጥር ግቢውን ለስብሰባዎች መጠቀም ለሚፈልጉ ሰዎች የእቀባው መረጃ ይሰጣቸዋል።

የድስትሪክቱ የበላይ አለቃ ወይም ተወካይ ይህንን ህግ የጣሰ/ች ማንኛውንም የማኅበረሰቡ አባል ካየ/ች የትምህርት ቤቱን ቅጥር ግቢ/ንብረት ለቆ/ቃ እንዲወጣ/እንዲትወጣ ይሆናል። ይህንን ህግ የጣሱ ሠራተኞች ተገቢው የሥርዓት እርምጃ ይወሰድባቸዋል።

ይህንን ፖሊሲ በሚጥሱ ተማሪዎች ላይ የሚወሰዱ እርምጃዎች በትምህርት ቤት ውስጥ የእገዳ ቅጣት፣ መብታቸውን መገደብና ከተጓዳኝ ትምህርት መከለከል፣ እንደዚሁም ከትምህርት ቤት ማገድን ያጣቃልላሉ። በክፍለ ግዛት ህግ መሰረት፣ ተማሪ የትንባሆ ምርትን ስለተጠቀመ ብቻ ከትምህርት ቤት አይወጣም።

የተደነገገው፣ 1991
ሥራ ላይ የዋለው፣ ይህ መመሪያ በወጣበት ቀን
የተሻሻለው፣ ሴፐተምበር፤ 10፣ 2012

ህጋዊ ዋቢዎች፣ 6 CCR 1010-6, ደንብ 5-306
20 U.S.C. 7181 et.seq. (የ 2001 ማንም ልጅ ወደ ኃላ እንዳይቀር የሚል አዋጅ ሥር የሚገኝ የ 2001 የቅድመ-ልጆች አዋጅ )
20 U.S.C. 3224a, በ1989 የተሻሻለው የ1986 ከአደንዛዥ ዕጽ ነጻ የሆኑ ትምህርት ቤቶችና ማኅበረሰቦች አዋጅ
41 U.S.C. §U§701 እና 702. የ1988 ከአደንዛዥ ዕጽ ነጻ የሆነ የሥራ ቦታ አዋጅ
21 U.S.C. §812 (ቁጥጥር የሚደረግባቸው እጾች ትርጉም)
C.R.S. 18-13-121 (የትንባሆ ምርቶችን ለልጆች መስጠት)
C.R.S. 22.32.109(1)(bb) (በትምህርት ቤቶች ውስጥ ትንባሆን መጠቀም የሚከለክል ፖሊሲ)
C.R.S. 22.32.109.1(2)(a)(I)(H)(ደህንነታቹ የተጠበቀ ትምህርት ቤቶች እቅድ ክፍል የሆነ ፖሊሲ)
C.R.S. 25-14-103.5 (በትምህርት ቤቶች ቅጥር ግቢና ንብረቶች አከባቢ ትንባሆን መጠቀም ክልክል ነው)
C.R.S. 25-14-301 (እድሜያቸው በአስራዎቹ ውስጥ ያሉትን ልጆች ከትንባሆ ምርቶች መጠበቅ የሚመለከት አዋጅ)

ጥምር ዋቢዎች: 4048፣ ከአደንዛዥ ዕጽ ነጻ የሆነ የሥራ ቦታ (የሥራ ባልደረቦች የአደንዛዥ ዕጽና የአልኮል መጠቀም)
IHAMA፣ ስለአደንዛዥ ዕጾች፣ አልኮል መጠጥና ትንባሆ ማስተማር
JICH፣ የተማሪዎች የአደንዛዥ ዕጽና አልኮል መጠቀም
KF፣ የማኅበረሰብ የትምህርት ቤት ህንጻዎችንና ቅጥር ግቢ መጠቀም
KFA፣ በትምህርት ቤት ንብረት/ቅጥር ግቢ ውስጥ
KI፣ የትምህርት ቤት ጎብኚዎች

## በአውቶቡሶች ውስጥ የሚታይ የተማሪ ምግባር
## (JICC)

የትምህርት ቤት አውቶቡስ የመጠቀም መብት የተማሪው/ዋ ጥሩ ምግባር እና በአውቶቡስ ማቆሚያና መሳፈሪያ ሥፍራዎች የተማሪን ምግባር አስመልክቶ የተሰጡትን ደንቦች ማክበር ላይ ይሞረኮዛል።

የትምህርት ቤት አውቶቡስ ሹፌር አውቶቡሱን በሚነዳበት/በሚትነዳበት ጊዜና ተማሪዎች ሲሳፈሩና ሲወርዱ በአውቶቡሱ ውስጥ ላሉት ተማሪዎች ኃላፊነት አለበት።ተማርዎች አዉቶቡስን ሠፈሩና ስጓዙ ለህጉ ተዛዥ መሆነቸዉን መረገገጥ አለበት። ስለዚህ ማንም ተማሪ የተሰጠውን ደንብ በተደጋጋምነት ከጣሰ ጉዳዩን ለአውቶቡሶች ስምርት ክፍል አለቃና ለትምህርት ቤት ኃላፊ ማሳወቅ የሹፌሩ የሥራ ድርሻ ነው።

የትምህርት ቤት ኃላፊው ወይም የስምርት አለቃው የተማሪው/ዋን የትምህርት ቤት አውቶቡስ የመጠቀም መብት ሊከለክሉ/ሏት ይችላሉ። በተጨማሪም ለጥንቃቄና ለሁሉም ደህንነት የተሰጠውን የትምህርት ቤት አውቶቡስ አጠቃቀም ምግባርና ደንብ ከመጣስ የተነሳ በትምህርት ቤት ቦርድ አበሎች ፖሊሲ መሰረት ተማሪው ትምህርት ቤት እንዳይገባ/እንዳይመዘገብ ሊከለከል/ሊትከለከል ይችላል/ትችላለች፤ ከትምህርት ቤት ሊባረር/ሊትባረር ወይም ሊታገድ/ሊትታገድ ይችላል/ትችላለች።

አሁን እየተሰራበት ያለው ህግ የተደነገገው EEAEC ( 1991)
የተሻሻለው ኦገስት 11፤2014
ሕጋዊ ዋቢዎች C.R.S. § 22-32-109.1 (2 a)(I)(B) የተማርዎች የአዉቶብስ ዉስጥ የስነምግባር ኮድ)
C.R.S. § 42-1-102 (88.5) የትምህርት ቤቶች መጓጓዣ አዉቶብሶችን ጨምሮ ትርጓሜ)

ጥምር ዋቢዎች፤EEA የተማርዎች ትራንስፖርት JIC፣ የተማሪ ምግባር፣ እና ናዑስ አንቀጾች
JK፣ የተማሪ ሥርዓት፣ እና ናዑስ አንቀጾች

በትምህርት ቤት ውስጥ ለተማሪ ስኬታማነት መስፈርት ከሆኑ ነገሮች ውስጥ አንዱ በትምህርት ቤት ውስጥ በመደበኛነትና በሰዓት መገኘት ነው። ብዙ ቀሪዎች በትምህርት ሰነፍ መሆን፣ የማኅበራዊ ዕድገት ማነስ እና በትምህርት መውደቅን ሊያስከትሉ ይችላሉ። ለትምህርት ፍላጎት ማደግ፣ ማኅበራዊነትን ለማዳበር እና ለትምህርት ክንውን/ውጤታማነት መደበኛ የትምህርት ክትትል በጣም አስፈላጊ ነው። እንደ ብዙ ጊዜ ማርፈድ ወይም ከትምህርት ቤት መቅረት ይበልጥ በቶሎ የተማሪን የትምህርት ክንውን የሚያዳክም ነገር የለም። ስለዚህ በመደበኛነት በሰዓቱ ትምህርት ቤት መገኘት ከእያንዳንዱ/ዷ ተማሪ ይጠበቃል።

በፌዴራል ህግ መሰረት በስራቸው የሚተዳደረው/የሚትተዳደረው ተማሪ ብቁ ትምህርትና ሥልጠና መውሰዱ/ዷን ማረጋገጥ የእያንዳንዱ ወላጅ/አሳዳጊ ግዴታ ነው።

የቀሪ መብዛት በመማር ሂደት ውስጥ መቀጠልንና ማኅበራዊነትን ማዳበርን በአደገኛ ሁኔታ ሊያናጋ ይችላል። ብዙ ጊዜ ያመለጠ የመማሪያ ክፍል ሥራ በበቂው ሁኔታ አይካካስም። ጥሩ የትምህርት ክትትል ያላቸው ተማሪዎች በትምህርታቸው ጥሩ ነጥብ ያመጣሉ፣ ትምህርትን የበለጠ ይወዳሉ፣ እና ትምህርት ከጨረሱ በኃላ አብዛኛዎቹ ሥራ ያገኛሉ። ቢያንስ ለእነዚህ ምክንያቶች ሙሉ የመማሪያ ክፍል ነጥብ ለማግኘት ተማሪ ማሟላት ያለበትን/ያለባትን ሁለት መሰረታዊ መስፈርቶች እንዳሉ የትምህርት ቦርድ ያምናል። እነሱም፡ (1) ሁሉንም የትምህርት መስፈርቶች ማሟላት እና (2) በዚህ ፖሊሲ ውስጥ እንደተገለጸው ጥሩ የትምህርት ክትትል ልማዶችን ማሳየት ናቸው።

ከተሰጠው ቀን በፊት ለመመረቅ ሁሉንም መስፈርቶች ካላሟሉ በስተቀር፣ ከመዋእለ ህጻናት እስከ 12ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች በሙሉ በተሰጠው የትምህርት ዘመን ውስጥ ትምህርታቸውን መከታተል ይጠበቅባቸዋል።

**የሚታለፉ ቀሪዎች (በፈቃድ ወይም በአሳማኝ ምክንያት መቅረት)**
የሚከተሉት ነጥቦች እንደሚታለፉ ቀሪዎች ይወሰዳሉ።

1. ለጊዜው የታመሙ ወይም አደጋ የደረሰባቸው ተማሪዎች፣ ወይም ከመቅረት በፊት አስቀድሞ በትምህርት ቤቱ የትምህርት ክትትል አስተዳደር ሲፈቀድ ነው። አስቀድሞ ማስፈቀድ የሚቻለው ለቀጠሮዎችና በትምህርት ሰዓት በስተቀር ሊፈጸም የማይችሉ አሳሳቢ ጉዳዮች/ሁኔታዎች ከሆኑ ብቻ ነው።
2. ከአካላዊ፣ ከአይምሮ ወይም ከስሜታዊ ጉዳዮች ጋር በተያያዙ ምክንያቶች ስንኩልነት ያለባቸው ተማሪዎች ለረዥም ጊዜ ቀሪ ሲሆኑ።
3. በትምህርት ቤት ቁጥጥር ሥር ሆኖ እየሰሩ መማር የሚባል መርሃ ግብር ውስጥ የታቀፈ ተማሪ።
4. በአስተዳደሩ አስቀድሞ የተፈቀደና በትምህርት ቤት ወጪ በሚካሄዱ ትምህርተ ነክ ተግባራት ውስጥ የሚሳተፍ/የሚትሳተፍ ተማሪ።
5. ታዋቂ የሆነውን የሀይማኖታዊ በዓል ለማክበር የቀረ/ች ተማሪ።
6. ስለ ተማሪው/ዋ ቀሪ ወላጁ/ጇ ወይም አሳዳጊው/ዋ የትምህርት ቤቱን ኃላፊ ሲጠይቅና ኃላፊው/ዋ ጉዳዩን ሲያረጋግጥ/ሲታረጋግጥ ነው።
7. ከትምህርት ቤት ለጊዜው የታገደ ወይም ወደ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት የተወሰደ/ች ተማሪ።

ድስትሪክቱ ከላይ የተዘረዘሩትን ልዩ ሁኔታዎች በተመለከተ አስፈላጊውን ማረጋገጫ እና የህክምና የጽሁፍ ማስረጃዎችን ሊጠይቅ ይችላል።
ከቤቱ/ቷ ውጪ የሆነ/ች ተማሪ (ጉዳዩ በ 'C.R.S. 22-32-138(1)(e)' በሚባለው እንደተገለጸ፣ ፍርድ ቤት ለመቅረብ ወይም በፍርድ ቤት በታዘዙ ተግባራት ምክንያት ከትምህርት ቤት ከቀረ/ች፣ እንደዚህ ያለ ቀሪ ይታለፋል። ለተማሪው/ዋ የተመደበው/የተመደበችው ማኅበራዊ ጉዳይ ሰራተኛ የተማሪው/ዋ ቀሪ መሆን ፍርድ ቤት ለመቅረብ ወይም በፍርድ ቤት የታዘዘውን/የታዘዘችውን ተግባር ለመፈጸም እንደሆነ ያረጋግጣል/ታረጋግጣለች።

**የማይታለፉ ቀሪዎች (ያለፈቃድ ወይም ያለአሳማኝ ምክንያት መቅረት)**
ከላይ የሚታለፉ ቀሪዎች ስር ከተዘረዘሩ ነጥቦች ውጪ የሆነ ቀሪ የማይታለፍ ቀር ነው። ለጊዜው የታገዱ ወይም የተባረሩ ተማሪዎች ጉዳይ የማይታለፉ ቀሪዎች ይሆናሉ።

ተከታታይ የማይታለፉ ቀሪዎች እና/ወይም በተደጋጋሚ ሁኔታ ማርፈድ ለሥርዓት እርምጃ መቅረብ ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ። በህግ መሰረት፣ ከመማሪያ ክፍል ያልተጠበቁ ቀሪዎችን አስመልክቶ ድስትሪክቱ ትምህርት ነክ የቅጣት እርምጃዎች ሊኖረው ይችላል። ለምሳሌ ማስጠንቀቅያ፤ በትምህርት ቤት እገዳ ልሆን ይችላል። ነገርግን የትምህርት ቅጣት ወይም ከትምህርት ማባረር ወይም ማገድ ቅጣቶች ለማይታለፉ ቀሪዎች መወሰድ የለባቸዉም።አስተዳደሩ አግባብ ያላቸውን ቅጣቶች ለመስጠት የሚያስችሉ የአፈጻጸም ሂደቶችን ያዘጋጃል። ይህ ፖሊስ እና የቀረቡት አስተዳደራዊ ሂደቶች የልዩ ሁኔታ ድንጋጌ እንድኖራቸው ተማሪዎችና ወላጆች/አሳዳጊዎች የትምህርት ቦርዱን በጽሁፍ መጠየቅ ይችላሉ።

ተማሪ ለተወሰነ ጊዜ ቀርቶ/ታ ወደ ትምህርት ቤት ስመለስ/ስትመለስ በወላጅ ፈቃድ እንደቀረ የሚገልጽ የማስረጃ ጽሁፍ ከነፈርማ ከወላጅ ይዞ/ዛ መምጣት አለበት/አለባት። ማስረጃው የወላጅ ሙሉ ስም፣ የቀሪው ቀንና ለስንት ቀን እንደሆነ ማካተት ይኖርበታል። ቀሪዎችን ለማረጋገጥ ስልክ በሚጠቀሙ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የጽሁፍ ማስረጃ አያስፈልግም።

ከትምህርት ቤት ለጊዜው በመባረር ወይም በህመም ወይም በሞት ሀዘን ምክንያት የሚታለፍ የረዥም ጊዜ ቀሪ ካልሆነ በስተቀር፣ በተሰጠው የትምህርት ዘመን ውስጥ ለተከታታይ ስድስት ሳምንታት ወይም ከዚያም በላይ ቀሪ የሆነ/ች ተማሪ እንደ "አቋራጭ" ይወሰድና የትምህርት ድስትሪክቱ ጉዳዩን ለኮሎራዶ የትምህርት ቢሮ ያሳውቃል። ነገር ግን ተማሪው/ዋ በመጨረሻው የትምህርት ዘመን ላይ ከሆነ/ች፣ በሌላ ትምህርት ቤት፣ ከቤት ሆኖ የሚጠና የትምህርት ዓይነት ወይም ወደ ትምህርት ቤት ሳይከድ በኮምፒዩተር በመታገዝ የሚሰጠውን ትምህርት ለመከታተል ከተመዘገበ/ች፣ እንደዚህ/ች ያለ/ች ተማሪ "አቋራጭ" አይባልም፣ ጉዳዩም ለትምህርት ቢሮም አይተላለፍም።በዝህም መሰረት በኮለራዶ ኮድ ኦፍ ረጉላእሽን(1CCR2.01(1) መሰረት በተሰጠው የትምህርት ዘመን ዉስጥ አንድ ተማር ለ10 ተከታታይ ቀናት ከቀረ አስፈላጊ የትምህርት ክትትል ተግባራዊ ይሆናል።
**የማካካሻ ሥራ**
ተማሪውን/ዋን በትምህርት ቤት እና በትምህርት ሂደት ላይ ለማሳተፍ በሚነደርገው ጥረት መሰረት
ከለሳ በሚታለፍ ቀሪ ለቀሩ ተማሪዎች ሊፈቀድ ይችላል። በትምህርት ቤቱ አስተዳደር የተለየ ውሳኔ ካልተሰጠ ወይንም ቀሪው የተከሰተው ከተማሪው/ዋ ከትምህርት ቤት መባረር ጋር ካልተያያዘ በስተቀር ፣ ተማሪው/ዋ በሚታለፍ ቀሪ ያጣቸው/ያጣቻቸው ትምህርቶች በሙሉ መከለስ ይችላሉ። ተማሪው/ዋ ወደ ትምህርት ቤት በሚመለስበት/በሚትመለስበት ቀን የተፈቀደውን ማንኛውንም የከለሳ ምደባ መቀበል የተማሪው/ዋ ኃላፊነት ነው።የትምህርት ቤቱ ረዕሰ መምህር የማካካሻ የጊዜ ሰሌዳዉን ለተማርዉ ያሳዉቃል።

ተማሪዎች በቀሪ ምክንያት ያጡትን ትምህርት ለማሻሻል እንድረዳቸዉና እንድሁም ትምህርት ቤትም እንድመጡ ለማበረታታትም ያለፍቃድ የቀሩትን ተማሪዎችና ለጊዜው ከትምህርት ቤት ለታገዱት ተማሪዎች የማካካሻ ስራ ይሰጣቸዋል።ተማርው/ዋ ለማካካሻው ምን ያህል ዉጤት መግኘት እንዳለበት ወሳኙ የትምህርት ቤቱ ድረክተር ነው።

በትምህርት ቤቱ አስተዳዳር ከልተወሰነ በቀር ከትምህርት ቤት ለታገዱት ተማሪዎች የማካካሻ ስራ አይሰጥም። በአንጻሩ ግን በኮላራዶ ዕግ መሰረት የትምህርት ድስትሪክቱ አማራጭ ትምህርት ይሰጣል።ተማሪው ለማካካሻው ምን ያህል ዉጤት ማግኘት እንዳለበት ወሳኙ የትምህርት ቢሮ/ድስትርክቱ ነው።
**ማርፈድ**
ማርፈድ ማለት ተማሪው/ዋ ያለ አሳማኝ ምክንያት መገኘት ያለበትን/ያለባትን ሰዓት አሳልፎ ትምህርት ከተጀመረ በኃላ ትምህርት ቤት መምጣት ማለት ነው። ማርፈድ በሚያመጣው ረብሻ እና በማያረፍዱ ተማሪዎች ትምህርት አቀባበል ላይ በሚያመጣው ተጽእኖ ምክንያት ማርፈድ ማብዛት ቅጣት ያስከትላል። ማርፈድን አስመልክቶ የሚሰጡት ቅጣቶች በሙሉ ለወላጆች/ለአሳዳጊዎች ይገለጽላቸዋል።

ከአቅም በላይ በሆኔ ሁኔታ በመጀመርያ ክፈለጊዜ መምህር ወይም በትምህርቱ አስተዳዳር እንድዘገይ የተደረገ ተማሪ ለሁለተኛ ክፈለጊዜ ብያረፍድ ከመጀመርያ ክፍለጊዜ መምህር የይለፍ ወረቀት እስከያዘ ድረስ አርፋጅ አትባልም/ባልም።መምህራኖችም በህጉ መሰረት የይለፍ ወረቀቱን መቀበል አለባቸው።ይህ ህግ ለዲስትሪክቱ ተማርዎች ሁሉ ይሰራል።

ሥራ ላይ የዋለው፣ ሴፕተምበር 10፣ 2012

ሥራ ላይ የዋለው፣ ኖቬምበር 10፣ 2008

ህጋዊ ዋቢዎች፡ C.R.S. 22-32-109 (1)(n),(w))(የትምህርት ዘመን ርዝማኔ፣ ትምህርትና ሰዓቱ)
C.R.S. 22-14-101, et. seq.(የተማሪዎች ከትምህርት ቤት ማቋረጥ መከልከልና ለትምህርት ማበረታታት)
C.R.S. 22-33-101, et.seq.(የ1963 የትምህርት ክትትል ሕግ)
C.R.S. 22-32-109.1 (2)(a)(የምግባርና የሥርዓት ሕግ)
C.R.S. 22-32-105(3)(d)(III)(ለጊዜው ከትምህርት ቤት ለተባረሩ ግዜያት የክለሳ ዕድል ማግኘት)
C.R.S. 22-32-138(6)(ቤታቸው ውስጥ ላልሆኑ ተማሪዎች የሚታለፉ ቀሪዎች መስፈርት)
C.R.S. 22-32-109 (1)(n) (የዓመቱ የትምህርት ጊዜ፣ የማስተማርና የክፍለ ጊዜ ብዛት)
C.R.S. 22-33-203 (ከመደበኛው ትምህርት ቤት ለታገዱ ተማሪዎች የሚሰጡ የትምህርት አማራጮችና የነጥብ አሰጣጥ ውሳኔ)
1 CCR 301-67, Rule 2.01 (7) (የ "አቋራጭ" ትርጉም)
1 CCR 301-78 Rules 1.00 et. Seq. (የተማሪን የትምህርት ክትትልና ቀሪ ለመቁጠር የሚረዳ መደበኛ ማስሊያ)
1 CCR 301-78 ደንቦች 1.00 et.seq. (ደረጃውን የጠበቀ የተማሪ የትምህርት ክትትልና ማርፈድ መቁጠሪያ ስሌት)

ጥምር ዋቢዎች፡ JK፣ የተማሪ ሥርዓት
JKD፣ ተማሪዎችን ለጊዜው ከትምህርት ቤት ማስወጣት/ማባረር
JLIB፣ ተማሪን ከማባረር በፊት የሚደረጉ ጥንቃቄዎች
JF፣ የትምህርት ምዝገባ እና ምዝገባን መከልከል
JF-R፣ የትምህርት ምዝገባ እና ምዝገባን መከልከል
JHB፣ የማይታለፉ ቀሪዎች/ያለፈቃድ ከትምህርት ቤት መቅረት
JFC፣ የተማሪ ከትምህርት ቤት መውጣት/ማቋረጥ

ማሳሰቢያ፣ ወሳኝ የሆነውን የትምህርት ክትትል ሕግ ለማጥበቅ፣ ተማሪዎችንና ወላጆችን ለመምከር፣ የትምህርት ክትትል ድክመቶች ምክንያቶችን ለማጣራት፣ እና ግኝቶቹን ለትምህርት ቦርድ ለማሳወቅ እንዲቻል የአከባቢው የትምህርት ቦርድ ለድስትሪክቱ የትምህርት ክትትል ኃላፊ እንዲሾም ሕጉ ያዛል።

## የማይታለፉ ቀሪዎች (ያለፈቃድ/ያለ አሳማኝ ምክንያት) መቅረት (JHB)

ተማሪው/ዋ ያለ ወላጅ ፈቃድ (በፍርማ የተረጋገጠ የጽሁፍ ማስረጃ መኖር አለበት) ከትምህርት ቤት ከቀረ/ች፣ ወይም ያለ አስተማሪው/ዋ ፈቃድ ወይም ከሚመለከተው የአስተዳደር ክፍል ፈቃድ ሳያገኝ/ሳታገኝ ከመማሪያ ክፍል ወይም ከትምህርት ቤት ከወጣ/ች፣ ተማሪው/ዋ ያለ ፈቃድ ከትምህርት ቤት እንደቀረ/ች ይወሰዳል። ቀሪዎች የሚታለፉ ወይም የማይታለፉ በመባል የሚወሰኑት JH. በሚባለው በትምህርት ቦርድ ፖሊሲ መስፈርት መሰረት ነው። ልማዳዊ የሆነ ከትምህርት ቤት ያለፈቃድ መቅረት የሚባለው ትርጉሙ የትምህርት ዕድሜ ላይ የደረሰ/ችና በአንድ ወር ውስጥ በጠቅላላ ለአራት ቀናት የማይታለፍ ቀሪ ያገኘ/ች ወይም በተሰጠው የትምህርት ዘመን ውስጥ ለአስር ቀናት ባልተጠበቀ ሁኔታ ቀሪ የሆነ/ች ተማሪ ነው። የልማዳዊ ቀሪ ሁኔታ የሚወሰነው ያለፈቃድ ቀሪዎች ተዳምረው ወደ ቀናትና ሽርፍራፊ ቀናት ተለውጠው ነው። እነዚህ ቀሪዎች በተሰጠው የትምህርት ዘመን ውስጥ የተለያዩ ጊዜያት ቀሪዎች ጥርቅሞሽ ናቸው፣ ተከታታይ ወይም በአንድ ክፍለ ጊዜ ላይወሰኑ ይችላሉ። ከትምህርት ቤት ለጊዜው በመታገድ ወይም በመባረር የሚሆኑ ቀሪዎች በማይታለፉ ቀሪዎች ውስጥ አይካተቱም።

ልማዳዊ በሆነ ሁኔታ ከትምህርት ቤት ያለፈቃድ በመቅረት የታወቀ ተማሪ ትምህርት ቤት ውስጥ እንዲቆይ ለማገዝ ይታቀዳል። ከተቻለም የጉዳዩ አሳሳቢነት ደረጃ አስፈላጊ ካላደረገው በስተቀር፣ የልጁ/ጇ ወላጆች፣ አሳዳጊዎች፣ ወይም ሕጋዊ ጠባቂዎች/ባለአደራዎች ከድስትሪክቱ ሰራተኞች ጋር ተባብረው በእቅዱ እንዲሳተፉ ይጠበቃሉ። የሚመለከተው የትምህርት ቤት የአስተዳደር ክፍል ከወላጆች፣ ከአሳዳጊዎች፣ ወይም ከሕጋዊ ጠባቂዎች/ባለአደራዎች ጋር ተገናኝቶ አብሮ የልጁ/ጇን ያለፈቃድ ከትምህርት ቤት መቅረት ምክንያቶች ለመመርመር አስፈላጊውን ጥረት ሁሉ ያደርጋል/ታደርጋለች።

ያለ ፈቃድ ከትምህርት ቤት የመቅረት ክስተቶችን ለመቀነስ ለትምህርት ቤት ዕድሜ የደረሱ ተማሪዎች ትምህርት ቤት በተገቢው ሁኔታ እንዲከታተሉ የማረጋገጥ ግዴታ እንዳለባቸው በእያንዳንዱ የትምህርት ዘመን መጀመሪያ ላይ ለሁሉም ተማሪዎች ወላጆች በጽሁፍ ይገለጽላቸዋል። ወላጆች ይህን ግዴታቸውን ተረድተው መቀበላቸውን በጽሁፍ እንዲገልጹ እና ትምህርት ቤቱ በትምህርት ሰዓት ሊያገኛቸው የሚችልበትን የስልክ ቁጥሮችና ሌሎች የመገናኛ መንገዶች ለትምህርት ቤቱ እንዲሰጡ ይጠበቅባቸዋል።

ሁሉም የዲስትሪክት ትምህርት ቤቶች በግለሰብ ሰበብ እና ያለምክንያት መቅረትን የሚቆጣጠርበት ስርዓት መዘርጋት አለባቸው። ተማሪው በመደበኛነት በተያዘለት የትምህርት ቀን ሪፖርት ካላደረገ እና የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ወላጅ/አሳዳጊ መቅረቱን እንደሚያውቁ የሚጠቁም ምንም ፍንጭ ካላገኙ፣የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ወይም ተወካዮቻቸው ለወላጅ/አሳዳጊ በስልክ፣በፅሁፍ ለማሳወቅ ምክንያታዊ ጥረት ማድረግ አለባቸው። መልእክት, ወይም ኢሜይል.የተማሪው/ዋን ከትምህርት ቤት መቅረት ምክንያት በተመለከተ አግባብ ያለውን የማስተካከያ እና/ወይም የሥርዓት እርምጃን በጊዜው እየወሰደ ትምህርት ቤቱ የተማሪን የማይታለፍ ቀሪ ምክንያት ለመወሰን ጥረት ያደርጋል።

በህግ መሰረት፣ ድስትሪክቱ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት በሚቀሩበት ጊዜ ለሚያመልጣቸው ትምህርቶች ተመጣጣኝ የሆኑ ቅጣቶችን ሊሰጥ ይችላል። ቅጣቶቹም ማስጠንቀቂያ፣ ከትምህርት ቤት መታገድ፣ በትምህርት ቤት ውስጥ መታገድ፣ ወይም ከትምህርት ቤት ከማገድ ፈንታ ሌሎች አማራጮችን መውሰድ ያካትታል። ለማንኛውም ቀሪ ምክንያት የትምህርት ቅጣቶች፣ ከመደበኛው ትምህርት ቤት ማገድ ወይም ወደ አማራጭ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት መላክ ቅጣቶች አይሰጡም።
የዲስትሪክቱ አስተዳደር ተደጋጋሚ መቅረትን ለመፍታት አግባይ ያልሆኑ ስልቶችን እና ሂደቶችን ለመተግበር ደንቦችን ያወጣል።

በመጀመሪያ የተሻሻለው ዲሰምበር 10፤2007
ኤፕሪል 12፣ 2010 ተሻሻለ
ዲሰምበር 10፣ 2007 ሥራ ላይ ዋለ
የቅርብ ጊዜ መሻሻል ጃንዋሪ 8፤2024

ሕጋዊ ዋቢዎች፤ C.R.S. 22-14-101፣ ቀጣይ (የተማሪን ትምህርት ማቋረጥ መከልከልና ወደ ትምህርት መመለስ)
C.R.S. § 22-32-109(1)(p)(የአተንዳንስ መኮንን ለመሾም መስፈርቶች )
C.R.S. 22-33-204 (የግዴታ የትምህርት ቤት ክትትል)
C.R.S. 22-33-105 (ለጊዜ ከትምህርት ቤት መታገድ፣ መባረር ወይም ምዝገባን መከልከል)
C.R.S. 22-33-107 (የግዴታ የትምህርት ቤት ክትትልን ማጥበቅ)
CCR 301-66፣ 7 Rule 2.01 (7) "(አቋራጭ" ትርጉም)
CCR 301-78 Rules 1.00 et.seq. (የተማሪን የትምህርት ክትትልና ቀሪ ለመቁጠር የሚረዳ መደበኛ ማስሊያ)

ጥምር ዋቢዎች፤ IHBG፣ የቤት ትምህርት
JEA፣ የግዴታ የትምህርት ክትትል ዕድሜ
JH፣ የተማሪ ቀሪዎችና የሚታለፉ ቀሪዎች
JFC፣ ተማሪ ከትምህርት ቤት/ትምህርት መውጣት

## የተማሪ ምግባር
## (JIC)

ተማሪዎች፣ አስተማሪዎች፣ አስተዳደሮች እና ሌሎች የድስትሪክቱ ሰራተኞች እያንዳንዳቸው መልካም የመማሪያ ቦታና አከባቢ እንዲሆን አስተዋጽኦ የማድረግ ግዴታ አለባቸው።

የትምህርት ቦርዱ ዓላማ ተማሪዎች ከፍተኛውን የግላዊ እውቀት፣ ችሎታና ብቃት እንዲያጎለብቱ፣እንደዚሁም ኃላፊነት እንዲኖራቸው የሚያስችልና የሚጠቅሙ/የሚረቡ የማኅበረሰቡ አባላት እንዲሆኑ የድስትሪክቱ ትምህርት ቤቶች አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርጉላቸው ነው።

ቦርዱ፣ በክፍለ ግዛት ሕግ ላይ በመመሰረት፣ እያንዳንዱ ተማሪ ኃላፊነት ያለባቸውን ሰዎች እንዲያከብራቸው/እንዲታከብራቸው እና እንዲታዘዝላቸው/እንዲትታዘዝላቸው ይጠበቅበታል/ይጠበቅባታል በሚል ህግጋት ላይ በመሞርኮዝ፣በጽሁፍ የተማሪዎችን የምግባር ሕግ አውጥቶ ያጸድቃል። ሕጉ በተጨማሪም የተወሰኑ ምግባራት፣ በተለይም የመማሪያ ክፍል እና አከባቢን የሚያውክ ምግባር ተቀባይነት እንደሌለውና የስነ- ሥርዓት ማጣት እርምጃም ሊያስከትል እንደሚችል ያተኩራል። ሕጉ ለሁሉም ተማሪዎች በአንድ አይነት መልኩ፣ ፍትሃዊና ጽኑ በሆነ መንገድ ሥራ ላይ የሚውል ይሆናል።

ቦርድ ያወጣቸው ፖሊሲዎች በሙሉና ቦርድ ያጸደቃቸው መተዳደሪያ ደንቦች በሙሉ እና የፋይል ስሙ ውስጥ 'JIC' የሚባሉትን ፍደላትን የያዙ ሁሉ  በሕግ የሚያስፈልግ የምግባር ክፍል እንደሆኑ ይወሰዳሉ።

ወላጆች፣ ተማሪዎች፣ አስተማሪዎች፣ አስተዳደሮች እና ሌሎች የማኅበረሰብ አባላት የምግባር ሕግ ሲዘጋጅ እንዲመክሩበት ይጋበዛሉ።

የመተዳደሪያ ደንቦቹ በሕገ መንግስት ውስጥ የተቀመጡትን መብቶች የሚጥሱ መሆን የለባቸውም፤ በግልጽና በውስን/በተለይ መገለጽ ይኖርባቸዋል፣ ለተማሪዎችና ለወላጆች/ለአሳዳጊዎች እንዲደርሳቸው የመተዳደሪያ ደንቦቹ በመጽሃፍ መልክ መታተም ወይም በሌላ ህትመት መልክ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፣ የታተመው የመመሪያ ደንብ መጽሃፉ ከተሰራጨ በኃላ ሥራ ላይ የሚውልበት ቀን መኖር አለበት።

የምግባርና የሥርዓት ሕጉ ለእያንዳንዱ የመጀመሪያ፣ የመለስተኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተማሪ አንደ መሰራጨት አለበት፤ በድስትሪክቱ አዲስ ለሆነ/ች ተማሪም አንደ መሰጠት አለበት። ግልባጮቹም በድስትሪክቱ እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ውስጥ መለጠፍ ወይም ከፋይል ጋር መያያዝ ይኖርባቸዋል። በተጨማሪም ከሕጉ ውስጥ የተሻሻለ ዋና ጉዳይ ካለ ለእያንዳንዱ ተማሪ መሰራጨትና በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ውስጥ መለጠፍ ይኖርበታል።

አስተማሪዎች ሥርዓት ያለው የመማሪያ ክፍል እና ውጤታማ የሆነ የመማሪያ አከባቢ እንዲፈጥሩ ይጠበቅባቸዋል።አስተዳደሩና ሌሎች የድስትሪክቱ ሰራተኞች ያንን ውጤታማና ሥርዓት ያለውን የመማሪያ አከባቢ ለመጠበቅ ለአስተማሪው/ዋ አስፈላጊውን ድጋፍና እርዳታ ያደርጋሉ። የድስትሪክቱ ሰራተኞች በሙሉ የተማሪዎችን ምግባር የመቆጣጠርና ለወጣው የምግባር መተዳደሪያ ደንቡ መታዘዛቸውን የመከታተል ኃላፊነታቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል።

ተማሪዎች የወጣውን የትምህርት ፕሮግራም/መርሃ ግብር መከታተል ይኖርባቸዋል፤ በትምህርት ቤት ውስጥ ሲገኙም የራሳቸውንም ሆነ የሌላውን ትምህርት እንዳያደናቅፉ ጥሩ ሥርዓትና ምግባር እንዲኖራቸው ይጠበቅባቸዋል። ተማሪዎች አስተማሪዎችን፣ አስተዳደሮችን፣ ሌሎች የድስትሪክት ሰራተኞችንና አብረው የሚማሩትን ተማሪዎች ማክበር እና በትምህርት ቤት መገኘታቸውም ውጤታማ የሆነውን የትምህርት አከባቢ እንዳያደናቅፍ መጠንቀቅ ይጠበቅባቸዋል።ተማሪዎች የድስትሪክት፣ የትምህርት ቤት እና የመማሪያ ክፍል ደንቦችን እንዲያከብሩ ይጠበቅባቸዋል።

ማንኛውም ድርጅት በትምህርት ቦርድ ፈቃድ ወይም ያለ ትምህርት ቦርድ ፈቃድ በትምህርት ቤት የሕግ ሥልጣን ውስጥ ገብቶ ሌሎችን የማዋረድ ወይም ተመሳሳይ ድርጊቶች ውስጥ መሳተፍ አይችልም። ሆን ብለው በፈቃዳቸው ይህንን ፖሊሲ የሚጥሱ ተማሪዎች ጉዳዩ በወጣው የመተዳደሪያ ደንብ መሰረት ለቅጣት ለአስተዳደር ይተላለፋል።

የተሻሻለው፣አገስት13፣ 2012
ሥራ ላይ የዋለው፣ አክቶበር  10፣ 2000

| | |
|---|---|
| ሕጋዊ ዋቢዎች፡ | C.R.S. 22-32-109-1 (2)(ሀ) (ደኅንነቱ የተጠበቀ ትምህርት ቤቶች እቅድ አካል የሆነ አስፈላጊ ፖሊሲ)<br>C.R.S. 22-32-109.1(2)(ሀ(የምግባርና የሥርዓት ህገ-ደንቡን ለተማሪ ለማሳወቅ ድስትሪክቱ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል)<br>C.R.S. 22-33-106 (1)(ከሀ-ረ) (ለጊዜው ከትምህርት ቤት ለመታገድ፣ ለመባረር ወይም ምዝገባን ለመከልከል መሰረቶች/ምክንያቶች የሚሆኑ) |
| ጥምር ዋቢዎች፡ | JICDA፣ የምግባር ሕግ<br>JIC፣ ናዑስ ሕግጋት (የተማሪ ምግባር)<br>JK፣  የተማሪ ሥርዓት<br>ACC፣ ማስፈራራት፣ ማዋከብና ማዋረድ |

## የተማሪን ምግባር ለመቆጣጠር የቪዲዮ ካሜራን መጠቀም
## (JICA)

የትምህርት ቦታ ምግባርን ለመጠበቅና ለማሻሻል፣ እንደዚሁም የሰራተኞቹንና የተማሪዎቹን ጤንነት፣ ሰላምና ደኅንነት ለማሻሻል ድስትሪክቱ በተከታታይ ኃላፊነቱን እየተወጣ መሆኑን የትምህርት ቦርድ ይረዳል።

የተማሪዎችን የግል ምስጥር መብቶች ከድስትሪክቱ ሥራ ጋር በጥንቃቄ ካመዛዘነና ካመጣጠነ በኃላ፣ የሰራተኞችንና የተማሪዎችን ምግባር፣ ጤንነት፣ ሰላምና ደኅንነት ለማሻሻል፣ ቦርዱ በማጓጓዣ ተሽከርካሪዎቹና በድስትሪክቱ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የቪዲዮ ካሜራን መጠቀም ይደግፋል።

የቪዲዮ ካሜራዎች በትምህርት ቤት ህንጻዎች ውስጥ እና ወደ ትምህርት ቤትና ከትምህርት ቤት ተማሪዎችን በሚያጓጉዙ የትምህርት ቤት ተሽከርካሪዎች ውስጥ የተማሪን ምግባር ለመቆጣጠር ሊጠቅሙ ይችላሉ።

የምግባር ደንቦች የሚጥሱ ተማሪዎች በወጣው የቦርድ ፖሊሲ እና የተማሪ ምግባርና ሥርዓትን በሚቆጣጠሩ የመተዳደሪያ ደንቦች መሰረት የሥርዓት (የድሲፕሊን) እርምጃ ይወሰድባቸዋል።

በድስትሪክቱና በሕግ በተደነገገው መሰረት የሚቀረጹ ቪዲዮዎች እንደ የተማሪው ምግባር ሰነድ ሆነው ሲያዙ፣ የቪዲዮ ቀረጻን በተመለከተ ድስትሪክቱ የሚመለከተውን የክፍለ ግዛትና የፌዴራል ሕጎችን ያከብራል።

የቪዲዮ ካሜራዎች ሥርዓት እና የተማሪዎች፣ የሰራተኞችና የንብረት ደኅንነት ለማሻሻል ብቻ ጥቅም ላይ መዋል አለበት።

የቀረበው፤ ጃንዋሪ11፣ 1999
ሥራ ላይ የዋለው፤ ፌቡራሪ 8፣ 1999
የጸደቀበት ቀን ፌቡራሪ 8፣ 1999

ሕጋዊ ዋቢዎች: 20 U.S.C. 1232g (በ1974 የወጣው የቤተሰብ የትምህርት መብትና የግል ምስጥር መጠበቅ አዋጅ)
42 U.S.C. 1201 ተከታታይ (የአሜሪካዊ አካለ ስንኩላን አዋጅ)
34 C.F.R. 99.1 ተከታታይ (መተዳደሪያ ደንቦች)

**የተማሪ ሰነዶች**

1. የቪዲዮ ቀረጻዎችን አስመልክቶ በድስትሪክቱ ሥራ ላይ የሚውሉትን የተማሪ ሰነዶች መስፈርቶች በተመለከተ ድስትሪክቱ ፌዴራልና ክፍለ ግዛት የሚሰጠውን ሕግን ያከብራል። እንደ የተማሪ ምግባር ሰነድ አካል የሚያዙ የቪዲዮ ቀረጻዎችን ማግኘት፣ መከለስ/ማየት እና ለሌላው ወገን መስጠት የሚቻለው የተሰጠው የተማሪ ሰነድ ማግኛ ሂደቶችን ተከትሎ ይሆናል።

2. ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤትና ከትምህርት ቤት በሚያጓጉዙ ተሽከርካሪዎች ውስጥ፣ በተጓዳኝ ትምህርት ተግባራት መፈጸሚያ ቦታዎችና በድስትሪክቱ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የቪዲዮ ካሜራዎች እንዳሉ ድስትሪክቱ በወላጅ/ተማሪ መመሪያ መጽሐፍ ውስጥ አስገነዝቧል። ድስትሪክቱ የቦርድ ቪዲዮ ካሜራ ፖሊሲ እና መተዳደሪያ ደንቦችን ግልባጭ ለተማሪዎችና ለወላጆች እንደ የማሳሰቢያ አካል አድርጎ አካትቷል።
3. በድስትሪክቱ ተሽከርካሪ ውስጥ ያለው የቪዲዮ ካሜራ ሥራ ላይ ሲሆን ለተማሪዎች ላይነገር ይችላል። የቪዲዮ ካሜራ ቁሳቁሶች በሚሰሩባቸው የትምህርት ቤት ህንጻዎች በሙሉ ውስጥ የቪድዮ ካሜራ እንዳለ የሚያመላክት ምልክት ይደረጋል።

**ማከማቻ/ጥንቃቄ**

1. የቪዲዮ ቀረጻዎች በሙሉ በጥብቅና በተጠበቀ ሁኔታ ይከማቻሉ/ይቀመጣሉ።

2. የተቀረጹት ቪዲዮዎች ለአምስት ቀናት ይቀመጣሉ፣ ከዚያ በኃላ ቀረጻዎቹ ሊጠፉ ይችላሉ።

3. የተማሪ ክስተቶች በተመለከተ የተቀረጹ ቪዲዎች ጉዳዩ እልባት እስኪያገኝ ድረስ በዋና መልኩ ይቆያሉ። ከዚያ በኃላ የተቀረጹ ምስሎች በተሰጠው የድስትሪክት ሂደት መሰረት እንደ አስፈላጊነቱ እንዲወገድ ወይም እንደ የተማሪ ምግባር ሰነድ አካል ሆኖ እንዲቆይ ይደረጋል።

**አጠቃቀም**

1. የቪዲዮ ካሜራዎች ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤትና ከትምህርት ቤት በሚያጓጉዙ የትምህርት ቤት ተሽከርካሪዎች ውስጥ ወይም የተጓዳኝ ትምህርት ተግባራት በሚፈጸሙበት ቦታዎች አከባቢ በስምሪት ክፍል ኃላፊ ውሳኔ መሰረት ይደረጋሉ። ተማሪን ለመቆጣጠር ዓላማ ሲባል የቪዲዮ ካሜራዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ለማሳወቅ በትምህርት ቤት አውቶቡሶች ውስጥ ማሳሰቢያ ሊለጠፍ ይችላል። በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ህንጻዎች ውስጥ ቪዲዮ ካሜራዎች በተከታታይ ይኖራሉ፤ እንደዚሁም ድስትሪክቱ አስፈላጊ ነው ብሎ ባመነባቸው በሌሎች ትምህርት ቤቶችና ህንጻዎች ውስጥም የቪዲዮ ካሜራዎች ሊኖሩ ይችላሉ።

2. ሰራተኞችና ተማሪዎች በቪዲዮ ካሜራ ቁሳቁሶችን ውስጥ መቀየር አይፈቀድላቸውም፤ እንድሁም ጣልቃ መግባት አይችሉም ።

**በቪዲዮ ካሜራ የተቀረጹትን ምስሎች ለማየት መጠየቅ**

1. የቪዲዮ ካሜራ ቀረጻዎችን ማየት የሚፈቀድላቸው አግባብ ያለው የአውቶቡስ ሾፌር፣ የትምህርት ቤት የስምርት ክፍል ኃላፊ፣ የትምህርት ቤት አስተዳደር፣ የዲስትሪክት እንሹራንስ አቅራቢዎች፣ ሕግ አስከባሪዎች፣ ወላጅ/አሳዳጊ ወይም መስፈርት የሚያሟላ ተማሪ (18 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ)፣ ወይም የትምህርት ቤት ኃላፊ፣ የኃላፊ ተወካይ፣ ወይም ምክትል የበላይ አለቃ እንዲያዩ የሚፈቅዱላቸው ሌሎች ሰዎች።

2. የቪዲዮ ካሜራ ቀረጻዎችን ለማየት እንዲፈቀድ ጥያቄ የሚቀርበው ከተቀረጸበት ቀን ጀምሮ በአምስት ቀናት ውስጥ ለትምህርት ቤት ስምርት ክፍል ኃላፊ፣ ለትምህርት ቤት ኃላፊ፣ ለኃላፊ ተወካይ፣ ወይም ለምክትል የበላይ አለቃ ነው።

3. የቪዲዮ ካሜራ ቀረጻዎችን ማየት የሚችሉ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ ተማሪዎች፣ ሾፌር እና በትምህርት ቤት ኃላፊ፣ የኃላፊ ተወካይ፣ ወይም ምክትል የበላይ አለቃ ፈቃድ መሰረት ለሥራ ሂደቶች/ጉዳዮች ሲባል የዲስትሪክት ኃላፊዎች ናቸው።

4. ለማየት የሚፈቀደው ውስን ክስተት የሚመለከት የቪዲዮ ካሜራው ቀረጻ በከፊል ነው።

5. ቀረጻዎቹን ለማየት ጥያቄ ከቀረበበት ቀን አንስቶ በአምስት የትምህርት ቀናት ውስጥ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ መልስ ለጠያቂው/ዋ ይገለጻል።

6. የጥያቄው አዎንታዊ መልስ ከጸደቀበት ቀን አንስቶ ቀረጻው በአምስት የትምህርት ቀናት ውስጥ እንዲታይ ይቀርባል።

**ማየት**

1. የቪዲዮ ቀረጻዎች እንዲታዩ የሚፈቀድባቸው ቦታዎች የትምህርት ቤት ስፍራዎች ሲሆን የስምሪት ቢሮ፣ የትምህርት ቤት ህንጻዎች፣ ወይም የአስተዳደር ቢሮዎች ሊሆን ይችላል።

2. ሁሉም የቪዲዮ ቀረጻዎች ሲታዩ አግባብ ካላቸው የድስትሪክት አስተዳደሮች ጋር ነው።

3. ቪዲዮ ቀረጻው ሲታይ የታየበት ቀን፣ የታየበት ምክንያቶች፣ ቀረጻው የተካሄደበት ቀን፣ ቀረጻው የተካሄደበት ተሽከርካሪ፣ የሾፈሩ ስም፣ እና ቀረጻውን ያየ ሰው ፊርማ ያካተተ ቅጽ መሞላት አለበት።

4. የቪዲዮ ቀረጻዎቹ የድስትሪክቱ ንብረት ይሆናሉ፤ ቀረጻዎቹም የሚካሄዱት በሕግ መሰረት እና በትምህርት ቤቶች የበላይ አለቃ ፈቅድ ነው።

በትምህርት ቤቶች የበላይ አለቃ Robert D. Tschirki የካቲት 8፣ 1999 ጸደቀ።

ጥራት ላለው የትምህርት ፕሮግራም (መርሃ ግብር) ደኅንነቱ የተጠበቀ እና ሥርዓት ያለው የመማሪያ አከባቢ ወሳኝ ነው። የተማሪ የደንብ ልብስን አስመልክቶ የድስትሪክት መስፈርቶች የወጡበት ዓላማ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ሥራ ላይ እንዲያተኩሩ፣ የሥርዓት ጉድለቶችን/ ችግሮችን ለመቀነስ፣ እና የትምህርት ቤት ሥርዓትና ደኅንነት ለማሻሻል እንዲረዳ ታስቦ ነው። ተማሪዎች በአለባበሳቸው እና በግላዊ ገጽታቸው (መልካቸው) ራሳቸውን የመግለጽ መብት እንዳላቸው የትምህርት ቦርዱ ይረዳል፤ ነገር ግን ተማሪዎች የመማሪያ ክፍል አከባቢን ሊረብሽ የሚችል ወይም ለትምህርት ቤት ደኅንነት እና ሥርዓት የማይመች ልብስ መልበስ የለባቸውም።

ይህንን የደንብ ልብስ ሥርዓት የጣሰ/ች ተማሪ አግባብ ባለው ልብስ እንዲቀይር ይገደዳል ወይም በአስቸኳይ አግባብ ያለው ልብስ ትምህርት ከቤት እንዲመጣለት ይሆናል። በዚህ ሁኔታ፣ ሌላ ተጨማሪ ቅጣት አይኖርም።

በመጀመሪያው የደንብ ልብስ መተላለፍ ተማሪው/ዋ ሥርዓት ካልያዘ/ች፣ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ለተማሪው/ዋ ተሰጥቶ የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ጉዳዩን ለተማሪው/ዋ ወላጆች/አሳዳጊዎች ያሳውቃል። የደንብ ልብስ ሥርዓትን በድጋሚ የጣሰ/ች ተማሪ በትምህርት ቤቱ የአስተዳደር ቢሮ ውስጥ እንዲቆይ/እንዲትቆይ እና የትምህርት ሥራው/ዋን እዚያው እንድያካሂድ/እንዲታካሂድ ይሆናል-በትምህርት ቤት ውስጥ መታገድን ያካትታል-ጉዳዩን አስመልክቶም ከወላጆች/ከአሳዳጊዎች ጋር ውይይት ይደረጋል። ለሦስተኛ ጊዜ የደንብ ልብስ ሥርዓትን የተላለፈ/ች ተማሪ ከትምህርት ቤት እንዲታገድ/እንዲትታገድ ሊሆን ይችላል ወይም በትምህርት ቤት የሥርዓት ሕግ ውስጥ በተቀመጡት ተገቢ የሥርዓት እርምጃዎች መሰረት ሌሎች የሥርዓት እርምጃዎች ሊወሰዱ ይችላሉ።

በትምህርት ቤት ህንጻዎች ውስጥ፣ በትምህርት ቤት ቦታዎች (ቅጥር ግቢ) ውስጥ፣ ወይም በትምህርት ነክ ተግባራት አከባቢ የሚከተሉት ነገሮች ተቀባይነት የላቸውም።

1. ሆድ፣ ትከሻ፣ የመቀመጫ አካል፣የላይኛውን የጭን (የታፋ) ክፍል፣ ጀርባ እና ደረት (ጡት) እና ሌሎች መገለጥ የሌለባቸውን የሰውነት ክፍሎች የሚገልጡ (የሚያሳዩ) አግባብ የለላቸው በጣም ቀጭን ወይም ሲስ፣ ጠባብ፣ አጭር እና የመሳሰሉ ልብሶች።

2. ከታች እንደተዘረዘሩት ማንኛውም ዓይነት ማስታወቂያ፣ ምልክት፣ ቃላት፣ መፈክሮች፣ ልጥፎች፣ ወይም ሥዕሎች ያሉባቸው ልብሶች፣ ነገሮች፣ ጌጣጌጥ፣ የጽም አቆራረጥ፣ የጸጉር ቀለም፣ ወይም የሰውነት ማጌጫዎች፡

- አሳፋሪ፣ ብልግና፣ ልቅ ምግባራትን የሚያሳዮ ልብሶች እና ሌሎች ነገሮች፣
- የማንኛውንም ሰው ደኅንነት እና ሰላም የሚያናጉ ሁኔታዎች በሙሉ፣
- በተማሪ የምግባር ሕግ የተከለከሉትን ድርጊቶች የሚቀሰቅሱ ሁኔታዎች በሙሉ፣
- አደንዛዥ ዕጽ፣ ትምባሆ፣ እና አልኮል ለመጠቀም ወይም ትጥቆችን (መሳሪያዎችን) ለመያዝ የሚቀሰቅሱ ሁኔታዎች በሙሉ፣
- ወሲባዊ ስሜቶችን የሚቀሰቅሱ ሁኔታዎች በሙሉ፣
- በቀለም፣ በንግድ ምልክት፣ ወይም ሌላ የአባልነት መለያን በሚያመላክቱ ሁኔታዎች እና እቅዶች ቡድን በመፍጠር አደንዛዥ ዕጽ መጠቀምን እና ሁከትን የሚያራምዱ ወይም ምግባረ ቢስ የሆኑ አደገኛ ቦዘኔዎች፣
- ወይም የመማር ማስተማር ሂደትን የሚያናጉ ሁኔታዎች በሙሉ።

በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ሁልጊዜ ጫማ ማድረግ ግዴታ ነው።

**ልዩ ሁኔታዎች**

አግባብ ያላቸው የአትሌትክስ ትጥቆች በሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት ክፍል ውስጥ ሊለበሱ ይችላሉ። በትምህርት ቤት ውስጥ የሚካሄዱ የተጓዳኝ ትምህርት ተግባራት ላይ ወይም የስፖርት ተግባራት ጊዜያት ሌላ ጊዜ የሚለበሱ (አስቂኝ የሆኑ እና ከተግባራቱ ጋር የሚሄዱ ማልያ ልብሶች እና የመሳሰሉት ልብሶችን)ተግባራቱን በሚያካሄዱ ሰዎች (ክፍሎች) ወይም በአሰልጣኝ ከተፈቀደ በትምህርት ቤት ውስጥ ሊለበሱ ይችላሉ።

የትምህርት ቤት ኃላፊዎች፣ ከትምህርት ቤቱ የተጠያቂነት ኮሚቴ ጋር በመሆን፣ በዚህ ፖሊሲ ውስጥ በተቀመጡት መመዘኛዎች መሰረት እንደ የትምህርት ቤት የመተዳደሪያ ደንብ አካል አድርገው የተወሰኑ አግባብ ያላቸው የትምህርት ቤት ልብስ ደንቦችን ማውጣት እና ሥራ ላይ ማዋል ይችላሉ።
ረቂቅ ህገ-ደንቡ የወጣው፤ ኦገስት 14፣ 2000
ሥራ ላይ የዋለው፤ ሰፕተምበር 11፣ 2000
የተሻሻለው፤ሴፕተምበር 10፣ 2012

ህጋዊ ዋቢዎች፤ JBB፣ ወሲባዊ ትንኮሳ
JIC፣ የተማሪ ሥነ-ምግባር
JICDA፣ የሥነ-ምግባር ህገ-ደንብ
JICF፣ የውንብድና ሥራዎች
JICH፣ እጽና የአልኮል መጠጦችን የሚጠቀሙ ተማሪዎች
JICI፣ የጦር መሳሪያዎችን/ትጥቆችን ወደ ትምህርት ቤት ማምጣት
JK፣ የተማሪ ሥርዓት
JKD/JKF፣ ከትምህርት ቤት መታገድ/ወደ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት መላክ
JLI፣ የተማሪ ደኅንነት
JICDE፣ የተማሪን ማስፈራራት/መበደል መከልከልና ትምህርት መስጠት

ትምህርት ቤቶች ምቹ የትምህርት ቦታዎች እንዲሆኑ፣ የተማሪዎች እና የሰራተኞች ደኅንነት እና ሰላም የተጠበቁ እንዲሆኑ እና የትምህርት ቦታዎች አላስፈላጊ ከሆኑ ረብሻዎች ነጻ እንዲሆኑ የትምህርት ቦርድ ይሻል።

ተማሪዎች የሚሰጠውን የትምህርት ፕሮግራም መከታተል አለባቸው፣ እንደዚሁም ምግባራቸው የራሳቸውን እና የየሌሎችን የመማር ማስተማር ሁኔታ የሚያናጋ መሆን የለበትም። ተማሪዎች አስተማሪዎችን፣ አስተዳደሮችን፣ ሌሎች የድስትሪክት ሰራተኞችን እና ሌሎች ተማሪዎችን (ጓደኞቻቸውን) ማክበር ይኖርባቸዋል፤ እንደዚሁም በትምህርት ቤት መገኘታቸው ውጤታማ የሆነውን የትምህርት አከባቢን የሚያናጋ መሆን የለበትም። ተማሪዎች የዲስትሪክት፣ የትምህርት ቤት እና የመማሪያ ክፍል ደንቦችን ማክበር አለባቸው።
(የ JIC ፖሊሲ)

ደንቦቹ፡ (1) በሕገ መንግስት የተጠበቁ መብቶችን መጣስ የለባቸውም፣ (2) በግልጽ እና በውስን መገለጽ አለባቸው፣
(3) ለወላጆች እና ለተማሪዎች ሊደርሱ እንዲችሉ በዲስትሪክቱ ድህረ ገጽ ላይ መታታም ወይንም በጹሁፍ መልክ መቅረብ ይኖርባቸዋል፣(4) የታተመው የመመሪያ መጽሃፉ ከተሰራጨበት ጊዜ ጀምሮ ሥራ ላይ የሚውልበት ቀን መገለጽ አለበት።

## I. ከትምህርት ቤት ለጊዜው መታገድ ወይንም ሊያስባርሩ የሚችሉ ወንጀሎች

(የ JIC ፖሊሲ) በትምህርት ቤቶች ቅጥር ግቢ ውስጥ፣ በትምህርት ቤት ቦታዎች ላይ፣ በትምህርት ቤት ተሽከርካሪዎች ውስጥ፣ ወይም በትምህርት ቤት ወጪ አማካይነት እና ከዲስትሪክት ንብረት ውጭ ድርጊቱ ከትምህርት ቤት ወይም ከማንኛውም የዲስትሪክት ስርአተ ትምህርት ወይም ከስርአተ ትምህርት ውጪ ግንኙነት ካለው በሚካሄዱት ተግባራት ጊዜያት ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ድርጊቶች ውስጥ በአንዱ ወይም ከዚያም በላይ ድርጊት የሚሳተፉ ከሶስተኛ ክፍል እና እስከ ከፍተኛ ደረጃ ያሉትን ተማሪዎች የትምህርት ቤቱ ኃላፊ ተማሪው/ዋን ለጊዜው እንዲታገድ ሊያደርግ ይችላል ወይም ከትምህርት ቤት እንዲወጣ/እንዲትወጣ ማሳሰቢያ ሊሰጥ/ሊትሰጥ ይችላል/ትችላለች። በC.R.S ውስጥ በተገለፀው መሰረት በፈጸሙት ወንጀል የተፈረደባቸው ወይም የተከሰሱ ከአስራ ስምንት አመት በታች ያሉ ተማሪዎች በ§ 22-33-106(1)(መ) በፍርዱ ወይም በፍርድ ውሳኔ ላይ በመመስረት የግዴታ መባረር አለበት። በፕሪስኩል፣ በኪንደርጋርተን ፣ አንደኛ ክፍል ወይም ሁለተኛ ክፍል የተመዘገቡ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ውጪ ብቻ ሊታገዱ ወይም ሊባረሩ የሚችሉት በC.R.S. § 22-33-106.1 (2) እና ፖሊሲ JKD-1 መሰረት ብቻ ነው።

1. በድስትርክቱ ንብረቶች ላይ ጉዳት ማድረስ ወይም ጉዳት ለማድረስ መሞከር፣ ወይም ዋጋ ያለውን የድስትርክቱን ንብረት መስረቅ ወይም ለመስረቅ መሞከር።
2. በግል ንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ ወይም ጉዳት ለማድረስ መሞከር፣ ወይም የግል ንብረትን መስረቅ ወይም ለመስረቅ መሞከር።
3. በክፍለ-ግዛት እንደተደነገገው በድስትርክቱ ቅጥር ግቢ ላይ እንደ ዝርፊያ ወይም ጥቃት የሚወሰድ ማንኛውም በአዋቂ ሰው የሚደረግ ድርጊት
4. በድስትርክቱ ላይ ወይም በተማሪዎች ወይም በሠራተኞች ጠቅላላ ደኅንነት ላይ ተጽእኖ የሚያመጣ የተደነገገውን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግን መጣስ።
5. የድስትሪክት ፖሊሲ ወይም የትምህርት ቤት መተዳደሪያ ደንቦችን መጣስ።
6. አደገኛ መሠሪያዎችን ትምህርት ቤት ይዞ መምጣት የሚከለክል የድስትሪክት ፖሊሲ መጣስ። (JICI ፖሊሲ) መሰረት በፌደራል ህግ መሰረት የጦር መሳሪያ ለመጠቀም ወይም ለመያዝ መባረር የግዴታ ይሆናል።
7. የዲስትሪክቱን አልኮሆል መጠጦችን ወይም አደንዛዥ ዕጽን መጠቀም የሚከለክል የድስትሪክቱን ፖሊሲ መጣስ። (JICI ፖሊሲ)
8. የሀይለኛነትን እና የጥለኛነትን ምግባር የሚከለክል የድስትሪክቱን ፖሊሲ መጣስ።(JICDB ፖሊሲ)
9. የዲስትሪክቱን ከትምባሆ-ነጻ ትምህርት ቤቶች ፖሊሲ መጣስ። (መመሪያ ADC)
10. ወሲባዊ ጥቃትን እና መድልዎን የሚከለክል የድስትሪክቱን ፖሊሲ መጣስ።( AC-R-2፣ AC-R-4 ደንቦች)
11. የትምህርት ቤት ተግባራት አካል የሆነ እና በድስትርክቱ ቁጥጥር ሥር ከሆነ በስተቀር፣ በአካል ወይም በንብረት ላይ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ነገሮችን መወርወር።
12. የልቅ (ብልግና) ንግግር ወይም በሌሎች ተማሪዎች፣ በትምህርት ቤት ሰራተኞች ወይም ለተለያዩ ጉዳዮች ወደ ድስትርክቱ በሚመጡት እንግዶች ላይ አግባብ የሌላቸውን አካላዊ እንቅስቃሴዎችን ማሳየት።
13. መሳደብ፣ ያም ስም ማጥፋት በቃልም ሆነ በጽሑፍ ወይም በኤሌክትሮኒክ መንገድ ፣;በጎሳ ወይም በዘር ልዩነት መሰዳደብ፣ ወይም በድስትርክቱ ረብሻን የሚቀሰቅስ ወይም ሁከትን የሚያነሳሳ ግልጽ የሆኑ ንግግሮች ማድረግ።
14. በማጭበርበር፣ ወይም በማስገደድ ገንዘብን ወይም ሌሎች ነገሮችን ከሰው መውሰድ፣ ወይም በዛቻና በማስፈራራት ተግባራት ሰውን ለሆነ ጉዳይ ማስገደድ።
15. ለትምህርት ቤት ሰራተኛ መዋሸት ወይም የቃልም ሆነ የጽሁፍ ወይንም በኤለክትሮኒክ መልክ የሀሰት መረጃ መስጠት።
16. በትምህርት ጉዳዮች ታአማንነትን ማጣት ሲሆን ፈተናዎችን መስረቅ፣ የሌላውን ሰው ጽሁፍ እንደ የራስ አድርጎ መውሰድ ወይም የጽሁፍ ሥራን ያለፈቃድ ከሌላው ሰው ጋር ተባብሮ ማዘጋጀት።
17. ሆን ብሎ አለመታዘዝ ወይም በግልጽና በእልኸኝነት አግባብ ያላቸውን ባለ ሥልጣናትን አለመታዘዝ፣ ለድስትርክቱ ሰራተኛ ሆን ብሎ አለመታዘዝን ያካትታል።
18. የትምህርት ዕድልን ለሌሎች ተማሪዎች ለማዳረስ ድስትርክቱ ባለው ብቃት/አቅም መሃል በተደጋጋሚ ጣልቃ በመግባት መገዳደር።
19. ለተማሪው ወይም ለሌላ ተማሪ የአካል ጉዳት ስጋት የሚፈጥር ባህሪን ጨምሮ ለሌሎች ተማሪዎች እና ለትምህርት ቤት ሰራተኞች ሰላም፣ ደኅንነት፣ ወይም ሞራል ወሳኝ የሆነ በድስትርክቱ ውስጥና ከዚያም ውጪ ያሉ ምግባራት።
20. የማስፈራራት፣ ትንኮሳ እና ጭቆናን በተመለከተ የዲስትሪክቱን ፖሊሲ መጣስ፣ በ"ማስፈራራት" ተግባራት ላይ በመሳተፍ ላይ ብቻ ሳይሆን፣ረዘም ያለ የአካል ብቃት እንቅስቃሴን ማስገደድ፣ ማንኛውንም ንጥረ ነገር ከመጠን በላይ እንዲወስዱ ማስገደድ፣ ለረጅም ጊዜ እንቅልፍ ማጣትን፣ ምግብን ወይም መጠጥን ወይም ሌላ ማንኛውም ባህሪን ማስገደድ ማንኛውም ሌላ ባህሪ በግዴለሽነት የግለሰብን ጤና እና ደህንነትን ወደ ማንኛውም የተማሪ ቡድን ለመጀመር ማቀድ ። (የACC ፖሊሲ
21. የድስትሪክቱ የተማሪን የደንብ ልብስ ፖሊሲ የሚያዘውን ሕግ መጣስ።(JICAB ፖሊሲ)
22. በድስትሪክቱ ፖሊሲ የተደነገገውን ተማሪዎች ሀሳባቸውን የመግለጽ መብት መጣስ።(JICED ፖሊሲ)
23. የድስትሪክቱን ሰራተኛ ለሕግ አስከባሪዎች ወይም ለድስትሪክት በውሸት የወንጀል ክስ መክሰስ።
24. አለማዳላትን የሚከለክል የድስትሪክቱን ፖሊሲ መጣስ።(መመሪያ AC)
25. ተማሪን ማስጨነቅ ወይም መቀባጠርና ትምህርት የሚመለከት የድስትሪክት ፖሊሲ መጣስ ናቸው። )( መመሪያ JICDE
26. የሚስጥር ማህበራት/አደገኛ ቡዞኔ እንቅስቃሴ ላይ ያለዉን የዲስትሪክቱን ፖሊሲ መጣስ። (JICF ፖሊሲ)

## II ከፕሪስኩል እስከ ሁለተኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች

ርእሰ መምህሩ ወይም የርእሰመምህሩ ተወካይ ስለ እገዳ፣ መባረር እና ሌሎች የዲሲፕሊን ጣልቃገብነቶችን ፣ በተመለከተ በሚመለከተው ህግ እና የቦርድ ፖሊሲ መሰረት በፕሪ ስኩል፣ በኪንደርጋርተን ፤በአንደኛ ክፍል ወይም በሁለተኛ ክፍል ያሉትን ተማሪዎችን ማገድ ወይም መባረርን ሊመክሩ የሚችሉት ከዝህ በታች ካሉት በአንድ ወይም ከዚያ በላይ ተግባራት ላይ በዲስትሪክቱ ንብረት ላይ፣ በዲስትሪክት መኪና ውስጥ፣ በዲስትሪክት እንቅስቃሴ ወይም ክስተት፣ ወይም ከዲስትሪክት ንብረት ውጪ ምግባር ከትምህርት ቤት ወይም ከማንኛውም የዲስትሪክት ስርአተ ትምህርት ወይም ከስርአተ ትምህርት ውጭ ግንኙነት ስሳተፉ ብቻ ነው።

1.በትምህርት ቤቶች ውስጥ የጦር መሳሪያዎችን በተመለከተ የቦርዱን ፖሊሲ መጣስ (ፖሊሲ JICI)። በፌደራል ህግ መሰረት የጦር መሳሪያን ወደ ትምህርት ቤት ማምጣት ወይም ይዞ መገኘት ከትምህርት ቤት መባረር ግዴታ ነው.

2. በአልኮል እና ሌሎች የሃሸሽ አጠቃቀም (JICH ፖሊሲ) ላይ የቦርዱን ፖሊሲ መጣስ።

3. የሌሎችን ጤና ወይም ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል ምግባር።

**ከተማሪ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ላላቸው ሰራተኞች የዲሲፕሊን አሰራር**
የትምህርት ቤት ኃላፊ ወይም ተወካይ በትምህርት ቤት ለተመዘገበ/ች የማንኛውም ተማሪ ሥርዓት በተመለከተ ከተማሪው/ዋ ጋር በመማሪያ ክፍል ውስጥ ቀጥተኛ ግንኙነት ላለው/ላላት አስተማሪ ወይም የተማሪ አማካሪ አስፈላጊውን መረጃ ይሰጣል/ትሰጣለች። መረጃውን የተቀበለ/ች አስተማሪ ወይም የተማሪ አማካሪ የተቀበለውን/የተቀበለችውን መረጃ በቤተሰብ የትምህርት መብቶች እና ግላዊነት ህግ ("FERPA") መሰረት ;በምስጥር ማያዝ አለበት/አለባት፤ መረጃውን ለሌላ ሰው የማስተላለፍ ሥልጣን የለውም/የላትም።

**IV. የደህንነት እቅድ**
በመማሪያ ክፍል ውስጥ፣ በድስትርክቱ ፣ በድስትርክቱ ተሽከርካሪዎች ውስጥ፣ ወይም በድስትርክቱ ተግባራት ወይም ድርጊቶች ላይ ረብሻን የሚያነሳሳ/የሚታነሳሳ ማንኛው/ዋም ተማሪ አግባብ ካለው የትምህርት ቤት ባለ ሥልጣን ጋር በመገኛኘት አለበት/አለባት፤ ይህም ባለ ሥልጣን ከሌላ የትምህርት ቤት ሰራተኛ ጋር በመሆን ለተማሪው እንደ አስፋላጊነቱ ለተማሪው የደህንነት እቅድ ያወጣል/ታወጣለች።

ሥራ ላይ የዋለው፣ ጃንዋሪ 12፣ 2009
የተሻሻለው፣ ኦገስት 13፣ 2012
የአሁኑ ክለሳ፡ጃንዋሪ 9፣

ሕጋዊ ዋቢዎች፣
20 U.S.C1232g (FERPA)
20 U.S.C.. § 7101 እና ተከታዮቹ። (የ1994 ከደህንነት እና ከድራግ -ነጻ ትምህርት ቤቶች እና ማህበረሰቦች ህግ)
21 U.S.C § 812 (ቁጥጥር የሚደረግበት ንጥረ ነገር ፍቺ)
C.R.S. 18-3-202 et. seq. (ሰውን ማስቀየም)
C.R.S. 18-4-301 et. seq. (ንብረትን መጉዳት)
C.R.S. 18-9-124 (2) (a) (ሰውን ማዋረድ ክልከላ)
C.R.S. 22-12-105 (3) (ለውሸት ክስ ለግዜው ተማሪን የማገድ ወይም የማባረር ሥልጣን)
C.R.S. 22-32-109.1 (2) (a)(II) (ደህንነቱ የተጠበቀ የትምህርት ቤት እቅድ የሚያስፈልግ ፖሊሲ)
C.R.S. 22-32-109.1 (9) (ጠቃሚ የትምህርት ቤት ሕጎችን ማጠንከር)
C.R.S. § 22-32-126 (ርዕሰ መምህራን - የድስፐሊን አሰጣጥ ስልጣን)
C.R.S. 22-33-106 (1)(a-e) (ለጊዜው ከትምህርት ቤት ለመታገድ፣ ለመባረር ወይም ትምህርት ቤት መግባትን የሚያስከለክሉ ምክንያቶች)
C.R.S. . § 22-33-106.1 (ከፕሪስኩል እስከ ሁለተኛ ክፍል ያሉትን ተማሪዎችን የማገድ እና ማባረር ህግ );
C.R.S. § 22-33-106.5(1).5(1) (በተማሪዎች የተፈጸሙ ጥፋቶችን በተመለከተ መረጃ);
C.R.S. § 24-10-106.3 (የክሌር ዴቪስ ትምህርት ቤት ደህንነት ህግ);

ጥምር ዋቢዎች፣
AC፣ አለማዳላት/ለሁሉም እኩል ዕድል
AC-R-2፣ የወሲብ ውክቢያ
AC-R-4፣ የተማሪዎች የወሲብ ውክቢያ
ACC፣ ሰውን ማስፈራራት፣ ማዋከብ እና ማዋረድ
ADC፣ ከትምባሆ ነጻ የሆኑ ትምህርት ቤቶች
ADD፣ ደኅንነታቸው የተጠበቁ ትምህርት ቤቶች
JIC፣ የተማሪ ምግባር፣
JICAB፣ የተማሪ የደንብ ልብስ
JICDB፣ ሀይለኛ እና ጥለኛ ምግባር
JICDE፣ መቀባጠርን መከልከልና ማስተማር
JICED፣ የተማሪ የሀሳብ መግለጽ መብቶች
JICF፣ ድብቅ/አደገኛ ቦዘኔዎች
JICH፣ የአልኮል መጠጥ እና ሌሎች ዕጾች አጠቃቀም በተማሪዎች
JICI፣ በትምህርት ቤቶች ውስጥ ትጥቅ/መሳሪያ መያዝ
JK፣ የተማሪ ምግባር፣
JKD-1 ተማሪዎችን ለጊዜው ከትምህርት ቤት ማገድ/ማባረር

## ሀይለኛና ጥለኛ ምግባር
## (JICDB)

በተማሪዎች እና በትምህርት ቤት ሠራተኞች ላይ የሚደረግ ሀይለኛ እና ጥለኛ የምግባር ክስተቶች በመማሪያ አከባቢ ደኅንነት ላይ አስጊ ሁኔታን እንደሚፈጥር የትምህርት ቦርድ ይገነዘባል። በእንደዚህ ያሉ የስሜታዊነት ምግባራት ሰበብ በሚፈጠሩ አደጋዎች ውስጥ ተማሪዎች በተለይ ተጠቂ ይሆናሉ። እንደዚሁም ማንኛውም ዓይነት የሀይለኛነት ወይም የጥለኛነት ምግባር ሲከሰቱ የተማሪዎች የትምህርት ክንዋኔም ይጎዳል። የተወሰኑ ምግባራት ከታለፉ፣ ጤናማ እና ምርታማ/ውጤታማ የሆነውን እና ደኅንነቱ የተጠበቀ የመማሪያ አከባቢን ሊያናጉ ይችላሉ። እነዚህ ምግባራት፣ ሀይለኛ ወይም ጥለኛ የሆኑ፣ የማይታለፉ እና በድስትሪክቱ አፋጣኝ እርምጃ የሚወሰዱባቸው ምግባራት ናቸው።

እንደዚህ ዓይነቱን አደገኛ ሁኔታ ለማስቀረት የተቀላጠፈ እርምጃ ያስፈልጋል። የትምህርት አከባቢን ደኅንነት እና ሰላም ለመጠበቅ እንዲቻል ይህ ፖሊሲ የሀይለኛነትን እና የጥለኛነትን የምግባር ድርጊቶች የመከላከል መመሪያዎችን ይሰጣል።
የሀይለኛነት እና የጥለኛነት ምግባር የሚታዩባቸው ተማሪዎች አደጋ ከመፈጠሩ በፊት አግባብ ያላቸው ምክር ይሰጣቸዋል፣ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ከትምህርት ቤት ለጊዜው መታገድ ወይም ከትምህርት ቤት መባረር ደረጃ የሚያደርሱ የሥርዓት እርምጃ ሊወሰዱባቸው ይችላል።

በትምህርት ቤት ሕንጻዎች፣ ቅጥር ግቢ፣ ወይም ተሽከርካሪዎች ውስጥ እና በትምህርት ቤት አማካይነት በተዘጋጁ የተለያዩ ፕሮግራሞች ላይ፣ እና በተወሰኑ ሁኔታዎች ከትምህርት ቤት ውጪ ማንኛውም ተማሪ ወይም ሰራተኛ ሌላውን ተማሪ ወይም ሰራተኛ መምታት፣ ለጉዳት መዳረግ፣ ወይም እንደዚህ ዓይነቱን ድርጊት መሞከር ይህንን ፖሊሲ መጣስ ይሆናል። የሀይለኛነት እና የጥለኛነት ድርጊት በማንኛውም መልኩ፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ፣ በንግግርም ሆነ በምግባር፣ ሆን ብሎ ሌላውን ሰው መምታት፣ ማቁሰል ወይም ሰውን ወይም ንብረትን የመጉዳት ተግባር ነው። በሀይለኛነት እና በጥለኛነት የማስፈራራት ዛቻ የሀይለኛነት እና ሌላውን ሰው የመጉዳት ወይም የማቁሰል ሥጋት ጽንሰ ሐሳብ ይይዛል።

የሚከተሉት ምግባራት እንደ የሀይለኛነት እና የጥለኛነት ምግባራት ይወሰናሉ፡

1. **ሆን ብሎ ሌላውን ሰው ለማሳመም ወይም ለመጉዳት አካላዊ ጥቃት ማድረስ**፡ ሰውን ወይም የሰውን ንብረት በአካል ወይም በመሳሪያ የመምታት ወይም የመንካት ድርጊት።
2. **መሳደብ**፡ ማኃላ፣ ጩኸት፣ ወይም አስቀያሚ/አሳፋሪ የሰውነት እንቅስቃሴዎች ያጠቃልላል፣ በእነዚህ ብቻ ግን አይወሰንም።
3. **ማስፈራራት/ዛቻ**፡ ቀጥተኛ በንግግር (በስልክ ሊሆን ይችላል)፣ በየሰውነት እንቅስቃሴ፣ ወይም በጽሁፍ ግለሰብን፣ ቤተሰቡን ወይም ቡድንን ማስፈራራት ሊሆን ይችላል።
4. **ማስፈራራት/መበደል**፡ ሌላውን ሰው በማስፈራራት የሆነ ጉዳይ እንዲፈጽሙ/እንዲታዘዙ በማሰብ በአካል ወይም በንግግር ማስገደድ፤ ወይም በሌሎች ሰዎች ላይ የበላይነት ለማግኘት/ለመቆጣጠር፣ ወይም በልማድ በሌሎች ላይ ለመጨከን፣ ወይም ማንኛውንም ዓይነት የጽሁፍ ወይም የቃል፣ አካላዊ እንቅስቃሴ ወይም ምልክት፣ ወይም የመሳሰሉትን አንድ ወይም ከዚያም በላይ የሆኑ ተማሪዎች ለማሳዘን በተጨማሪ በድስትሪክቱ ሌላውን ሰው የማሳፈር/የማዋረድ ተግባር የሚከለክል እና 'JICDE' የሚባለው የትምህርት ፖሊሲ።
5. **ማጭበርበር**፡ በቃላት ዛቻ ወይም በአካል በማስገደድ ገንዘብን ወይም ንብረቶችን ከሰው መውሰድ።
6. **ሰውን መከታተል**፡ ሰውን የሙጥኝ ብሎ መከታተል፣ በአካል/በስልክ መገናኘት፣ ሰውን መመልከት ወይም የሰውን የአእምሮ ሰላም የሚነሱ ወይም ለግል ደኅንነት የሚያሰጉ ሌላ ዓይነት የዛቻ ድርጊቶች።
7. **አለመታዘዝ**፡ ሕጋዊ ባለ ሥልጣንን ያለመታዘዝ አሳሳቢ ሁኔታዎች ወይም ድርጊቶች።
8. **በቡድን መለያየት**፡ ቀጥተኛ ስድብ፣ አሽሙር፣ ወይም የዘር፣ የጾታ፣ የጾታ አመለካከት፣ የኃይማኖት፣ የአገር ወይም የህገረሰብ ሁኔታን በተመለከተ ወይም አካለ ስንኩልነትን የሚመለከት በተዘዋዋሪ ሁኔታ የንቀት አስተያየቶችን መስጠት/መተቸት።
9. **ንብረትን ማውደም**፡ ሆን ብሎ የሌላውን ሰው ንብረት ማውደም/ማጥፋት።
10. **ሽብርተኝነት**፡ ሆን ብሎ ለሽብር ዓላማ ሁከትን ለማካሄድ መዛት፤ ወይም ለሽብር ድሪጊቶች ሥጋት ግድ የለሽ መሆን፤ ወይም ለህዝብ ደኅንነትና ሰላም አሳሳቢ የሆኑ ሁኔታዎችን መፍጠር፣ ለምሳሌ ህዝብ ከትምህርት ቤት ወይም ካለበት ሕንጻ/ቤት/ክፍል ውስጥ ሸሽቶ እንዲወጣ የሚያስገድድ ሁኔታን መፍጠር።
11. **መቀባጠር**፤ በድስትሪክት ፖሊሲ ውስጥ እንደተገለጸው ተማሪን መበደል/ማስጨነቅና ተያያዥ ትምህርት።
12. **ቴክኖሎጂ ወይም ሥነ-መላን በመጠቀም መቀባጠር**፤ በጽሁፍ፣ በምስል፣ በድምጽ ወይም በቭዲዮና በመሳሰሉት መንገዶች ራስን በመግለጽም ሆነ በመደበቅ ተማሪን የሚያሳፍሩና የሚያስጨንቁና አላስፈላጊ የሆኑ መልዕክቶችን በእንቴርኔት መስመሮች በመጠቀም መላክ። በተጨማሪም፣ በተመሳሳይ መልኩ የሚደረጉና ጤናማና ደህንነቱ የተጠበቀ የትምህርት ቦታን የሚያውኩ ጉዳዮች መፈጸም ከዚሁ ጎራ ይመደባሉ። ተማሪዎች የግላቸውንም ሆነ የድስትሪክቱን የእንቴርኔት መስመሮች በመጠቀም እነዚህን ጉዳዮች ከመፈጸም መቆጠብ አለባቸው።

የሀይለኛ እና የጥለኛ ምግባራት የማስጠነቀቂያ ምልክቶችን እንዲያውቁ ተማሪዎች እና ሰራተኞች ስልጠና ማግኘት ይገባቸዋል። እንደዚሁም አጠራጣሪ ምግባራትን ወይም ለትምህርት ቤት አስተዳደሮች እና ለሌሎች የትምህርት ቤት ኃላፊዎች አደገኛ እና አሳሳቢ ሁኔታዎች የሚፈጥሩ የቀውስ/የሽብር ድርጊቶች/ሁኔታዎች በተቋቋመው በትምህርት ቤት ድስትሪክት መጠቆሚያ ስልክ ቁጥር ሁኔታውን/ድርጊቱን መጠቆም አለባቸው። ሁሉም ጥቆማዎች በሥርዓቱ ይያዛሉ። እንደዚህ ያሉትን ጥቆማዎች አለማድረግ ለቅጣት እርምጃ ይዳረጋሉ።

የሀይለኛነት እና የጥለኛነት ምግባር ድርጊቶች/ሁኔታዎች ሰነዶች በደንብ መያዝ አለባቸው፣ በተጨማሪም ለጊዜው ከትምህርት ቤት ማስወጣት/ማባረር ጨምሮ ለቅጣት እርምጃዎች እንዲረዳ ሰራተኞች አስፈላጊውን መረጃ ለትምህርት ቤት ኃላፊ መስጠት አለባቸው። የወላጆች/የአሳዳጊዎች በጉዳዩ መሳተፍም አስፈላጊ ነው። ለአጣዳፊ የሕግ/የደንብ ጥሰቶች አግባብ ላለው/ላላት የድስትሪክት አስተዳዳሪ ጉዳዩን ማሳወቅ ያስፈልጋል። የሕግ ጥሰት ከሆነ የሕግ አስከባሪ ባለ ሥልጣናትም በጉዳዩ ይሳተፋሉ።

የተሻሻለው፤ ሴፕተምበር 10፣ 2012
የጸደቀው፣ ጃንዋሪ 9፣ 2012
ህጋዊ ዋቢ፤ C.R.S.22-32-109.1(1)(b)(የመቀባጠር ፍቺ ወይም ትርጉም)
ጥምር ዋቢዎች፤ ACC፣ ማስጨነቅና መበደል
AC R-2, AC R-4፣ የጾታዊ ጭቆናና በደል
JICDA፣ የሥነ-ምግባር ህገ-ደንብ
JICDE፣ በደልን መከልከልና ማስተማር
JICF፣ የውንብድና ተግባራት
JICI፣ የጦር መሳሪያዎች/ትጥቆች በትምህርት ቤት ውስጥ
JICJ፣ የተማሪዎች የእንቴርኔት መስመሮችና ቁሳቁሶች መጠቀም
JK፣የተማሪ ሥርዓትና ንዑሳን አንቀጾች

## ሰውን ማሳዘን መከልከል እና ማስተማር
## (JICDE)

የትምህርት ቦርድ ደኅንነቱ የተጠበቀ የትምህርት ቦታን ይፈልጋል፣ ለማስተማር እና ለመማር ምቹ የሆኑ እና ከዛቻ፣ ከጭንቀት (ከወከባ)፣ እና ከማንኛውም ዓይነት የማሳዘን ምግባራት ነጻ የሆነ የትምህርት ቦታን መፍጠር ይፈልጋል። የዚህ ፖሊሲ ዓላማ  የትምህርት ቀረቤታን በጽኑነት ማሻሻል/ማሳደግ እና ሁሉም ዓይነት ማስፈራራቶች ተቀባይነት እንዳይኖራቸው የማድረግ ሁኔታን መፍጠር ነው።

መቀባጠር ከፍተኛ የአካላዊና የሥነ-ልቦናው ቀውስን ሊያስከትል ይችላል። ሰውን ማስጨነቅ/መበደል ማለት በጽሁፍ ወይም በንግግር ፣ በአካል ወይም በምልክት፣ ወይም በሌሎች መንገዶች ሆን ብሎ በትምህርት ቤት አከባቢ አንዷን ወይም ከዚያም በላይ የሆኑትን ተማሪዎች በተለያዩ መንገዶች ማስቆጣት/ማሳዘን/ማስጨነቅ ነው። በማንኛውም ዓይነት የሰው ዘር ላይ የሚደረጉ እንደነዚህ ዓይነቶቹ ተግባራት ፈጽሞ የተከለከሉ ናቸው።

ተማሪን በትምህርት ቤት አከባቢ፣ በትምህርት ቤት ተሽከርካሪዎች ውስጥና በትምህርት ቤት በሚዘጋጁ ተግባራትን/ድርጊቶችና ፕሮግራሞች አከባቢና በሌሎችም ሥፍራ ማስጨነቅ/መበደል ፈጽሞ የተከለከለ ነው።

በማንኛውም ዓይነት መንገድ ሰውን የማሳዘን/የማስቆጣት ሁኔታዎች/ድርጊቶች ውስጥ የተሳተፈ ተማሪ ተገቢውን ቅጣት ያገኛል/ታገኛለች፤ ቅጣቶቹም ለጊዜው ከትምህርት ቤት ማባረር፣ ከትምህርት ቤት ማስወጣት፣ ወይም ጉዳዩ ለሕግ አስከባሪ ባለሥልጣናት ይተላለፋል። የቅጣት እርምጃው ሲወሰድ የጉዳዩ አጣዳፊነት እና ሁኔታ ከግምት ይገባሉ። ይህንን ድርጊት በሚፈጽሙ ተማሪዎች ላይ በቦርድ ፖሊሲውና ህገ-ደንቡ መሰረት አስፈላጊው እርምጃ ይወሰዳል። የድርጊቱ ሰለባ የሆኑት ተማሪዎችም በቦርዱ ፖሊሲና ህገ-ደንብ መሰረት ተጨማሪ ሙብትና ጥበቃ ይኖራቸዋል።

በሁሉም ትምህርት ቤቶች ተማሪን ማሳዘን/ማስቆጣት በተመለከተ ጠቅላላ መርኃ ግብር (ፕሮግራም) በየበላይ አለቃው/ዋ  ይወጣል። ፕሮግራሙም ቀጥሎ ያሉትን ግቦች ማሳካት ላይ ያተኩራል፡

1. ተማሪን ማሳዘን/ማስጨነቅ/ማስፈራራት እንደማይፈቀድ ለተማሪዎች፣ ለሰራተኞች፣ ለወላጆች፣ እና ለማኅበረሰብ አባላት ግልጽ የሆነ መልዕክት መላክ።
2. ተማሪን ማሳዘን/ማስጨነቅ/ማስፈራራት ለማስቀረት አስቀድመው አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ እንዲችሉ ሰራተኞችን እና ተማሪዎችን ማሠልጠን።
3. የማስፈራራት/ የማስጨነቅ ድርጊቶች ለደረሰባቸው ተማሪዎች አፋጣኝ እርዳታ እንዲደረግላቸው፣ ሁኔታውን ማጣራት፣ እና ድርጊቱን የፈጸሙ ተማሪዎችን ለመጋፈጥ የአፈጻጸም ሂደቶችን ሥራ ላይ ማዋል።
4. ተቀባይነት ያላቸውን ምግባራት፣ ውይይት፣ ምክር፣ እና አግባብ ያላቸው አሉታዊ ውጤቶችን እንደገና በማስተማር በማስፈራራት/በማስጨነቅ ድርጊቶች የተሳተፉ ተማሪዎችን ምግባር ለመቀየር ጥረት ማድረግ።
5. ከማሳዘን/ከማስጨነቅ ነጻ የሆነ የትምህርት አከባቢ ለማድረግ በወላጆች እና በማኅበረሰብ አባላት መካከል ውጤታማ የሆነ ሽሪክነት ማጠንከር።
6. በሌሎች ተማሪዎች የማስፈራራት/የማሳዘን/የማስጨነቅ ሁኔታዎች/ድርጊቶች የደረሰባቸው እና በዚህ ለተጎዱ ተማሪዎች በግል እና በጋራ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ።
7. የጓደኛ ድጋፍ፣ የማኅበራዊ ችሎታዎች፣ እና ለሁሉም ተማሪዎች በራስ መታመንን እንዲያሳድጉ መርዳት።
8. በመደበኛነት አዎንታዊ እና በተማሪዎች መኃል የመረዳዳት ምግባራት እንዲበረታቱ ማሳወቅ እና ስለዚህም ማመስገን።
9. የተማሪ በደልን በተመለከተ ለአስተማሪዎችና ለሰራተኞች ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠናን መስጠት።
10. የበደልን መከላከል ሥራ የሚሰሩ ቡድኖችን በየትምህርት ቤቶች ማዋቀር።
11. የተማሪ በደልን በተመለከተ ከተማሪዎች፣ ከወላጆችና ከሰራተኞች ጋር የጋራ መደበኛ የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ ናቸው።

የቀረበው፤ ኖቬምበር  12፣ 2001
ሥራ ላይ የዋለው፡ ዲሴምበር  10፣ 2001
የተሻሻለው፣ ሴፕተምበር 10፣ 2012

ህጋዊ ዋቢ፤ C.R.S. 22-32-109.1 (2) (a) (I)(k)(የትምህርት ቤት ደህንነት የሚመለከት ፖሊሲ)

ጥምር ዋቢዎች፤ AC፣ እኩል ሙብት/እድል
AC-R-7፣ አካለ-ስንኩልነት (የጠንነት ችግር) ላይ የተመረኮዘ ጭቆናን ማስቀረት
JB፣ እኩል የትምህርት ሙብት
AC-R-1፣ ጾታን መሰረት ያደረገ ጭቆናን ማስቀረት
AC-R-4፣ የተማሪዎች ወሲባዊ ትንኮሳ
JICDA፣ የሥነ-ምግባርና ሥርዓት ህገ-ደንብ
JICDB፣ አዋኪና አደገኛ ምግባር
JK፣ የተማሪ ሥርዓት (እና ንውሳን አንቀጾች)

## ትምህርት-ነክ የሆኑ የተማሪ ህትመቶች
## (JICEA)

በትምህርት ቤት ወጪ የሚዘጋጁ ህትመቶች ለተማሪዎች እና ለትምህርት ሥራዎች የህዝብ መድረኮች ናቸው። ከዚህ ሥራ ተማሪዎች ሪፖርት ማቅረብ፤ የጽሁፍ፣ የእርማት(የማደት) እውቀቶችን እና ኃላፊነት ያለው ጋዜጠኝነትን የመረዳት ልምድ ያገኛሉ። ተገቢውን የመማር ማስተማር ሥራን እስካልናጋ ድረስ በትምህርት ቤት ውስጥ ቦርዱ የተማሪ የፈጠራ ችሎታን ለትምህርት ፋይዳ እንዳለው የትምህርት ልምድ ስለሚያይ፣ የሀሳብ መግለጽ ነጻነትን፣ የቃል እና የጽሁፍ፣ ያበረታታል።

በትምህርት ቤት ወጪ በሚዘጋጁ ህትመቶች ላይ ተማሪዎች ሐሳባቸውን እንዲገልጹ እና ተጠያቂነት ያለበት የጋዜጠኝነት ሙያ የሚያከብራቸውን ሕጎች እንዲያውቁ እና እንዲያከብሩ ቦርዱ ያበረታታቸዋል። የውሸት፣ ሰውን የሚጎዳ ወይም የሚያዋርድ፣ የሐሜት፣ የሥም ማጥፋት ሐሳቦች በክፍለ ግዛት ሕግ መሰረት ሕገ ወጥ የሆኑ ድርጊቶች የሆኑ እና የትምህርት ቤት ሥርዓትና ደንብ ጥሰት የሆኑ ወይም ተገቢውን የመማር ማስተማር ሥራን በማንኛውም መንገድ የሚያናጉ ድርጊቶች፣ የሌሎችን የግል ሙብቶች የሚጥስ፤ ወይም በግለሰብ ወይም በንብረት ላይ ያነጣጠረ ዛቻ አይፈቀዱም።

በትምህርት ቤት ወጪ የሚዘጋጁትን ህትመቶች የሚያርሙ (የሚያድቱ) ተማሪዎች ዜናዎቹን፣ ሐሳቦቹን እና የህትመቶቹን የማስታወቂያዎች ይዘት በዚህ ፖሊሲ እና በክፍለ ግዛት ሕግ መሰረት የመወሰን (የመገደብ) ኃላፊነት አለባቸው። በየትምህርት ቤቱ ውስጥ ያሉት የህትመቶች አማካሪዎች በትምህርት ቤት ወጪ የሚዘጋጁ ህትመቶችን የመቆጣጠር እና ተማሪዎች በነጻነት ሐሳባቸውን መግለጽ እንዲችሉ እና የጋዜጠኝነት ሙያ መመዘኛዎችን የማስተማር እና የማበረታታት ኃላፊነት አለባቸው።

በትምህርት ቤት ወጪ በሚዘጋጁ ህትመቶች ላይ መሳተፍ ነጥብ (ማርክ) የሚሰጠው የትምህርት ሥራ ወይም ተግባር ሲሆን፣ የህትመቶች አማካሪዎች የህትመት ሥራ የሚሰሩ ተማሪዎችን የጽሁፍ ሥራ የማዘጋጀት  ወይም የመወሰን ሥልጣን አላቸው፤ አለበለዚያ ህትመቶቹ የሚዘጋጁበትን ዓላማ አስመልክቶ ተማሪዎች የሚቀስሙትን የትምህርት ልምድ የመምራት እና የመቆጣጠር ሥልጣን አላቸው።

የበላይ አለቃው/ዋ የሚከተሉትን ነጥቦች የሚይዝ እና ለውሰኔ ለትምህርት ቦርድ የሚቀርበውን የትምህርት ህትመቶች ሕግ በጽሁፍ ያዘጋጃል/ታዘጋጃለች።

1. የትምህርት ህትመቶች ዓላማ መግለጫ
2. የትምህርት ህትመቶች አማካሪዎች እና ህትመቶቹን የሚያርሙ (ኢድተሮች) ተማሪዎች ኃላፊነቶች
3. በክፍለ ግዛት የተወሰነውን የሐሳብ መግለጽ ነጻነትን የሚገድቡ ልዩ መመሪያዎች
4. በሕጋዊ የትምህርት ድስትሪክት ክልል ውስጥ መሰረት ያላቸው የጊዜ፣ የቦታ እና በትምህርት ወጪ የሚዘጋጁ የተማሪ ህትመቶችን የማሰራጫ መንገዶች አቅርቦት
5. በተማሪዎች እና በትምህርት ቤት ኃላፊዎች መሃል የሚፈጠሩት የልዩነት ጉዳዮች የሚፈቱበት ሂደቶች

የህትመቶቹ ሕጎች ለሁሉም ተማሪዎች እና አስተማሪዎች በእያንዳንዱ የትምህርት ዘመን መጀመርያ ላይ መሰራጨት አለበት።

ሥራ ላይ የዋለው፡ ጥቅምት 10፣ 2000

ሕጋዊ ዋቢዎች፤ C.R.S. 22-1-120 (የህዝብ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የሐሳብ መግለጽ ነጻነት)
C.R.S. 22-1-122(5)(e) (በፌደራል ሕግ እስካልተከለከለ ድረስ፣ ቢጋዜጠኝነት ሙያ አስተማሪ ወይም በአዘጋጅ ቁጥጥር ሥር ሆኖ የሚሰራን/የሚትሰራን ተማሪ ያለ ወላጅ ፈቃድ የዳሰሳ ጥናትን ማዘጋጀት ወይም በጥናቱ መሳተፍ፣ ጥናቱን መተንተን ወይም መገምገም የክፍለ ግዛት ሕግ አያግድም)
C.R .S. 22-32-110 (1)(r) (ዝሙትን የሚመለከቱ ወይም ጎጂ የሆኑ ጽሁፎችን የመከልከል ሥልጣን)

ጥምር ዋቢዎች፤ JICED፣ የተማሪ የሐሳብ መግለጽ ነጻነት መብቶች

## ትምህርት-ነክ የሆኑ የተማሪ ህትመቶች
## (የትምህርት ህትመቶች ሕጎች: JICEA-R)

1. የትምህርት ህትመቶች ዓላማዎች

ሥር ዓተ-ትምህርት ነክም ሆነ ተጓዳኝ ትምህርት ነክ ማንኛቸውም ዓይነት የተማሪ ህትመቶች ሕዝብ ሐሳብ እንዲሰጥበት ለሕዝብ መድረክ ይቀርባሉ። በዚህ ሁኔታ ማንኛውም ህትመት ሊያስከትል በሚችለው አወዛጋቢ ሁኔታ ወይም በይዘቱ ስሜት ቀስቃሽ በመሆኑ ምክንያት ብቻ ሊገደብ አይችልም።

2. የትምህርት ቤት ህትመቶች አማካሪዎች እና ህትመቱን የሚያርሙ ተማሪዎች ኃላፊነቶች

ሀ. በየአመቱ በአማካሪ እና በአስተዳደር እገዛ በትምህርት ቤት ወጪ የሚታተሙ የተማሪ ጽሁፎች ሥራ ለመምራት አብሮ ከሚሄዱት ፖሊሲዎች ጋር እና ከዚህ የሕትመት ሕግ ጋር የጸኑ የእርማት ፖሊሲ ያወጣሉ።

ለ. በትምህርት ቤት በተማሪ ህትመት ላይ የሚሰሩ ተማሪዎች የሚታተመውን የጽሁፍ ይዘት ይወስናሉ፣ ኃላፊነቱንም ይወስዳሉ።

ሐ. የትምህርት ቤት ህትመት አማካሪዎች ቀጥሎ ላሉት ነጥቦች ተጠያቂዎች ናቸው፡

(1) በትምህርት ቤት የሚታተሙ ህትመቶች ቁጥጥር

(2) ነጻ እና ኃላፊነት የተሞላቸው ሀሳቦች እንዲኖሩ ማስተማር እና ማበረታታት

(3) የጋዜጠኝነት ባለሙያ መመዘኛዎችን ማስተማር እና ማበረታታት

3. በክፍለ ግዛት የተወሰነውን የሀሳብ መግለጽ ነጻነትን መገደብ

ሀ. ለልጆች "የማይገባ" ህትመት። ይህም የወሲብ ጉዳይ ያዘለ ወይም የተጋነነ ጉዳይ የያዘ ህትመት ሊሆን ይችላል። ተገቢ ያልሆኑ ህትመቶች በአጠቃላይ አሳሳቢ የሆኑ የስነ ጽሁፍ፣ የጥበብ፣ የ (ፖለቲካ) አመለካከት ወይም የሳይንስ ፋይዳ ጉዳዮች ይጎላቸዋል።

ለ. ወንጀል ነክ ወይም የሰውን ስም የሚያጠፋ ጽሁፍ (ህትመት)። የወንጀል ወይም የስም ማጥፋት መግለጫዎች ውሸት ሊሆኑ ይችላሉ፣ በተጨማሪም የሰውን መብት የሚነኩ እና ሰውን የሚጎዱ ወይም በማኅበረሰቡ ውስጥ የሰውን ስም (ታዋቂነትን) የሚያጠፉ ሊሆኑ ይችላሉ። ጉዳዩ ስለ አንድ "ታዋቂ ሰው" ወይም "የህዝብ ባለ ሥልጣን" ከሆነ፣ ለተንኮል የተዘጋጀውን ህትመት ውድቅ ለማድረግ ባለ ጉዳዩ የሐሰት ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት። ተንኮል ማለት ሐሰት የሆኑትን መረጃዎች ሆን ብሎ ማሳተም ወይም የመረጃን (ትክክለኛነት) እውነተኛነት (ሳያጣሩ) ሳያረጋግጡ በግድ የለሽነት ማሳተም ነው።

ሐ. ግልጽ እና አደገኛ የሆኑ ህገ ወጥ የሆኑ ድርጊቶችን መፈጸም፣ ህጋዊ የትምህርት ቤት መተዳደሪያ ደንቦችን መጣስ፣ ወይም ቁስ አካላዊም ሆነ መጠነ ሰፊ የሆኑትን ሁከቶች በመቀስቀስ በሥርዓት ያለውን የትምህርት ቤት ሥራ መበጥበጥ፤ ወይም በንብረት ወይም በሰው ላይ ሁከትን ለማንሳት የመዛት ሁኔታዎች የተከለከሉ ናቸው።

መ. የግለሰብን የግል ምስጥር መጠበቅ መብትን የሚጥስ ህትመት።

4. በየትምህርት ቤት ክልል ውስጥ የተማሪ ህትመቶች የሚሰራጩበት ጊዜ፣ ቦታ እና ሁኔታ በትምህርት ቤቱ ኃላፊ እና በህትመት አማካሪዎች እና ህትመቶቹን በሚያርሙ (በሚያድቱ) ተማሪዎች ይወሰናሉ።

5. በተማሪዎች እና በሰራተኞች መሃል ባለው ገደብ ምክንያት የሚነሱ ክፍተቶችን (ልዩነቶች) የመፍታት ሂደቶች 'JII' በሚባለው የተማሪ ጉዳዮች፣ አቤቱታዎች እና ቅሬታዎች እና ተያያዥ መተዳደሪያ ደንቦች በሚመለከት ፖሊሲ ይፈታሉ። ከመተዳደሪያ ደንቦቹ "ደረጃ 1 ቅድመ ሁኔታ" የሚባል እንደሚከተለው ተሻሽሎ ቀርቧል፡
" አቤቱታ (ቅሬታ ከተቀበሉ በኃላ በ 48 ሰዓታት ውስጥ ምላሹ በጽሁፍ ይሰጣል። አሉታዊ ምላሽ ከሆነ ከነምክንያቱ ይገለጻል።"

በየበላይ አለቃ ሞንተ ሙሴ (Monte C. Moses) ኦክቶበር 10 ቀን፣ 2000 ዓ.ም. ተረጋገጠ።

## በተማሪዎች የሚሰራጩ ትምህርት-ነክ ያልሆኑ ህትመቶች (JICEC)

እንደ የህሳብ መግለጽ ነጻነት ያሉትን የሕገ መንግስቶች ፋይዳ ለመረዳት፣ ተማሪዎች እነዚህን ሕግጋት መማር ብቻ ሳይሆን ለመተግበርም ዕድሉን አላቸው። ነገር ግን፣ የትምህርት ቤት ቦታ እና ሁኔታ የተለየ በመሆኑ በፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረት በትምህርት ቤት ውስጥ የተማሪዎች የሀሳብ መግለጽ ነጻነት ገደብ አለው።

የተማሪዎችን የሀሳብ መግለጽ ነጻነት መጠበቅ እና ትምህርት ቤትን ሥርዓት ያለው እና በትምህርት ቤት ክልል ውስጥ እና በትምህርት ቤት በሚዘጋጁ ተግባራት ጊዜ የሁሉንም ተማሪዎች መብት የሚወክል ደኅንነቱ የተጠበቀ የመማሪያ ቦታ ለማድረግ ያለበትን ኃላፊነት ለመወጣት አስፈላጊውን ማመዛዘኛ ማድረግ የዚህ ፖሊሲ ግብ ነው።

በጊዜ፣ በቦታ እና በሁኔታ ገደብ በተሰጠው መተዳደሪያ ደንብ መሰረት እና ከታች በተሰጠው ክልከላ መሰረት እና በክፍለ ግዛት ሕግ በተወሰነው መሰረት በትምህርት ቤት ክልል ውስጥ ተማሪዎች ትምህርት ነክ ያልሆኑ ህትመቶችን እንዲያከፋፍሉ ይፈቀድላቸዋል።

በማንኛውም ዓይነት ሚዲያ (የዜና ማሰራጫ) አማካይነት አግባብ የለለው፣ የወንጀል ወይም ሰውን የመጉዳት ድርጊት፣ የሐመት ወይም የሥም ማጥፋት ድርጊትን የሚገልጽ ማንኛውም ዓይነት ህትመት የተከለከለ ነው። ተማሪዎች ሥርዓት ባለው ትምህርት ቤት ላይ፣ ወይም በንብረት ወይም ሰውን ለመጉዳት ወይም ለመረበሽ ዛቻን የሚፈጥር የቁስ አካል እና መጠነ ሰፊ የሆነ ሁከትን የሚፈጥር የሌላውን ሰው የግል ምስጥር መጠበቅ መብት የሚጥስ ሕገ ወጥ ተግባርን የሚደግፍ ወይም የትምህርት ቦርድን ፖሊሲ እና/ወይም የመተዳደሪያ ደንብ የሚጥስ ተግባር መፈጸም አይችሉም።

ይህንን ፖሊሲ በሚጥስ ሁኔታ እና/ወይም በሰው ወይም በንብረት ላይ የቁስ አካል እና መጠነ ሰፊ የሆነ ሁከት ወይም ጉዳት የሚያመጣ፣ ወይም በንብረት ወይም በሰዎች ላይ የሁከት ዛቻን የሚፈጥሩ ህትመቶችን በሚያከፋፍሉ ተማሪዎች ላይ በትምህርት ቤት ኃላፊዎች ውሳኔ መሰረት ተገቢው የቅጣት እርምጃ ይወሰድባቸዋል።

በትምህርት ቤት አማካይነት የሚዘጋጅ መሆኑ ካልተረጋገጠ ለእንደዚህ ያሉ ህትመቶች የትምህርት ቤት ቁሳቁስ ወይም ወጪ መጠቀም አይቻልም።

ይህ ፖሊሲ እና ተያያዥ መተዳደሪያ ደንቦች በተማሪ መመሪያ መጽሀፍ ውስጥ መካተት አለባቸው።

ሥራ ላይ የዋለው፤ ኦክቶበር 10፣ 2000

ሕጋዊ ዋቢዎች፤ C.R.S. 22-1-120 (ለህዝብ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የተሰጠ የሀሳብ መግለጽ ነጻነት መብት)
C.R.S. 22-32-110 (1)(r) (ወሲባዊ ወይም ጎጂ ህትመቶችን የመከልከል ሥልጣን )

ጥምር ዋቢዎች፤ JICEA፣ ትምህርት-ነክ የሆኑ የተማሪ ህትመቶች
JICED፣ የተማሪ የሀሳብ መግለጽ ነጻነት መብቶች
JK፣ የተማሪ ምግባር፣ እና ናዑስ አንቀጾች (ሕጎች)
KHC፣ የማስታወቂያ ህትመቶችን ማከፋፈል/መለጠፍ

## የተማሪ የሀሳብ መግለጽ ነጻነት መብት (JICED)

ተማሪዎች ትምህርት ቤት ሲገቡ ወይም በትምህርተ-ነክ ተግባራት ሲሳተፉ ሕገ-መንግስታዊ መብታቸውን ሲጠብቁ፣ በተማሪዎች መሃል ተገቢው ምግባር እንዲኖር ለማድረግ እና ውጤታማ የሆነ የመማሪያ ቦታ ለመፍጠር አሳማኝ እና አስፈላጊ የሆኑትን የመተዳደሪያ ደንቦች ማውጣት እና ሥራ ላይ ማዋል የትምህርት ቦርድ ኃላፊነት ነው።

ስለዚህም የተማሪ መግለጫዎች በሙሉ ከትምህርት ድስትሪክቱ፣ ከሥርዓተ ትምህርት እና ከዚህ ፖሊሲ ተልዕኮ ዓላማ እና ግብ ጋር አብሮ መሄድ ይኖርበታል። ለዚህ ፖሊሲ ዓላማዎች፣ የተማሪ መግለጫ በማንኛውም ሚዲያ (የዜና ማሰራጫ) የሚተላለፉትን መግለጫዎች ያካትታል፣ ይህም በሁሉም የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ እና በሌሎች ትምህርተ-ነክ የሆኑ ተግባራት፣ አሳይመንቶች፣ እና ፕሮጀክቶች የጽሁፍ፣ የቃል፣ የሚታይ (የዐይን)፣ የድምፅ፣ እና የኤሌክትሮኒክ ሚዲያ ያጠቃልላል፣ በነዚህ ብቻ ግን አይወሰንም።
ተማሪዎች ከታች የተዘረዘሩትን መግለጫዎች ዓይነት ማስገባት፣ ማሳተም ወይም ማስረከብ የለባቸውም፡

1. የተማሪ ምግባርን የሚያበላሽ
2. የወንጀል ድርጊት ያለበት ወይም ሰውን የሚጎዳ ወይም የሚያዋርድ፣ የሰውን ስም የሚያጠፋ፣ ወይም አለበለዚያ በክፍለ ግዛት ሕግ መሰረት ሕገ ወጥ የሆነ መግለጫ
3. በማንኛውም ተራ ሰው ወይም በህዝብ ጉዳይ ውስጥ በሚሳተፍ (የህዝብ ኃላፊነት ያለበት) ሰው የተረጋገጠ ውሸት የሆነ ጉዳይ
4. ግልጽ እና አደገኛ የሆኑ ሕገ ወጥ ድርጊቶች ተልዕኮ ያለው፣ ሕጋዊ የሆኑ የትምህርት ቤት መተዳደሪያ ደንቦችን የሚጥስ፣ ወይም ሥርዓት ባለው የትምህርት ቤት ሥራ ላይ ቁስ አካላዊ እና መጠነ ሰፊ የሆኑ ሁከቶችን የሚያመጣ
5. የብልግና ወይም የልቅነት ሀሳብ ያለበት
6. የሌሎችን የግል ምስጥር መጠበቅ መብት የሚጥስ
7. በንብረት ላይ ወይም በሰው ላይ የሁከት ዛቻ የሚገልጽ
8. በዘር፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በዕድሜ፣ በኃይማኖት፣ በአገር፣ በሰውነት ጉድለነት፣ ወይም በአካለ ስንኩልነት ምክንያት በማንኛውንም ሰው ላይ ጥቃት ማድረስ
9. ጠላትነትን የሚፈጥር ወይም አለበለዚያም ሥርዓት ያለውን የትምህርት ሂደት ሥራን የሚያውክ
10. ሥርዓት ያለውን የመማሪያ አከባብ የማወክ ዛቻን የሚፈጥር ስሜት ያለበት ማንናውንም ዓይነት ሕገ ወጥ ድርጊት የሚደግፍ

ይህንን ፖሊሲ በሚጥሱ ተማሪዎች ላይ በድስትሪክት የተማሪ ሥርዓት ፖሊሲዎች መሰረት የቅጣት እርምጃ ይወሰድባቸዋል።

ሥራ ላይ የዋለው: ሴፕተምበር 11፣ 2000

ሕጋዊ ዋቢዎች፤ C.R.S. 22-1-120 (ለህዝብ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የሀሳብ መግለጽ ነጻነት መብቶች)
C.R.S. 22-32-110 (1) (የዝሙት ወይም ወሲባዊ እና ጎጂ የሆኑትን ህትመቶች የመከልከል ሥልጣን)

ጥምር ዋቢዎች፤ JICDA፣ የምግባር እና የሥርዓት ሕግ
JICDB፣ ኃይለኛ እና ጥለኛ ምግባር
JICEC፣ በተማሪዎች የሚከፋፈሉ ትምህርተ-ነክ ያልሆኑ ህትመቶች
JK፣ የተማሪ ሥርዓት

## ድብቅ ማኅበረሰቦች/አደገኛ ቦዘኔዎች
(JICF)

**ድብቅ ቡድኖች/ማፊያዎች**

እንደዚህ ያሉ ማኅበራት ትምህርት ቦርድ እገዳ/እቀባ ባስቀመጠው መሰረት ካልሆነ በስተቀር፣ ተማሪዎች የማንኛውም ድብቅ ማኅበር (ቡድን) አባል ወይም ከድስትሪክት ትምህርት ቤቶች በሙሉ ወይም በከፍል አባልነት መፍጠር ከሚፈልጉ ጋር ወይም የድርጅቱ እንዲሆኑ ወይም በድርጅቱ እንዲሳተፉ ከሚፈልጉ ጋር መወገን ወይም የማንኛውም ድብቅ ቡድን ወይም ማኅበር አባል እንዳይሆኑ ተማሪዎች በሕግ የተከለከሉ ናቸው።

በአባላት መኃል ድብቅ መብት ያለው ወይም ለአንድ ወይም ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ ግልጽ የሚሆኑ የግል ጉዳዮች (አጀንዳዎች) ያለው ማንኛውም ተቋም በትምህርት ቦርድ ተቀባይነት አይኖረውም።

**አደገኛ ቦዘኔዎች**

የድስትሪክት ትምህርት ቤቶች እና ተማሪዎች ከዛቻዎች እና ከማንኛውም ቡድኖች ወይም የአደንዛዥ ዕጽን መጠቀም፣ ሁከትን ወይም ረብሻን የሚፈጥር ምግባር ከሚደግፉ አደገኛ ቦዘኔዎች ጥቃት እና ጎጂ ተጽኖዎች ነጻ እንዲሆኑ የትምህርት ቦርድ ይመኛል። የአደገኛ ቦዘኔ ተማሪዎች ማስፈራራት ለማስቀረት እና ከተለያዩ የአደገኛ ቦዘኔዎች ቡድን መኃል መጋፈጥ እንዳይኖር የትምህርት ቤት ኃላፊ ወይም ተወካይ ተከታታይ እና ግልጽ የሆነ የትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ቁጥጥር ያደርጋል/ታደርጋለች።

በዚህ ጥረት ውስጥ መረጃን ለመለዋወጥ እና ለመደጋገፍ የበላይ አለቃ ወይም ተወካይ ከአከባቢው የሕግ አስከባሪ አካላት ጋር ግልጽ የሆነ የመገናኛ መስመሮችን መዘርጋት አለበት። አደገኛ ቦዘኔዎችን እና ምልክቶቻቸውን መለየት እንዲችሉ፣ የሁከት ተግባራት መገለጫዎችን ቀደም ብለው እንዲያውቁ እና ለአደገኛ ቦዘኔዎች ምግባር አግባብ ያለውን ምላሽ መስጠት እንዲችሉ የበላይ አለቃው/ዋ ወይም ተወካይ ለሰራተኞቹ የሥራ ላይ ሥልጠና መስጠት አለበት። ሰራተኞች ተማሪዎችን ሊረዱ የሚችሉ የግጭቶች አያያዝ ዘዴዎችን እና በግጭቶች ጣልቃ የመግባት ሂደቶችን እና ለማኅበረሰብ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን እና ሌሎች ነገሮች ማወቅ አለባቸው።

በቀለም፣ በአለባበስ (በአደራረግ)፣ በንግድ ምልክት ወይም በሌላ ዓይነት መለያ የአደገኛ ቦዘኔዎች አባል መሆንን የሚገልጽ እና የአደንዛዥ ዕጽን መጠቀም፣ ሁከትን ወይም የሁከት ምግባርን የሚደግፍ ማንኛውም ዓይነት ልብስ፣ ጌጣጌጥ፣ ሌሎች አላስፈላጊ ነገሮች፣ የማስታወሻ ደብተር ወይም የጸጉር እና የጽም አቆራረጥን የትምህርት ቦርድ ይከለክላል። ይህ ፖሊሲ በየትምህርት ቤቱ ሲያስፈልግ ከበላይ አለቃ ወይም ከተወካይ ጋር ከተመካከሩበት በኃላ በትምህርት ቤት ኃላፊ ውሳኔ መሰረት ሥራ ላይ ይውላል።
ብዙ ተማሪዎች የአደገኛ ቦዘኔነት የሚያስከትለውን መዘዝ ሳይረዱ እንደሚገቡበት የትምህርት ቦርድ ይገነዘባል። የአደገኛ ቦዘኔዎችን መደራጀት ለማፍረስ ከሚደረጉ ጥረቶች ውስጥ ጉዳዩን ለማስቆም በግዜ ጣልቃ መግባት ቁልፍ ተግባር ነው። ስለዚህም ከሦስተኛ ክፍል ጀምሮ የአደገኛ ቦዘኔዎች ሁከት ክልከላ ትምህርት ይሰጣል።

ሥራ ላይ የዋለው ፣ አገስት 8፣ 1966
በቅርብ የተሻሻለው ፣ ሴፕተምበር 10፣ 1979
አሁን የተሻሻለው ፣ ሴፕተምበር 10፣ 2012
ህጋዊ ዋቢዎች፤ C.R.S. 22 1 117
C.R.S. 22 1 118
C.R.S. 22-23-109.1(2)(a)(1)(F)(ደህንነቱ የተጠበቀ ትምህርት ቤት እቅድ ክፍል የሆነ ፖሊሲ)
ጥምር ዋቢዎች፤ JJA፣ የተማሪ ማህበራት

## የተማሪዎች አልኮል መጠጥ እና ሌሎች የአደንዛዥ ዕጾችን መጠቀም
(JICH)

**1 መግቢያ**

የቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤት ዲስትሪክት አልኮልን፣ አደንዛዥ እጾችን እና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ንጥረ ነገሮችን እና አላግባብ መጠቀምን በተመለከተ ትምህርትን፣ ድጋፍን እና የውሳኔ አሰጣጥ ችሎታዎችን በመስጠት ለተማሪዎች ጤናማ አካባቢን መፍጠር አለበት። ይህንን ግብ ለማሳካት በትምህርት ቤቶች፣ በወላጆች/አሳዳጊዎች፣ በማህበረሰቡ እና በማህበረሰብ ኤጀንሲዎች መካከል የትብብር ጥረት መደረግ አለበት። የአልኮል መጠጥ እና ሌሎች የአደንዛዥ እጾች አስከፊ የጤና ችግር ሊያመጡ እንደሚችሉ የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት ያውቃል። በተጨማሪም የአደንዛዥ ዕጾችን እና የአልኮል መጠጦችን መጠቀም፣ ይዞ መገኘት፣ ማከፋፈል፣ ማደል፣ መሸጥ፣ ለሌላ ሰው መስጠት ወይም መቀያየር ሕገ ወጥ ተግባር እንደሆነ፣ ለተማሪዎች ጤንነት አደገኛ እንደሆነ እና ጤናማ የሆነ የመማሪያ አከባቢን እንደሚጎዳ የትምህርት ቦርድ ያውቃል።
1.ማንኛውም ተማሪ የአልኮል መጠጥ፣ ሀሺሽ፣ ሌሎች የተከለከሉ አደንዛዥ ዕጾችን (C.R.S. 12-22-301 et seq. የሚባል በ1981 በወጣው በኮሎራዶ የአደንዛዥ እጽ ሕግ መሰረት የተከለከሉ አደንዛዥ ዕጾች)፣ ወይም የአደዛዥ እፅ ዕቃዎችን በቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት ንብረት ላይ ይዞ መገኘት፣ መጠቀም፣ ማከፋፈል፣ ማደል፣ መሸጥ፣ ለሌላ ሰው መስጠት ወይም መቀያየር ተግባራት የትምህርት ቦርድ ፖሊሲን መጣስ ይሆናል፤ በተጨማሪም የእያንዳንዱን ተማሪ፣ የሌሎች ተማሪዎችን ወይም የትምህርት ቤት ሰራተኞችን ሰላም እና ደኅንነት የሚጎዳ ምግባር ተደርጎ ይወሰዳል።

ሀ.በዚህ ፖሊሲ ውስጥ የተከለከሉ አደንዛዥ እጾች፣ በነዚህ ብቻ ባይወሰኑም፣ የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፡ የናርኮትክ እጽ፣ ሃሉሲኖጀኒክ ወይም አይምሮን የሚቀይሩ (የሚነኩ) እጾች ወይም አምፌታሚን (amphetamines) ፣ ባርቢቱሬትስ (barbiturates) ፣ አይምሮን ወይም ሰውነትን የሚያነቃቁ፣ ድብርት ወይም መጫጫንን የሚያመጡ፣ ሀሺሽ፣ 'anabolic steroids' የሚባሉ እና በሕግ በተወሰነው መሰረት ሌላ ማንኛቸውም ዓይነት የተከለከሉ እጾች፣ ወይም የታዘዙ ወይም ያልታዘዙ እጾች፣ መዲሃኒት፣ ቫይታሚን ወይም ለተማሪዎች በሃኪም ትእዛዝ የሚሰጥ መዲሃኒት መስጠትን የሚመለከት የቦርዱ ፖሊሲ እና መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ሌሎች የሚከለከሉ የኬሚካል እጾች ናቸው።

ለ፣ ይህ ፖሊሲ በተጨማሪም ማንኛውንም የተከለከለ እጽ ወይም ተማሪ የተከለከለ እጽ ነው ብሎ የሚያምነውን ማንኛውንም አደንዛዥ እና ሱስ አስያዥ እጽ ያጠቃልላል።

2. ይህ ፖሊሲ በትምህርት ቤት ንብረት አከባቢ ያለ/ች፣ ትምህርት ቤት የሚከታተል (የሚትከታተል)፣ በትምህርት ቤት ማጓጓዣ ውስጥ ያለ/ች ወይም በትምህርት ቤት በሚዘጋጁ ተግባራት ወይንም ከት/ቤት ንብረት ውጪ ሆኖ ነገር ግን ምግባሩ ከትምህርት ቤት ወይም ከማንኛውም የዲስትሪክት ሥርዓተ ትምህርት ወይም ከሥርዓተ-ትምህርት-ያልሆኑ ክስተቶች ጋር ምክንያታዊ ግንኙነት ሲኖረ የሚሳተፍ/የሚትሳተፍ፣ ወይም በማንኛውም ጊዜ ወይም ቦታ ምግባሩ/ሯ የድስትሪክቱን ሥራ የሚያሰናክል ወይም የተማሪዎችን እና የሰራተኞችን ሰላም እና ደኅንነት የሚያውክ ማንኛውንም ተማሪ ይመለከታል።

3.ይህንን ፖሊሲ በሚጥሱ ተማሪዎች ላይ እስከ ከትምህርት ቤት ለጊዜው ከመደበኛው ትምህርት ቤት ማገድ እና/ወይም ከትምህርት ቤት ማስወጣት የሚደርሱ የቅጣት እርምጃዎች ይወሰድባቸዋል፤ በተጨማሪም ጉዳዩ ለሕጋዊ ቅጣት ይተላለፋል።

II. **ሕክምና እና መከላከያ ዘዴዎች**

1.ተማሪው የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀምን ለማሸነፍ ከአማካሪ ምክር ወይም መረጃ የሚፈልግባቸው ሁኔታዎች እንደየጉዳዩ ተፈጥሮ እና ዝርዝር ሁኔታ በግለሰብ ደረጃ መስተናገድ አለባቸው።አስፈላጊ ሲሆን ወላጆች/አሳዳጊዎች ይሳተፋሉ እና ሱሰኛ አላግባብ መጠቀምን ለመቅረፍ ተማሪውን በቀጥታ መረጃዎችን የሚያገኙባቸዉን ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ጥረት ማደረግ አለባቸው።

2. ቦርዱ በትምህርት ቤት ዕድሜ ላይ ባሉ ወጣቶች የአደንዛዥ ዕፅ እና አልኮል ዕፅ እና አልኮል አላግባብ መጠቀም የህብረተሰቡ ችግር መሆኑን በመገንዘብ ከህግ አስከባሪዎች፣ ሰብአዊ ማህበራዊ አገልግሎቶች ወይም ሌሎች ኤጀንሲዎች እና ድርጅቶች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ሌሎች እውቅና ያላቸው የማህበረሰብ ሀብቶች ጋር በህገ-ወጥ አጠቃቀም ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን ለመቀነስ በንቃት መተባበር አለበት።

3.ተማሪዎች ከአደንዛዥ እፅ እና አልኮል አጠቃቀም ጋር ተያይዘው የሚያጋጥሟቸውን ተግዳሮቶች ለመቋቋም በሚቻልበት ጊዜ የትምህርት ቤት ሰራተኞች ለወላጆች/አሳዳጊዎች እና ተማሪዎች ከአደንዛዥ እፅ አጠቃቀም ጋር የተያያዙ የትምህርት እና የማገገሚያ ፕሮግራሞችን መረጃ መስጠት አለባቸው።

4.ስለማህበረሰብ እፅ አላግባብ መጠቀምን አያያዝ ፕሮግራሞችን ወይም ሌሎች ግብአቶችን በተመለከተ የሚሰጠው መረጃ ዲስትሪክቱ ከዚህ ጋር ተያይዞ በተጠቀሰው ደንብ ካልተገለጹ በስተቀር በሌሎች ኤጀንሲዎች ለሚሰጠው የአደንዛዥ እፅ ወይም አልኮል ግምገማ ወይም ህክምና ምንም አይነት የገንዘብ ሃላፊነት እንደማይወስድ ለማብራራት ለተማሪዎች እና/ወይም ለወላጆች/አሳዳጊዎች የማስተባባያ ቅጽ መያያዝ አለበት። እንዲሁም ድስትሪክቱ ለተሰጡት ፕሮግራሞች ውጤታማነት ኃላፊነቱን አይወስድም። 5.የዚህ ፖሊሲ ግልባጭ እና ተጓዳኝ ሂደቶች በየአመቱ በዲስትሪክቱ ድረ-ገጽ ላይ መቅረብ አለባቸው።

6. ዲስትሪክቱ የአደንዛዥ ዕፅ እና የአልኮሆል መከላከያ መርሃ ግብሩን ውጤታማነት ለመወሰን እና አስፈላጊ ለውጦችን ለመተግበር በየጊዜው ግምገማ ያካሂዳል።

*በመጀመሪያ ሥራ ላይ የዋለው: ማርች 10፣ 2003*
*ለመጨረሻ ጊዜ የተሻሻለው፤ ፌቡራሪ 13፣ 2017*
*የአሁኑ ክለሳ ማርች 2023*

ሕጋዊ ዋቢዎች፤ 20 U.S.C. Section 3221 (የአደንዛዥ እፅ ሱስ ትምህርት እና ክልከላን ይመለከታል)
20 U.S.C. Section 7116 (በ1994 የወጣው ደኅንነቱ የተጠበቀ እና ከአደንዛዥ እፅ ነፃ የሆኑ ትምህርት ቤቶች እና ማኅበረሰቦች ሕግ)
U.S.C. § 812 ("ቁጥጥር የሚደረግባቸው ንጥረ ነገሮች" ፍቺ እና ቁጥጥር የሚደረግባቸው ንጥረ ነገሮች መርሃ ግብሮች
C.R.S. 18-18-102(3), (5) ( "anabolic steroid" እና "የተከለከሉ እጾች" ትርጉም)
C.R.S. 18-18-407(2) (በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ/ አከባቢ ወይም በትምህርት ቤት አውቶቡስ ውስጥ የተከለከሉ እጾችን የመሸጥ፣ የማከፋፈል ወይም ይዞ የመገኘት ወንጀል)
C.R.S. 22-1-110 (የአልኮል መጠጥ እና የአደንዛዥ እፆችን የሚመለከት መመሪያ)
C.R.S. § 22-1-119.3 (3)(c), (d) (የሕክምና ማሪዋና እና የተማሪ የማሩዋና ይዞታ ወይም መድሃንቱን በራሳቸው መዉሰድ አይችሉም)

C.R.S. 22-32-109.1 (2)(a) (I) (G)(ደኅንነታቸው ለተጠበቁ ትምህርት ቤቶች እቅድ አስፈላጊ የሆነ ፖሊሲ)
C.R.S. 22-33-106(1)(d) (አደንዛዥ እጽን ወይም የተከለከለ እፅን መሸጥ በተመለከተ ለጊዜው ከመደበኛው ትምህርት ቤት የመታገድ ምርጫ)
C.R.S. § 25-1.5-106 (12)(b)(IV) ((በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ወይም በትምህርት ቤት አውቶቡስ ውስጥ የሕክምና ማሪዋና መያዝ ወይም መጠቀም የተከለከለ ነው);
C.R.S. § 25-14-103.5(የትምህርት ቦርድ በትምህርት ቤት ንብረት ላይ የቸርቻሮ ማሪዋና መጠቀምን የሚከለክሉ ፖሊሲዎችን ማርቀቅ አለባቸው);

ጥምር ዋቢዎች፤ IHAMA፣ ስለ አደንዛዥ እፆች፣ የአልኮል መጥጥ እና ትምባሆ ማስተማር
JTH፣ የተማርዎች ቃለ መጠይቅ፣ ፍተሻ እና እስራት
JKD/JKE፣ ተማሪዎችን ከትምህርት ቤት ማስወጣት/ከመደበኛው ትምህርት ቤት ማገድ
JLCA፣ የተማሪዎች የጤና አገልግሎቶች እና መስፈርቶቹ
JLCD - መድሃኒቶችን ለተማሪዎች መስጠት
JLCDB - በዲስትሪክት ንብረት ላይ ብቁ ለሆኑ ተማሪዎች የህክምና ማሪዋናን መስጠት

## የተማሪዎች የአልኮል መጠጥ እና ሌሎች አደንዛዥ እጾችን መጠቀም (JICH-R)

'JICH' የሚባለውን ፖሊሲ ሥራ ላይ ለማዋል የሚከተሉት መተዳደሪያ ደንቦች በጥብቅ ያስፈልጋሉ

I. ***መግቢያ***

' JICH' የሚባል ፖሊሲ ሲሰጥ፣ ቀደም ብለው የተዘጋጁት እነዚህ ቀጥሎ የተሰጡት ሂደቶች መከተል አለባቸው። እነዚህ ሂደቶች የቦርድ ፖሊሲውን ያጠብቃሉ እንጂ አያሳንሱም። ተማሪዎች በሚመለከተው የቦርድ ፖሊሲ መሰረት ሥነ-ሥር ዓታዊ እርምጃ ይወሰድባቸዋል።

II. **ትርጉሞች**

*ሀ.* **የተከለከሉ እጾች**

1. ክልክል የሆኑ እጾች ኮኬን፣ ሄሮይን፣ የአልኮል መጠጥ፣ ማርዋና፣ እና ሌሎች የሚጨሱና ተመሳሳይ ምርቶችን ያካትታል።

2. እንደዚሁም ክልክል የሆኑ እጾች በ1992ቱ (C.R.S. 18-18-101, et seq.)አዋጅ ውስጥ የተካተቱትን ምርቶች ያካትታል።

ለ. **በትምህርት ቤት ሕጋዊ ቅጥር ግቢ ውስጥ**

በትምህርት ድስትሪክት ንብረት ውስጥ ሲሆኑ፣ በትምህርት ቤት በሚዘጋጁ ተግባራት ላይ ሲሳተፉ፣ በትምህርት ድስትሪክት በሚሰራጩ ማጓጓዣዎች በሚጓዙበት ጊዜ ወይም የትምህርት ቤትን አውቶቡስ ለመሳፈር ሲጠብቁ ወይም ከአውቶቡሱ ሲወርዱ ተማሪ በትምህርት ቤት ሕጋዊ ቅጥር ግቢ ውስጥ እንዳለ/ች ይወሰዳል።

ሐ. 'Paraphernalia' (ፓራፈርናሊያ) የሚባል እጽ

'Paraphernalia' (ፓራፈርናሊያ) የሚባል እፅ በ 1992፣ 18-18-426 በአንድ ዓይነት የተከለከሉ እጾች ሕግ ውስጥ እንደተወሰኑ ማናቸኛውንም መዲሃኒት፣ መሣሪያ ወይም መገልገያ ዕቃዎች ነው።

መ. **ሐሰተኛ እፆች**
ሀሰተኛ እፅ በተከለከለ እፅ ውስጥ የሚካተት ማንኛውም ዓይነት እፅ ነው።

ሠ. **የተማሪዎች የተከለከሉ እፆች መውሰድ/መጠቀም ምልክቶች**
በትምህርት ድስትሪክት ሕጋዊ ክልል ውስጥ የተማሪ ምግባር፣ ሁኔታ፣ አነጋገር ወይም ገጽታ ሲቀየሩ ወይም ምልክቶቹ ሲታዩበት ተማሪው/ዋ የተከለከሉ እፆችን እንደወሰደ/ች ተደርጎ ይወሰዳል ወይም ከዚህ በፊት እነዚህን የተከለከሉ እፆችን ሲጠቀም/ሲትጠቀም እንደነበር ያመለክታል።

ረ. **የተከለከሉ እፆችን ይዞ መገኘት**
ተማሪ የተካላከሉ እፆችን እንዳለው/እንዳለት ካመነ/ች፣ ወይም ክልክል የሆነውን ፓራፈርናሊያ እፅ በተማሪው/ዋ እጅ፣ በግል ንብረቱ/ቷ ውስጥ፣ በመኪናው/ዋ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ውስጥ፣ በዕቃ ማስቀመጫ ሳጥኑ/ኗ ውስጥ፣ በመቀመጫ ሥፍራው/ዋ ወይም በሌላ የዕቃ ማከማቻው/ዋ ሥፍራ ከተገኘ፣ በትምህርት ድስትሪክት ክልል ውስጥ ተማሪው/ዋ የተከለከሉ ፓራፈርናሊያ እፆችን እንዳለው/እንዳላት ተደርጎ ይወሰዳል። ተማሪው/ዋ ክልክል የሆኑትን እፆች ወይም ፓራፈርናሊያ እፅ አለው/አላት ሲባል ተማሪው/ዋ ያንን እፅ ይዞ/ዛ መገኘት፣ የግል አድርጎ መያዝ፣ ባለአደራ ሆኖ መያዝ፣ ወይም ማንኛውንም ዓይነት መጠን ክልክል ይሆኑትን ፓራፈርናሊያ እፆች ይዞ መገኘት ማለት ነው።

ሰ. **ክልክል የሆኑትን እፆች ማከፋፈል፣ ማደል፣ መሸጥ፣ ለሌላ ሰው መስጠት ወይም ከሌላ ሰው ጋር መለዋወጥ**
ክልክል የሆኑ እፆች ወይም ሐሰተኛ የሆኑ እፆች ከአንዱ ሰው ወደ ሌላው የሚተላለፉባቸው ማንኛቸውም ዓይነት መንገዶች ናቸው።

III. **መረጃዎችን ማስተላለፍ**
ክልክል የሆኑ እፆችን ወይም ፓራፈርናሊያ እፅ መጠቀምን የሚመለከቱ መጠነ ሰፊ የሆኑ የሕገ ወጥ ድርጊቶች መረጃዎች ድርጊቱ የተፈጸመበት ቀን፣ የሕገ ወጥ ድርጊቱ ዓይነት፣ እና የተወሰደው የቅጣት እርምጃ በተማሪ የምግባር ፋይል (ሰነድ) ውስጥ በትምህርት ቤት ደረጃ ተይዞ ተማሪው/ዋ በድስትሪክቱ ወደ የሚቀጥለው የትምህርት ቤት ደረጃ ሲሻገር/ሲትሻገር ጉዳዩ አግባብ ላለው የምግባር አስተዳደር ይተላለፋል። የተማሪ ፋይሎችን (ሰነዶችን) መያዝ ዓላማው ተማሪን ለመቅጣት ሳይሆን ልዩ ትኩረት የሚያስፈልጋቸውን የተማሪ ታሪክ መረጃን ጉዳዩን እንዲከታተሉ ለትምህርት ቤት ኃላፊዎች ለመስጠት ነው። ከተማሪ ምግባር ፋይል (ሰነድ) ማንኛውም የተማሪ መረጃ የሚወጣው በክፍለ ግዛት እና በፌዴራል ሕጎች መሰረት መሆን አለበት።

IV. **የቅጣት እርምጃ**
ክልክል የሆኑ እጾችን ወይም የፓራፈርናሊያ እፅ ይዘው የተገኙ፣ የሚያከፋፈሉ፣ የሚያድሉ፣ የሚሸጡ፣ ለሌላ ሰው የሚሰጡ ወይም የሚለዋወጡ ተማሪዎች እስከ ከመደበኛው የትምህርት ቤት ለጊዜው መታገድ ወይም ከትምህርት ቤት መባረር የሚደርሱ የቅጣት እርምጃዎች ይወሰድባቸዋል። የትምህርት ቤት ኃላፊ ወይም ተወካይ የተማሪን እያንዳንዱን የሕገ ወጥ ክስተት አግባብ ላላቸው የሕግ አስከባሪ ኃላፊዎች
ያመለክታል/ታመለክታለች።

ለጊዜው ከመደበኛው ትምህርት ቤት የማገድ ወይም የማባረር ሂደት 'JKD-1' የሚባል የትምህርት ድስትሪክት ፖሊሲ በሚያዘው መሰረት መሆን አለበት።

የልዩ ትምህርት ድጋፍ አገልግሎትን እያገኘ ያለ አካለ ስንኩል (የአካል ጉዳተኛ) ተማሪ ከላይ ከተገለጹት ሕገ ወጥ ተግባራት በማንኛውም ሕገ ወጥ ድርጊት ከተሳተፈ/ች ፣ መደበኛ የቅጣት ሥርዓት ሊወሰድበት/ሊወሰድባት ይችላል። 'Individual Education Program (IEP)' የሚባል የተማሪው/ዋ የግል የትምህርት ፕሮግራም (መርሃ ግብር) ይከለሳል። በትምህርት ቦርድ ፖሊሲ እና በፌዴራል ሕግ መሰረት፣ አካለ ስንኩል (የአካል ጉዳተኛ) ተማሪ በጠቅላላው ወይም በተካታታይ በአንድ የትምህርት ዘመን ውስጥ ከ10 ቀናት በላይ ከትምህርት ቤት ከታገደ/ች የማስፋፊያ ውሳኔ ይወሰዳል።

ሁሉም ሕገ ወጥ ድርጊቶች በተዘረዘረው የቅጣት እርምጃ መሰረት ቅጣት ይወሰድባቸዋል። እንደነዚህ ዓይነቶቹ ሕገ ወጥ ድርጊቶች ብዛት ሲደመሩ በነጠላ ምድብ ወይም የሁሉም ምድቦች ጣምራ ሊሆን ይችላል።

የተማሪዎችን ክልክል የሆኑ እፆችን ወይም ፓራፈርናሊያ እፅ መጠቀም፣ ይዞ መገኘት፣ ማከፋፈል፣ ማደል፣ መሸጥ፣ ለሌላ ሰው መስጠት ወይም መለዋወጥ መመርመር በተመለከተ ሁሉም ሰራተኞች አግባብ ያላቸውን የሕግ አስከባሪዎች መርማሪዎችን ይተባበራሉ።

ሀ. **ክልክል የሆኑ እፆችን መጠቀም**
ማንኛውንም ክልክል የሆኑ እፆችን(የአልኮል መጠጥ፣ ሀሺሽ፣ ክልክል የሆነ እፅ ወይም ሐሰተኛ እፅ) ለሚጠቀሙ ተማሪዎች የሚከተሉት ሂደቶችን መከተል አለባቸው፤

1. ሕጋዊ በትምህርት ድስትሪክት ክልል ውስጥ ክልክል የሆነ እፅ ሲጠቀም/ሲትጠቀም የታየ/ች ተማሪ፣ የትምህርት ቤት የሥራ ባልደረባ ጉዳዩን ተማሪውን/ተማሪዋን ለሚከታተል/ለሚትከታተል ለትምህርት ቤቱ ኃላፊ ወይም ተወካይ ያሳውቃል/ታሳውቃለች።
2. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣ የእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የአደጋ ጊዜ ሂደቶች ይከተላሉ።
3. በትምህርት በት ኃላፊ ወይም ተወካይ ከተወሰነ፣ ያልተለመደ ገጽታ ወይም ያልተለመደ፣ ሁከት የሚፈጥር፣ ወይም አደገኛ ምግባር የሚከሰተው ተማሪው/ዋ ክልክል የሆኑ እፆችን ሲወስድ/ሲትወስድ ሊሆን ይችላል፣ ጉዳዩ በአስቸኳይ ለወላጆች እንዲታወቅ ይደረጋል። የተማሪው/ዋ ገጽታ እና ምግባር ለወላጆች ይነገራል።
4. የትምህርት ቤት ኃላፊ ወይም ተወካይ በቀጥታ ተማሪን በመጠየቅ ወይም በትምህርት ቦርድ መተዳደሪያ ደንብ ክፍል V ውስጥ በተነደፈው የመረጃ ማጣራት ሂደትን በመከተል መረጃን ለማግኘት ጥረት ያደርጋል/ታደርጋለች።
5. ወላጅን ወይም የሕክምና እርዳታን ሲጠብቁ፣ ተማሪው/ዋ ፀጥተኛ ቦታ በጥበቃ ሥር ይቆያል/ትቆያለች።
6. ጉዳዩን በተመለከተ ከሕግ አስከባሪ ባለሥልጣናት ጋር ግንኙነት ይደረጋል፣ ለወላጅ እና ለተማሪ ስለግንኙነቱ ይነገራቸዋል።
7. ከላይ እንደተገለጸው ተማሪው/ዋ ክልክል የሆነ እጽ እንደተጠቀመ ከተውሰነበት/ከተወሰነባት፣ በተማሪው/ዋ ላይ ከታች የተሰጠው የቅጣት እርምጃ ይወሰድበታል/ይወሰድባታል።

**የመጀመሪያ ጊዜ ጥፋት**

ሀ. ተማሪው/ዋ ለአምስት (5) የትምህርት ቀናት ከትምህርት ቤት ይታገዳል/ትታደጋለች፣ የትምህርት ቤት ኃላፊ የበላይ አለቃን በመጠየቅ ጊዜውን ለአምስት ቀናት በማራዘም በአጠቃላይ ለአስር (10) የትምህርት ቀናት ተማሪው/ዋ ከትምህርት ቤት እንዲታገድ/እንዲትታገድ ሊሆን ይችላል።

1. ተማሪው/ዋ የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት የአልኮል መጠጥ እና/ወይም የእጽ ትምህርት/የጣልቃ መግባት መርሀ ግብርን ከተቀበለ/ች፣

የአስር (10) የትምህርት ቀን ቅጣት ወደ ሦስት (3) ቀን ሊቀንስ ይችላል። በራስ ተነሳሽነት ጣልቃ የመግባት እና ነገሮቹን የማስተካከል፣ እንደዚሁም በመርሀ ግብሩ ጉዳዩን የመጨረስ ኃላፊነት የተማሪው/ዋ እና የወላ(ጆቹ)/የወላ(ጆቿ)/የአሳዳጊ(ዎቹ)/የአሳዳጊ(ዎቿ) ድርሻ ነው። የድስትሪክቱን መርሀ ግብር (ፕሮግራም) የሚመለከት የማንኛውም ዓይነት የአገልግሎት ክፍያ (ሂሳብ) የተማሪው/ዋ እና የወላጆቹ(ቿ)/የአሳዳጊዎቹ (ቿ) ብቻ ኃላፊነት ይሆናል። የዲስትሪክቱን የትምህርት/የጣልቃ መግባት መርሀ ግብር (ፕሮግራም) ማጠናቀቅን የሚገልጽ መረጃ በዲስትሪክቱ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ መቅረብ አለበት። በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ይህንን መረጃ አለማቅረብ ለአስር (10) የትምህርት ቀናት ከትምህርት ቤት የመታገድ ውሳኔን ያጸድቃል።

2. ተማሪው/ዋ እና ወላ(ጆቹ)/ወላ(ጆቿ) የድስትሪክቱን መርሀ ግብር (ፕሮግራም) ትተው የአልኮል መጠጥ ወይም የእፅ ትምህርት/ያጣልቃ መግባት መርሀ ግብር መርጠው ሊፈጽሙ ይችላሉ። ይህ የአማራጭ ፕሮግራም በይዘቱ እና በሚወስደው ጊዜ ከድስትሪክቱ ፕሮግራም ጋር እኩል መሆን አለበት፤ በተጨማሪም ተማሪው/ዋ፣ ወላጁ(ጆቹ)/ወላጇ(ጆቿ) እና የትምህርት ቤት አስተዳደር በጉዳዩ መስማማት አለባቸው። ከአማራጭ ፕሮግራሙ ጋር የሚያያዝ ማንኛውም ዓይነት ወጪ ወይም ክፍያ የተማሪው/ዋ እና የወላጁ (ጆቹ)/የወላጇ(ጆቿ)ብቻ ኃላፊነት ይሆናል። የአማራጭ መርሀ ግብር (ፕሮግራም) ማጠናቀቅን የሚገልጽ መረጃ በዲስትሪክቱ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ መቅረብ አለበት።በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ይህንን መረጃ አለማቅረብ ለአስር (10) የትምህርት ቀናት ከትምህርት ቤት የመታገድ ውሳኔን ያጸድቃል።

ለ. ተማሪው/ዋ ወደ ትምህርት ቤት ከመመለሱ በፊት ከወላጅ ጋር ስብሰባ ይደረጋል። ተማሪው/ዋ በተሰማሙበት የትምህርት/የጣልቃ መግባት ፕሮግራም ለመሳተፍ መታቀፉን/መታቀፏን ካሳየ/ች፣ ከተሰጠው የ10 (አስር ቀን) ከትምህርት ቤት መታገድ ጊዜ ውስጥ ከሦስተኛ ቀን በኃላ የተማሪው/ዋን ወደ ትምህርት ቤት መመለስ በተመለከተ የቅድሚያ ስብሰባ ለማድረግ መስፈርቱን ያሟላል/ታሟላለች። ተማሪው/ዋ የቅድሚያ ስብሰባው አካል የሆነውን በፕሮግራሙ ለመሳተፍ መታቀፉን/መታቀፏን የሚገልጽ ማስረጃ ማምጣት አለበት/አለባት። ተማሪው/ዋ በቅድሚያ ስብሰባ ጊዜ በፕሮግራሙ መሳተፉን/መሳተፏን የሚገልጽ መረጃ ካቀረበ/ች፣ የቀሩት ሰባት (7) ቀናት ከምግባር ሰነዱ/ዷ ተሰርዘውለት/ተሰርዘውላት እንደገና ወደ ትምህርት ቤት እንዲመለስ/እንዲትመለስ ይደረጋል። በተጨማሪም፣ ስለተማሪው/ዋ ወደ ትምህርት ቤት መመለስ የቅድሚያ ስብሰባ ጊዜ፣ ወደ ፊት እንደዚህ ዓይነቶቹን ሕገ ወጥነት ለማስቀረት በሚያደርጉት ጥረት፣ የትምህርት ቤት ኃላፊዎች፣ ከወላጅ እና ከተማሪው/ዋ ጋር በመሆን የወላጅ፣ የተማሪ እና የትምህርት ቤቱን ኃላፊነቶች ንድፍ የሚመለከት የጽሁፍ ስምምነት ያዘጋጃሉ። ይህም ስምምነት ተማሪው/ዋ ከትምህርት ቤት የሚታገድበት/የሚትታገድበት ጊዜያት እንዲያጥሩ የሚረዱ መስፈርቶችና በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተማሪው/ዋ የጣልቃ መግባቱን ፕሮግራም (መርሃ ግብር) ካላጠናቀቀ ተጨማሪ ለ ሰባት (7) የትምህርት ቀናት ከትምህርት ቤት መታገድ መግለጫ ይጸድቃል። ወደ ትምህርት ቤት ለመመለስ የቅድሚያ ውይይት ጊዜ የተማሪው/ዋን መረጃ ከትምህርት/ከጣልቃ መግባት ፕሮግራም/መርሃ ግብር ለማግኘት እና ተማሪው/ዋ በጣልቃ መግባቱ ፕሮግራም መሳተፉ/ፏን እና ፕሮግራሙን ማጠናቀቁ/ቋን ለማረጋገጥ አስፈላጊውን መረጃ ለማረጋገጥ ተማሪው/ዋ ወይም ወላጁ(ጆቹ)/ጇ(ጆቿ) መረጃው እንዲታይ መፍቀዳቸውን በጽሁፍ እንዲያረጋግጡ ሊጠየቁ ይችላሉ። በተጨማሪም፣ ይህ የጽሁፍ ስምምነት የሁለተኛ ጊዜ መተላለፍ የሚያስከትለውን ጉዳይ በውስን ይገልጻል።

ሐ. ድስትሪክቱ ለተማሪው/ዋ እና ለወላጆቹ/ለወላጆቿ/ ለጠባቂዎቹ(ቿ) የአልኮል መጠጥ እና/ወይም የእጽ ትምህርት /ጣልቃ መግባት፣ ምክር እና/ወይም ከዚህ የመፈወሻ/የእርዳታ አማራጮችን በተመለከተ የመረጃ ዝርዝርን ይሰጣል። የአቅራቢዎቹን ሁኔታ፣ አዘገጃጀቱን፣ ሥልጠናውን ወይም አገልግሎቶቹን ዝርዝር መስጠት ትምህርት ቤቱ ወይም ድስትሪክቱ ይህንን ነገር ይደግፋል ወይም ለጉዳዩ ዋስትና ይሰጣል ማለት አይደለም። ትምህርት ቤቱም ሆነ የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት በግል በተማሪ እና በአቅራቢዎች መሃል ለሚደረገው ስምምነት ኃላፊነት አይወስድም።

**የሁለተኛ ጊዜ ጥፋት**

ሀ. ተማሪው/ዋ ለአምስት(5) የትምህርት ቀናት ከትምህርት ቤት ይታገዳል/ትታገዳለች። የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ መተላለፍ እና ተማሪው/ዋ ከትምህርት ቤት እንዲታገድ/እንዲትታገድ የሚያስገድድ አሳሳቢ ሁኔታ ሲፈጠር የትምህርት ቤቱ ኃላፊ የበላይ አለቃው/ዋን በመጠየቅ ለአምስት(5) ተጨማሪ ቀናት በማስረዘም በአጠቃላይ ለአስር(10) የትምህርት ቀናት ተማሪው/ዋ ከትምህርት ቤቱ እንዲታገድ/እንዲትታገድ ይሆናል።

1. ከመጀመሪያዎቹ አምስት(5) የትምህርት ቀናት መታገድ በኃላ፣ ተማሪው/ዋ እና ወላጆቹ/ቿ/ ሕጋዊ ጠባቂዎቹ/ቿ/ ተማሪው/ዋ በግሉ የአልኮል መጠጥ እና /ወይም የእጽ ምርመራ ለመሳተፍ መምረጡን እና ተማሪው አግባብ ያለውን ህክምና/እርዳታ እቅድ እና በአልኮል መጠጥ ወይም በእጽ ትምህርት/ጣልቃ መግባት/የህክምና (የድጋፍ ማግኛ) ፕሮግራም (መርሃ ግብር) ለመመዝገብ ማቀዱን/ማቀዷን ማስረጃ ሲያቀርብ/ሲታቀርብ ተማሪው/ዋ ከትምህርት ቤት ለአስር(10) የትምህርት ቀናት መታገድ ሁኔታ ወደ አምስት(5) ቀናት ሊቀንስ ይችላል፤ ከትምህርት ቤት እንዲታገድ/እንዲትታገድ የተፈለገውም ሊቀር ይችላል። የምርመራውን ሁኔታ መጀመር እና የምርመራውን እና የህክምና/የድጋፍ እቅዱን ተከታትሎ መጨረስ የተማሪው/ዋ እና የወላጆቹ(ቿ) ብቻ ኃላፊነት ይሆናል። ከምርመራው ጋር የተያያዘ ማንኛውም ወጪ ወይም ክፊያ እና/ወይም የህክምና (የድጋፍ) እቅድ ወይም በህክምናው መሳተፍ የተማሪው/ዋ እና የወላጆቹ/ቿ/የጠባቂዎቹ/ቿ ብቻ ኃላፊነት ይሆናል።

2. የአልኮል መጠጥ እና የእጽ ጣልቃ መግባት፣ የምክር እና/ወይም የህክምና (የድጋፍ አገልግሎት) አማራጮች የመረጃ ዝርዝር ለተማሪዎች እና ለወላጆቹ ሲጠይቁ ይሰጣቸዋል። የአቅራቢዎቹን ሁኔታ፣ አዘገጃጀቱን፣ ሥልጠናውን ወይም አገልግሎቶቹን ዝርዝር መስጠት ትምህርት ቤቱ ወይም ድስትሪክቱ ይህንን ነገር ይደግፋል ወይም ለጉዳዩ ዋስትና ይሰጣል ማለት አይደለም። ትምህርት ቤቱም ሆነ የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት በግል በተማሪ እና በአቅራቢዎች መሃል ለሚደረገው ስምምነት ኃላፊነት አይወስድም።

ለ. ተማሪው/ዋ ቀደም ብሎ/ብላ እንደገና ወደ ትምህርት ቤት የመመለስ ሂደትን ቢመርጥም/ቢትመርጥም ወይም ባይመርጥም/ባትመርጥም፣ ተማሪው/ዋ ወደ ትምህርት ቤት ከመመለሱ/ሷ በፊት ከወላጅ ጋር ውይይት ይደረጋል። ተማሪው/ዋ ቀደም ብሎ ወደ ትምህርት ቤት የመመለስ ሂደትን እና ቀሪ ቀናትን የማስቀረት ሂደት ቢመርጥ/ቢትመርጥ፣ ተማሪው/ዋ የመጀመሪያዎቹን አምስት(5) የትምህርት ቀናት እገዳ ካጠናቀቀ/ች በኃላ ውይይት ያደርጋል። ቀደም ብሎ ወደ ትምህርት ቤት የመመለስ ውይይት ሲደረግ፣ ተማሪው/ዋ እና ወላጆቹ/ቿ/ ሕጋዊ ጠባቂዎቹ/ቿ የተማሪው/ዋን የአልኮል መጠጥ እና/ወይም የእጽ ምርመራ ማጠናቀቁ/ቋን እና በአልኮል መጠጥ እና/ወይም በእጽ ህክምና መርሃ ግብር መሳተፉ/ፏን እና የታዘዘውን የህክምና መርሃ ግብር ንድፍ ማስረጃ ማቅረብ አለበት/አለባት። ከምርመራው ጋር የተያያዘ ማንኛውም ዓይነት ወጪ ወይም ክፊያ እና/ወይም የህክምና (የድጋፍ) እቅድ ወይም በህክምናው መሳተፍ የተማሪው/ዋ እና የወላጆቹ/ቿ/የጠባቂዎቹ/ቿ ብቻ ኃላፊነት ይሆናል። በቀደም ብሎ ወደ ትምህርት ቤት መመለስ ውይይት ጊዜ ይህንን ሰነድ ማዘጋጀት ተማሪው/ዋ በትምህርት ቤቱ እንደገና እንዲመዘገብ/እንዲትመዘገብ ያስችላል። በተጨማሪም የቀሩትን አምስት (5) የትምህርት ቀናት እገዳ እና ተማሪው/ዋ ከትምህርት ቤት እንዲታገድ/እንዲትታገድ የተደረገውን ጉዳይ ያስቀራል። ተማሪው/ዋ ቀደም ብሎ ወደ ትምህርት ቤት በመመለስ ህደት መሳተፍን ካልመረጠ/ች፣ተማሪው/ዋ የእገዳ ጊዜ ገደቡን እንዳጠናቀቀ/ች ይህንን የመተዳደሪያ ደንብ ለመከለስ ዓላማዎች እና ስለ ወደፊት ሕግን መተላለፍ ሊያስከትሉ የሚችሉትን ሁኔታዎች ለተማሪው/ዋ ለማሳወቅ ከተማሪው/ዋ ጋር የወደ ትምህርት ቤት መመለስ ውይይት ይደረጋል።

ሐ. ከትምህርት ቤት አስተዳደር፣ ከተማሪው/ዋ እና ከወላጅ ጋር የጽሁፍ መግለጫዎች ይሞላሉ። ተማሪው/ዋ ቀደም ብሎ ወደ ትምህርት ቤት መመለስን ከመረጠ/ች፣ ተማሪው/ዋ የቀሩትን አምስት (5) የትምህርት ቀናት እገዳ ለመቀነስ እና ተማሪው/ዋን ለማባረር የተወሰነውን ውሳኔ ለማስቀረት መስማማቱ/ቷን በፍርማው/ዋ ያረጋግጣል/ታረጋግጣለች። ስምምነቱ የቀሩት አምስት (5) የትምህርት ቀናት እገዳ ላይ የተደረገው ቅነሳ እና ተማሪው/ዋን ለማባረር የተወሰነው ውሳኔ መቅረቱ ጉዳይ ተማሪው/ዋ የቀረበውን የህክምና/የድጋፍ መርሃ ግብር ካላጠናቀቀ/ች ለአልኮል መጠጥ እና ለእጽ ጉዳይ የተወሰነው ውስኔ ተመልሶ ይጸድቃል። ተማሪው/ዋ በጣልቃ ገብ መርሃ ግብሩ እየተሳተፈ/ች እና መርሃ ግብሩን እያጠናቀቀ/ች መሆኑን/መሆኗን ለማረጋገጥ እንዲችሉ ከመርሃ ግብሩ አቅራቢ አስፈላጊውን መረጃ ማግኘት እንዲችሉ የትምህርት ቤት ኃላፊ ወይም ተወካይ የተማሪው/ዋን ወላጆች/ሕጋዊ ጠባቂዎችን መረጃው ለትምህርት ቤት እንዲሰጥ ፈቃዳቸውን በጽሁፍ እንዲያሳውቁ ሊጠይቁ ይችላሉ።

መ. አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ፣ ለዲስትሪክቱ ውስጥ ለውስጥ ዝውውር ልዩ አስተያየት ሊደረግ ይችላል፣ እንደዚሁም ሌሎች የትምህርት አማራጮች ሊኖሩ ይችላሉ። በዲስትሪክቱ ውስጥ ለውስጥ ዝውውር የሁለቱ ትምህርት ቤቶች አስተዳደሮች የጋራ ስምምነት ያስፈልጋል። ለአዲሱ ትምህርት ቤት የማጓጓዥ አገልግሎት የተማሪው/ዋ እና የወላጆቹ/ቿ ኃላፊነት ይሆናል።

**የሦስተኛ ጊዜና በተከታታይ የጥፋት ድርጊቶችን መፈጸም**

ሀ. JKD-1-R በሚባለው የትምህርት ቦርድ መተዳደሪያ ደንብ በተነደፈው መሰረት የእገዳው ሁኔታ እስከታይ ድረስ ተማሪው/ዋ ከትምህርት ቤት ይታገዳል/ትታገዳለች።

ለ. ተማሪን ከትምህርት ቤት ለማገድ የሚከተሉት ሂደቶች JKD-1-R በሚባለው በትምህርት ቦርድ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት በተነደፈው ይሆናል።

**ለ. አደገኛና ጎጂ መሳሪያዎችንና ቁስ አካሎችን ይዞ መገኘት**

በትምህርት ድስትሪክት ቅጥር ግቢ ውስጥ ተማሪ ክልክል የሆኑትን እጾች ፣ ወይም ፓራፈርናሊያ የሚባል እጽን መያዝ አስመልክቶ የሚከተሉት ሂደቶች መከተል አለባቸው:

1.ተማሪ ክልክል የሆኑትን እጾች ወይም ፓራፈርናሊያ የሚባልን እጽ እንደያዘ/ች የተጠራጠረ/ች የሥራ ባልደረባ ጉዳዩን በአስቸኳይ ለትምህርት ቤቱ ኃላፊ ወይም ተወካይ ማሳወቅ አለበት/አለባት።

2.ተማሪ ክልክል የሆኑትን እጾች ወይም ፓራፈርናሊያ የሚባልን እጽ እንደያዘ/ች አሳማኝ መረጃ ያለው የሥራ ባልደረባ ተማሪው/ዋን ቁጥጥር ስር በማድረግ፣ ተማሪው/ዋ የስራ ባልደረባውን በመከተል ወደ የትምህርት ቤቱ ኃላፊ ወይም ተወካይ እንዲሄድ/እንዲትሄድ ይጠይቃል/ትጠይቃለች።

ተማሪው/ዋ ካልታዘዘ/ች፣ የስራ ባልደረባው/ዋ ለትምህርት ቤቱ ኃላፊ ወይም ተወካይ ጉዳዩን ሲያሳውቅ/ሲታሳውቅ፣ በተቻለ መጠን ከተማሪው/ዋ ጋር ለመሆን አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል/ታደርጋለች።

3. ኃላፊው/ዋ ወይም ተወካይ ከተማሪው/ዋ በቀጥታ በመጠየቅ ወይም በትምህርት ቦርድ የመተዳደሪያ ደንቦች (ፍተሻዎች) ውስጥ በክፍል V ውስጥ በተነደፉት የፍተሻ ሂደቶች መሰረት መረጃን ለማግኘት ጥረት ያደርጋል/ታደርጋለች።

4.ተማሪው/ዋ ክልክል የሆኑትን እጾች ወይም ፓራፈርናሊያ የሚባልን እጽ ከያዘ/ች፣ ኃላፊው/ዋ ወይም ተወካይ መረጃውን በፖስታ ውስጥ ያደርጋል/ታደርጋለች። ፖስታው ይታሸጋል፣ ቀን ይጻፍበታል እናም መጀመሪያ መረጃውን ባገኘ/ች ግለሰብ እና በኃላፊው/ዋ ወይም በተወካይ ተፈርሞበት በጥንቃቄ ይያዛል።

5. ኃላፊው/ዋ ወይም ተወካይ ጉዳዩን አግባብ ላለው የህግ አስከባሪ ክፍል በማሳወቅ ፖሊስ እጽ ያለበትን የታሸገውን ፖስታ ለምርመራ እንዲወስድ/እንዲትወስድ ይጠይቃል/ትጠይቃለች።

6.ተማሪው/ዋ ማንኛውንም ክልክል የሆነውን እጽ ወይም ፓራፈርናሊያ የሚባል እጽን ይዞ/ዛ ከተገኘ/ች፣ ወይም ተማሪው/ዋ ማንኛውንም ክልክል የሆነውን እጽ ወይም ፓራፈርናሊያ የሚባል እጽ መያዙ/ዟን ካመነ/ች፣ በተማሪው/ዋ ላይ ከታች የተሰጠው የቅጣት እርምጃ ይወሰድበታል/ይወሰድባታል:

**የመጀመሪያ ጊዜ ጥፋት**

ሀ. ተማሪው/ዋ ለአምስት (5) የትምህርት ቀናት ፣ የትምህርት ቤቱ ኃላፊ ለትምህርት ቤቶች የበላይ አለቃ ጊዜው እንዲራዘም በሚያቀርበው/በሚታቀርበው ጥያቄ መሰረት ለተጨማሪ አምስት (5) ቀናት በማራዘም በአጠቃላይ ለአስር (10) የትምህርት ቀናት ከትምህርት ቤት እንዲታገድ/እንዲትታገድ ይደረጋል/ትደረጋለች።

1. ተማሪው/ዋ የቼሪ ክሪክ ድስትሪክት የእጽ እና የአልኮል መጠጥ ትምህርት/ጣልቃ መግባት ፕሮግራምን ተከታትሎ/ላ ለማጠናቀቅ ከተስማማ/ች፣ የአስር (10) የትምህርት ቀናት ከትምህርት ቤት እገዳ ወደ ሦስት ሊቀነስ ይችላል። ፕሮግራሙን ጀምሮ የማጠናቀቅ ኃላፊነት የተማሪው/ዋ እና የወላጆቹ/ቿ/የአሳዳጊዎቹ/ቿ ነው። ከድስትሪክት ፕሮግራሙ ጋር የተያያዙ ማንኛቸውም ወጪዎች/ክፊያዎች የተማሪው/ዋ እና የወላጆቹ/ቿ/የአሳዳጊዎቹ/ቿ ብቻ ኃላፊነት ይሆናል። የተማሪው/ዋ የድስትሪክቱን የእጽ እና የአልኮል መጠጥ ትምህርት/ጣልቃ መግባት ፕሮግራምን ተከታትሎ/ላ ማጠናቀቅን የሚገልጽ የትምህርት መረጃ በድስትሪክቱ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ መቅረብ አለበት። ይህንን መረጃ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ አለማቅረብ የተሰጠውን ሙሉ የአስር (10) የትምህርት ቀናት ከትምህርት ቤት እገዳ መጽደቅን ያስገድዳል።

2. ተማሪው/ዋ እና ወላጆቹ/ቿ ወይም አሳዳጊዎቹ/ቿ የድስትሪክት ፕሮግራሙን ትተው ሌላ የአልኮል መጠጥ ወይም የእጽ ትምህርት/ጣልቃ መግባት ፕሮግራምን መምረጥ ይችላሉ። ይህ አማራጭ ፕሮግራም ይዘቱ እና ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ ከድስትሪክት ፕሮግራሙ ጋር እኩል መሆን አለበት፣ እንደዚሁም ተማሪው/ዋ፣ ወላጆቹ/ቿ ወይም አሳዳጊዎቹ/ቿ እና የትምህርት ቤቱ አስተዳደር በአማራጭ ፕሮግራሙ መስማማት አለባቸው። ከአማራጭ ፕሮግራሙ ጋር የሚያያዝ ማንኛውም ወጪ/ክፊያ ኃላፊነት የተማሪው/ዋ እና የወላጁ/ጂ ወይም የአሳዳጊው/ዋ ብቻ ይሆናል። የተማሪው/ዋ አማራጩን የእጽ እና የአልኮል መጠጥ ትምህርት/ጣልቃ መግባት ፕሮግራም ተከታትሎ/ላ ማጠናቀቅን የሚገልጽ የትምህርት መረጃ በድስትሪክቱ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ መቅረብ አለበት። ይህንን መረጃ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ አለማቅረብ የተሰጠውን ሙሉ የአስር(10) የትምህርት ቀናት ከትምህርት ቤት እገዳ መጽደቅን ያስገድዳል።

ለ. ተማሪው/ዋ ወደ ትምህርት ቤቱ ከመመለሱ/ሷ በፊት ከወላጅ ጋር ውይይት ይካሄዳል። ተማሪው/ዋ አግባብ ባለው የትምህርት/የጣልቃ መግባት ፕሮግራም ለመሳተፍ ፈቃደኛ ከሆነ/ች፣ ተማሪው/ዋ ከተሰጠው አስር (10) የትምህርት ቀናት እገዳ ውስጥ ከሦስተኛ ቀን በኋላ ቀደም ብሎ ወደ ትምህርት ቤት የመመለስ ውይይት ሊካሄድ ይችላል። በዚያን ጊዜ ተማሪው/ዋ በፕሮግራሙ መመዝገቡ/ቧን እና ትምህርቱን/ስልጠናውን

መከታተሉ/ሏን የሚገልጽ ማስረጃ/ሰነድ ማቅረብ አለበት/አለባት። በዚህ ጊዜ የሚቀርበው የስልጠናው ማስረጃ/ሰነድ ተማሪው/ዋ ቀደም ብሎ/ላ እንዲመዘገብ/እንዲትመዘገብ እና የቀረው ሰባት (7) የትምህርት ቀናት እገዳ ከተማሪው/ዋ ፋይል/መዝገብ ውስጥ እንዲነሳ ያስችላል። በተጨማሪም፣ በውይይቱ ጊዜ፣ የትምህርት ቤቱ ኃላፊ ከተማሪው/ዋ እና ከወላጁ/ጇ ጋር በመሆን የወላጅ፣ የተማሪ እና የትምህርት ቤት ኃላፊነትን ይነድፋሉ። ይህ ንድፍ ተመሳሳይ የወንጀል ድርጊቶችን ለመከልከል ሲሆን፣ በእነዚህ ብቻ ባይወሰኑም፣ የተማሪው/ዋ ከትምህርት ቤት እገዳ የትምህርት ቀናት እንዲቀነሱለት/እንዲቀነሱላት የሚያስፈልጉ መስፈርቶች እና ተማሪው/ዋ በተሰጠ የጊዜ ገደብ ውስጥ የጣልቃ መግባት ትምህርቱን/ስልጠናውን ካላጠናቀቀ/ች፣ ተጨማሪው ሰባት (7) የትምህርት ቀናት ከትምህርት ቤት እገዳ ተመልሶ እንደሚጸድቅ የሚገልጽ ነው። ወደ ትምህርት ቤት መመለስን በተመለከተ በሚደረገው የውይይት ጊዜ፣ የትምህርት ቤቱ ኃላፊ ወይም ተወካይ ከጣልቃ መግባት ትምህርት/ስልጠና ፕሮግራሙ የተማሪው/ዋን የትምህርት/የስልጠና ክትትል እና የስልጠናውን ማጠናቀቅ ሁኔታ አስመልክቶ አስፈላጊውን መረጃ ማግኘት እንዲቻል፣ የተማሪው/ዋን ወላጅ መረጃው እንዲሰጥ ፈቃደኝነታቸውን በጽሁፍ እንዲያሳውቁ ሊጠየቁ ይችላሉ። በተጨማሪም፣ ይህ የጽሁፍ ስምምነት የሁለተኛ ጊዜ የወንጀል ድርጊት የሚያስከትለውን ውጤት በግልጽ ያስቀምጣል።

ሐ. ድስትሪክቱ ለተማሪው/ዋ እና ለወላጆቹ/ቿ ወይም ለአሳዳጊዎቹ/ቿ የአልኮል መጠጥ እና/ወይም የእጽ ጣልቃ መግባት፣ ምክር እና/ወይም የእዳታ/የድጋፍ/የህክምና አማራጮችን ዝርዝር የያዙ መረጃ ሰጪ መጽሃፍትን ይሰጣቸዋል። ትምህርት ቤቱ ወይም ድስትሪክቱ የአገልግሎት ሰጪ ዝርዝሮችን መስጠት ማለት እነዚህን የአገልግሎት ሰጪዎችን ሁኔታ፣ ዝግጅት፣ ስልጠና ወይም የሚሰጡትን አገልግሎቶችን ይደግፋል ወይም ስለሚሰጡ አገልግሎቶች ዋስትና ይወስዳል ማለት አይደለም። ትምህርት ቤቱም ሆነ የቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት በተማሪው/ዋ እና በእርዳታ/ድጋፍ/ህክምና አገልግሎት ሰጪ መሃል ለተደረገው ስምምነት ተጠያቂ አይደሉም/ኃላፊነት አይወስዱም።

**የሁለተኛ ጊዜ ጥፋት**

ሀ. ለአሳሳቢ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ጥሰት ለአምስት (5) የትምህርት ቀናት፣ ጊዜው እንዲራዘም የትምህርት ቤቱ ኃላፊ ለትምህርት ቤቶች አለቃ በሚያቀርበው ጥያቄ መሰረት ለተጨማሪ አምስት (5) የትምህርት ቀናት፣ በአጠቃላይ ለአስር (10) የትምህርት ቀናት ተማሪው/ዋ ከትምህርት ቤት እንዲታገድ/እንዲትታገድ ይደረጋል/ትደረጋለች።

1. ከመጀመሪያዎቹ አምስት (5) የትምህርት ቀናት እገዳ በኃላ፣ ተማሪው/ዋ እና ወላጆቹ/ቿ ወይም አሳዳጊዎቹ/ቿ የቼሪ ክሪክ ድስትሪክት የግል የእጽ እና የአልኮል መጠጥ የማጣሪያ ግምገማ ለተማሪው/ዋ እንዲደረግ ከተስማሙ እና የተፈለገውን የህክምና/የእርዳታ/የድጋፍ እቅድ ንድፍ እና በአልኮል መጠጥ እና በእጽ የጣልቃ መግባት ትምህርት/ስልጠና ፕሮግራም ለመመዝገብ ማቀዱ/ዷን የሚገልጽ መረጃ ካቀረበ/ች፣ የአስር (10) የትምህርት ቀናት ከትምህርት ቤት እገዳ ወደ አምስት (5) ተቀንሶ፣ ከትምህርት ቤት እገዳውም ሊቀር ይችላል። ፕሮግራሙን ጀምሮ የማጠናቀቅ እና በህክምና/በእርዳታ/በድጋፍ ፕሮግራሙ የመሳተፍ ኃላፊነት የተማሪው/ዋ እናየወላጆቹ/ቿ/የአሳዳጊዎቹ/ቿ ብቻ ነው። ከህክምና/ከእርዳታ እቅዱ ጋር ወይም ከህክምና/ከእርዳታ ፕሮግራሙ ጋር የተያያዙ ማንኛቸውም ወጪዎች/ክፊያዎች ኃላፊነት የተማሪው/ዋ እና የወላጆቹ/ቿ/የአሳዳጊዎቹ/ቿ ብቻ ይሆናል።

2. ድስትሪክቱ ለተማሪው/ዋ እና ለወላጆቹ/ቿ ወይም ለአሳዳጊዎቹ/ቿ የአልኮል መጠጥ እና/ወይም የእጽ ጣልቃ መግባት፣ ምክር እና/ወይም የእዳታ/የድጋፍ/የህክምና አማራጮችን ዝርዝር የያዙ መረጃ ሰጪ መጽሃፍትን ይሰጣቸዋል። ትምህርት ቤቱ ወይም ድስትሪክቱ የአገልግሎት ሰጪ ዝርዝሮችን መስጠት ማለት እነዚህን የአገልግሎት ሰጪዎችን ሁኔታ፣ ዝግጅት፣ ስልጠና ወይም የሚሰጡትን አገልግሎቶችን ይደግፋል ወይም ስለሚሰጡ አገልግሎቶች ዋስትና ይወስዳል ማለት አይደለም። ትምህርት ቤቱም ሆነ የቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት በተማሪው/ዋ እና በእርዳታ/ድጋፍ/ህክምና አገልግሎት ሰጪ መሃል ለተደረገው ስምምነት ተጠያቂ አይደሉም/ኃላፊነት አይወስዱም።

ለ. ተማሪው/ዋ ቀደም ብሎ ወደ ትምህርት ቤት የመመለስ ሂደት ውስጥ ለመሳተፍ ቢመርጥም ባይመርጥም፣ ተማሪው/ዋ ወደ ትምህርት ቤት ከመመለሱ/ሷ በፊት የወላጅ-መምህር ህብረት ስብሰባ ይካሄዳል። ተማሪው/ዋ ቶሎ ወደ ትምህርት ቤት የመመለስ እና ከትምህርት ቤት እገዳውን የማስቀረት ሂደት ውስጥ ለመሳተፍ ከመረጠ/ች፣ ከመጀመሪያዎቹ አምስት (5) የትምህርት ቀናት እገዳ በኃላ፣ ቶሎ ወደ ትምህርት ቤት የመመለስ ውይይት ያደርጋል/ታደርጋለች። ቶሎ ወደ ትምህርት ቤት የመመለስ ውይይት ጊዜ፣ ተማሪው/ዋ የግል የአልኮል መጠጥ እና የእጽ ማጣሪያ ግምገማ ማጠናቀቁ/ቋን እና የአልኮል መጠጥ እና የእጽ ህክምና/ድጋፍ/እርዳታ ፕሮግራም እንደሚሳተፍ/እንደሚትሳተፍ የሚገልጽ መረጃ እና የታዘዘውን የህክምና/የእርዳታ እቅድ ንድፍ ተማሪው/ዋ እና ወላጆቹ/ቿ ወይም አሳዳጊዎቹ/ቿ ማቅረብ አለባቸው። ከማጣሪያ ግምገማው፣ ከህክምና/ከእርዳታ/ከድጋፍ እቅዱ ወይም ከፕሮግራሙ ጋር የሚያያዝ ማንኛውም ወጪ/ክፊያ ኃላፊነት የተማሪው/ዋ እና የወላጆቹ/ቿ ወይም የአሳዳጊዎቹ/ቿ ብቻ ነው። በውይይቱ ጊዜ የተማሪው/ዋ ይህንን መረጃ ማቅረብ ወደ ትምህርት ቤት መመለስን ያስችላል፤ ቀሪውን አምስት (5) የትምህርት ቀናት እገዳው እና ወደ አማራጭ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት የመላክ ትዕዛዝንም ያስቀራል። ተማሪው/ዋ ቶሎ ወደ ትምህርት ቤት የመመለስ ሂደትን ካልመረጠ/ች፣ ይህንን ፖሊሲ እና መተዳደሪያ ደንቦችን ለመከለስ እና ወደፊት የሚከሰቱት የህገ-ወጥ ተግባራት ውጤቶችን ለተማሪው/ዋ ለማሳወቅ የከትምህርት ቤት እገዳው/ዋን ከጨረሰ/ች በኃላ፣ ተማሪው/ዋ ወደ ትምህርት ቤት ሲመለስ/ሲትመለስ ውይይትይኖረዋል/ይኖራታል።

ሐ. ከትምህርት ቤት ኃላፊ፣ ከተማሪው/ዋ እና ከወላጅ ጋር የጽሁፍ ስምምነት ይደረጋል። ተማሪው/ዋ ቶሎ ወደ ትምህርት ቤት የመመለስ ሂደት ውስጥ መሳተፊን ከመረጠ/ች፣ ቀሪውን ለአምስት (5) የትምህርት ቀናት ከትምህርት ቤት እገዳ ለመቀነስ እና ወደ አማራጭ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት እንዲላክ/እንዲትላክ የቀረበው ሀሳብ እንዲቀር መስማማቱ/ቷን በፍርማ ያረጋግጣል/ታረጋግጣለች። ተማሪው/ዋ የታቀደውን

የአልኮል መጠጥ እና የእጽ ህክምና/እርዳታ ፕሮግራሙን ካላጠናቀቀ/ች፣ ቀሪውን ለአምስት (5) የትምህርት ቀናት ከትምህርት ቤት እገዳ ለመቀነስ እና ወደ አማራጭ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት እንዲላክ/እንዲትላክ የቀረበው ሀሳብ እንዲቀር የተደረገው ስምምነት እንደሚፈርስ እና ውሳኔው እንደሚጸድቅ በስምምነቱ ውስጥ መካተት አለበት። የትምህርት ቤቱ ኃላፊ ወይም ተወካይ ከጣልቃ መግባት ትምህርት/ስልጠና ፕሮግራሙ የተማሪው/ዋን የትምህርት/የስልጠና ክትትል እና የስልጠናውን ማጠናቀቅ ሁኔታ አስመልክቶ አስፈላጊውን መረጃ ማግኘት እንዲቻል፣ የተማሪው/ዋን ወላጅ መረጃው እንዲሰጥ ፈቃደኝነታቸውን በጽሁፍ እንዲያሳውቁ ሊጠየቁ ይችላሉ።

መ. ሁኔታዎች ሲፈቅዱ፣ ለድስትሪክት ውስጥ-ለውስጥ ዝውውር ልዩ ትኩረት ይሰጣል። እንደዚሁም ሌሎች የትምህርት አማራጮች ይወሰዳሉ። ለድስትሪክት ውስጥ-ለውስጥ ዝውውር የሚመለከታቸው የሁለቱ ትምህርት ቤቶች አስተዳደሮች የጋራ ስምምነት ያስፈልጋል። ለአዲሱ ትምህርት ቤት የሚያስፈልግ ማጓጓዣ የተማሪው/ዋ እና የወላጆቹ/ቿ ኃላፊነት ይሆናል።

**ሦስተኛና ቀጣይ የጥፋት ድርጊቶች**

ሀ. ወደ አማራጭ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት መላክ ሁኔታ እስክ ከለስ ድረስ፣ በትምህርት ቦርድ መተዳደሪያ ደንብ 'JKD-1-R' ውስጥ በተነደፈው መሰረት ተማሪው/ዋ ከትምህርት ቤት ለጊዜው ይታገዳል/ትታገዳለች።

ሊ. ከትምህርት ቤት እንዲታገዱ የሚቀርበው ጥያቄ ሂደቶች በትምህርት ቦርድ መተዳደሪያ ደንብ 'JKD-1-R' ውስጥ ተነድፈዋል።

ሐ. **ክልክል የሆኑ ነገሮችን ማከፋፈል፣ መሸጥ፣ ሌላ ሰው መስጠት ወይም መቀያየር**

ማንኛውንም ክልክል የሆነ ነገር ወይም ፓራፈርናሊያ የሚባል እጽን በትምህርት ድስትሪክቱ ሕጋዊ ክልል ውስጥ ሲያከፋፍል/ሲታከፋፍል፣ ሲሸጥ/ሲትሸጥ፣ ለሌላ ሰው ሲሰጥ/ሲትሰጥ ወይም ከሌላ ጋር ሲቀያይር/ሲትቀያይር የተገኘ/ች ተማሪ ላይ የሚከተሉት የሥርዓት እርምጃ ሂደቶች ይወሰዱበታል/ይወሰዱባታል፡

1. ተማሪው/ዋ ክልክል የሆኑ ነገሮችን ወይም ፓራፈርናሊያ የሚባልን እጽ የማሰራጨት፣ የማደል፣ የመሸጥ፣ ለሌላ የመስጠት፣ ወይም ከሌላ ጋር የመቀያየር ተግባራት ላይ ሲሳተፍ/ሲትሳተፍ አይቶ/ታ የትምህርት ቤቱ የሥራ ባልደረባ ከመሰከረ/ች፣ ወይም በምርመራ ውጤቱ ከተወሰነ፣ የሥራ ባልደረባው/ዋ ወይም መርማሪው/ዋ በአስቸኳይ ተማሪው/ዋን ይዞ/ዛ (ቁጥጥር ሥር አድርጎ/ጋ) ተማሪው/ዋ አብሮት/አብሯት ወደ የትምህርት ቤቱ ኃላፊ ወይም ተወካይ ቢሮ እንዲሄድ/እንዲትሄድ ይጠይቃል/ትጠይቃለች። ተማሪው/ዋ እምቢ ካለ/ች፣ የሥራ ባልደረባው/ዋ ወይም መርማሪው/ዋ ጉዳዩን በአስቸኳይ ለትምህርት ቤቱ ኃላፊ ያሳውቃል/ታሳውቃለች። ይህ ከሆነ፣ ኃላፊው/ዋን ወይም ተወካይን እስኪያገኝ/እስኪታገኝ ድረስ፣ የሥራ ባልደረባው/ዋ ወይም መርማሪው/ዋ በተቻለ መጠን ከተማሪው/ዋ ጋር መሆን አለበት/አለባት።

2. የትምህርት ቤቱ ኃላፊ ወይም ተወካይ ቀጥታ ተማሪው/ዋን በመጠየቅ ወይም በዚህ ትምህርት ቦርድ መተዳደሪያ ደንብ (ምርመራዎች) በሆነው በ V ክፍል ውስጥ በተነደፈው የምርመራ ሂደቶች አማካይነት የትምህርት ቤት ኃላፊ ወይም ተወካይ መረጃን ለማግኘት ጥረት ያደርጋል/ታደርጋለች።

3. ተማሪው/ዋ በጊዜው ክልክል የሆኑ ነገሮችን ወይም ፓራፈርናሊያ የሚባል እጽን ይዞ/ዛ ከተገኘ/ች፣ የትምህርት ቤት ኃላፊ ወይም ተወካይ ማስረጃውን በፖስታ ውስጥ ያደርጋሉ።

4. የትምህርት ቤት ኃላፊ ወይም ተወካይ አግባብ ላለው የሕግ አስከባሪ ድርጅት/ተቋም በመደወል ፖሊስ ወይም አግባብ ያለው ሰው መጥቶ የታሸገውን ፖስታ ለምርመራ እንዲወስድ ይጠይቃል/ትጠይቃለች።

5. ተማሪው/ዋ ለአምስት (5) የትምህርት ቀናት ከትምህርት ቤት እንዲታገድ/እንዲትታገድ ይደረግና ከትምህርት ቤትም ሊባረርም/ሊትባረርም ይችላል/ትችላለች፤ ነገር ግን፣ Revised Statute 22-33-106(1)(D) የሚባለው የተሻሻለው የኮሎራዶ ሕግ እጽን ወይም ሌላ ክልክል የሆነ ነገርን የሚሸጥ/የሚትሸጥ ተማሪ የሚባረረው/የሚትባረረው በ Section 12-9-303 C.R.S. በሚባለው ክፍል ውስጥ በተወሰነው ሕገ ደንብ መሰረት እንዲሆን ያዛል።

6. የእገዳ ጊዜው ካለቀ በኃላ፣ ተማሪው/ዋ ወደ ትምህርት ቤት ከመመለሱ/ሷ በፊት ከትምህርት ቤት ኃላፊ ወይም ተወካይ እና ከወላጅ እና ከተማሪ ጋር ውይይት ይካሄዳል።

V. **ፍተሻዎች**

ፍተሻዎች 'JIH' በሚባለው በትምህርት ቦርድ ፖሊሲ መሰረት መካሄድ አለባቸው፡ ለተማሪ ቃለ መጠይቅ ማድረግ፣ መፈተሽ እና ማሰር።

VI. **የመቆጣጠር ኃላፊነት**

በህግ ከተቀመጠው ሌላ፣ የከዚህ በፊቱ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ ያለው ማንኛውም ነገር ሳይጸድቅ የትምህርት ድስትሪክት ተማሪዎችን ወይም በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚደረገውን ተግባር የመቆጣጠር የሥራ ድርሻ እንደሚያሰፋ ተደርጎ መወሰድ የለበትም።

በትምህርት ቤቶች የበላይ አለቃ ሞንተ ሙሴ (Monte C. Moses) ግንቦት 14፣ 2007 ጸደቀ።
የተሻሻለው፤ ኦገስት 13፣ 2012

## የተማሪዎች ትምባሆን ማጤስ የሚመለከት (JICHA)

የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት ለግለሰብ እና ለህዝብ ጤንነት እና ደህንነት መጠበቅ ከፍተኛውን ደረጃ ጥንቃቄ ያደርጋል።አጠቃላይ ጤንነትን ለማሻሻል፣ ለተማሪዎች እና ለሰራተኞች ሰላም እና ደህንነት ሲባል ትምባሆን ማጨስ፣ ማኘክ፣ መቃም፣ ወይም በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ፣ ወይም በትምህርት ቤት ህጋዊ ቅጥር እና በትምህርት ሰዓት፣ ወይም ትምህርት ቤት በሚያዘጋጃቸው ዝግጅቶች ቦታ እና አከባቢ በማንኛውም መልኩ የትምባሆ ምርቶችን መጠቀም ክልክል ነው።

ለዚህ መመሪያ ዓላማ ሲባል የሚከተሉት ትርጉሞች ሥራ ላይ ይውላሉ፡

1. “የትምህርት ቤት ንብረት” የትምህርት ቤት ይዞታ የሆኑ፣ ትምህርት ቤት የሚከራያቸው ወይም የሚጠቀምባቸው ንብረቶች ሁሉ ማለት ነው። እነዚህም የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፣ በነዚህ ብቻ ግን አይወሰኑም፡

   ሀ) ለመሰረተ ልማት፣ ለአስተዳደር፣ ለድጋፍ ሰጪ አገልግሎቶች፣ ለጥገና ወይም ለዕቃ ማከማቻ የሚያገለግሉ የማንኛውም ሕንጻ ውስጠኛው ክፍል እና ሌሎች ሕንጻዎች።

   ለ) የትምህርት ቤት ሕንጻ አከባቢ፤ የመጫወቻ ቦታዎች፤ የሩጫ፣ የውርወራ እና የዝላይ ሜዳዎች (አትሌትክስ)፤ የመዝናኛ ሥፍራዎች እና የመኪና ማቆሚያ ሥፍራዎች የሆኑ ትምህርት ቤት የሚቆጣጠራቸው የትምህርት ቤት መሬት(ቦታዎች)።

   ሐ) ድስትሪክቱ ተማሪዎችን፣ ሰራተኞችን፣ ጎብኚዎችን ወይም ሌሎች ሰዎችን የሚያጓጓዝበት ተሽከርካሪዎች በሙሉ።

2. “ትንባሆ” ስጋራዎችን፣ ፒፖዎችን፣ የሚታኙኩ የትንባዎ ምርቶች እና ለማኘክ፣ ለማጨስ ወይም ለሁለቱም እንዲያመቹ ተደርገው የተዘጋጁ ሌሎች የትንባሆ ዓይነቶችን በሙሉ ያጠቃልላል። “ትንባሆ” ለማጨስ ታሽጎ የተዘጋጀ ማንኛውንም ምርት ያጠቃልላል።

3. “መጠቀም” ማለት ማንኛውንም የትንባሆ ምርት ማቀጣጠል፣ ማኘክ (መቃም)፣ መሳብ ወይም ማጨስ ማለት ነው።

ይህንን ፖሊሲ (ሕግ) በሚጥሱ ተማሪዎች ላይ የቅጣት እርምጃ ይወሰዳል። በክፍለ ግዛት ሕግ መሰረት፣ ለትንባሆ መጠቀም ብቻ ተማሪ ከትምህርት ቤት አይታገድም።

ሥራ ላይ የዋለው፡ ጁን 11፣ 2001

| | |
|---|---|
| ሕጋዊ ዋቢዎች፡ | 20 U.S.C. Section(ክፍል) 6083 (ለልጆች የትምህርት አገልግሎቶች በሚሰጥበት ክፍል/ሕንጻ/ቦታ ውስጥ ስጋራን ማጨስ የፌዴራል ሕግ ይከለክላል)<br>C.R.S. 18-13-121<br>C.R.S. 22-32-109(1)(bb)<br>C.R.S. 25-14-103.5<br>6 CCR 1010-6, Rule 5-306 |
| ጥምር ዋቢዎች፡ | ADC፣ ከእጽ እና ከትንባሆ ነጻ የሆኑ ትምህርት ቤቶች<br>IHAMA፣ ስለ እጾች፣ የአልኮል መጠጥ እና ትንባሆ ማስተማር<br>JKD/JKE፣ ተማሪዎችን ከትምህርት ቤት ማገድ፣ ማስወጣት |

## በትምህርት ቤቶች ውስጥ የጦር ትጥቅ (መሳሪያ) መያዝ (JICI)

በድስትሪክቱ ውስጥ የተማሪዎች የጦር ትጥቅ (መሳሪያ) መያዝ ለተማሪዎች እና ለትምህርት ቤት ሰራተኞች ሰላም እና ደኅንነት አስጊ እንደሆነ የትምህርት ቦርድ ይወስናል። በድስትርከቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ የጦር ትጥቆችን አደገኛ (መሳሪያዎችን)፤የጦሪ መሳሪያ ይዞ መገኘት ማለት ተማሪው/ዋ የጦር ትጥቅ (መሳሪያ) በገሃድ ታጥቆ መገኘት ወይም በመኪናው/ዋ ወይም በዕቃ ማስቀመጫው/ዋ ሳጥን፣ ሻንጣ(ቦርሳ)፣ ወይም ሌላ ቦታ ሆኖ በተማሪው/ዋ ቁጥጥር ሥር የሆነ ወይም ተማሪው/ዋ የሚጠቀምበት/የሚትጠቀምባት ነገር ወይም ሥፍራ ውስጥ ማስቀመጥ ማለት ነው።

ይህንን መመሪያ JICI በመጣስ መሳሪያ፣ አደገኛ መሳሪያ እና/ወይም የጦር መሳሪያ የያዙ፣ ያመጡ፣ የተጠቀሙ ወይም የያዙ ተማሪዎች የተማሪን እገዳ፣ መባረር እና ሌሎች የዲሲፕሊን ጣልቃገብነቶችን በሚመለከት በቦርድ ፖሊሲ መሰረት የዲሲፕሊን እርምጃ ሊወሰድባቸው ይችላል።

የዲስትሪክቱ አስተዳዳሪዎች መታገድ፣ መባረር ወይም ማናቸውንም ሌላ የዲሲፕሊን እርምጃ ለመወሰን ከግለሰባዊ እውነታዎች እና ሁኔታዎች በመነሳት ይህን የፖሊሲ ድንጋጌ መጣስ በየሁኔታው ማጤን አለባቸው።

I. ***የጦር መሣሪያ ፍቺ***

በዚህ ፖሊሲ ውስጥ ፤ "መሳሪያ" ማለት በአጠቃላይ ለአመጽ ወይም አደገኛ ላልሆኑ ዓላማዎች የሚያገለግል ነገር ግን በዚህ ፖሊሲ መሠረት በአጠቃቀሙ፣ ሊጠቀምበት በሚችልበት ወይም በታሰበው ወይም በተሰነዘረበት አጠቃቀሙ ምክንያት እንደ መሳሪያ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ነገር ነው። . . . . ለምሳሌ፣ የቤዝቦል መምቻ ዱላ በተለምዶ እንደ መሣሪያ አይቆጠርም። ነገር ግን በጥል ወቅት የሌላ ሰውን ጭንቅላት ለመምታት ጥቅም ላይ ሲውል ወይም ዛቻ ሲሰነዘርበት በዚህ ፖሊሲ መሰረት እንደ መሳሪያ ይቆጠራል። በተጠቀሱት ሁኔታዎች ውስጥ የጦር መሣሪያ ሊሆኑ ከሚችሉ ነገሮች መካከል በአስጊ ወይም ተገቢ ያልሆነ መንገድ ጥቅም ላይ የሚዉሉ በምሳሌነት የሚታጠቁ ጠመንጃዎች፣ ቋጥኞች፣ ጠርሙሶች እና ጣሳዎች፣ ሰንሰለት፣ ጫማዎች፣ በተለይም የወታደር ቦት ጫማዎች፣ የቤዝቦል መምቻ ዱላ ፣ ገመዶች፣ መዶሻ ወይም ተመሳሳይ ጎጂ ኬሚካላዊ ንጥረ ነገሮችን ያካትታሉ።

**II, አደገኛ መሳሪያዎች**

የትምህርት ድስትሪክቱን ሳያስፈቅዱ በማንኛውም የትምህርት ቤት ሕንጻ፣ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ፣ በማንኛውም የትምህርት ቤት ተሽከርካሪ ውስጥ ወይም በማንኛውም በትምህርት ቤት በሚዘጋጁ ተግባራት ወይም ዝግጅቶች ሥነ ምግባሩ ከማንኛውም የዲስትሪክት ዲስትሪክት ሥርዓተ ትምህርት ወይም ከሥርዓተ-ትምህርት-ያልሆኑ ክስተቶች ጋር ምክንያታዊ ግንኙነት ሲኖረው ላይ አደገኛ የሆኑ መሳሪያዎችን መያዝ (መሸከም)፣ ማምጣት፣ መጠቀም ወይም እንደ ክልክል ነው። ይህ ጉዳይ በተፈቀደ ተጓዳኝ ትምህርት የሚሳተፉ ተማሪዎችን ወይም የጠመንጃ (መሳሪያ) አጠቃቀም ላይ የሚሳተፉ ቡድኖችን አይመለከትም።

ተማሪ አደገኛ መሳሪያ መያዙን ካወቀ/ች እና ወዲያው ጉዳዩን ለአስተማሪ፣ ለአስተዳደር ወይም በዲስትሪክቱ ውስጥ ለሌላ ሕጋዊ ለሆነ ሰው ካሳወቀ/ች፣ እና በአስቸኳይ መሳሪያውን ለዚያ ሰው ካሰረከበ/ች፣ ከትምህርት ቤት መታገድ የግዴታ አይሆንም፣ በተጨማሪም ምናልባት አግባብ ያለው የቅጣት እርምጃ ከተወሰደ እንደዚህ ያለ ተግባር ከግምት ውስጥ ይገባል።

በዚህ ፖሊሲ ውስጥ እንደተወሰደው የሚከተሉት በግምታዊ "አደገኛ መሳሪያ ናቸው

ሀ. ጠመንጃ (ጥይት ያለው ወይም ባዶ ሊሆን ይችላል)፣ C.R.S. § 18-1-901(3)(h).ውስጥ እንደተገለጸው

ለ. ማንኛውም የሚተኮስ፣ BB የሚባል ጠመንጃ ወይም ሌላ ለመተኮስ ወይም ለማፈንዳት ዓላማ የተዘጋጀ መሳሪያ (የሚሰራ ወይም የማይሰራ ሊሆን ይችላል)። ወይም የእሳት ነበልባሎች፣ ጥጥ ወይንም ወረቀት የምተፋ እና/ወይም ጭስ የሚያወጣ ጠመንጃ።

ሐ. ማንኛውም ዓይነት የተበጀ እና ከሦስት እንች በላይ የሚረዝም ስለታም ቢላ (ሰንጢ ወይም ጩቤ) ወይም የሚተጣጠፍ እና የሚዘረጋጋ ስለታም ቢላ(ሰንጢ ወይም ጩቤ) ወይም ከሦስት እንች እና ተኩል በላይ የሚረዝም ኪስ ውስጥ የሚያዝ ስለታም ሰንጢ ወይም ጩቤ።

መ. ሌላ ፤ወንጭፍ፣ ቀስት፣ በማርሻል አርት ከጎማ የምሰራ ዱላ ቦንብ፣ የኮከብ ቅርጽ ያለውና የሚወረወር ስሌታማ ብረት፣ዱላ/በትር፣ የብረት ቦክስና የመሳሰሉት ሰውን ለመጉዳት ወይም ለመግደል የተዘጋጁ ማንኛውም ዓይነት መሳሪያዎች ወይም ቁሳቁሶች።

በፌዴራል ሕግ መሰረት፣ ይህንን ፖሊሲ ወይም ሕገ ደንብ በሚንጻረር መልኩ ጠመንጃን ወይም አደገኛ መሳሪያን ይዘው በድስትርከቱ ቅጥር ግቢ በሚመጡት ተማሪዎች ላይ ከአንድ ዓመት የትምህርት ዘመን ላላነሰ ጊዜ ከትምህርት ቤት እገዳ ይደረግባቸዋል። ሱፐርንተንደንቱ የዚህን የፌዴራል መስፈርት ርዝማኔ በየሁኔታው ሊያስተካክለው ይችላል። ማንኛውም ዓይነት ማሻሻያ በጽሑፍ መሆን አለበት.

**የጦር መሳሪያ የሚመስሉ ቁሳቁሶች**

በተጨማሪም፣ የትምህርት ድስትሪክቱን ሳያስፈቅዱ በማንኛውም በድስትሪክት ንብረት አካባቢ፣ በድስትሪክቱ በሚሰማሩት ተሽከርካሪዎች ሲጓዙ፣ ወይም በድስትሪክት በሚዘጋጁ ዝግጅቶች ጊዜና ከትምህርት ቤት ንብረትና ቅጥር ግቢ ውጪ ሆኖ የሚታየው ምግባር ከትምህርት ቤት ጋር ወይም ከማንኛውም የድስትሪክት ሥርዓተ-ትምህርት ወይም ተጓዳኝ ትምህርት ዝግጅት ጋር ግንኙነት ሲኖረው፣ አሳሳችና ከእውነተኛው ጠመንጃ ጋር የሚመሳሰል ጠመንጃ ይዞ መገኘት፣ ለሌሎች ማሳየት ወይም ሰውን ማስፈራራት ክልክል ነው። ይህንን ፖሊሲ በሚጥሱ ተማሪዎች ላይ ከትምህርት ቤት መታገድና/ ወይም ወደ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት መላክን ጨምሮ የቅጣት እርምጃዎች ይወሰድባቸዋል።
ተማሪ ለትምህርተ-ነክ ወይም ትምህርተ-ነክ ላልሆኑ ተግባራት ዓላማ ጠመንጃ መሳይ መሳሪያን ይዞ ለመገኘት፣ ትምህርት ቤት ለማምጣት፣ ለመጠቀም ወይም ለመያዝ ከትምህርት ቤት ኃላፊ አስቀድሞ ፈቃድ ማግኘት አለበት/አለባት። ይህንን አለማድረግ የፖሊሲ መጣስ ስለሚሆን በተማሪው/ዋ ላይ ከትምህርት ቤት መታገድና/ ወይም ወደ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት መላክን ጨምሮ የቅጣት እርምጃዎች ይወሰድባቸዋል። ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ለተማሪው/ዋ ፈቃድ መስጠት ወይም አለመስጠት የኃላፊው ውሳኔ የመጨረሻ ውሳኔ ነው።

**ከጎጂ ቢላዋ/ጩቤ ጋር በተያያዘ ምክንያት የግዴታ ያልሆነ ከትምህርት ቤት መታገድ ጋር የተያያዙ ሌሎች ቁጥጥሮች**
ለተማሪዎች ደኅንነት ከፍተኛ ጥንቃቄዎችን ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ የትምህርት ቦርድ ወስኗል በተለይም የክሌር ዴቪስ ትምህርት ቤት ደህንነት ህግ ግዴታዎችን ግምት ኡስጥ በማስጋባት ።ስለዚህ፣ በማንኛውም የትምህርት ቤት ሕንጻ ውስጥ፣ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ፣ በማንኛውም የትምህርት ቤት ተሽከርካሪ ውስጥ ወይም በትምህርት ቤት በሚዘጋጁ በማንኛውም ዝግጅቶች ላይ ያለ ሕጋዊ ፈቃድ ምንም ዓይነት ርዝመት ያለውን ቢላ/ጩቤ/ሰንጢ መሸከም፣ ማምታት፣ መጠቀም ወይም ይዞ መገኘት ለተማሪው/ዋ፣ ለሌሎች ተማሪዎች እና ለትምህርት ቤት አስተዳደሮች ሰላም እና ደኅንነት አስጊ የሆነ ምግባር ስለሆነ እንደዚህ ዓይነቱ ድርጊት ክልክል ነው። ይህንን ፖሊሲ (ሕገ ደንብ) የሚጥሱ ተማሪዎች ክስተት ጉዳይ አግባብ ላለው የቅጣት እርምጃ ይመራል።

***መረጃ መያዝ***
የጦር መሳሪያዎችን ትምህርት ቤት ይዞ በመምጣት ክስተቶች ምክንያት ከትምህርት ቤት የታገዱትን ተማሪዎች ሰነዶችን የትምህርት ድስትሪክት ይይዛል። ሰነዶቹም የትምህርት ቤት ስም፣ ከትምህርት ቤት የታገዱንትን የተማሪዎች ብዛት እና በሕግ እንደሚፈለገው የመሳሪያዎቹን ዓይነት ያጠቃልላሉ።

***ጉዳዩን ወደ ህግ ማስተላለፍ***
በህግ መሰረት፣ የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ያለትምህርት ቤት ወይም የትምህርት ድስትሪክት ፈቃድ ጎጂ የሆኑትን መሳሪያዎች ወይም ጠመንጃ ይዘው ትምህርት ቤት የሚመጡ ተማሪዎች ጉዳይን ለህግ አስከባሪዎች (ለፖሊስ) ያስተላልፋል።
በመጀመሪያ ሥራ ላይ የዋለው፤ ዴሰምበር 8፣ 2003
የተሻሻለው፤ ኦገስት 13፣ 2012
የአሁኑ ክለሳ፡ ኤፕሪል 10፣2023
ሕጋዊ ዋቢዎች 18 U.S.C. Section 921 (A)(3)(የጠመንጃ (ሽጉጥ) የፌዴራል ፍች/ትርጉም)

20 U.S.C. ክፍል § 715 (ከሽጉጥ ነፃ የትምህርት ቤቶች ህግ)
C.R.S. 22-32-109.1 (2)(a)(I) (G)( ደኅንነታቸው የተጠበቁ የትምህርት ቤቶች እቅድ አካል እና አስፈላጊ የሆነ ፖሊሲ (ሕገ ደንብ))
20 U.S.C. Section 7151(h) (ትምህርት ቤቶች ጉዳዩን ወደ ህግ ማስተላለፍ የሚያስገድድ) C.R.S. § 22-32-109.1 (2)(a)(I)(G)(የደህንነቱ የተጠበቀ ትምህርት ቤት እቅድ አካል ሆኖ የሚፈለግ ፖሊሲ);
C.R.S. 22-32-102 (4)(የአደገኛ መሳሪያዎች ፍች)

## የተማሪዎች የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ቁሳቁሶችን መጠቀም (JICJ)

C.R.S. 22-33-106(1)(ከትምህርት ቤት ለመባረር፣ ለጊዜው ለመታገድ ወይም ምዝገባን ለመከለከል መሰረቶች)
C.R.S. 22-33-106(1)(f)(መሳሪያ ለሚመስሉ ቁሳቁሶች ፖሊሲ መውጣት አለበት)
C.R.S. § 24-10-106.3 (የክሌር ዴቪስ ትምህርት ቤት ደህንነት ህግ);
ሰዎች v. ዩናይትድ ስቴትስ v. Saleh, 45 P.3d 1272 (ኮሎ. 2002);

ጥምር ዋቢዎች፤ JKD፣ ተማሪዎችን ከትምህርት ቤት ማገድ/ማስወጣት
JKD-2፣ የስንኩላን ተማሪዎች ምግባራት
KFA፣ በትምህርት ቤት ንብረት አከባብ የሕዝብ ምግባር

የኤሌክትሮንክስ የመገናኛ ቁሳቁሶች በአደጋ ጊዜም ሆነ በትምህርት ቤት ውስጥ ለትምህርት ጉዳይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳላቸው የትምህርት ቦርድ ይገነዘባል። ይሁን እንጂ እነዚህን የመገናኛ ቁሳቁሶች ለግል ህጋዊ ባልሆነ መልኩ ለግል ጥቅም ማዋል የትምህርት ሀደትን የሚረብሽ ሊሆን ይችላል። ለዚህ ፖሊሲ ዓላማ የኤሌክትሮኒክስ የመገናኛ ቁሳቁሶች የእጅ ስልኮችን፣ የመነጋገሪያ ራድዮዎችን/ቁሳቁሶችንና ሌሎች ድምጽ ወይም ምልክት የሚሰጡና ለሌሎች የስልክ የመገናኛ ቁሳቁሶች (ለምሳሌ፤ ኮምፒዩትሮች፣ አይ ፓድ፣ ታብሌት፣ ስማርት ፎን የሚባሉ ዘመናዊና ትናንሽ ኮምፒዩተሮች ወይም የእጅ ስልኮች ሊሆኑ ይችላሉ) መልዕክት የሚያስተላልፉትን ነገሮች ሁሉ ያጠቃልላል። ለዚህ ፖሊሲ ዓላማ ሲባል፣ ዝርዝሩ የመዝናኛና የካሴት መጫወቻ የኤሌክትሮንክስ ቁሳቁሶችን/ቴፖችን ያካትታል።

በትምህርት ቀንና በትምህርት ቤት በተዘጋጁ ፕሮግራሞች ላይ እንድሁም በትምህርት ቤቶች መመላለሻ መኪናዎች ተማሪዎች የተዘረዘሩትን የኤሌክትሮንክስ የመገልገያ ቁሳቁሶችን መያዝ ይችላሉ። በትምህርት ቤትም ሆነ በትምህርት ቤት በተዘጋጁ የተለያዩ ፕሮግራሞች ላይ የስልኮችን ወይም የሌሎችን የኤሌክትሮኒክስ መገልገያ ቁሳቁሶች አጠቃቀም በተመለከተ ተማሪዎች የአስተዳዳሪዎችን ወይም የሰራተኞችን መመሪያ መከተል አለባቸው። ተማሪዎች ስልክን ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ቁሳቁሶች መጠቀም የሚችሉት በትምህርት ቤት ኃላፊ በሚሰጠው መመሪያ መሰረት ነው። የየትምህርት ቤቱ ኃላፊ የእነዚህን ቁሳቁሶች መጠቀም የሚቻለው በትምህርት ቤት ውስጥ በተወሰነ ቦታ ብቻ እንድሆነ ሊወስኑ ይችላሉ።

ስልክን ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ቁሳቁሶች መያዝ ለተማሪዎች እንደ መብት ሊቆጠር ይቻላል፤ ነገር ግን ከፖሊሲው በሚጻረር መልኩ መጠቀም የትምህርት ቤትን ህግ መጣስ ወይም የቦርድ ፖሊሲ ወይም ህግ መጣስ ስለሚሆን በተማሪ ምግባር ፖሊሲዎች መሰረት አስፈላጊውን ቅጣት ሊያስከትል ይችላል። በትምህርት ቤት አግባብ የሌላቸው የስልክ ወይም ተመሳሳይ ቁሳቁሶችን መጠቀም ምሳሌዎች የሚከተሉት ሲሆኑ፣ በእነዚህ ብቻ ግን ላይወሰኑም ይችላሉ፤

1. በትምህርት ቤት ተማሪዎች ማየት የተከለከሉትን የኢንቴርነት ድረ-ገጾችን ለማየት መሞከር።
2. አግባብ የሌላቸውና ሌሎችን የሚረብሽ ኢሜልና ሌሎች መልዕክቶችን መላክ።
3. ካሜራን በመጠቀም ሌሎችን የሚረብሽ ፎቶ ማንሳትና መላክ ወይም ማሳየት።
4. እነዚህን ቁሳቁሶች በመጠቀም የሌሎችን የትምህርት የሥራ ውጤት መስረቅ/እንደ የራስ አድርጎ መጠቀም።
5. እነዚህን ቁሳቁሶች በመጠቀም በድስትሪክት ኮምፒዩተር ላይ ትምህርተ-ነክ ያልሆኑትንና የግል ፋይሎችን መጫን።
6. እነዚህን ቁሳቁሶች በመጠቀም ሌሎች ሰዎችን የሚያስጨንቅና የትምህርት ቤትን የሚያውክ ተግባራት መፈጸም ናቸው።

ካሜራ የተገጠመለትን ማንኛዉንም የኤሌክትሮንክስ መሳርያን ክልክል በሆኑ ቦታዎች መጠቀም ወይንም የሌላውን ሰው የግል ሚስጥርና ደህንነት መጠበቅ የሚጋፋ ከሆነ ይከለከላል።

እነዚህን ቁሳቁሶች መጠቀም ክልክል በሆኑ ቦታዎችና ጊዜዎች ዘግቶ ማስቀመጥ የተማሪ ኃላፊነት ነው። አግባብ ባልሆነና የዚህን ፖሊሲ ወይም ሌሎች የድስትሪክቱን ፖሊሲ በሚጻረር መልኩ የኤሌክትሮኒክስ የመገልገያ ቁሳቁሶቹን መጠቀም አስፈላጊውን ቅጣት ያስከትላል። በህገ-ወጥነት ምክንያት የተቀሙ ቁሳቁሶች ለተማሪ የሚመለሱት ከተማሪው/ዋ ወላጅ/አሳዳጊና ከትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪ ጋር ውይይት ከተደረገ በኃላ ነው። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በትምህርት ቤቱ ኃላፊ ወይም ተወካይ አማካይነት ጉዳዩ ለፖሊስ ሊተላለፍ ይችላል።

ይህ በህገ-ወጥ ሁኔታ የኤሌክትሮኒክስ ቁሳቁሶች መጠቀም ተግባር እንደተከናወነ ጥርጥር ካለ፣ በድስትሪክቱ ፖሊሲ መሰረት አስፈላጊው የመረጃ ማሰባሰብ ሂደት ይከናወናል። በህገ-ወጥ ተግባር ምክንያት ተማሪ የኤሌክትሮንክስ መገልገያውን እንዲያሰረክብ ተጠይቆ ካልታዘዘ፤ አስፈላጊው ቅጣት ይወሰዳል።

ለጊዜው የተያዘና ለፖሊስ ያልተሰጠ የኤሌክትሮኒክስ እንደ ስልክ ያሉ የመገልገያ ቁሳቁሶች ለምርመራ ሂደት አላስፈላጊ ሆነው ሲገኙ ለወላጅ ወይም ለአሳዳጊ ይመለሳሉ። የትምህርት ቤቱ ሃላፊ እቃው በቀጥታ ለተማሪው/ዋ እንዲመለስ ሊያዝ ይችላል።

ተማሪ ወደ ትምህርት ቤት ይዞ የሚመጣቸውን እነዚህ ቁሳቁሶች ጥበቃና ጥንቃቄ በተመለከተ ድስትሪክቱ ምንም ዓይነት ሃላፊነት የለውም። እቃው ከጠፋ፣ ከተሰረቀ ወይም ምንም ዓይነት ጉዳት ከደረሰበት ድስትሪክቱ ኃላፊነት የለበትም፤ ኃላፊነቱ የባለንብረቱ ይሆናል።

ስራ ላይ የዋለው፤ ጃንዋሪ 9፣ 2012
የተሻሻለው ኦገስት 11 ፡2014

ጥምር ዋቢዎች፤ JIC፣ የተማሪ ምግባርና ንዑስ አንቀጾች
JIH፣ የተማሪ የምርመራ መጠይቆች፣ ፍተሻዎች፣ እስራት
JK ፣ የተማሪ ምግባርና ንዑስ አንቀጾች

## ለተማሪ ቃለ መጠይቅ ማድረግ፣ መፈተሽ እና ማሰር (JIH)

የትምህርት ቤቶች ሁኔታ ለመማር ማስተማር እና ለሰራተኞች እና ለተማሪዎች ሰላም እና ደኅንነት መጠበቅ ምቹ እንዲሆኑ የትምህርት ቦርድ ይፈልጋል። ይህንን ከግብ ለማድረስ፣ የትምህርት ቤት አስተዳደሮች ግለሰቡን እና/ወይም የተማሪው/ዋን የግል ንብረቶች መፈተሽ እና ጎጂ ወይም ለተማሪዎች እና ለሰራተኞች ሰላም እና ደኅንነት አስጊ የሆኑትን ማንኛውንም ንብረቶች መያዝ አስፈላጊ ነው።

በትምህርት ቤት አስተዳዳሪ የሚደረግ የተማሪ ፍተሻ

ፍተሻው የሚካሄደው በትምህርት ቤት ኃላፊ ሲሆን ለፍተሻው አሳማኝ የጥርጣሬ ምክንያት ሊኖር እና ተማሪው/ዋ ሕግን ወይም የቦርድ ፖሊሲን (ሕገ ደንብን) እንደጣሰ/ች ማስረጃ ሊገኝ ይገባል። ለፍተሻው በቂ ምክንያት ሲገኝ፣ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ወይም በትምህርት ቤት በተዘጋጁ ዝግጅቶች ጊዜ በዚህ ፖሊሲ (ሕገ ደንብ) ውስጥ በተነደፈው መሰረት የትምህርት ቤት አስተዳደር ተማሪን እና/ወይም ንብረቱን/ንብረቷን መፈተሽ እና ማንኛውንም ሕገ ወጥ፣ ክልክል ወይም የኮንትራባንድ ዕቃዎችን መያዝ ይችላል።

በትምህርት ቤት ኃላፊ የሚካሄደው ማንኛውም ፍተሻ የተማሪው/ዋን የግል ሚስጢር መጠበቅ እና የተማሪውን ዕድሜ እና ጾታ እና የተጠርጣሪውን የሕግ መተላለፍ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት አላስፈላጊ ጉዳዮች ውስጥ ጣልቃ አለመግባት አስፈላጊ ነው።

በተቻለ መጠን፣ ተማሪው/ዋ ለምን እንደሚፈተሽ/እንደሚትፈተሽ እና ፍተሻውን ለማካሄድ የተማሪው/ዋ ፈቃድ ይጠየቃል። ተማሪው/ዋ ለፍተሻው ከትምህርት ቤት ኃላፊዎች ጋር ካልተባበረ የቅጣት እርምጃን ለመውሰድ መሰረት ይሆናል።

**በትምህርት ቤት ሰራተኞች የሚደረግ ፍተሻ**

ፍተሻ በትምህርት ቤት ኃላፊ የሚካሄድ ቢሆንም፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣ የትምህርት ቤት ሰራተኞች በዚህ ፖሊሲ ውስጥ በተቀመጠው ህገ-ደንብ መሰረት ተማሪንና ንብረቱን በመፈተሽ ህገ-ወጥ የሆኑ ነገሮች መያዝ ይችላሉ።

ማንኛውም ፍተሻ ሲካሄድ፣ የተማሪን ዕድሜና ጾታ እንደዚሁም የጉዳዩን ሁኔታ ከግምት በማስገባት፣ አላስፈላጊ የሆነ ንኪኪ ከማድረግ መቆጠብ አስፈላጊ ነው።

በተቻለ መጠን የፍተሻው ዓላማ ለተማሪ መገለጽና ፍተሻውን ለማካሄድ ከተማሪ ፈቃድ መወሰድ አለበት። የተማሪው በዚህ ጉዳይ ያለመተባበር ለተማሪ ሥነ-ምግባር ጉድለት እርምጃ መውሰድ መሰረት ይሆናል።

የፍተሻው ምክንያት፣ ውጤቱና የምስክሮች ስም ዝርዝር ሪፖርት በትምህርት ቤት ኃላፊ መዘጋጀት አለበት። የፍተሻው ሂደት ከተማሪ ሥነ-ምግባር ጉድለት ጋር የሚያያዝ ከሆነ ፣ ሪፖርቱ ከተማሪ ሰነድ ጋር መያያዝ አለበት።

**ትርጉሞች**

1. "አሳማኝ (መሰረት ያለው) ጥርጣሬ" በትምህርት ቤት ንብረት አከባቢ ወይም በትምህርት ቤት ኃላፊዎች አማካይነት በሚካሄዱት የትምህርት ቤት ዝግጅቶች ላይ ለሚደረገው ፍተሻ መደበኛ ትርጉም ነው። መሰረት ያለው ጥርጣሬ ታአማንነት ባላቸው ሰዎች በሚሰጡት ተጨባጭ ማስረጃዎች ወይም በግል አስተውሎት ላይ የሚመሰረት እና የትምህርት ቤት ኃላፊዎችን የሚያሳምን፣ እንደዚሁም ከባለፈው ልምድ በመነሳት፣ ያንን ሰው፣ ቦታ ወይም ነገር መፈተሽ የቦርድ ፖሊሲ (ሕገ ደንብ) ወይም የክፍለ ግዛት ሕጎችን መጣስ አስመልክቶ ተጨባጭ ማስረጃ የሚያስገኝ መሆን አለበት። አሳማኝ (መሰረት ያለው) ጥርጣሬ ከዝም ብሎ ከጥርጣሬ ብቻ ያለፈ መሰረታዊ ጥርጣሬ ነው።

2. "ኮንትራባንድ" በ 'JICI' ፖሊሲ ውስጥ በተገለጸው መሰረት በቦርድ ፖሊሲ ወይም በክፍለ ግዛት የተከለከሉ ቁስ አካላት ሆኖ እጾች፣ የአልኮል መጠጦች፣ ገዳይ የሆኑ ጠመንጃዎች (ሽጉጦች)፣ "የጦር መሳሪያዎች" ወይም " አርትፍሻል (እውነተኛ ያልሆኑ) የጦር መሳሪያዎች" ያካትታል፣ በነዚህ ብቻ ግን አይወሰንም።

**የትምህርት ቤት ንብረትን መፈተሽ**

የትምህርት ቤት ሎከሮች(የዕቃ ማስቀመጫ ሳጥኖች)፣ ዴስኮች( የመጻፊያ ጠረጴዛዎች) እና ሌሎች የዕቃ ማከማቻ ሥፍራዎች የትምህርት ቤት ንብረቶች በመሆናቸው ሁሉ በትምህርት ቤት ቁጥጥር ሥር ናቸው። በዚህ ፖሊሲ መሰረት ለተማሪዎች አገልግሎት የሚቀርቡ የትምህርት ቤት ንብረቶች ለምርመራ፣ ለጽዳት፣ ለጥገና እና ለፍተሻ ጉዳዮች ሲፈለጉ አይከለከሉም።

ለሎከራቸው (ለዕቃ ማስቀመጫ ሳጥናቸው) እና/ወይም በአስተዳደሩ በተፈቀደው መሰረት ለሌሎች የዕቃ ማስቀመጫ ሥፍራዎች ተማሪዎች ሙሉ ኃላፊነት (ተጠያቂነት) አለባቸው። ትምህርት ቤት በሰጣቸው ዴስኮች እና ሎከሮች ውስጥ ላሉ ማናቸውም ነገሮች ተማሪዎች ኃላፊነት አለባቸው።

ከትምህርት ቤቱ ከተሰጠው ወይም በትምህርት ቤቱ ኃላፊ ከተፈቀደው ቁልፍ በስተቀር ተማሪ ሌላ ቁልፍን ተጠቅሞ/ማ የትምህርት ቤቱ/ቷን ሎከር ወይም የዕቃ ማስቀመጫ ሳጥን መቆለፍ ወይም እንዳይከፈት መከልከል አይችልም/አትችልም። ያልተፈቀዱ ቁልፎች ይወሰዳሉ።

አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ እና አሳማኝ ምክንያት ካለው/ካላት ኃላፊው/ዋ ወይም ተወካይ የተማሪ ዴስክ፣ ሎከር፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የዕቃ ማከማቻ ሥፍራ እና በውስጡ ያሉትን ዕቃዎች መፈተሽ ይችላል/ትችላለች። በተቻለ መጠን፣ ፍተሻው ሲካሄድ ሌላ ሰው ለአይን ምስክርነት በቦታው ይገኛል።

***የመኪና ማቆሚያ ቦታን/ተሽከርካሪን መፈተሽ***

በተማሪ የሚነዳን መኪና ይዞ ትምህርት ቤት የመምጣት መብት የሚጠበቀው ለአሳማኝ ምክንያት እና በተጨባጭ ለኮንትራባንድ ዕቃዎች ሲጠረጠር መኪናውን ለማስፈተሽ ተማሪው/ዋ ፍቃደኛ ከሆነ/ች ነው።

በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ መኪናው ለፍተሻ ሲፈለግ ተማሪው/ዋ፣ ወላጅ ወይም ሕጋዊ አሳዳጊ ወይም የመኪናው ባለቤት ፈቃደኛ ካልሆነ/ች፣ ያለ ተጨማሪ መረጃ ወዲያው መኪናን ይዞ/ዛ ትምህርት ቤት የመምጣት መብትን ይነፈጋል/ትነፈጋለች።በተጨማሪም፣ ለፍተሻ አለመተባበር፣ የቅጣት እርምጃን ያስከትላል፤ ጉዳዩም ለሕግ አስከባሪዎች (ፖሊስ) ይተላለፋል።

መደበኛ የተማሪዎች የመኪና ማቆሚያ ቦታ ቁጥጥርም ሁል ጊዜ ይደረጋል።

***ተማሪን መፈተሽ***

የትምህርት ቤት ኃላፊ ወይም ተወካይ ተጨባጭ መረጃ ካለው/ካላት እና ተማሪን ለኮንትራባንድ ዕቃ ከተጠራጠረ/ች ተማሪው/ዋን ልፈተሽ ይችላል/ትችላለች፤

ሀ. የቦርድ/የድስትሪክት ፖሊሲዎችን፣ የትምህርት ቤት ህገ-ደንቦችን፣ ወይም የፌዴራል፣ የክፍለ-ግዛት፣ ወይም የወረዳ ህጎች ጥሰት መረጃ።
ለ. በማንኛውም ሰው ላይ አደጋ፣ ጉዳት፣ ወይም ህመም ሊያመጣ የሚችል ማንኛውም ነገር።

ፍተሻው የሚደረገው ቦታዎችም የተማሪ ኪስ፣ ሻንጣ፣ ቦርሳ፣ እና/ወይም የተማሪው/ዋን የውጨኛው ክፍል ልብስ ሊሆን ይችላል።

ፍተሻው ሲደረግ ሌሎች ተማሪዎች በሌሉበት ቦታ ሆኖ በተቻለ መጠን የተማሪው/ዋን የግል ሚስጢር በመጠበቅ ይሆናል።ነገር ግን ቢያንስ አንድ፣ ከሦስት መብለጥ የለበትም፣ ተመሳሳይ ጾታ ያላቸው ተማሪዎች ፍተሻው ሲካሄድ ለአይን ምስክርነት በቦታው ይገኛሉ፣ በፍተሻው ግን አይሳተፉም።

ማንኛውም የተፈተሸ ተማሪ ጉዳይ በተቻለ መጠን በአስቸኳይ ለወላጅ ወይም ለሕጋዊ አሳዳጊ ይገለጻል።

ኮት ወይም ጃኬት ወይም ጫማ ከማውለቅ ውጪ ሌሎች የውስጥ ልብሶችን ማውለቅ የሚያስፈልግ ፍተሻ ለሕግ አስከባሪዎች (ለፖሊስ) ይተላለፋል። ማንኛውም የትምህርት ቤት ሰራተኛ እንደዚህ ዓይነቶቹን ጠቅላላ ፈተሻዎች ማካሄድ አይችልም/አትችልም።

**የሕግ አስከባሪዎች/የፖሊስ በጉዳዩ መሳተፍ**

ኃላፊው/ዋ ወይም ተወካይ የትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ በሕግ አስከባሪ (ፖሊስ) እንዲፈተሽ መጠየቅ ይችላል/ትችላለች። ፖሊስ በፍተሻው ሲሳተፍ፣ ፍተሻው የሚካሄደው በዚህ ሕገ ደንብ መሰረት ሳይሆን በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መስፈርት መሰረት ነው።

ፖሊስ ለጥያቄው መልስ ሲሰጥ፣ ከፖሊስ ቀጥተኛ ትዕዛዝ ካልተሰጠ በስተቀር፣ ማንኛውም የትምህርት ቤት ሰራተኛ በፍተሻው ሂደት አይሳተፍም።

ኃላፊው/ዋ ወይም ተወካይ ለሚከተሉት ጉዳዮች የፖሊስን ድጋፍ ሊጠይቁ ይችላሉ፡

1. ሎከሮችን (የዕቃ ማስቀመጫ ሳጥኖችን)፣ ዴስኮችን (የመጻፊያ ጠረጴዛዎችን) እና ሌሎች የዕቃ ማከማቻ ሥፍራዎችን ጨምሮ ሌሎች የትምህርት ቤት ንብረቶችን ይፈትሻል/ትፈትሻለች፤
2. ማናኛውንም የሞተር ተሽከርካሪ ወይም ቦርሳ፣ ሻንጣ ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ነገሮችን መፈተሽ፤ ባለንብረቱ (ተማሪው/ዋ) ለማስፈተሽ ፈቃደኛ ካልሆነ/ች፤

   በዚህ ሁኔታ ውስጥ ኃላፊው/ዋ ወይም ተወካይ፣ ግዳጅ ባይሆንም፣ የሕግ አስከባሪዎችን (ፖሊስ) ከመጥራቱ/ቷ በፊት የተማሪው/ዋን ወላጅ ማሳወቅ እና ድጋፋቸውን ሊፈልግ/ሊትፈልግ ይችላል/ትችላለች።
3. በዚህ ክፍል ውስጥ በተቀመጠው መሰረት ፍተሻ ተካሂዶ ክልክል የሆኑ ነገሮች ሲገኙ፤

ፖሊስ ከወንጀል ሥራዎች ጋር በተገናኘ መልኩ መረጃን ፈልጎ ተማሪን፣ የተማሪው/ዋን ወይም የትምህርት ቤት ንብረት ለመፈተሽ  ከትምህርት ቤት ኃላፊዎች ፈቃድ ከፈለገ፣ የትምህርት ቤት ኃላፊዎች ፖሊስ ለፍተሻ መስተማመኛ ወይም የዋስትና  ሕጋዊ ደብዳቤ እንዲያመጣ ይጠየቃል፣ አሊያም፡

1. ተማሪው/ዋ ለፍተሻው ፈቃደኛ ከሆነ/ች፤

2. ፖሊስ ለፍተሻው ሕጋዊ የዋስትና ደብዳቤ እስኪያቀርብ ድረስ የፍተሻ ሁኔታው ዓላማ የሚያስተጓጉል እና  አስጊ ጉዳይ የሚሆን ከሆነ፤

3. ፍተሻው ለእስራት መነሻ የሚሆን እና ጉዳዩ በተወሰነ ግለሰብ እና በአከባቢው በሚገኙት ላይ የሚያነጣጥር ከሆነ።

***የምርመራ ቃለ መጠይቅ***

በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ፖሊስ ተማሪን ለቃለ መጠይቅ ሲፈልግ፣ የትምህርት ቤት ኃላፊ በሥፍራው ይገኛል/ትገኛለች። ልጁ/ጇ በክፍለ ግዛት ውስጥ በተወሰነው ሕግ መሰረት ከቤተሰቦቹ/ቿ ወይም ከሕጋዊ አሳዳጊዎቹ/ቿ ካልተለየ/ች በስተቀር፣ ተማሪው/ዋ ከ18 ዓመት በታች ከሆን/ች፣ የተማሪው/ዋ ወላጅ(ጆች) ወይም ሕጋዊ አሳዳጊ(ዎች) በፍተሻ ሥፍራው ይገኛሉ።

በዚህ ሂደት ውስጥ ሕግ ተጥሷል ተብሎ ከታመነበት፣ የትምህርት ቤት ኃላፊዎች አግባብ ያለውን የሕግ አስከባሪ ክፍል በማሳወቅ የተጠራጠሩትን የሕግ ጥሰት ይጠቁማሉ። ይህ ጥቆማ የሚደርሳቸው የሕግ አስከባሪዎች (ፖሊስ) ለጉዳዩ ሕጋዊ እርምጃዎችን መውሰድ  ይጠበቅባቸዋል። በነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ፣ ተማሪው/ዋ ከ18 ዓመት በታች ከሆነ እና ፣ በክፍለ ግዛት ውስጥ በተወሰነው ሕግ መሰረት ከበተሰቦቹ/ቿ ወይም ከሕጋዊ አሳዳጊዎቹ/ቿ ካልተለየ/ች በስተቀር ፣ ዲስትሪክቱ በተቻለ መጠን ጉዳዩን ለተማሪ ወላጆች ወይም ሕጋዊ አሳዳጊዎች በአስቸኳይ ያሳውቃል።

ተማሪው ከ18 ዓመት በታች ከሆነ፣ የተማሪው ወላጅ/አሳዳጊ ቀጥሎ ከተዘረዘሩ ሁኔታዎች በስተቀር መገኘት አለባቸው፤ (1)ልጁ በክፍለ-ግዛት ህግ መሰረት ነጻ ከወጣ፣ (2) በዚህ ፖሊሲሲ መሰረት የተማሪው ወላጅ/አሳዳጊ ጉዳዩ ካልተገለጸላቸው፣ (3)የተማሪው ወላጅ/አሳዳጊ ያለነሱ መጠይቁ እንዲካሄድ ከፈቀዱ ናቸው።

የፍተሻው ሂደት እንዳይስተጓጎል እና ተማሪው/ዋ እንዳይረበሽ/እንዳትረበሽ በተቻለ መጠን አስፈላጊው ጥረት ሁሉ ይደረጋል።

**ፍተሻና እስራት**
ፖሊስ ተማሪን ቁጥጥር ሥር ማዋል ወይም ማሰር ሲፈልግ፣ የትምህርት ቤት ኃላፊ የሕግ አስከባሪዎቹ የሚወስዱት እያንዳንዱ እርምጃ በጥንቃቄ እና ሕጋዊ በሆነ መልኩ እንዲሆን ይጠይቃል። ይህም፣ በነዚህ ብቻ ባይወሰንም፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ይታሰር የሚል ሕጋዊ የዋስትና ደብዳቤ ማቅረብ እና ሌሎች ጉዳዮችን በጊዜው እና ሕጋዊ በሆነ መንገዱ ማከናወን ናቸው።

**ይዞታና/ወይም እስራት**
ፖሊስ ለጥያቄ ከፈለገ እወላጅ/አሳዳጊና ተማሪ ፈቃድ መሰረት ተማሪው ከታሰረበት ይለቀቃል፡፡ለፖሊስ ጥያቄ ተማሪ ከትምህርት ቤት ሲወሰድ፣ የትምህርት ቤት ኃላፊ ጉዳዩን ለወላጅ/አሳዳጊ ለማሳወቅ አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል።

በዚህ ሂደት ውስጥ ፖሊስ ተማሪን የሚያስር ከሆነ የትምህርት ቤት ኃላፊ ጉዳዩ ህጋዊ መሆኑን ያጣራል። የድስትሪክት ሰራተኞች ለፖሊስ እርምጃ ህጋዊ መሆን ተጠያቂ አይደሉም።

***ዕቃዎችን መያዝ***
በትምህርት ቤት ኃላፊዎች በሚደረግ ፍተሻ ወቅት የተገኙ ማንኛቸውም ሕገ ወጥ እና አደገኛ የሆኑ ዕቃዎች:

1. የተያዙ/የተመረመሩ እና/ወይም ለማስረጃነት የተሰጡ ዕቃዎች ተማሪን ከትምህርት ቤት ለማገድ ወይም ለማስወጣት ሂደት ውስጥ እንድ ማስረጃ ይረዳሉ፤

   እንደነዚህ ያሉ ዕቃዎች በአበቱታ ማቅረቢያ ችሎት ጊዜ ለማስረጃነት እስከቀርቡ ድረስ በትምህርት ቤት ኃላፊ በጥንቃቄ ይያዛሉ። የተያዘው
   ዕቃ ክልክል ወይም ሕገ ወጥ ንጥረ ነገር ወይም እጽ መሆኑ በምርመራ ከተደረሰበት፣ የምርመራ ውጤቱ እና ተያያዥ ሰነዶች በአበቱታ
   ማቅረቢያ ችሎት ጊዜ ለማስረጃነት እስከቀርቡ ድረስ በትምህርት ቤት ኃላፊ በጥንቃቄ ይያዛሉ።

2. በዚህ ፖሊሲ መሰረት ለማንኛውም የሕግ አስከባሪ ክፍል ይመለሳል።

ከተያዙ ዕቃዎች ጋር የተያያዘ ማናቸኛውም የሕግ አስከባሪ (ፖሊስ) ሰነዶች፣ ምርመራዎች ወይም መግለጫዎች በአቤቱታ ማቅረቢያ ችሎት ጊዜ እንደ ማስረጃ ያገለግላሉ።
**ይግባኝ መጠየቅ**
ከፍተሻው በኃላ በአስር የትምህርት ቀናት ውስጥ ተማሪው/ዋ የፍተሻውን ምክንያት እና ሁኔታ ለሚያጣራው/ለሚታጣራው ለበላይ አለቃ አቤቱታ ሊያቀርብ/ሊታቀርብ ይችላል/ትችላለች። ይግባኙ ከደረሰው/ከደረሳት በኃላ፣ የበላይ አለቃው/ዋ በአምስት የትምህርት ቀናት ውስጥ የፍተሻውን ግኝት በጽሁፍ ያሳውቃል/ታሳውቃለች። የበላይ አለቃው/ዋ ውሳኔ የድስትሪክቱ የመጨረሻ ውሳኔ ይሆናል።
*ሥራ ላይ የዋለው፤ ሜይ 10፣ 1999*
የተሻሻለው፤ ሴፕተምበር 10፣ 2012

ህጋዊ ዋቢዎች፤ C.R.S. 19-2-511 et. seq
C.R.S. 22-32-109.1 (2)(a)(I)(II)(ደህንነቱ የተጠበቀ ትምህርት ቤት እቅድ ክፍል የሆነ ፖሊሲ)

ጥምር ዋቢዎች፤ JK፣ የተማሪ ምግባርና ንዑስ አንቀጾች
JICI፣ በትምህርት ቤት ውስጥ መሳሪያ መያዝ

## የትምህርት ቤቶች አትሌትክስ
(JJJ)

***መግቢያ***
የትምህርት ቤቶች ፕሮግራም የሚኖረው ተሳታፊዎች እምቅ ችሎታቸውን እንዲጠቀሙበትና ትምህርት ቤቶቻቸውን እንዲወክሉ ነው።
ተሳታፊዎች የሚወክሉት ራሳቸውን ብቻ ሳይሆን ተማሪዎችን፣ ሰራተኞችንና የትምህርት ቤቶቻቸውን ደጋፊዎች ሁሉ ነው። በትምህርት ቤቶች አትሌትክስ መሳተፍ ጥሩ እድል ሆነ፣ በዚህ ክፍል ውስጥ ለሚገለጹት ደንቦች፣ መተዳደሪያ ደንቦችና መመዘኛዎች መታዘዝ ያስፈልጋል።

የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት የትምህርት ቤቶች አትሌትክስ ፕሮግራም እንደ የተጓዳኝ ትምህርት ፕሮግራም የሚታይ ሆኖ፣ በፕሮግራሙ ለመሳተፍ ለሁለቱም ጾታዎች እኩል እድል መሰጠት አለበት። ይህ ፕሮግራም የግዴታ አይደለም፣ ደግሞም የድስትሪክቱ የመደበኛ ትምህርት ፕሮግራም አካል አይደለም።

ከላይ በተሰጡት ግቦች ላይ በመመሰረት፣ የትምህርት ቦርድ የሴቶችን ስፖርቶች ከወንዶች ስፖርቶች በእኩልነት ለመደጎምና የተወሰኑ ስፖርቶች ለተጓዳኝ ትምህርት ምቹ ሆነው ሲገኙ የተጓዳኝ ትምህርት ቡድኖችን ለመፍቀድና ለማበረታታት ይፈልጋል። የትምህርት ቦርድ ተማሪዎችን፣ ሰራተኞችንና ማኅበረሰቡን ማበረታታትና በአጠቃላይ የትምህርት ፕሮግራሞች ውስጥ የአትሌትክስን ጠቀሜታ እንዲያውቁ ይፈልጋል።
በትምህርት ቤቶች አትሌትክስ ለመሳተፍ መስፈርቱ የሚወሰነው በህገ-መንግሥቱና በኮሎራዶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተግባራት ህጎች፣ እንደዚሁም በድስትሪክቱ የመተዳደሪያ ደንቦች መሰረት ነው።

**የሥርዓት ሂደቶችና የአትሌትክስ እቀባዎች**
ይህንን የተሰጠውን ፖሊሲና አጃቢ የመተዳደሪያ ደንቦችን በሚጥሱ ተማሪዎች ላይ በአጃቢ የመተዳደሪያ ደንብ ንድፍና በሌሎች የትምህርት ቦርድ ፖሊሲዎች መሰረት አግባብ ያላቸው የሥርዓት እቀባዎች ይጣልባቸዋል። በትምህርት ቤቶች አትሌትክስ መሳተፍ በተመለከተ የሚጣለው እቀባና የእቀባው ሁኔታ በተማሪው/ዋ የትምህርት ቤት ኃላፊ ወይም ተወካይ ይወሰናል።

**የፖሊሲ አፈጻጸም**
ተማሪ በስፖርት (በጨወታ) በሚሳተፍባቸው/በሚትሳተፍባቸው ወቅቶች በሙሉ በዚህ ፖሊሲ ሥር ነው/ናት። ወቅቱም ከመጀመሪያ የልምምድ ቀን ጀምሮ እስከ ውድድሩ ማለቂያ ድረስ ነው። በተጨማሪም፣ በተሰጠው የትምህርት ዘመን ውስጥ፣ በትምህርት ቤት ውስጥ ወይም ውጪ፣ እንደዚሁም ትምህርት ሳይኖርም አግባብ ያለው ቦታ ለሚከሰቱት አሳሳቢና መጠነ ሰፊ ለሆኑ ሁከቶች በማንኛም ጊዜ እቀባዎች ሊጣሉ ይችላሉ።

**የተለያዩ ጉዳዮች**
በዚህ ክፍል ውስጥ ከተገለጹት ጉዳዮች ውስጥ አሰልጣኝን ወይም ዝግጅቱን ያዘጋጀ ክፍል ለተግባራቱ/ለድርጊቶቹ አስፈላጊ የሆኑትን ተጨማሪ ደንቦች፣ ሰዓታትን መገደብና ለቡድኑ ተግባር ተገቢ የሆኑትን ሌሎች ጉዳዮች ከማውጣትና ከመተግበር የሚያግዳቸው ምንም ነገር የለም። መለስተኛ ሁከቶች ሲከሰቱ የሚመለከተው አሰልጣኝ ከአትሌትክስ ኃላፊና/ወይም ከሚመለከተው የድስትሪክቱ አስተዳደር ጋር ከተመካከሩበት በኃላ ጉዳዩ በቀጥታ በአሰልጣኙ መፍትሄ እንደሚያገኙ ይጠበቃል።

በዚህ ፖሊሲ ውስጥ ከተገለጹት ጉዳዮች ውስጥ የትምህርት ድስትሪክት ባለሥልጣናትን በ1967ቱ የትምህርት ቤት ክትትል ህግና በተገቢው

የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ መሰረት ተማሪን እንዳይቀጡ የሚያግዳቸው ምንም ጉዳይ የለም።
በማንኛውም የድስትሪክት ሰራተኛ ወይም በማንኛውም ሌላ ተማሪ ስፖርተኞችን ከሌሎች የክትትል ዙሪያዎች መመልመል ክልክል ነው።
ለተሳታፊ ተማሪና ለማንኛውም የድስትሪክት ሰራተኛ (ሰራተኞች) የቅጣት እርምጃዎች መሰረት ሊኖረው ይገባል። እንደዚሁም ወላጆችና
የማህበረሰብ አባላት ለአትሌትክስ ዓላማ ብቻ ምልመላን ከማካሄድ እንዲቆጠቡ ይበረታታሉ።

ሥራ ላይ የዋለው ቀን፡ ኦገስት 16፣ 2004
ተዛማጅ ዋቢዎች፡ JJ፣ የተማሪ ተግባራት (ሥርዓተ-ትምህርትና ተጓዳኝ ትምህርት)
JICDA፣ የምግባርና የሥርዓት ህግ
JKD-1-E፣ ተማሪን ከትምህርት ቤት ለጊዜው ማገድ፣ ከመደበኛው ትምህርት ቤት ማገድና ምዝገባን መከልከል
JICH፣ የተማሪዎች የአልኮል መጠጥና ሌሎች የአደንዛዥ እጽ መጠቀም

## የትምህርት ቤቶች አትሌትክስ
## (የአትሌትክ ህግ)
## (JJJ-R)

**መስፈርት**
በትምህርት ቤቶች አትሌትክስ ለመሳተፍ መስፈርቱ የሚወሰነው በህገ-መንግሥቱና በኮሎራዶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ድርጊቶች/ተግባራት ህጎች፣ እንደዚሁም በድስትሪክቱ የመተዳደሪያ ደንቦች መሰረት ነው።

**የትምህርት ቤቶች አትሌትክስ ህግ**
የህገ መንግሥቱ አንቀጽ 111አ ና የቼሪ ክሪክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ህግ/መተዳደሪያ ደንብ በክፍል የሚከተለውን ያቀርባል፤

3. የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተማሪዎች ትምህርት ቤታቸውን ወክለው በትምህርት ቤቶች ተግባራት እንዲሳተፉ ይፈቀድላቸዋል፡
ሀ. ተማሪው/ዋ ያልተመረቀና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አባል መሆኑ/ኗ የተረጋገጠ።

ለ. በኃላፊው/ዋ ውሳኔ መሰረት፣ ተማሪው/ዋ በምግባር፣ በዜግነትና በስፖርቶች ጉዳዮች ትምህርት ቤቱን ይወክላል።

ሐ. በተሳትፎው ጊዜ፣ ተማሪው/ዋ ቢያንስ በአንድ ሴሚስቴር ለ 2.5 ክሬዲት መመዝገብና፣ ከግማሽ ነጥብ በላይ ማጣት የለበትም/የለባትም።
ለሚቀጥለው ሴሚስቴር መቀጠል መስፈርት መሙላትን ለመወሰን የሩብ ክሬዲት ኮርሶች በሴሚስቴሩ መጨረሻ ላይ ይጣመራሉ፣
እንደዚሁም በድስትሪክቱ ውሳኔ መሰረት በተካታታይ ይከለሳል።

መ. ያለፈው ሰሚስቴር መጨረሻ ላይ ከላይ በ ‘ሐ’ ሥር በተገለጸው መሰረት ተማሪው/ዋ መስፈርት መሙላት አለበት/አለባት።

ሠ. ከተመዘገበ/ችና ትምህርትን ለ15 ቀናት ወይም ከዚያም በላይ ከተከታተለ/ች በኃላ ያቋረጠ/ች ተማሪ የሚቀጥለውን ሰሚስቴር ትምህርት ለመከታተል መስፈርት አይሞላም/አትሞላም። የሚቀጥለውን ሰሚስቴር ትምህርት ለመከታተል፣ ተማሪው/ዋ ከተመዘገበ/ችና ለ15 ቀናት ወይም ለከዚያም በላይ ትምህርቱን ከተከታተለ/ች፣ የሚቀጥለውን ሰሚስቴር ትምህርት ለመቀጠል የጀመረውን/የጀመረችውን ሰሚስቴር ክሬዲት በሙሉ ማጠናቀቅ ይኖርበታል/ይኖርባታል።

ረ. ተማሪው/ዋ በሕግ የተከለከለ የማንኛውም ድርጅት አባል መሆን የለበትም/የለባትም።

የትምህርት ድስትሪክቱ የሚከተሉትን ተጨማሪ ህጎችና የመተዳደሪያ ደንቦች አውጥቷል፤

1. የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተሳታፊ ተማሪዎች የሚፈለገውን አካላዊ ምርመራ ማለፍ አለባቸው፣ በተጨማሪም ምርመራውን ለማካሄድ ከተሳታፊዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል። የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተሳታፊ ተማሪዎች በትምህርት ቤቶች አትሌቲክ ተግባራት ከመሳተፋቸው በፊት አካላዊ ምርመራን ማለፍ የግድ ነው።
2. የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተሳታፊ ተማሪዎች የሚፈለገውን የትምህርት ቤት የአትሌትክ እንሹራንስ ወይም በቤተሰብ/በአሳዳጊ የተመሰከረበትና የተረጋገጠ ተገቢውን የቤተሰብ የእንሹራንስ ዋስትና ሽፋን ሊኖራቸው ይገባል። ለመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተሳታፊ ተማሪዎች በትምህርት ቤቶች አትሌቲክ ተግባራት ከመሳተፋቸው በፊት የትምህርት ቤት የአትሌትክ ወይም የቤተሰብ እንሹራንስ መኖር የግድ ነው።
3. በትምህርት ቤት አትሌትክስ ለሚሳተፉ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ወይም ውጪ የሚከተሉትን ተግባራት መፈጸም ክልክል ነው፤
   ሀ. የአልኮል መጠጦችን፣ ትንባሆ፣ ሀሺሽ፣ ወይም ሌሎች ህገ-ወጥ አደንዛዥ እጾችንና ተመሳሳይ ነገሮችን መጠቀም፣ መያዝ፣ መሸጥ፣ ማደል ወይም በሌላ ነገር መለወጥ።
   ለ. አግባብ ያላቸውን ባለሥልጣናት ሆን ብሎና በግልጽ ያለማቋረጥ አለመታዘዝ።
   ሐ. የትምህርት ቤት ንብረትን ሆን ብሎ ማጥፋት/ማበላሸት።
   መ. ሌሎች ሰዎች ወይም ለትምህርት ቤት ሰራተኞች ሰላምና ደኅንነት ወይም ሞራል/ግብረ ገብ አስጊ የሆነ ምግባርን ማሳየት።
   ሠ. ለማንኛውም የወንጀል ድርጊት በማዘጋጀ፣ በቀበሌ ወይም በድስትሪክት ፍርድ ቤቶች በጥፋተኝነት መፈረድ፤ መለስተኛ የትራፊክ መተላለፎችን አያካትትም።
4. ተሳታፊ ተማሪዎች አግባብ ያለውን የትምህርት ክንዋኔና የትምህርት ክትትል መመዘኛዎችን ማሟላት አለባቸው።
5. ተሳታፊ ተማሪዎች አጠቃላይ የትምህርት ቤት ህግንና በማህበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት ያለውን የጨዋ ስፖርተኛ ምግባር ማክበር አለባቸው።

**የቅጣት እርምጃ ሂደቶችና የአትሌትክስ እቀባዎች**
ከላይ የተዘረዘሩትን ህጎች በሚጥሱ ተማሪዎች ላይ አግባብ ያለው ቅጣታዊ እቀባ ይጣልባቸዋል። የዚህ ጉዳይ አፈጻጸምም በትምህርት ቤቱ ኃላፊ ወይም ተወካይ ይወሰናል።

በቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት ውስጥ ያሉ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአትሌትክስ ህግን በተመለከተ በየሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአትሌትክስ ተሳታፊ ካርድ ላይ እንደተገለጸው ተማሳሳይ ሂደቶች እንዲጠቀሙ የሚከተሉት ሂደቶች ተዘጋጅተዋል። እነዚህ ሂደቶች ሲዘጋጁ አጠቃላይ የትምህርት ቤቶች የአትሌትክስ ህግ እንድጸናና የተወሰኑ

ትምህርት ቤቶች ደግሞ የአትሌትክስ እቀባዎችን መጣል በተመለከተ የአፈጻጸም ነጻነት እንዲኖራቸው ተደርጎ ነው። እነዚህ ሂደቶች በፖሊሲ 'JJJ' ሥር ተቀምጠዋል፣ በተጨማሪም ምናልባት ግጭት ካለ፣ በዚህ የአትሌትክ ህግ ውስጥ የተወሰኑት ህጎችና የመተዳደሪያ ደንቦች ይተገበራሉ።

**የሕግ ጥሰት(ቶች)ን ለማረጋገጥ የሚደረግ ምርመራ**
የትምህርት ቤቶችን የአትሌትክስ ህግ ጥሰት በተመለከተ የሚከሰት ምግባረ-ቢስነት ጉዳይ ክሱ ከቀረበ በኃላ በተቻለ መጠን በአስቸኳይ በአሰልጣኞችና በአትሌትክስና /ወይም በአስተዳደር ሰራተኞች ይመረመራል።

**ማሳሰቢያ**
ሀ. የትምህርት ቤቶችን የአትሌትክስ ህግ በመጣስ ምክንያት በምግባረ-ቢስነት የሚከሰስ/የሚትከሰስ ማንኛውም አትሌት ተማሪ ጉዳይ ለተማሪው/ዋ ቶሎ ይገለጽለታል/ይገለጽላታል።
ለ. እንደ የምርመራው ክፍል፣ ተማሪው/ዋ የራሱ/ሷን ሀሳብ እንዲሰጥ/እንዲትሰጥ ዕድል ይሰጠዋል/ይሰጣታል። ይህ ግን መረጃን የመጠበቅ፣ መስቀለኛ ጥያቄዎችን የመጠየቅና መረጃዎችን የማሰባሰብ፣ ወይም የተማሪውን ምስክር ጠርቶ የተከሰተውን ጉዳይ የማጣራት መብት አያካትትም። ተማሪው/ዋ ክሱን/ክሶቹን ካልተቀበለ/ች፣ ኃላፊው/ዋ ወይም ተወካይ ያገኙትን መረጃ ያብራሩለታል/ያብራሩላታል።
ሐ. የወላጅን ሃሳብ ለማግኘት በተቻለ መጠን አስፈላጊው ጥረት ይደረጋል።

መ. በምርመራው ጊዜ፣ የአትሌትክ ኃላፊው/ዋና/ወይም አስተዳደር ተጠርጣሪ ተማሪው/ዋ በአትሌትክስ እንዳይሳተፍ/እንዳትሳተፍ ማገድ ይችላሉ።
ሠ. ምርመራው ሲጠናቀቅ፣ በምግባረ-ቢስነት ምክንያት በአትሌትክስ እንዳይሳተፍ/እንዳትሳተፍ እቀባ ከመደረጉ በፊት፣ የትምህርት ቤት ኃላፊ ወይም ተወካይ የምርመራውን ውጤትና የሚጣለውን እቀባ ሁኔታ ለተማሪው/ዋና ለወላጅ/ለአሳዳጊ ማሳወቅ ያስፈልጋል። የተወሰደውን እርምጃ አስመልክቶ ተማሪው/ዋና ወላጅ/አስዳጊ ጥያቄ ካላቸው እንዲጠይቁ ኃላፊው/ዋ ወይም ተወካይ ዕድል ይሰጧቸዋል። ነገር ግን፣ ኃላፊው/ዋ ወይም ተወካይ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ እንደዚህ ዓይነቱን ውይይት ላለመፍቀድ ይችላሉ።

**የአትሌትክስ እቀባዎች**
የሚጣሉት እቀባዎች የሚከተሉትን ሀሳቦች ያካትታሉ፣ በነዚህ ብቻ ግን አይወሰኑም፤
1. ለቅጣት እርምጃ አግባብ ላለው አሰልጣኝ ጉዳዩን ማስተላለፍ።
2. ለተወሰኑ ቀናት መገምገምና/ወይም በዚህ ሁኔታ ውስጥ አግባብ ካለው፣ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አትሌትክስ ተሳታፊ ካርድ ላይ በተገለጸው መሰረት የግምገማ መመሪያዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት ያካትታል።
4. ከተወሰኑ የአትሌትክስ ዝግጅቶች መሳተፍን ለጊዜው ማገድ፣ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አትሌትክስ ተሳታፊ ካርድ ላይ እንደተገለጸው የታገዱትን የአትሌትክስ ዝግጅቶች የቀናት ብዛት ከግምት ማስገባትን ያካትታል።
4. ለቀረው የአትሌትክስ ዝግጅት ከቡድኑ መታገድ።
5. የህግ መተላለፍ ሲከሰት ተማሪው/ዋ የተሳተፈበትን/የተሳተፈችበትን ስፖርት አስመልክቶ የሚሰጡትን የትምህርት ቤት ሽልማቶችን የማግኘት ዕድል መከልከል (የአትሌትክ ሽልማቶች በውድድሩ መሳተፍን ብቻ ሳይሆን ውድድሩን በጨዋነት ማጠናቀቅ ይፈልጋል)።
6.ለቀሪው የትምህርት ዘመን ከአትሌትክ ውድድር መታገድና/ወይም እስከሚቀጥለው የትምህርት ዘመን እገዳውን ማስረዘም።

**ውሳኔ**
ኃላፊው/ዋ ወይም ተወካይ የህግ መተላለፍ መከሰትና አለመከሰትን፣ እንደዚሁም የሚጣሉትን እቀባዎች አስመልክቶ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣሉ። የመጨረሻው ውሳኔ በተወካይ ከተሰጠ፣ ሁኔታውን ለትምህርት ቤቱ ማሳወቅ አለበት/አለባት። በዚያን ጊዜ፣ የእቀባዎቹ ሁኔታ ለተማሪው/ዋ በአካል ይገለጽለታል/ይገለጽላታል። ጉዳዩ በተቻለ መጠን በጊዜ ለወላጅ በስልክ፣ በኢ-ሜል፣ ወይም በአካል ይገለጻል።

የአትሌትክስ እቀባን አስመልክቶ የተሰጠው የኃላፊው/ዋ ወይም የተወካይ ውሳኔን በመቃወም የኃላፊ ወይም የተወካይ ውሳኔን የሚያይ/የሚታይ ለድስትሪክት የአትሌትክስ ኃላፊ ይግባኝ ማለት ይቻላል። የድስትሪክት የአትሌትክስ ኃላፊ ውሳኔ የመጨረሻ ውሳኔ ይሆናል።
ተማሪ ከትምህርት ከታገደ/ች ወይም ለጊዜው ከመደበኛ ትምህርት ቤት ካታገደ/ች፣ የትምህርት እገዳው ሁኔታ በቀጥታ ለተመሳሳይ ጊዜ በአትሌትክስ ከመሳተፍ ያሳግዳል።

ተዛማጅ ዋቢዎች፤ ለበለጠ መረጃ የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት አትሌትክ/የተግባራት መመሪያን ይመልከቱ
የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት ቁ. 5የ ትምህርት ቤቶች አትሌትክስ የመሳተፊያ ካርድ

## የተማሪ ሥርዓት
## (JK)

ውጤታማ የሆነ የተማሪ ሥርዓት ለጥሩ የመማር ማስተማር ተግባር እና ውጤታማ ለሆነ ትምህርት አስፈላጊ እንደሆነ ቦርድ ያምንበታል። የተማሪን ሥርዓት ማስያዝ ዓላማ ተማሪው/ዋ ራስን ለመግዛት ጥሩ አስተሳሰብ እንዲኖረው/እንዲኖራት እና በማኅበረሰብ ውስጥ ተቀባይነት ያለው ምግባር እንዲኖረው/እንዲኖራት ነው።

ቦርዱ፣ በክፍለ ግዛት ሕግ መሰረት፣ እነዚህን ሰፊ ግቦች ለማሳካት እና የድስትሪክቱን ተማሪዎች በሙሉ ጠቅላላ እና አብይ የሆኑ የሥርዓት ችግሮችን ለመቆጣጠር የሚረዱ የመተዳደሪያ ደንቦች እና ሂደቶችን በማውጣት ሥራ ላይ ያውላል። ሕግ ወጥ የሆኑ ተማሪዎችም ሲታረሙ፣ ደኅንነቱ የተጠበቀ የመማሪያ ቦታ ሳይናጋ እና አላስፈላጊ የሆኑ ረብሻዎች ሳይነሱ መሆን አለበት።
ቦርዱ፣ በክፍለ ግዛት ህግ መሰረት፣ ሁሉም ተማሪዎች ተቀባይነት ያላቸውን የምግባር ደንቦች እንዲከተሉ፣ እንደዚሁም ባለሥልጣናትን እንዲያከብሩና እንዲታዘዙ የሚሉ ወጎች ላይ በመመሰረት የተማሪ ምግባርና ሥርዓት መመሪያ ህገ-ደንብ በጽሁፍ መልክ አዘጋጅቷል። በተጨማሪም፣ የተወሰኑ ምግባራት፣ በተለይም የመማሪያ ክፍልን የሚረብሹ ምግባራት ተቀባይነት እንደሌላቸውና የቅጣት እርምጃም ሊያስከትሉ እንደሚችሉ ህጉ ይገልጻል። አንቀጹ ተመጣጣኝ የሆነ የሥነ-ምግባር ጣልቃ-ገብና ተማሪዎችን በትምህርት ገበታ ላይ ማቆየትን ያተኩራል።

'JK' የሚሉ ፍደላትን የያዙ የቦርድ ፖሊሲዎችና በቦርድ የጸደቁ መተዳደሪያ ደንቦች ሁሉ ህጋዊና አስፈላጊ የሆኑ የሥርዓት ክፍል ናቸው።

**የሥርዓት ህግን ማጠንከር**
የሥርዓት ፖሊሲዎችና ሂደቶች፣ በህግ የተወሰነውን ልጅ መበደል ትርጉም ጋር ሳይቃረን፣ አግባብ ያላቸውን አካላዊ ጣልቃ ገብነትን (የኃይል/የጉልበት መጠቀም) ሊያካትት ይችላል። ለበጎነትና በቦርድ ፖሊሲና ሂደቶች መሰረት ከሆነ የአስተማሪ ወይም የሌላ የሥራ ባልደረባ አካላዊ ጣልቃ መግባት እንደ በደል አይቆጠርም።

**የተማሪ ሥርዓትን በተመለከተ የአስተዳደርና የሰራተኞች ኃላፊነቶች**

የመማሪያ ክፍልን ሥርዓት ለማስያዝ እና ለመቆጣጠር፣ እንደዚሁም ግልጽና አስቸጋሪ ምግባር ያላቸውን ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ለማገድ የትምህርት ቤቱ አስተዳደር አስፈላጊውን ድጋፍና ሙሉ ትብብር ከሰራተኞች የማግኘት መብት አለው።

ቁጥጥር ለሚያስፈልጋቸው የሥርዓት ችግሮች ላይ ለመሥራት ለተመደቡት አስተማሪዎች እና ሰራተኞች አስተዳደሩ ምክር እና ጠቃላላ ድጋፍ ያደርጋል።

የሥርዓት እርምጃው የአስተዳደር ድጋፍ እና ልዩ ትኩረት ሲፈልግ፣ ሰራተኞች ጉዳዩን በጽሁፍ ለአስተዳደሩ ያሳውቃሉ።

የቅጣት እርምጃው የአስተዳደር ድጋፍና ትኩረት ሲሻ፣ ሰራተኞቹ ጉዳዩን በጽሁፍ ለአስተዳደሩ እንዲያቀርቡ ሊጠየቁ ይችላሉ።

አስተዳደሩም ጉዳዩን በልዩ ትኩረት በማየት የተወሰደውን እርምጃም ጉዳዩ ለሚመለከተው ሰራተኛ ያሳውቃል።

የመማሪያ ክፍልን ሥርዓት ማስያዝ የአስተማሪው/ዋ ወይም የአስተማሪው/ዋ ረዳት ዋነኛ ኃላፊነት ቢሆንም እንኳን፣ አስተማሪው/ዋ መሸማቀቅ የትምህርት ቤቱን ኃላፊ ምሪትና ድጋፍ መጠየቅ ይችላል/ትችላለች።

**የማስተካኪያ የሥርዓት እቅድ**
በመማሪያ ክፍል ውስጥ፣ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ፣ በትምህርት ቤት ተሸከርካሪዎች ውስጥ ወይም በትምህርት ቤት ዝግጅቶች ላይ በመረበሽ የንብረትና መጠነ-ሰፊ ጥፋት ላደረሰ/ች ተማሪ ኃላፊው/ዋ ወይም ተወካይ የማስተካኪያ የሥርዓት እቅድ ያወጣል/ታወጣለች። የዚህ እቅድ ግብ ተማሪው/ዋን በትምህርት ቤት ውስጥ በማቆየት የተማሪው/ዋን ምግባረ-ቢስነትና የትምህርት ፍላጎቶች ላይ ማተኮር አለበት።

**የልማዳዊ ረባሽ ተማሪ ሥርዓት**
በመማሪያ ክፍል ውስጥ፣ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ፣ በትምህርት ቤት ተሸከርካሪዎች ውስጥ ወይም በትምህርት ቤት ዝግጅቶች ላይ በመረበሽ የንብረትና መጠነ-ሰፊ ጥፋት በማድረስ በተሰጠው የትምህርት ዘመን ውስጥ ለሦስት ጊዜ ለጊዜው ከትምህርት ቤት የታገዱ ተማሪዎች የልማዳዊ ረባሽ ተማሪ ይባላሉ። ይህ ጉዳይ ማንኛውንም በድስትሪክቱ የተመዘገበውን/የተመዘገበችውን ተማሪ ይመለከታል። የልማዳዊ ረባሽ ተማሪ መባል ከመደበኛው ትምህርት ቤት መታገድን ሊያስከትል ይችላል።

**የምግባርና የሥርዓት ህገ-ደንብ ስርጭት**
የተማሪ የምግባርና የሥርዓት ህገ-ደንብ በአንደኛ ደረጃ፣ በመለስተኛና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ እንደዚሁም በድስትሪክቱ ለአዳዲስ ተማሪዎች አንዴ እንዲሰራጭ የትምህርት ቤቶች የበላይ አለቃ ሁኔታዎችን ያመቻቻል። ግልባጮቹም/ቅጂዎቹም በድስትሪክቱ እያንዳንዱ ትምህርት ቤት መኖር አለበት። በተጨማሪም፣ ከህገ-ደንቡ ማንኛውም ተጽዕኖ ያለው ለውጥ ለተማሪዎች መሰራጨት አለበት፤ እንደዚሁም በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት መለጠፍና በድስትሪክቱና/ወይም በትምህርት ቤት ድረ-ገጽ ላይ መውጣት አለበት።

የተማሪ የምግባርና የሥርዓት ህገ-ደንብ ሲያዘጋጅ፣ ቦርዱ ከአስተዳደሮች፣ ከአስተማሪዎች፣ ከወላጆች፣ ከተማሪዎችና ከሌሎች የማኅበረሰብ አባላት ጋር መማከር አለበት።

ሥራ ላይ የዋለው ኦገስት 8፣ 1966
በቅርብ የተሻሻለው ኦገስት 13፣ 2012
እንደገና የተሻሻለው፣ መመሪያው በተዘጋጀበት ቀን
ህጋዊ ዋቢዎች፤ C.R.S. 18 6 401 (1)(የልጅ በደል ትርጉም)

C.R.S. 22 33 106 (1)(f) (ተማሪን ለጊዜው ከትምህርት ቤት ማገድ፣ ከመደበኛው ትምህርት ቤት ማገድና ምዝገባ መከልከል)

C.R.S. 22 32 109.1 (2) (a)(የምግባርና የሥርዓት ህግ ማውጣትና ሥራ ላይ ማዋል)

C.R.S. 22 32 109.1(2)(a)(I)(ተማሪን ከተማሪ ምግባርና ሥርዓት መመሪያ ጋር ለማስተዋወቅ የትምህርት ድስትሪክቱ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል )

C.R.S. 22-32-109.1(2)(a)(I)(C)(ልማዳዊ ረባሽ የሆኑ ተማሪዎች ምግባር ደህንነቱ የተጠበቀ ትምህርት ቤት እቅድ ክፍል)

C.R.S. 22 32 109.1 (9) (ደኅንነቱ የተጠበቀ ትምህርት ቤት ህግ ማጠንከር)
C.R.S. 22 33 106 (1) (c) (5) (የልማዳዊ ረባሽ ተማሪ)
C.R.S. 22-33-106(1)(c)(5)(ልማዳዊ ረባሽ ተማሪዎች)

ጥምር ዋቢዎች፡ JIC፣ የተማሪ ምግባር፣ እና ንኡስ አንቀጾች

JK፣ ናኡስ አንቀጾች (ሁሉም ከተማሪ ሥርዓት ጋር ይያያዛሉ)

## ተማሪን በቅጣት መልክ ከመማሪያ ክፍል ማስወጣት (JKBA)

በመማሪያ ክፍል ውስጥ የተማሪ ምግባር የአስተማሪን በብቃት የማስተማር እና የተማሪዎችን በሥርዓት የመማር ሁኔታን የማያስተጓጉል መሆኑን ማረጋገጥ የቦርዱ ሕገ ደንብ ነው።

ሥርዓትን ለመጠበቅ እና የመማሪያ ቦታን ምቹ ለማድረግ ተማሪዎች ቦርድ ለሚያወጣው ሕገ ደንብ እና በትምህርት ቤቱ ኃላፊ እና/ወይም በአስተማሪ በሚወጡ ለማንኛቸውም ሌሎች አግባብ ላላቸው የመማሪያ ክፍል የምግባር ደንቦች መታዘዝ አለባቸው። የምግባር ደንቡን ወይም ሌሎች የመማሪያ ክፍል ደንቦችን ሥርዓት የሚጥሱ ተማሪዎች ከመማሪያ ክፍል እንዲወጡ ይደረጋሉ እና/ወይም የሥርዓት እርምጃ ይወሰድባቸዋል።

ተማሪን ከመማሪያ ክፍል ውስጥ ማስወጣት ትልቅ እርምጃ ስለሆነ አላግባብ በሆነ መንገድ ወይም ግልጽ ባልሆነ ምክንያት አይደረግም። ግልጽ በሆነ ሁኔታ ከተማሪዎች የሚጠበቀውን የምግባር ሁኔታዎች ከተነጋገሩበት ገንቢ እና ለመከተልም ቀላል ይሆናል። ነገር ግን፣ እያንዳንዱን አግባብ ያልሆነ ምግባር፣ ወይም በዚህ ሕገ ደንብ መሰረት ተማሪን ከመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚያስወጡ የምግባር ሁኔታዎችን ሁሉ መለየት አይቻልም፣ አስፈላጊም አይደለም።በዚህ ሁኔታ ውስጥ የአስተማሪ ሙያዊ ውሳኔ ይጠበቃል። ተማሪን ህጋዊ በሆነ መልኩ ከመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚያስወጡ ሁኔታዎች በሙሉ በሰነድ ይያዛሉ።
የሚከተሉት የተማሪ ምግባር ከታዩ አስተማሪ ተማሪው/ዋን ከመማሪያ ክፍሉ የማስወጣት ሥልጣን ይኖረዋል/ይኖራታል፡

1. በትምህርት ቦርድ የወጣውን የምግባር ህግ ከጣሰ/ች፤

2. አደገኛ፣ ሥርዓተ ቢስ፣ ወይም ረባሽ ከሆነ፣ ወይም

3. በአሳሳቢ ሁኔታ የአስተማሪን ሥራ እና የተማሪ የመማር ሁኔታ የሚያቃውስ ከሆነ።

በክፍል ግዛት እና በፌዴራል ሕጎች እና መተዳደሪያ ደንቦች መሰረት አካለ ስንኩል የሆነ/ችን ተማሪን ከመማሪያ ክፍል አስወጥቶ በሌላ አማራጭ የመማሪያ ቦታ ማቆየት ይቻላል። በዚህ ሕገ ደንብ መሰረት ተማሪን ከመማሪያ ክፍል ማስወጣት የድስትሪክቱን ቀጣይ የቅጣት እርምጃዎችን ከመውሰድ አይከለክልም። እነዚህም ተማሪው/ዋ ከመማሪያ ክፍል እንዲወጣ/እንዲትወጣ የተደረገበትን የምግባር ችግር መሰረት የእስራት እና ከትምህርት ቤት የማስወጣት እርምጃዎች ሊሆኑ ይችላሉ፤ በነዚህ ብቻ ግን አይወሰንም።

ይህን ሕገ ደንብ ሥራ ላይ የሚያውል በበላይ አለቃ መመሪያ መሰረት ነው። ይህም የሚሆነው ተማሪን ከመማሪያ ክፍል ውስጥ ማስወጣት ጉዳይ በድስትሪክቱ ውስጥ በአንድ ዓይነት መልኩ እንዲተገበር ነው።
የታቀደው፤ ነሐሴ 14፣ 2000
ሥራ ላይ የዋለው፤ መስከረም 11፣ 2000
የተሻሻለው፤ መስከረም 10፣ 2012
ህጋዊ ዋቢዎች፤ C.R.S., 22-32-109.1(2)(a)(II) (ደኅንነቱ የተጠበቀ ትምህርት ቤት ሕገ ደንብ ክፍል)
ጥምር ዋቢዎች፤ JIC፣ ንኡስ አንቀጾች (ሁሉም ከተማሪ ምግባር ጋር ይያያዛሉ)
JK፣ የተማሪ ምግባር፣ እና ንኡስ አንቀጾች

## ከመማሪያ ክፍል ውስጥ ተማሪን ለቅጣት ማስወጣት (JKBA-R)

ሰራተኞች፣ አስተዳደር እና አስተማሪዎችን ጨምሮ፣ ያገኙትን ሥልጠና፣ ያላቸውን ልምድ፣ እና ያላቸውን ሥልጣን በመጠቀም ትምህርት ቤቶች እና የመማሪያ ክፍሎች ውጤታማ የመማር ማስተማር የሚካሄዱበት ቦታዎች እንዲሆኑ ጠንክረው መስራት አለባቸው።ተማሪዎችም ከስጋትና ካላስፈላጊ ረብሻዎች ነጻ ሆነው ትምህርታቸውን መከታተል መቻል አለባቸው። የመማሪያን ክፍል ሁኔታ የሚያቃውሱ ምግባራት አይፈቀዱም።

የተማሪ ምግባር ሕገ ደንብን የሚንጻረር ምግባረ ቢስነት ወይም ሥርዓተ ወጥነት ሁኔታ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ሲከሰት አስተማሪ ተማሪው/ዋን በሂደቶቹ መሰረት ከመማሪያ ክፍል በማስወጣት በሌላ አማራጭ ሥፍራ እንዲቆይ/እንዲትቆይ ይደረጋል።

ለዚህ ሕገ ደንብ እና ሂደት ዓላማ፣ "መማሪያ ክፍል" መደበኛ የመማሪያ ክፍልን፣ ልዩ የመማሪያ ክፍልን፣ የትምህርት ማበልጸጊያ ክፍሎችን፣ የቤተሙከራ ክፍሎችን፣ የማጥኛ አደራሾችን፣ የቤተ መጽሃፍት ጊዜዎችን፣ የትምህርት ቤት ስብሰባዎችን፣ እና ሌሎች በአስተማሪ የሚካሄዱ የመማሪያ ዕድሎችን ያካትታል። "አስተማሪ" ማለት የክፍለ ግዛትን የማስተማር የሙያ ፈቃድ ያለው/ያላት እና ተቀጥሮ በትምህርት መርሃ ግብር ውስጥ የማስተማር፣ የመምራት ወይም የመቆጣጠር ሥራን የሚሰራ ሰው ነው።

**መደበኛ ባልሆነ ሁኔታ ተማሪን ከመማሪያ ክፍል አስወጥቶ ወደ ትምህርት ቤቱ ኃላፊ ቢሮ መላክ**

መደበኛ ባልሆነ ሁኔታ ተማሪን ከክፍል ማስወጣት የሚከሰተው በትምህርት ቀን ባሉት የትምህርት ክፍለ ጊዜያት ውስጥ አንድ ወይም የተወሰኑ የመማሪያ ክፍል ደንቦች በተማሪ ሲጣሱ ነው። አስተማሪው/ዋ በተሰጡት የሥርዓት ቁጥጥር ስልቶች መሰረት ተማሪን ከመማሪያ ክፍል ማስወጣት ይችላል/ትችላለች፣ ወይም ተማሪው/ዋን ወደ የትምህርት ቤቱ ኃላፊ ቢሮ፣ የዲን (የመማር ማስተማር ኃላፊ) ቢሮ፣ ለተወሰነ ጊዜ ለመቆጣጠር የሚያመች ሌላ ደኅንነቱ የተጠበቀ ቦታ ማቆየት ይቻላል። በአጠቃላይ ሁኔታ ተማሪው/ዋ የዚያኑ ቀን ወደ መማሪያ ክፍል እንዲመለስ/እንዲትመለስ ይፈቀዳል። ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሂደቶች መደበኛ ባልሆኑ ሁኔታዎች ተማሪን ከመማሪያ ክፍል ለማስወጣት አይተገበሩም።

**መደበኛ በሆነ ሁኔታ ተማሪን ከመማሪያ ክፍል ማስወጣት**

ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ምክንያቶች ለአንድ የትምህርት ክፍል ጊዜ ላልበለጠ ጊዜ አስተማሪ ተማሪን ከመማሪያ ክፍል ማስወጣት ይችላል/ትችላለች:

1. በተማሪ የምግባር ሕግ ውስጥ ክልክል የሆነ ምግባር። የትምህርት ቤት አስተዳደር ተማሪን ለጊዜው ከትምህርት ቤት ማገድ እንደሚችል እና ለአማራጭ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት ደግሞ የበላይ አለቃ አስተያየት እንደሆነ መታወቅ አለበት። በዚህ መሰረት፣ በድስትሪክት ሕገ ደንብ ውስጥ የተቀመጠው ከተማሪ ምግባር ጋር በተያያዘ መልኩ ከትምህርት ቤት መታገድ ወይም ወደ አማራጭ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት መወሰድ ሁኔታ አስመልክቶ፣ የአስተማሪ ተማሪን ከመማሪያ ክፍል ውስጥ የማስወጣት ውሳኔ ተማሪው/ዋ ከትምህርት ቤት እንዲወጣ/እንዲትወጣ ወይም ወደ አማራጭ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት እንዲወሰድ/እንዲትወሰድ ይደረጋል ማለት ወይም ላይሆንም ይችላል።

2. ረብሻ፣ አደገኛ ፣ ወይም ሥርዓተ ቢስ ምግባር: የሚከተሉት ምግባራት፣ በነዚህ ብቻ ግን ባይወሰኑም: የረብሻ፣ የአደገኛ፣ ወይም ሥርዓተ ቢስ ምግባራት ምሳሌ ናቸው:

    ሀ. ሰውን መምታት፣ መንከስ፣ መግፋት፣ መንካካት፣ መቆንጠጥ ወይም መገፍተር እና ሌሎች አላስፈላጊ እና ጎጂ የሆኑ አካላዊ ልፊያዎች፤

    ለ. ሰውን ሆን ብሎ ለማናደድ፣ ለማሰናከል፣ ወይም ለመረበሽ ብሎ መሳደብ፣ መላከፍ፣ ማስፈራራት እና ሌሎች ተመሳሳይ ነገሮችን መፈጸም፤

    ሐ. ከወሲብ ጋር የተገናኘ የማስፈራራት ወይም ተመሳሳይ ምግባር፤

    መ. የትምህርት ቤት አከባቢን ለመረበሽ፣ በተለይም ሌሎች ሰዎች ሲናገሩ(ምሳሌ፡ አስተማሪ ሲያስተምር፣ ተማሪ መልስ ሲሰጥ፣ በእንግዳ ወይም በትምህርት ቤት ጎብኚ ንግግር ሲደርግ) ወይም በጥሞና የጥናት ጊዜ ተደጋጋሚ ወይም አግባብ ያልሆነ ንግግር ወይም ጩኼት እና የመሳሰሉትን ድርጊቶችን መፈጸም፤

    ሠ. ሰውን ለመጉዳት አስቦ መጽሀፍት፣ እርሳሶች፣ መቀሶች እና የመሳሰሉ ነገሮችን መወርወር፤

    ረ. ሌሎች ተማሪዎች እንዲረብሹ ወይም ለአስተማሪ ወይም ለትምህርት ቤት ወይም ለመማሪያ ክፍል ሕገ ደንቦች እንዳይታዘዙ፣ ሌሎች ሰዎች ከመማሪያ ክፍል ወይም ከትምህርት ቤት እንዲወጡ ጭምር (በነዚህ ብቻ ግን አይወሰንም) መቀስቀስ፤

    ሰ. የትምህርት ቤት፣ የአስተማሪ ወይም የሌላ ተማሪ ንብረት ማውደም፤ ወይም

    ሸ. ረባሽ፣ መጥፎ፣ ወይም አደገኛ እና አስቸጋሪ ምግባር።

3. አስተማሪ በደንብ እንዳያስተምር የሚያስተጓጉል ምግባር። ከታች የተዘረዘሩት የነዚህ ምግባር ምሳሌ ቢሆኑም፣ በነዚህ ብቻ ግን አይወሰንም።
    ሀ. በግልጽ ለአስተማሪ አለመታዘዝ፣ በቃላት ወይም በምልክት መግለጽ፣ ወይም ሌላ ግልጽ የሆነ ምግባር ማሳየት፤
    ለ. በግልጽ አስተማሪን አለማክበር፣ በቃላት ወይም በምልክት መግለጽ፣ ወይም ሌላ ግልጽ የሆነ ምግባር ማሳየት፤ ወይም

ሐ. የመማሪያ ክፍል የትምህርት ሂደትን የሚያደናቅፍ ሌላ ምግባር።

**ተማሪን ከመማሪያ ክፍል ለማስወጣት መከተል ያለባቸው ሂደቶች**

በአስተማሪ አስተያየት ምግባሩ አሳሳቢ ካልሆነ፣ እንደዚህ ዓይነቱ ምግባር ከቀጠለ ተማሪው/ዋ ከመማሪያ ክፍል እንደሚወጣ/እንደሚትወጣ አስተማሪው/ዋ ማስጠንቀቅ አለበት/አለባት። ተማሪን ከመማሪያ ክፍል ማስወጣት አግባብ ሆኖ ሲገኝ እና አስፈላጊ ነገሮች ከተሟሉ፣ አስተማሪው/ዋ ከታች ከተሰጡት ውስጥ አንዱን እርምጃ መውሰድ አለበት/አለባት፡

1. ከትምህርት ቤት ዋና ቢሮ፣ ከዲን ቢሮ፣ ወይም ከሌላ በአቅራቢያ ካለ የሥራ ባልደረባ ድጋፍ መፈለግ። ድጋፉን የሚያደርግ ሰው ሲመጣ፣ አስተማሪው/ዋ ወይም ሌላ የሥራ ባልደረባ ተማሪው/ዋን ወደ የሚመለከተው ቢሮ ይወስዳሉ። ለትምህርት ቤቱ ኃላፊ ወይም ተወካይ ተማሪው/ዋ ከመማሪያ ክፍል እንዲወጣ የተደረገበትን ምክንያት መረጃ መስጠት።

2. ሌላ የሥራ ባልደረባ የመማሪያ ክፍለ ጊዜውን እንዲሸፍን ተደርጎ አስተማሪው/ዋ ተማሪው/ዋን ወደ ዋና ቢሮ ወይም የዲን ቢሮ በመውሰድ፣ ለትምህርት ቤቱ ኃላፊ ወይም ተወካይ ተማሪው/ዋ ከመማሪያ ክፍል እንዲወጣ/እንዲትወጣ የተደረገበትን ምክንያት መንገር።

3. ተማሪው/ዋ ወደ ዋና ቢሮ ወይም የዲን ቢሮ እንዲሄድ/እንዲትሄድ ይነገራል።ለአስቸኳይ ሁኔታዎች ካልተቻለ በስተቀር፣ አስተማሪው/ዋ ተማሪው/ዋ ከመማሪያ ክፍል እንዲወጣ/እንዲትወጣ የተደረገበትን ምክንያት የሚገልጽ ማስታወሻ በተማሪው/ዋ ለትምህርት ቤቱ ኃላፊ መላክ።

ተማሪው/ዋ ከመማሪያ ክፍል እንዲወጣ/እንዲትወጣ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ በ24 ሰዓት ውስጥ አስተማሪው/ዋ ተማሪው/ዋ ከመማሪያ ክፍል እንዲወጣ/እንዲትወጣ የተደረገበትን ምክንያት የሚገልጽ አጭር እና ግልጽ የሆነ ሀሳብ በጽሁፍ ለትምህርት ቤቱ ኃላፊ ወይም ተወካይ ያቀርባል/ታቀርባለች። የትምህርት ቤቱ ኃላፊ/ተወካይ ከአስተማሪው/ዋ ጋር በመሆን ክስተቱን፣ የተከተሉትን ሂደቶች፣ እና ተማሪው/ዋ ከመማሪያ ክፍል እንዲወጣ/እንዲትወጣ የተደረገበትን ምክንያት ይገመግማሉ።

**ለወላጅ/ለአሳዳጊ ማሳወቅ**

በተቻለ መጠን በአስቸኳይ አስተማሪው/ዋ ከመማሪያ ክፍል እንዲወጣ/እንዲትወጣ የተደረገውን/የተደረገችውን የተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ ጉዳዩን ማሳወቅ አለበት/አለባት። ይህም ሲደረግ ከየትኛው የመማሪያ ክፍል፣ ለምን ያህል ጊዜ፣ እና ምክንያቱ ምን እንደሆነ መገለጽ አለበት። ይህ ማስታወቂያ በጉዳዩ ላይ በወላጅ-መምህር ኅብረት ስብሰባ ላይ እንዲነጋገሩበት ለወላጆች አጋጣሚን ይፈጥራል። የተማሪው/ዋ ከመማሪያ ክፍል መውጣት ወደ የቅጣት እርምጃ የሚያመራም ከሆነ (ያም ለጊዜው ከትምህርት ቤት ማገድ ወይም ወደ ሌላ አማራጭ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት መላክ ከሆነ) ለተፈጠረው የመማሪያ ክፍል ምግባር ማጣት፣ ለተማሪው/ዋ ወላጅ/አሳዳጊ ሕጋዊ በሆነ እና በሕገ ደንቡ መሰረት ይገለጻል።

**ጊዜያዊ የመቆያ ሥፍራ ሂደቶች**

እያንዳንዱ/ዷ የትምህርት ቤት ኃላፊ ተማሪ ከመማሪያ ክፍል እንዲወጣ/እንዲትወጣ ሲደረግ/ሲትደርለአጭር ጊዜ የሚቆይበትን/የሚትቆይበትን ቦታ በትምህርት ቤት ውስጥ ሆኖ ተገቢው ቁጥጥር የሚደረግበት ክፍል ወይም ሌላ አመቺ ቦታ ማዘጋጀት አለበት/አለባት።

ተማሪው/ዋ ዋና ቢሮ ወይም የዲን ቢሮ ሲደርስ/ሲትደርስ፣ የትምህርት ቤቱ ኃላፊ ወይም ተወካይ ተማሪው/ዋ የተከሰተውን ጉዳይ በአጭሩ እንዲናገር ዕድል ይሰጣሉ። ተማሪው/ዋ ቢሮ ሲደርስ/ሲትደርስ፣ የትምህርት ቤቱ ኃላፊ ወይም ተወካይ ካልኖሩ፣ ተማሪው/ዋ ወደ ጊዜያዊ የተማሪ ማቆያ ክፍል/ቦታ ይወሰድና/ትወሰድና ኃላፊ ወይም ተወካይ በተቻለ መጠን እንደተመለሱ ተማሪው/ዋን እንዲያነጋግሩ ይሆናል።

በትምህርት ቤቱ ኃላፊ ወይም ተወካይ ውሳኔ መሰረት፣ በነዚህ አማራጭ የትምህርት ስፍራዎች የተማሪ ቁጥጥር ይኑር እንጂ፣ ተማሪው/ዋ ሌላ አግባብ ያለው ክፍል፣ መርሃ ግብር ወይም የትምህርት ሥፍራ እንዲሆን/እንዲትሆን ይደረጋል።

የአጭር ጊዜ መቆያ ሥፍራ እንዲቆዩ የተደረጉ ተማሪዎች ቁጥጥር ሥር መሆን አለባቸው። በመቆያ ሥፍራው ሲሆኑ፣ ተማሪዎች የትምህርት ነክ ጉዳዮችን እንዲፈጽሙ ይጠበቅባቸዋል። ከተቻለ፣ ተማሪዎች በመቆያ ሥፍራው የሚፈጽሙት ተግባር ከወጡበት የመማሪያ ክፍል የትምህርት ሥራ ወይም ከተማሪው/ዋ ጥሩ ምግባር ማጣት ጋር የተገኛኘ ጉዳይ መሆን አለበት።ተማሪ በጊዜያዊ የመቆያ ሥፍራ ሲሆን ጊዜው የመዝናኛ ወይም ነጻ ጊዜ መሆን የለበትም።

ብዙ ጊዜ፣ ተማሪ በጊዜያዊ የመቆያ ሥፍራ የሚቆየው እንዲወጣ ከተደረገው የመማሪያ ክፍል ክፍለ ጊዜ እስኪያልቅ ድረስ ነው። ተማሪው/ዋ ለቀጣዩ ክፍለ ጊዜ ወደ መደበኛ የመማሪያ ክፍሉ ከመመለሱ በፊት፣ የትምህርት ቤቱ ኃላፊ ተማሪውን/ዋን ዝግጁ መሆኑን/መሆኗን እና ምግባሩ/ምግባሯ መስተካከሉን ለማረጋገጥ ያነጋግራል/ታነጋግራለች። ተማሪው/ዋን ወደ መደበኛ መማሪያ ክፍል መመለስ አግባብ ሆኖ ካልተገኘ፣ የትምህርት ቤቱ ኃላፊ ተማሪው/ዋን ሌላ አማራጭ የማቆያ ሥፍራ ይፈልጋል/ትፈልጋለች።

**የምግባር እቅድ**

ተማሪው/ዋ ከመማሪያ ክፍል እንዲወጣ/እንዲትወጣ ሲደረግ፣ ኃላፊ ወይም ተወካይ ለተማሪው/ዋ የስነ ምግባር እቅድ መዘጋጀት እናዳለበት ይወስናሉ። የስነ ምግባር እቅዱ ንJK' በሚባለው ሕገ ደንብ መሰረት ለረባሽ ተማሪዎች የሚዘጋጅ የምግባር ማስተካኪያ እቅድ ጋር፣ አንድ ባይሆንም፣ ይመሳሰላል። የስነ ምግባር እቅድ የሚዘጋጀው አስተማሪ ተማሪው/ዋን ለሁለተኛ ጊዜ በመደበኛነት ከመማሪያ ክፍል ካስወጣ በኃላ መሆን አለበት።

**ለቀረው ሴሚስቴር በሙሉ ተማሪን ከመማሪያ ክፍል ማስወጣት**

ተማሪ ለሦስተኛ ጊዜ ከመማሪያ ክፍል እንዲወጣ ከተደረገና የጉዳዩ አግባብነት እና ሕጋዊነት በኃላፊ ከተረጋገጠ በኃላ፣ ተማሪው/ዋ ለቀረው ሴሚስቴር ከአስተማሪው/ዋ መማሪያ ክፍል እንዲታገድ ይደረጋል/ትደረጋለች። ኃላፊው/ዋ ተማሪው/ዋን አግባብ ባለው የትምህርት ሥፍራ የመመደብ ኃላፊነት አለበት/አለባት፤ ከተለያዩ ሁኔታዎች የተነሳ፣ ምደባው ተመሳሳይ ክፍል አይሆንም። በዚህ ጉዳይ የኃላፊው/ዋ ውሳኔ ለኃላፊው/ዋ ተቆጣጣሪ ቀርቦ ይታያል።

ተማሪው/ዋ በመደበኛነት ከመማሪያ ክፍሉ ከታገደ በኃላ፣ የሴሚስቴሩ ትምህርት ከተጀመረ በኃላ ተማሪው/ዋን ሌላ ክፍል ማስገባት የትምህርቱን ሂደት ሊረብሽ እንደሚችል ኃላፊ ከወሰነ፣ የተማሪው/ዋ የመመዝገብ ዕድል የመነመነ ነው።

**የኃላፊ ክለሳ**

ተማሪ በአስተማሪ ከመማሪያ ክፍል እንዲወጣ/እንዲትወጣ የሚደረገው/የሚትደረገው በዚህ ሕገ ደንብ እና ተገቢው የክፍለ ግዛት እና የፌዴራል ሕግ መሰረት አስፈላጊው መስፈርት ከተጠናቀቀ በኃላ ነው። በዚህ ሕገ ደንብ ውስጥ የአስተማሪዎች ተግባር በሙሉ፤ የግምገማ ሕገ ደንብን ጨምሮ በትምህርት ድስትሪክት ውስጥ በተቀመጡት ሕገ ደንቦች እና ሂደቶች መሰረት በአስተማሪ ተቆጣጣሪ አማካይነት ይገመገማሉ፣ ቁጥጥርም ይደረግባቸዋል።

በዓመቱ ውስጥ ከመማሪያ ክፍል የታገዱ የተማሪዎች ቁጥር መረጃ መያዝ ከኃላፊ ይጠበቃል። ይህ መረጃ ለማኅበረሰብ ይደርሳል። ይህንን መረጃ ሲተነትኑ የተለያዩ ሁኔታዎች ከግንዛቤ ውስጥ የሚገቡ ሆኖ፣ ከመማሪያ ክፍል ውስጥ የታገዱት የተማሪዎች ቁጥር ያልተለመደ እና ብዙ ከሆነ አሳሳቢ እና ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ይሆናል። ኃላፊው/ዋ ከአስተማሪዎች ጋር ቢያንስ በየዓመቱ ይህንን መረጃ ይከልሳሉ።

በየበላይ አለቃ ሞንተ ሙሴ (Monte C. Moses) መስከረም 11፣ 2000 ጸደቀ።

የተሻሻለው፤ ሴፕተምበር 10፣ 2012

## የተማሪዎችን መታገድ ወይም ማባረር (እና ሌሎች የዲሲፕሊን ጣልቃገብነቶች) (JKD-1)

(JKD-1)

**አጠቃላይ ግምቶች**

የትምህርት ቦርዱ ለተማሪዎች፣ ለወላጆች እና ለትምህርት ቤት አስተዳደር ከሕግ አንጻር በማየት ተማሪዎች ለጊዜው ከመማሪያ ክፍል የሚታገዱበትን ወይም ወደ ጊዜያዊ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት የሚወሰዱበትን እና ምዝገባን የሚከለከሉበት የሂደት መመሪያ በጽሁፍ ያቀርባል።የተማሪውን መጥፎ ስነምግባር ለመቅረፍ እና ለተማሪዎች እና ለሰራተኞች ደህንነቱ የተጠበቀ እና ደጋፊ የትምህርት አካባቢን ለመጠበቅ ተመጣጣኝ የዲሲፕሊን ጣልቃገብነቶች እና መዘዞች መተግበር አለባቸው።

ያለውን የሂደት መመሪያ በየጊዜው እንዲከልሱት እና፣ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም፣ ከዚህ ሕገ ደንብ ጋር የሚሄድ አዳዲስ ሂደቶችን በማውጣት ቦርዱ እንዲያጸድቅ እንዲያቀርቡለት ቦርዱ የበላይ አለቃው/ዋን ያዛል።

ቦርዱና ተወካዩ ተማሪን ለጊዜው ከትምህርት ቤት ከማስወጣት ወይም ከማገድ በፊት የሚከተሉትን ሁኔታዎች ከግምት ያስገቡ ይሆናል፤

1. የተማሪውን ዕድሜ፤
2. የተማሪውን የሥነ-ምግባር ታሪክ፤
3. ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች መስፈርት መሙላት፤
4. በተማሪው የተከሰተው የጉዳዩ ከባድነት፤
5. በማንኛውም ተማሪ ወይም ሰራተኛ ላይ የተደረገ ዛቻ፤
6. ቀላል እርምጃ ጉዳዩ የሚበቃ እንደሆነ ናቸው።

ዲስትሪክቱ አማራጭ መፍትሄዎች ተገቢ መሆናቸውን እና ተማሪውን ከትምህርት ቤት ማግለል የትምህርት አካባቢን ለመጠበቅ አስፈላጊ መሆኑን ካላወቀ በስተቀር ተማሪው ሊባረር ወይም ሊከለከል አይችልም።

ይህ ፖሊሲ ለሁሉም ተማሪዎች እና ቤተሰቦቻቸው በዲስትሪክቱ ድህረ ገጽ በኩል በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ መቅረብ አለበት።

### II. ከፕሪስኩል እስከ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች መባረር/መታገድ

ከቅድመ ትምህርት ቤት እስከ ሁለተኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች፣ ተማሪውን ከማገድ ወይም ከማባረሩ በፊት ዲስትሪክቱ የሚጠቀምባቸውን ማንኛውንም አማራጭ የስነምግባር እና የዲሲፕሊን ጣልቃገብነቶች መመዝገብ አለበት።በፕሪስኩል፣ በኪንደርጋርተን ፣ አንደኛ ክፍል ወይም ሁለተኛ ክፍል ላለ ተማሪ ከትምህርት ቤት ውጭ እገዳ ወይም መባረር ሊጣል የሚችለው

1. ተማሪው በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ፣ በትምህርት ቤት መኪና ወይም በትምህርት ቤት ስፖንሰር ባደረገው ተግባር ላይ፡ከድስትሪክቱ ፈቃድ ውጭ አደገኛ መሳሪያ መያዝን ያካትታል; ወይም

ሀ.-በC.R.S ላይ እንደተገለጸው የመድኃኒት ወይም ቁጥጥር የሚደረግበት ንጥረ ነገር መጠቀምን፣ ይዞታን ወይም ሽያጭን ያካትታል። § 18-18-102 (5); ወይም

ለ.በC.R.S ላይ እንደተገለጸው የመድኃኒት ወይም ቁጥጥር የሚደረግበት ንጥረ ነገር መጠቀምን፣ ይዞታን ወይም ሽያጭን ያካትታል። § 18-18-102 (5); ወይም

ሐ.የሌሎችን ጤና ወይም ደህንነት አደጋ ላይ ይጥላል; እና

2.. ተማሪውን ከትምህርት ቤቱ ህንጻ ውስጥ ማስወጣት አለመቻሉ ይህ ካልሆነ ሊወገድ የማይችል የደህንነት ስጋት እንደሚፈጥር ተወስኗል; እና

3.. በC.R.S § 22-33-106(1.2) እና ከዚህ በላይ በክፍል 1 የተገለጹት እያንዳንዳቸው ተማሪውን ከማገድ ወይም ከማባረር በፊት ለእያንዳንዱ ጉዳይ ግምት ውስጥ ይገባሉ።

**III. ለሁሉም ተማሪዎች ሌሎች የዲሲፕሊን ጣልቃገብነቶች**

1.ከትምህርት ቤት ውጭ መታገድ ወይም መባረር እና በሚመለከተው ህግ መሰረት፣ ርእሰመምህሩ ወይም የርእሰመምህሩ ተወካይ የተማሪውን እኩይ ተግባር ለመቅረፍ ያሉትን ጣልቃገብነቶች መጠቀም ሊያስቡ ይችላሉ። የእንደዚህ አይነት ጣልቃገብነቶች አጠቃቀም እንደየግለሰብ ሁኔታ እና ሁኔታ ይለያያል። እንደዚህ አይነት ጣልቃገብነቶች በርዕሰመምህሩ ወይም በርዕሰመምህሩ ተወካይ ብቻ መሆን አለባቸው እና በእነዚህ ብቻ ያልተገደቡ መሆን አለባቸው፡-

2እንደ ማገድ አማራጭ፣ ርእሰ መምህሩ ወይም የርእሰ መምህሩ ተወካይ ተማሪው ወላጁ/አሳዳጊው ከተማሪው ጋር ክፍል ውስጥ ከተከታተለ ርእሰመምህሩ ወይም የትምህርት ቤቱ ተወካይ በተማሪው መምህራን ፈቃድ ተማሪው ትምህርት ቤት እንዲቆይ ሊፈቅድለት ይችላል። የርእሰመምህር ተወካይ. ወላጅ/አሳዳጊ ካልተስማሙ ወይም ከተማሪው ጋር ክፍል ካልገቡ፣ተማሪው በሚመለከታቸው ደንቦች መሰረት መታገድ አለበት።

.ሀ. ይህ የመባረር ሂደት ከተጀመረ ወይም ሊጀመር ከሆነ ወይም ርእሰመምህሩ ወይም የርእሰመምህሩ ተወካይ የተማሪው በትምህርት ቤት መገኘት፣ ከወላጅ/አሳዳጊ ጋር ቢሆንም እንኳን፣ ስራውን የሚያናጋ እንደሆነ ከወሰነ ይህ ከታገደ አማራጭ መጠቀም አይቻልም። የትምህርት ቤቱን፣ የመማሪያ አካባቢን የሚጎዳ፣ ወይም ለተማሪዎች እና/ወይም የትምህርት ቤት ሰራተኞች አደገኛ እና ደህንነቱ ያልተጠበቀ አካባቢ መፍጠር።

የአቤቱታ ሂደት ጊዜ ከደረሰ፣ ወይም የተማሪው በትምህርት ቤት ውስጥ መገኘት አሳሳቢና አደገኛ ከሆነ፣ ኃላፊው ይህንን አማራጭ ሊያስቀር ይችላል።

ይህንን ሕገ ደንብ እና ተያያዥ ሂደቶችን ለማዘጋጀት እና ተማሪዎች ለጊዜው ከመማሪያ ክፍል የሚታገዱበት ወይም ወደ ጊዜያዊ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት የሚወሰዱበት መስፈርቶች፣ ለአንደኛ ደረጃ፣ ለመለስተኛ እና ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች እና በድስትሪክቱ ለአዲስ ተማሪዎች አንደ እንዲሰራጭ የበላይ አለቃው/ዋ ሁኔታዎችን ያመቻቻል/ታመቻቻለች። ይህ ሕገ ደንብ እና ተያያዥ ሕገ ደንቦች እና ተማሪን ለጊዜው ከመማሪያ ክፍል ማገድ ወይም ወደ ጊዜያዊ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት መውሰድ መስፈርቶች በድስትሪክቱ ትምህርት ቤቶች ሁሉ ውስጥ ይለጠፋሉ። በተጨማሪም፣ በዚህ ሕገ ደንብ እና በተያያዥ ሂደቶች ላይ ማንኛውም ዓይነት ዋና ለውጥ ከተደረገ፣ የተደረገው ለውጥ ለእያንዳንዱ ተማሪ ይሰራጫል፣ በሁሉም ትምህርት ቤቶች ውስጥም ይለጠፋል።

**የሥልጣን ተዋረድ**

**፤** ከመዋለ ሕጻናት እስከ ሁለተኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች፡- በቅድመ ትምህርት ቤት፣ በመዋለ ሕፃናት፣ አንደኛ ክፍል ወይም ሁለተኛ ክፍል ተማሪን ከሦስት (3) ላልበለጠ የትምህርት ቀናት የማገድ ሥልጣንን ቦርዱ ለርዕሰ መምህራን ወይም ርዕሳነ መምህራን ውክልና ይሰጣል። በሲ.አር.ኤስ. § 22-33-106.1(2)፣ ርእሰመምህሩ ወይም የርእሰመምህሩ ተወካይ የደህንነት ስጋትን ለመፍታት ረዘም ያለ የእገዳ ጊዜ አስፈላጊ መሆኑን ካልወሰኑ ወይም ተማሪው በC.R.S መሰረት እንዲባረር ካልመከረ በስተቀር።
§ 22-33-105(2)(ሐ)።

1. የትምህርት ቦርድ ለትምህርት ድስትሪክት ኃላፊዎች ወይም በኃላፊዎች በጽሁፍ ለተወከሉት ሰዎች በ §22-33-106(1), (1)(b) (1)(c), C.R.S. ውስጥ በተገለጸው መሰረት ለአምስት የትምህርት ቀን ላልበለጠ ጊዜ ፣ ወይም በ §22-33-106(1)(d) C.R.S. 10 (KKD-1-E ውስጥ በተገለጸው መሰረት ከአስር የትምህርት ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ተማሪን ከትምህርት ቤታቸው ለግዜው ማገድ እንዲችሉ ሥልጣን ይሰጣል።
2. 2. ለሶስተኛ ክፍል እና ለከፍተኛ ክፍል ተማሪዎች፡ ቦርዱ በC.R.S ላይ በተገለፀው መሰረት ተማሪን ከአምስት (5) ላልበለጠ ጊዜ የትምህርት ቀናት የማገድ ስልጣን ለርዕሰ መምህራን ወይም ለርዕሰ ማምህራን ተወካዮች ውክልና ይሰጣል። §22 33 106(1)(ሀ)፣ (1)(ለ)፣ (1)(ሐ) ወይም 1(ሠ)፣ ወይም ከአስር (10) ያልበለጠ የትምህርት ቀናት በሲ.አር.ኤስ. §22-33-106(1)(መ)፣ ወይም ተማሪው በC.R.S መሰረት እንዲባረር ለመምከር። §22-33-105(2)(ሐ)።

3. የትምህርት ቦርድ ለትምህርት ቤቶች የበላይ አለቃ በ §22-33-105 C.R.S. ውስጥ በተገለጸው መሰረት ለተጨማሪ አሥር የትምህርት ቀናት ፣ እና በተጨማሪም፣ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ፣ በ §22-33-105(b) C.R.S. ውስጥ በተገለጸው መሰረት ለሌላ ተጨማሪ አሥር የትምህርት ቀናት ተማሪን ከትምህርት ማገድ እንዲችል/እንዲትችል ሥልጣን ይሰጣል። ጠቅላላ የከትምህርት እገዳ ጊዜ ከሃያ አምስት የትምህርት ቀናት በላይ መሆን የለበትም። ለሌሎች ተማሪዎች ሰላም እና ደኅንነት እና ለትምህርት ቤት አከባቢ አስጊ የሆነን የምግባር ችግር ለመቅረፍ ድስትሪክቱ የተማሪን ከትምህርት ቤት ለጊዜው መታገድ ሁኔታ አስመልክቶ አዲስ መረጃ ካገኘ ምርመራውን እንደገና የማካሄድ እና አስፈላጊውን አግባብ ያለው እርምጃ የመውሰድ ሙብት አለው። እንደዚህ ያሉ የእንደገና ምርመራ ሁኔታዎች ሂደቶች ባሉት መስፈርቶች መሰረት ይካሄዳሉ።

4. . የሌሎች ተማሪዎችን ደህንነት እና ደህንነት የሚቃወሙ የስነምግባር እና የስነምግባር ችግሮችን ለመፍታት ዲስትሪክቱ አዲስ የተገኘ መረጃ ወይም ማስረጃ ከተገኘ የእገዳውን ምርመራ እንደገና የመክፈት እና የመውሰድ ሙብቱ የተጠበቀ ነው። ማንኛውም እርምጃ ተገቢ ነው. ማንኛቸውም እንደዚህ ዓይነት ዳግም መክፈት ለሥርዓታዊ የፍትህ ሂደት መስፈርቶች ተገዢ ነው።

5. የትምህርት ቦርድ ለትምህርት ቤቶች የበላይ አለቃ በ §22-33-105 C.R.S. ውስጥ በተገለጸው መሰረት ተማሪን ምዝገባ የመከልከል ሥልጣን፣ ወይም በ ሪዕስ 22፣ አንቀጽ 33 በኮሎራዶ ክፍለ ግዛት በተሻሻለው ሕገ ደንብ ውስጥ በተገለጸው ውስንነት መሰረት፣ ተማሪን ለአንድ አመት የትምህርት ዘመን ላልበለጠ ጊዜ ከትምህርት የማገድ ሥልጣን ይሰጣል፤ እና የቦርድ ፖሊሲ ለምዝገባ ብቁ ያልሆኑትን ወይም በድስትሪክቱ የህዝብ ትምህርት ቤቶች መቀጠል የማይችሉትን ተማሪዎች ሁኔታ ውሳኔ ይሰጣል።

ለሕገ ወጥ የወሲብ ምግባር ወይም ለወንጀል /ለሁከት ድርጊት ተማሪን ወደ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት መውሰድ

ዕድሜያቸው ከ12-18 ዓመት የሆኑ ተማሪዎች በሕገ ወጥ የወሲብ ምግባር ምክንያት በ 18-3-411 C.R.S. ውስጥ በተወሰነው መሰረት በፍርድ ቤት ከተከሰሱ፣ ወይም በወንጀል ድርጊት/ሁከት በ16-11-309 C.R.S. ውስጥ በተወሰነው መሰረት፣ ድርጊቱ በአዋቂ ከተፈጸመ፣ መሠረታዊ የመለያ መረጃ፣ በክፍለ ግዛት ሕግ ውስጥ በተወሰነው መሰረት፣ ከተጠርጣሪው የወንጀል ድርጊት ዝርዝር መግለጫ ጋር፣ ተማሪው በተመዘገበበት የትምህርት ድስትሪክት በአስቸኳይ እንዲቀርብ ሕግ ያዛል።

የተማሪው/ዋ ምግባር ለሌሎች ተማሪዎች ሰላም እና ደኅንነት፣ እና ሞራል(ግብረ ገብ) ወይም ለትምህርት ቤት አስተዳደር አስጊ መሆኑን እና ተማሪው/ዋን በትምህርት ቤቱ ትምህርት እንዲቀጥል መፍቀድ የመማሪያ ቦታን የሚረብሽ መሆኑን፣ ለሌሎች ተማሪዎች መጥፎ አርዓያን የሚፈጥር መሆኑን፣ ወይም ለተማሪዎች፣ ለአስተማሪዎች፣ እና ለሎች የትምህርት ቤቱ አስተዳደር አደገኛ እና ጎጂ መሆኑን ለመወሰን መረጃው በትምህርት ቦርድ ወይም በተወካዩ ይፈለጋል። ቦርዱ በተማሪ ሥነ-ምግባር ደንብ እና በተያያዥ ፖሊሲዎች መሰረት ተማሪን ለጊዜው ከትምህርት ማገድ ወይም ወደ አማራጭ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት መውሰድ ሊያካትት የሚችል አግባብ ያላቸወ የቅጣት እርምጃዎችን ይወስዳል።

በክፍለ ግዛት ሕግ ውስጥ የተገለጸውን የድስትሪክቱ ለተማሪ አማራጭ የትምህርት መርሃ ግብር የማቅረብ ኃላፊነት መሰረት ለተማሪው/ዋ አማራጭ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት ለመወሰን ቦርዱ የፍርድ ቤቱ ሂደት ማጠቃለያ ድረስ ለመጠበቅ ሊወስን ይችላል።

**ዓመታዊ ሪፖርቶች**

በሥነ ምግባር ችግር ወይም የከትባት ወረቀት ባለማምጣት ምክንያቶች ከድስትሪክቱ ትምህርት ቤቶች የታገዱትን የተማሪዎች ቁጥር መረጃ ቦርዱ ለክፍለ ግዛት የትምህርት ቦርድ በየዓመቱ ያቀርባል። ከትምህርት ቤት የታገዱ የተማሪዎች ቁጥር ትምህርት ቤትን ወይም ድስትሪክትን ከለቀቁ የተማሪዎች ቁጥር ጋር አይጨመርም።

**ለወላጆች የሚሰጥ መረጃ**

ተማሪ ከትምህርት ቤት ሲታገድ/ሲትታገድ፣ በእገዳው ጊዜ ለተማሪው/ዋ ያሉትን የትምህርት አማራጮች፣ ወላጅ/አሳዳጊ በእገዳው ጊዜ ድስትሪክቱ ለተማሪው/ዋ አስፈላጊውን አገልግሎቶች እንዲሰጥ የመጠየቅ ሙብት ጨምሮ፣ የድስትሪክት አስተዳዳሪ ለተማሪው/ዋ ወላጅ ወይም አሳዳጊ ተገቢውን መረጃ ይሰጣል። ወላጅ/አሳዳጊ የቤት ትምህርት መርሃ ግብር ለተማሪው/ዋ እንዲሰጥ ከመረጠ፣ ወላጅ/አሳዳጊ ለተማሪው/ዋ ተገቢውን ሥርዓት ትምህርት ከድስትሪክት አስተዳደር ሊጠይቅ ይችላል።

ተማሪው/ዋ ከትምህርት ቤት የታገደው/የታገደችው ዓመቱን በሙሉ ከሆነ እና ከድስትሪክት የትምህርት አገልግሎት የማይሰጠው/የማይሰጣት ከሆነ፣ የትምህርት ድስትሪክት ከትምህርት ቤት የታገደውን/የታገደችውን የተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ እስከ ቀጣዩ የትምህርት ዘመን ድረስ ቢያንስ በየ60 ቀናት እያገኛቸው ተማሪው/ዋ ከሌላ ቦታ የትምህርት አገልግሎት እያገኘ/ች መሆኑን/መሆኗን ለማረጋገጥ ይጠይቃል።

፤ ሥራ ላይ የዋለው፤ ኖቨምበር 8፣ 2004

በቅርብ የተሻሻለው፤ኦገስት 13 2012
የአሁኑ ድሰምበር 11፤2023
ሕጋዊ ዋቢዎች፡ C.R.S. 16-11-309 (የሁከት ወንጀል)
C.R.S. 18-3-411 (ሕገ ወጥ የወሲብ ድርጊት)
C.R.S. 22-32-109.1 (2)(a) (የሥነ ምግባር ሕገ ደንብ ሥራ ላይ ማዋል እና መቆጣጠር)
C.R.S. 22-32-109.1 (2)(a)(I)(E) (ደኅንነታቸው ለተጠበቁ ትምህርት ቤቶች የሚያስፈልግ ፖሊሲ)
C.R.S. 22-32-109.1(3) (ከክፍለ ግዛት ተቋማት/ድርጅቶች ጋር መስማማት)
C.R.S. 22-33-106(ተማሪን ለጊዜው ከትምህርት ማገድ፣ ወደ አማራጭ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት መውሰድ እና አለመቀበል)C.R.S. § 22-33-106.1 (ከቅድመ ትምህርት እስከ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች መታገድ እና መባረር)
R.S § 22-33-106.5 (ፍርድ ቤቶች በተማሪዎች የተፈጸሙ አንዳንድ ጥፋቶችን ለት / ቤት ዲስትሪክቶች ማሳወቅ አለባቸው)

C.R.S.. § 24-10-106.3 (የክሌር ዴቪስ ትምህርት ቤት ደህንነት ህግ)
C.R.S. 22-33-106.5 (በተማሪዎች ስለሚፈጸሙ የወንጀል ድርጊቶች መረጃ)
C.R.S. 22-33-107 (የግዴታ የተማሪ የትምህርት ክትትል ሕግ)
C.R.S. 22-33-107.5 (ትምህርት ባለመከታተል ምክንያት የሚሰጥ የማሳሰቢያ ጽሁፍ)
C.R.S. 22-33-108 (የወጣቶች የፍርድ ቤት ሂደቶች)
C.R.S. 25-4-903(1) (ክትባት)

## ተማሪዎችን ለጊዜው ከትምህርት ማገድ ወይም ወደ አማራጭ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት መውሰድ (JKD-1-R)

### ሀ. የ10 ቀናት ወይም የከዚያ በታች ተማሪን ከትምህርት ቤት የማገድ ሂደት

የትምህርት ቦርድ ለማንኛውም የትምህርት ቤት ኃላፊ አምስት ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ተማሪን ከትምህርት የማገድ ሥልጣን እንዳለው/እንዳላት በጽሁፍ በጸደቀ ፖሊሲ ውስጥ አስቀምጧል። የበላይ አለቃው/ዋ ለተጨማሪ ቀናት ተማሪን ከትምህርት የማገድ ሥልጣን አለው/አላት። (ተያያዥ ፖሊሲን ይመልከቱ)

በሥነ-ምግባር ችግር ምክንያት ተማሪን ከትምህርት ማገድ አስመልክቶ የትምህርት ቤት አስተዳደር ቀጥሎ የተሰጡትን ሂደቶች መከተል አለባቸው። የትምህርት ቤት አስተዳደር ሲባል እንደ ሁኔታው ኃላፊ ወይም ተወካይ፣ የበላይ አለቃ ወይም የትምህርት ቦርድ ሊሆን ይችላል።

1. **ማሳሰቢያ፡** ድርጊቱን ለፈጸመ/ች ተማሪ እንዲያሰላስል/እንዲታሰላስል ስለ ድርጊቱ አንዳንድ ነጥቦች ይሰጡታል/ይሰጧታል።

2. **የማሳሰቢያ ይዘቶች፡** ማሳሰቢያው ቀጥሎ የተሰጡትን መሰረታዊ መረጃዎች መያዝ አለበት፡

   ሀ. ተማሪው/ዋ የተከሰሰበት የድርጊት መግለጫ
   ለ. የክሱ መሰረት/መነሻ መግለጫ። የምስክሮችን ስም መደበቅ ካስፈለገ፣ ስሞች አይገለጹም።

   ይህ መረጃ እንደ መደበኛ ሆኖ የሚሰራጭ ሳይሆን ለተማሪው/ዋ ስለ ድርጊቱ በቂ መረጃ ለመስጠት ነው።

3. **መደበኛ ያልሆነ የችሎት አቤቱታ**

   ሀ. በመማሪያ ክፍል ውስጥ ስለሆነ ረብሻ ወይም ስለተከሰተው የሥነ ምግባር ችግር አስመልክቶተማሪው/ዋ የራሱን/የራሷን ሀሳብ እንዲገልጽ/እንዲትገልጽ ዕድል ይሰጠዋል/ይሰጣታል።

   ለተማሪው/ዋ የተከሰሰበትን/የተከሰሰችበትን ጉዳይ እንዲያምን/እንዲታምን ወይም እንዲክድ/እንዲትክድ ዕድል ይሰጠዋል/ይሰጣታል።

   ሐ. ያሉት እውነታዎች ሲጋጩ፣ የቅጣት እርምጃ ከመውሰዳቸው በፊት የትምህርት ቤት አስተዳደሮች ሁኔታውን ያጣራሉ።

4. **ጊዜ፤** ተማሪን ከትምህርት ቤት ከማገድ በፊት ማሳሰቢያው እና መደበኛ ያልሆነ የችሎት አቤቱታ ይቀድማሉ። ማሳሰቢያ የተሰጠበት እና የአቤቱታ ጊዜ መሃል ዘግይታ መኖር የለበትም።

5. **የተማሪው/ዋ ትምህርት ቤት ውስጥ መሆን አሳሳቢ/አደገኛ ጉዳይ የሚፈጥር ከሆነ፤** የተማሪው/ዋ ትምህርት ቤት ውስጥ መቆየት በሰዎች እና በንብረቶች ላይ፣ እንደዚሁም በመማር ማስተማር ሂደት ላይ አደጋን የሚፈጥር ከሆነ ማሳሰቢያው እና የአቤቱታው ሂደት ይቀርና ተማሪው/ዋ ከትምህርት ቤት እንዲታገድ/እንዲትታገድ ይደረጋል። ጉዳዩም በአስቸኳይ ትኩረት ይሰጥበታል።

6. **ተማሪን ከትምህርት ለጊዜው ካገዱ በኃላ ጉዳዩን ማሳወቅ፤** ተማሪ ከትምህርት ካታገደ/ች፣ ጉዳዩን የፈጸመው ኃላፊ በአስቸኳይ ተማሪው/ዋ ከትምህርት መታገዱን/መታገዷን፣ ምክንያቱን እና የጊዜ ገደቡ ለወላጅ፣ ለአሳዳጊ፣ ወይም ለሕጋዊ ጠባቂ ያሳውቃል። ማሳሰቢያው ወላጅ፣ አሳዳጊ፣ ወይም ሕጋዊ ጠባቂ ጉዳዩን ከፈጸመው ኃላፊ ጋር ተገናኝተው ስለጉዳዩ መነጋገር የሚችሉበትን ጊዜ እና ቦታ ያካትታል።

7. **ተማሪን ከትምህርት ቤት ማገድ፤** ከትምህርት የታገደ ተማሪ ከወላጅ፣ ከአሳዳጊ፣ ወይም ከሕጋዊ ጠባቂ እና ከኃላፊ ጋር ከተረጋገጠ እና ከተወሰነ በኃላ በአስቸኳይ የትምህርት ቤትን ቅጥር ግቢ መልቀቅ አለበት/አለባት፤ይህ ደግሞ ከትምህርት የታገደውን/የታገደችውን ተማሪ በወላጅ፣ በአሳዳጊ፣ ወይም በሕጋዊ ጠባቂ ቁጥጥር ሥር የሚደረጉበት አማራጭ መንገድ ነው።

   ከትምህርት እገዳ እንደ አማራጭ፣ በኃላፊ ወይም በተወካይ ለተወሰነ ጊዜ ወላጅ ከተማሪ ጋር መማሪያ ክፍል ውስጥ መሆን ከፈለጉ፣ ኃላፊ ወይም ተወካይ ተማሪን ከትምህርት ከማገድ ይልቅ ይህንን መፍቀድ ይችላል/ትችላለች። ወላጅ ይህንን ማድረግ ካልቻለ፣ ተማሪው/ዋ በነዚህ ሕገ ደንቦች መሰረት ከትምህርት ይታገዳል/ትታገዳለች። ተማሪን ወደ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት የመውሰድ ሂደት ከተጀመረ ወይም ሊጀመር ከሆነ እና ከወላጅ ጋርም ቢሆን የተማሪው/ዋ በትምህርት ቤት መገኘት ሁከትን ሊፈጥር እንደሚችል ኃላፊ ወይም ተወካይ ካመነበት/ካመነችበት፣ ይህ ተማሪን ከትምህርት ቤት የማገድ አማራጩ፣ ከወላጅ ጋር መማሪያ ክፍል ውስጥ የመሆን ሁኔታ፣ ይቀራል።

8. **ተማሪን እንደገና መቀበል፤** ከወላጅ፣ ከአሳዳጊ ወይም ከሕጋዊ ጠባቂ ጋር ስብሰባ እስኪደረግ ድረስ፣ ወይም እንደ ኃላፊው አስተያየት ወላጅ፣ አሳዳጊ፣ ወይም ሕጋዊ ጠባቂ ስለ እገዳው ለመወያየት መስማማታቸው እስኪረጋገጥ ድረስ ተማሪን ወደ ትምህርት ቤት መመለስ አይቻልም። የተማሪው/ዋን የወደፊት የሥነ ምግባር ችግር ለመከልከል ስብሰባው አማራጭ የሥነ ምግባር እቅዶችን ማካተት አለበት። ነገር ግን፣ እገዳውን የፈጸመው ኃላፊ ለወላጅ፣ ለአሳዳጊ፣ ወይም ለሕጋዊ ጠባቂ ማሳወቅ ካልቻለ ወይም ወላጅ፣ አሳዳጊ፣ ወይም ሕጋዊ ጠባቂ በስብሰባው ላይ በተከታታይ መገኘት ካልቻሉ፣ እገዳውን ያካሄደው ኃላፊ ተማሪው/ዋን ወደ ትምህርት ቤት ሊመልስ ይችላል። ከትምህርት ቤት ከታገደ/ች በኃላ እስከተቻለ ድረስ በአስቸኳይ አቤቱታ የሚሰማበት አስቸኳይ ሁኔታ ካልተፈጠረ በስተቀር፣ አሥር ቀናት ወይም ከዚያ በታች ለሆነ ጊዜ ከትምህርት ቤት የታገደ/ች ተማሪ ከመታገዱ በፊት መደበኛ ያልሆነ አቤቱታ እንዲያቀርብ/እንዲታቀርብ ይደረጋል። ከአሥር ቀናት በላይ ከትምህርት ቤት የታገደ/ች ማንኛውም ተማሪ አግባብ ባለው የትምህርት ድስትሪክት ኃላፊ ፍት ለፊት የእገዳው ሁኔታ እንዲከለስ እንዲጠይቅ/እንዲትጠይቅ ዕድል ይሰጠዋል/ይሰጣታል።

   እገዳውን ያካሄዱ ኃላፊዎች፡

   ሀ. በእገዳው ወቅት ከተማሪው/ዋ ወላጅ፣ አሳዳጊ፣ ወይም ሕጋዊ ጠባቂ ጋር ለመገናኘት አስፈላጊውን ጥረት ማድረግ አለባቸው፤

ለ. እገዳውን ያካሄዱ ኃላፊዎች ከወላጅ፣ ከአሳዳጊ፣ ወይም ከሕጋዊ ጠባቂ ጋር መገናኘት ስላልቻሉ የእገዳውን ጊዜ ማራዘም የለባቸውም፤

ሐ. በእገዳው ጊዜ ያመለጣቸውን የትምህርት ክፍለ ጊዜያትን እንዲያካክሱ ዕድል መስጠት አለባቸው። የክለሳው ዓላማ ተማሪዎች የተዘጋጀውን የድስትሪክቱን የትምህርት መርሃ ግብር እንዲያገኙ ሲሆን፣ የትምህርት ድስትሪክቱ በእገዳው ጊዜ የባከነውን እና መሸፈን ያለበትን የትምህርት ክፍለ ጊዜ ይወስናል። ለተማሪዎቹም ለሚያደርጉት የክለሳ ሥራ ሙሉ ወይም ከፊል የትምህርት ውጤት ይሰጣቸዋል።

**ለ. *ወደ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት የመውሰድ ወይም ወደ ትምህርት ቤት መመለስን የመከልከል ሂደት***

የበላይ አለቃው/ዋ ማንኛውንም ተማሪ ወይም ወደ ፊት ሊመዘገቡ ካሉት ተማሪዎች ወደ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት ለመላክ ወይም ወደ ትምህርት ቤት መመለስን ለመከልከል ሲወስን/ሲትወስን፣ ከታች ያሉት ሂደቶች መከተል አለበት/አለባት፡

1. ***ማሳሰቢያ፤*** የትምህርት ቦርድ ወይም የድስትሪክቱ አስተዳደር የዚህን እቅድ ተግባር በጽሁፍ ለተማሪው/ዋ ወላጅ/አሳዳጊ እቅዱ ከመተግበሩ በፊት ከ5 ቀናት ባላነሰ ጊዜ ውስጥ ማሳወቅ አለበት።ይህም የሚካሄደው ሰነድ ላይ ባለው የተማሪውን ወይም የተማሪውን ወላጅ/አሳዳጊ አድራሻ በመጠቀም በዩናይትድ ስቴትስ ፖስታ በመላክ ነው።

2. ***አስቸኳይ/ድንገተኛ ማሳሰቢያ፤*** አስቸኳይ ሁኔታ ሲፈጠር እና የአጭር ጊዜ መልዕክት ሲያስፈልግ፣ ተማሪው/ዋ የተማሪው/ዋ ወላጅ/አሳዳጊ አስቀድሞ የአቤቱታ ማቅረቢያ ማስታወሻ ካላቸው፣ የማስታወሻውው ጊዜ ያጥራል።

3. ***የማሳሰቢያ ይዘቶች፤*** ማስታወሻው የሚከተሉትን መሰረታዊ መረጃዎችን ይይዛል፡
   ሀ. ተማሪው/ዋ ወደ አማራጭ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት የተወሰደበት/የተወሰደችበት ወይም ወደ ትምህርት ቤት መመለስ የተከለከለበትን/የተከለከለችበትን ዋና ምክንያት መግለጫ።
   ለ. ተማሪው/ዋ ወደ አማራጭ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት የተወሰደበት/የተወሰደችበት ወይም ወደ ትምህርት ቤት መመለስ የተከለከለበትን/የተከለከለችበትን ጉዳይ በተመለከተ የሚቀርበውን አቤቱታ የመስማት ሁኔታ መግለጫ።
   ሐ. የተጠየቀው አቤቱታ የሚሰማበት ቀን፣ ጊዜ እና ቦታ መግለጫ።
   መ. ተማሪው/ዋ በአቤቱታ ማቅረቢያው ቦታ ተገኝቶ/ታ በእርሱ/ሷ ላይ የሚነሳውን ሃሳብ አስመልክቶ ተገቢውን ምላሽ እንዲሰጥ/እንዲትሰጥ፣ እና ተማሪው/ዋ ከወላጅ/አሳዳጊ እና ከጠበቃው/ዋ ጋር መሆን እና መወከል መቻል መግለጫ።
   ሠ. በአቤቱታ ማቅረቢያው ሂደት አለመሳተፍ ተያያዥ መብቶችን ማጣት የሚገልጽ መግለጫ።

4. ***የክለሳ ሥነ-ምግባር፤*** አቤቱታ ማቅረብ በወላጅ/በአሳዳጊ መጠየቅ ይችላል። ወደ ጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት መውሰድ/ትምህርት ቤት መከልከል አቤቱታ በድስትሪክቱ የአቤቱታ ሰሚ ኃላፊ መካሄድ አለበት። ችሎቱ ዝግ መሆን አለበት፣ በችሎቱ ላይ የሚገኙ የትምህርት ቤት ኃላፊዎች፣ ተማሪው/ዋ፣ ወላጁ/ጇ ወይም አሳዳጊው/ዋ፣ ወይም ሕጋዊ ጠባቂው/ዋ፣ እና ሌሎች፣ ለምሳሌ ተማሪው/ዋ ወይም ወላጅ፣ አሳዳጊ፣ ወይም ሕጋዊ ጠባቂ እንዲገኝ የሚፈልጉ ጠበቃ በችሎቱ ላይ መገኘት ይችላል/ትችላለች። የተጠርጣሪው/ዋ መረጃ የሚቀርበው በትምህርት ቤቱ ነው። ምስክር እና መረጃ የሚቀርበው በመሃላ ነው። ተማሪው/ዋ ክስተቱን እና ተገቢውን መረጃ ያቀርባል/ታቀርባለች። የምስክርነት ሙያዊ ሕገ ደንቦች ሥራ ላይ አይውሉም፣ እና የችሎቱ ኃላፊ አግባብ አለው የሚለውን/የሚትለውን መረጃ ወይም ማስረጃ ሊወስድ/ሊትወስድ ይችላል/ትችላለች። የተማሪው/ዋ የጽሁፍ መግለጫ ካለ፣ ሕጋዊ በሆነ መንገድ እንደ ማስረጃ ሊቀርብ ይችላል።ተማሪው/ዋ ወይም የተማሪው/ዋ ተወካይ መረጃ ይሚያቀበውን ግለሰብ ጥያቄ መጠየቅ ይችላሉ።

   የችሎቱ ሂደት በተገቢው ሰነድ ተይዞ ትራንስክሪፕት ሲፈለግ ለሚመለከተው አካል ይሰጣል። የትራንስክርፕቱ ዝግጅት ወጪ የጠያቂው አካል ይሆናል።

   ተማሪን ወደ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት መላክ በተመለከተ የችሎቱ ኃላፊ ያገኛቸውን እውነታዎችን ከአስተያየት ጋር ለየበላይ አለቃ ያስተላልፋል። የበላይ አለቃው/ዋ የችሎቱ ኃላፊ ግኝቶችን እና አስተያየት በመከለስ ችሎቱ ከተካሄደበት ቀን አንስቶ በአምስት ቀናት ውስጥ ውሳኔው/ዋን በጽሁፍ ያሳውቃል/ታሳውቃለች።

5. ***ይግባኝ መጠየቅ፤*** ከየበላይ አለቃው ውሳኔ በኃላ፣ ተማሪው/ዋ በ10 የትምህርት ቀናት ውስጥ ለትምህርት ቦርድ ስለተሰጠው ውሳኔ ይግባኝ ማለት ይችላል/ትችላለች። ተማሪው/ዋ ይህንን በ10 ቀናት ውስጥ ካላደረገ/ች፣ መብቱ/ቷን አልተጠቀመም/አልተጠቀመችም፤ የበላይ አለቃው/ዋ ውሳኔም ይጸናል።

   ይግባኝ በተገቢው ሁኔታ ከተጠየቀ፣ ቦርዱ የተማሪው/ዋን ወደ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት መላክ ሰነድን ይከልሳል። ሰነዱ ለጊዜው ከትምህርት መከልከል እና መታገድ፣ የምስክርነቱ ትራንስክርፕት፣ የችሎቱ ትርዓኢት ካለ፣ የችሎቱ ኃላፊ ግኝቶች እና አስተያየት፣ የችሎቱ ኃላፊ የጽሁፍ ውሳኔ፣ እና ስለ ከትምህርት እገዳው ሌሎች ሰነዶች የሚመለከት ማስታወሻዎች እና ሌሎች ሰነዶችን ያካትታል። በይግባኙ ጊዜ ተማሪው/ዋ የሕግ አማካሪን ሊወክል ይችላል/ትችላለች። የድስትሪክቱ እና የወላጆች ተወካይ የቦርዱን አጭር መግለጫ ሊሰጡ ይችላሉ፣ ነገር ግን፣ በይግባኙ ጊዜ በአሳማኝ ሁኔታ ካልተገኘ በስተቀር፣ አዲስ ማስረጃ/መረጃ አይቀርብም። የቦርዱ አባላት በሰነዱ ውስጥ ግልጽ ያልሆነ ነገር ካለ መጠየቅ ይችላሉ።

   የተማሪው/ዋ ወደ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት መላክ አስመልክቶ ቦርዱ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፤ ተማሪው/ዋን እና የተማሪው/ዋ ወላጅ/አሳዳጊ የሕጋዊ ክለሳ መብት እንዳላቸውም ያሳውቃል።

6. ***ለወላጆች የሚሰጥ መረጃ፤*** ተማሪ ከትምህርት ሲታገድ፣ የድስትሪክት አስተዳደር በድስትሪክቱ የሚሰጡትን አገልግሎቶች ጨምሮ፣ በእገዳው ወቅት ለተማሪው/ዋ ያሉትን የትምህርት አማራጮች መረጃ ለተማሪው/ዋ ወላጅ/አሳዳጊ ይሰጣል። ወላጅ/አሳዳጊ ለተማሪ የቤት ውስጥ የትምህርት መርሃ ግብር መስጠት ከመረጡ እና ይህን በተመለከተ ድጋፍ ከጠየቁ፣ የድስትሪክት አስተዳደር ተማሪው/ዋ ተገቢውን ሥርዓተ ትምህርት እንዲያገኝ ለወላጅ/ለአሳዳጊ ድጋፍ ሊያደርግ ይችላል።

   ለቀሪው የትምህርት ዘመን በሙሉ ተማሪው/ዋ ከትምህርት ከታገደ/ች፣ እስከ የሚቀጥለው ዓመት መጀመሪያ ድረስ ተማሪው/ዋ የትምህርት አገልግሎቶችን እያገኘ/ች መሆኑን ለማረጋገጥ፣ የትምህርት ድስትሪክት የተማሪው/ዋን ወላጅ በየ60 ቀናት እየደወለ ይጠይቃል። ተማሪው/ዋ በሌላ የትምህርት ድስትሪክት፣ በግል ወይም በሌላ ትምህርት ቤት ከተመዘገበ/ች በኃላ፣ ወይም ለህዝብ አገልግሎት ክፍል የሚሰራ ከሆነ ወይም ከታሰረ/ቁጥጥር ሥር ከሆነ፣ የድስትሪክት አስተዳደር ከወላጅ/ከአሳዳጊ ጋር መገናኘትን ያቆማል።

7. ***ወደ ትምህርት ቤት መመለስ፤*** በክፍለ ግዛት ሕግ መሰረት፣ ከትምህርት የታገደው/የታገደችዋ ተማሪ ተጠቂው/ዋ ወይም የድርጊቱ ሰለባ ወይም የቅርብ ቤተሰብ በተመዘገበበት ወይም በሚሰራበት ትምህርት ቤት ተመልሶ ሊገባ አይችልም/አትችልም። ይህም የሚሆነው፡

   ሀ. ከትምህርት የታገደው/የታገደችዋ ተማሪ በጥፋተኝነት ከተፈረደበት/ከተፈረደባት፣ ከትምህርት ሊታገደበት/ሊታገደችበት ምክንያት በልጆች የወንጀል ቅጣት የተዳኘ/ች ከሆነ፣ ሌላ ፍርድ ያገኘ/ች ከሆነ ወይም በሌላ ተመሳሳይ መርሃ ግብር ውስጥ

የታቀፈ/ች ከሆነ፤

ለ. የተጠቂው/የድርጊቱ ሰለባ ግልጽ የሆነ የወንጀል ድርጊት ካለ፤ እና

ሐ. ተማሪው/ዋ የተባረረበት/የተባረረችበት ወንጀል ለንብረት የማያሰጋ ከሆነ።
መ. ድስትሪክቱ የተጠቂውን ስም ከለለው፣ ጉዳዩ የሚካሄደው በተጠቂው ወይም በተጠቂው የቅርብ ዘመድ ጥያቄ መሰረት ነው።
የንብረት ወንጀል ከሆነ ግን ይህ ጉዳይ አይካሄድም።

ድስትሪክቱ የተጠቂው/ዋን ትክክለኛ ስም የማያውቅ ከሆነ፣ መስፈርቱ ሥራ ላይ የሚውለው ተጠቂው/ዋ ወይም የተጠቂው/ዋ የቅርብ ቤተሰብ ሲጠይቁ ነው። ተማሪው/ዋ ከትምህርት የታገደበት/የታገደችበት የወንጀል ድርጊት ለንብረት የሚያሰጋ ከሆነ፣ ይህ መስፈርት ሥራ ላይ አይውልም።

**ሐ. በሁከት ወንጀሎች ወይም በሕገ ወጥ የወሲብ ምግባር ከትምህርት መታገድ ሂደት**

ተማሪ በድስትሪክት ፍርድ ቤት ወይም በሌላ በሁከት ወንጀል ወይም በክፍለ ግዛት ውስጥ በተወሰኑ ሥያሜዎች መሰረት በሕገ ወጥ የወሲብ ምግባር መከሰሱ/ሷን ድስትሪክት መረጃ ሲደርሰው የሚከተሉት ሂደቶች ሥራ ላይ ይውላሉ፡፡

1. በሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ በመሞርከዝ፣ ቦርዱ ወይም ተወካይ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት መላክን በተመለከተ አቤቱታ መኖሩን የቅድሚያ ውሳኔ ያደርጋል።

   ሀ. ተማሪው/ዋ ለሌሎች ተማሪዎች፣ ወይም ለትምህርት ቤት አስተዳደር ሰላም እና ደኅንነት አስጊ የሆነ ምግባር የሚያሳይ/የሚታሳይ መሆኑ/ኗን።

   ለ. ተማሪው/ዋን በትምህርት ቤቱ ውስጥ ማስተማር የመማሪያ አከባቢውን የሚያውክ መሆኑን፣ ለሌሎች ተማሪዎች መጥፎ ምሳሌ መሆኑን ወይም ለተማሪዎች፣ ለአስተማሪዎች እና ለሌሎች የትምህርት ቤት አስተዳደሮች አደገኛ እና ጎጂ ሁኔታን መፍጠሩን።

2. በክፍለ ግዛት በተፈቀደው ደረጃ መጠን፣ ውሳኔ በዋና ስብሰባ ላይ ይሰጣል። ተማሪው/ዋ በድስትሪክቱ ትምህርት ቤቶች እንዳይማር/እንዳትማር ከተወሰነ እና ወደ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት ለመላክ ምክንያቶች ካሉ፣ ድስትሪክቱ ከላይ በተሰጡት ሂደቶች መሰረት ተማሪው/ዋን ከትምህርት ማገድ ወይም ወደ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት መላክ ይችላል።

3. ሌላው አማራጭ፣ የፍርድ ቤት ሂደት እስኪያልቅ እና ውጤቱ እስኪታወቅ ድረስ፣ ተማሪው/ዋን ከትምህርት የማገድ ወይም ወደ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት የመላክ ሂደትን ማቆየት ነው። በዚህ ጊዜ ተማሪ ወደ ትምህርት ቤት መመለስ አይችልም/አትችልም። የፍርድ ቤት ሂደት እስኪያልቅ እና ውጤቱ እስኪታወቅ ድረስ በቆይታው/ዋ ጊዜ አግባብ ያለው የትምህርት መርሃ ግብር፣ በክፍለ ግዛት ሕግ የተፈቀደ በኮምፒዩተር የታገዘ ትምህርት ወይም የቤት ውስጥ የትምህርት መርሃ ግብር ለተማሪው/ዋ ሊሰጥ ይችላል። ተማሪው/ዋ በአማራጭ የትምህርት መርሃ ግብር የሚያውለው/የሚታውለው ጊዜ እንደ ከትምህርት ቤት እገዳ ወይም የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት ጊዜ አይቆጥርም።

4. ተማሪው/ዋ በተከሰሰበት/በተከሰሰችበት ጉዳይ ወንጀለኛ መሆኑ/ኗን ካመነ/ች፣ ወንጀለኛ መሆኑ/ኗ ከተደረሰበት/ከተደረሰባት፣ ወይም በልጆች የወንጀል ድርጊት መሰረት ከተፈረደበት/ከተፈረደባት፣ ቦርዱ ወይም የቦርዱ ተወካይ በነዚህ ሕገ ደንቦች ውስጥ በተቀመጡት ሂደቶች መሰረት ተማሪው/ዋን ወደ አማራጭ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት ይልካሉ።

5. የተጠርጣሪው/ዋ የሁከት ወንጀል ዝርዝር መረጃ በቦርዱ ወይም በቦርዱ ተወካይ በዚህ ፖሊሲ ውስጥ ለተሰጡት ዓላማዎች ሥራ ላይ ይውላል፣ ነገር ግን በሕግ መሰረት መረጃው ለህዝብ ይፋ ካልተደረገ በስተቀር፣ የመረጃው ሰነድ በምስጥር ይያዛል።

በየበላይ አለቃ Monte C. Moses ኖቬምበር 8፣ 2004 ጸደቀ።
የተሻሻለው፤ አገስት 13፣ 2012

## ተማሪን ከትምህርት ለማገድ፣ ለማባረር ወይም መልሶ ላለመቀበል ምክንያቶች (JKD-1-E)

**የመታገድ፣ የመባረር ወይም የመልሶ መቀበል መከልከል ምክንያቶች**
በተሻሻለው የኮሎራዶ ሕገ ደንብ 22-33-106 (1) (ሀ-ረ) እና 3 (ሐ, ሠ, እና ረ) እና 22-12-105(3) መሰረት፣ የሚከተሉት ከትምህርት ቤት ለመታገድ፣ ወደ አማራጭ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት ለመላክ ወይም ከህዝብ ትምህርት ቤት ለመከለከል ምክንያቶች ይሆናሉ።

1. በተከታታይነት ሆን ብሎ አለመታዘዝ እና የሙጥኝ ብሎ ተገቢውን ኃላፊ አለመታዘዝ።C.R.S 22-33106(1)a)

2. ሆን ብሎ የትምህርት ቤት ንብረትን ማውደም ወይም ማበላሸት። C.R.S 22-33106(1)b)
3. በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ወይም ውጪ ለሌሎች ተማሪዎች ወይም ለድስትርክት አስተዳደሮች ሰላም እና ደኅንነት አስጊ የሆነ ምግባር እና ባህሪውን የሚያሳይ ተማሪ ወይም ሌላ ተማሪን ጨምሮ በልጆች ወይም በሌሎች ልጆች ላይ የአካላዊ ጉዳት ዛቻን የሚፈጥር ምግባር።***(C.R.S. § 22-33-106(1)(c))***

4. የድስትርክቱን ለሌሎች ተማሪዎች የትምህርት ዕድሎች የመስጠት አቅም/ብቃት በተከታታይነት የሚያደናቅፍ። ***(C.R.S. § 22-33-106(1)(e))***
5. በድስትሪክት ሰራተኛ ላይ በውሸት የወንጀል ድርጊት ለሕግ አስከባሪ ወይም ለድስትሪክት መክሰስ። C.R.S. § 22-12-105 (3))
6. ለቀደሙት አሥራ ሁለት ወራት(12) ከማንኛውም የትምህርት ድስትሪክት መታገድ(C.R.S. § 22 33 106(3)(c))
7. በቀደሙት አሥራ ሁለት ወራት ለተማሪዎች እና ለትምህርት ቤት አስተዳደሮች ሰላም እና ደኅንነት አስጊ የሆነ በሌላ የትምህርት ድስትሪክት ሲታይ የነበረ ምግባር።(C.R.S. § 22 33 106(3)(f))

8. በትምህርት ቤት ግቢ፣ C.R.S. § 18-18-102 (5), በትምህርት ቤት መኪና ወይም በትምህርት ቤት ስፖንሰር የተደረገ እንቅስቃሴ አደዛዥ /ሱስ አስያዥ ዕጽን ወይም ክልክል የሆኑ ቁስ አካልን መሸጥ መያዝ ወይንም መጠቀም። C.R.S. § 22 33 106(1)(d)(II))

9. በትምህርት ቤት ግቢ፣ በትምህርት ቤት መኪና ወይም በትምህርት ቤት ስፖንሰር የተደረገ እንቅስቃሴበዐዋቂ የሚፈጸም ድርጊት በክፍል 3፣ አንቀጽ 4፣ ርዕስ 18 C.R.S. መሰረት እንደ ስርቆት/ዝርፊያ ድርጊት የሚወሰድ ወይም በክፍል 2፣

አንቀጽ 3፣ ርዕስ 18 C.R.S. መሰረት እንደ ጥቃት የሚወሰድ ድርጊት ይሆናል፤ ከዚህ ውጪ በ C.R.S. 13-3-204 መሰረት በዐዋቂ የሚፈጸም ሦስተኛ ደረጃ የመግደል ሙከራ አጥቂ/ጥቃት አድራሽ ይሆናል። C.R.S. § 22 33 106(1)(d)(III))

10. ያለ ትምህርት ቤት ወይም ያለ የትምህርት ድስትሪክት ፈቃድ አደገኛ መሳሪያዎችን ወደ ትምህርት ቤት ፤ በትምህርት ቤት መኪና ወይም በትምህርት ቤት ስፖንሰር የተደረገ እንቅስቃሴ ላይ ይዞ መገኘት ፤ ማስታወሻ፤ በፌዴራል ህግ መሰረት፣ የጦር መሳሪያን ይዞ ወደ ትምህርት ቤት የመጣ ተማሪ ከአንድ አመት ላላነሰ ጊዜ ከትምህርት ቤት ይታገዳል። የትምህርት ድስትሪክቱ የበላይ አለቃ ይህንን የጊዜ ገደብ ሊያሻሽል ይችላል፤ ይህም በጽሁፍ የሚገለጽ ይሆናል። (C.R.S. § 22 33 106(1)(d)(III))

በዚህ አንቀጽ ውስጥ እንደተጠቀመው "አደገኛ መሳሪያዎች"

ሀ. ጠመንጃ፣ ባዶ ወይም ጥይት ያለው ሊሆን ይችላል፣ (C.R.S. § 22 33 106(1)(d)(I)) እንደተገለጸው

ለ. ማንኛውም "Pellet" ወይም "bee-bee" የሚባል ጠመንጃ ወይም ሌላ መሳሪያ፣ ሊሰራም ላይሰራም ይችላል፣ የሚወነጨፍ ወይም የሚፈነዳ፤ ወይም የእሳት ነበልባሎች፣ /ወይም ጭስ የሚያወጣ ጠመንጃ;

ሐ. ርዝመቱ ከሦስት(3) እንች በላይ የሆነ እና የተበጀ ስለታማ ቢላ ወይም ከሦስት ተኩል(3 1/2) እንች በላይ ርዝመት ያለው የኪስ ጩቤ። ስለታማ ቢላ የሚለካው ብረቱ መያዣውን ከሚነካበት ጫፍ አንስቶ ይለካል።

መ. ሰውን ለመግደል ወይም ለመጉዳት የተሰራ ማንኛውም ዓይነት ነገርመሳሪያ፣ ወይም ቆስ አካል፣ ወንጭፍ፣ ስፕሪንግ ሽጉጥ፣ ተወርዋሪ ኮከብ፣ ብሉጅዮን፣ የነሐስ አንጓዎችን ወይም ማንኛውንም ዓይነት ሰው ሰራሽ ጥፍጥፎችን ጨምሮ ግን በዝህ ብቻ አይወሰንም ።

11. በትምህርት ቤት ውስጥ ወይም ቅጥር ግቢ ውስጥ ከጠመንጃ ጋር የሚመሳሰሉትን መሳሪያዎች መያዝ፣ መጠቀም፣ ለሌላ ሰው ማሳየት፣ ወይም መዛት። C.R.S. § 22 33 106(1)(f))
12. በC.R.S.25-4-901 ውስጥ የተሰጠውን (የክትባት መስፈርቶች) ሥራ ላይ ባለማዋል ምክንያት ከትምህርት ቤት እገዳ፣ ወደ ወይም ትምህርት ቤት መከለከል የመሳሰሉት የቅጣት እርምጃ አይወሰድም፣ ነገር ግን ከተማሪው የክትባት ሰነድ ጋር ከተገቢው ገለጻ ጋር ሊያያዝ ይችላል። (C.R.S. § 22 33 106(3)(e))
13. ወደ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት መላክ የግዴታ የሆነ ዘወትር ረባሽ የሆነ/ች ተማሪ መግለጫ።

ሀ. ለዚህ አንቀጽ ዓላማዎች፣ "ዘወትር ረባሽ የሆነ/ች ተማሪ" ማለት በመማሪያ ክፍል፣ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ፣ በትምህርት ቤት ተሽከርካሪ ውስጥ ወይም በትምህርት ቤት ተግባራት ወይም ዝግጅቶች ላይ ግልጽ በሆነ መንገድ ሆን ብሎ/ላ፣ ፈልጎ/ጋ የንብረት እና መጠነ ሰፊ የሆነ ረብሻ/ሁከት በመፍጠር በአንድ የትምህርት ዘመን ውስጥ ሦስት ጊዜ(3) የተለለፈች/ለፈ ተማሪ ማለት ነው። በህዝብ ትምህርት ቤት ውስጥ የተመዘገበ/ች ማንኛውም ተማሪ በዚህ ጎራ ሊመደብ/ሊትመደብ ይችላል/ትችላለች።

ለ. ተማሪን በዘወትር ረባሽ ጎራ የሚመድበውን የተማሪው/ዋን ከትምህርት ቤት የመታገድ ሁኔታ በጽሁፍ፣ በስልክ፣ ወይም በሌላ የወላጅ ወይም የአሳዳጊ የቤት ወይም የሥራ መገናኛ መንገድ በመጠቀም የ"ዘወትርት ረባሽ ተማሪ" ትርጉም እና የግዴታ የሆነውን ተማሪው/ዋን ወደ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት መላክ ሁኔታን ለወላጅ፣ ለሕጋዊ አሳዳጊ፣ ወይም ለሌላ ሕጋዊ ጠባቂ ማሳወቅ ያስፈልጋል።

በ **C.R.S.** 22-33-106 (2) መሰረት፣ በአንቀጽ 20 ሥር የድስትሪክቱ ኃላፊነት የሆነውን አንቀጽ (የልዩ ልጆች የትምህርት ሕግ)፣ C.R.S. § 22-20-101 et seq.), ወደ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት ለመላክ ወይም የህዝብ ትምህርት ቤት ለመከለከል ወይም አግባብ ባለው አማራጭ መርሃ ግብር ለመዘዋወር የሚከተሉት ምክንያቶች ናቸው፤

1. ካለው መርሃ ግብር መጠቀም የሚያዳግት አሳማኝ የሆነ የተማሪው/ዋ የአካል ወይም የአይምሮ ስንኩልነት።

የአካል ወይም የአይምሮ ስንኩልነት ወይም ለሌሎች ተማሪዎች ጤንነት አስጊ የሆነ ተላላፊ በሽታ።

መጀመሪያ የተወሰደ፡ ኖቨምበር 9 ቀን 2009

የተሻሻለው፣ ኦገስት፤ 13፣ 2012

በቅርቡ ኤፕሪል 10፤2023 ተሻሻለ

ህጋዊ ዋቢዎች.: C.R.S. § 18-1-901(3)(ሥ) እና (ሽ) (የግዛት ህግ የ"ገዳይ መሳሪያ" እና "ሽጉጥ" ትርጓሜዎች

C.R.S. § 18-3-202 በጥቃት ላይ የኮሎራዶ የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች)

C.R.S. § 18-4-301 C.R.S.(Colorado Criminal Code provisions on robbery) § 22-12-105(3) C.R.S. § 22-33-106(1)(ሀ – (የሐሰት ዘገባዎች) ረ) C.R.S. §

C.R.S. § 22-20-101 የልዩ ህፃናት የትምህርት ህግ)

C.R.S. § 22-33-102(4) የስቴት ህግ ትርጉም "አደገኛ መሣሪያ")

22-33-106(2) **የመታገድ፣** የመባረር እና የመልሶ መግባት መከልከል ምክንያቶች)

C.R.S. § 22-33-106.1 የመታገድ፣ የመባረር፣ ህግ ከቅድመ ትምህርት ቤት እስከ ሁለተኛ ክፍል)

C.R.S. § 22-33-106(3)(ሐ, እና ረ)

C.R.S. § 25-4-901 ትምህርት ቤት ከመጀመሪዎ
በፊት ክትባት ማግኘት )

## የአካለ ስንኩል ተማሪዎች የቅጣት ደንብ
## (JKD-2)

አካለ ስንኩላን ተማሪዎች ከትምህርት ድስትሪክት የሥርዓት ሂደቶች ነጻ አይደሉም፤ በተጨማሪም ምግባራቸው የሌሎች ተማሪዎችን ትምህርት የሚጎዳ ከሆነ ባሉት መርሃ ግብሮች አይሳተፉም። የሁከት ተግባራትን እና/ወይም ለራሳቸው ወይም ለሌሎች አደገኛ የሆኑ ድርጊቶችን የሚፈጽሙ ስንኩላን ተማሪዎች IEP በሚባለው የግል የትምህርት እቅድ/መርሀ፣ በማንኛውም የምግባር ጣልቃ መግባት እቅድ፣ እና በዚህ ፖሊሲ መሰረት ይታረማሉ/ይቀጣሉ።

የ IEP (የግል የትምህርት እቅድ) ቡድንን ለሚረብሽ ወይም ተቀባይነት ለለው ሥርዓት እንደ የተማሪው/ዋ የ IEP (የግል የትምህርት እቅድ) እና/ወይም የሥርዓት ጣልቃ መግባት እቅድ ከማውጣት የሚያግድ ነገር በዚህ ፖሊሲ ውስጥ የለም።

**ተማሪን ለጊዜው ከትምህርት ቤት ማገድ፣ ማበረር እነ አገልግሎቶችን መስጠት**

የአካለ ስንኩልና ሌላ ተመሳሳይ ችግር ያለባቸው ተማሪዎች የተማሪ ሥነ-ምግባር ህገ-ደንብ ካጣሱ በተሰጠው የትምህርት ዘመን ውስጥ እስከ 10 የትምህርት ቀናት ከትምህርት ቤት ሊታገዱ ይችላሉ። እነዚህ 10 ቀናት በተከታታይ ላይሆኑ ይችላሉ። በእገዳው ጊዜ፣ ተማሪው/ዋ ትምህርተ-ነክ አገልግሎቶችን አያገኝም/አታገኝም።

**የዉሳኔ መገለጫ**

ተማሪው/ዋ ከ 10 የትምህርት ቀናት በላይ በተከታታይ ከትምህርት ቤት ከታገደ/ች ወይም በህግ መሰረት በተከታታይ ከትምህርት ቤት ከታገደ/ች፣ ለተማሪው/ዋ የሥነ-ሥርዓት ማስያዣ የቦታ ለውጥ ሊደረግለት/ሊደረግላት ይችላል።

ከእገዳው በኃላ በአሥራ አንደኛው የትምህርት ቀን ለተማሪው/ዋ የሥነ-ሥርዓት ማስያዣ የቦታ ለውጥ ካልተደረገ፣ 'IEP' የሚባል የግል የትምህርት እቅድ ለመፈጸም እንዲቻለው/እንዲቻላት ለተማሪው/ዋ በሌላ ቦታ የትምህርት አገልግሎት ይሰጣል። የትምህርት ቤት አስተዳደር ቢያንስ ከአንድ የተማሪው/ዋ አስተማሪ ጋር በመሆን በእገዳው ወቅት ለተማሪው/ዋ መሰጠት ያለበትን የትምህርት አገልግሎት በጋራ ይወስናሉ።

ተማሪ የሥነ-ሥርዓታዊ የቦታ ለውጥን የሚያስከትል ከትምህርት ቤት እገዳ ከተጣለበት/ከተጣለባት፣ 'IEP' የሚባል የግል የትምህርት እቅድ ለመፈጸም እንዲቻለው/እንዲቻላት በተማሪው/ዋ 'IEP' የሚባል የግል የትምህርት እቅድ ቡድን ውሳኔ መሰረት ለተማሪው/ዋ በሌላ ቦታ የትምህርት አገልግሎት ይሰጣል።

ተማሪን ወደ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት ከመላክ ወይም የሥነ-ሥርዓታዊ የቦታ ለውጥን ከማድረግ በፊት፣ ጉዳዩን በውሳኔው ዕለት ለተማሪው/ዋ ወላጆች ማሳወቅ ያስፈልጋል።

**የሥነ-ምግባር ጉድለት መገለጫ ባህሪ ውሳኔ**

የተማሪው/ዋ ምግባር ከአካለ ስንኩልነቱ/ቷ ወይም ከሌላ ተመሳሳይ ሁኔታ የመነጨ መሆኑን ለመመርመርና ውሳኔ ላይ ለመድረስ፣ የሥነ-ሥርዓታዊ የቦታ ለውጥን የሚያስከትል የሥነ-ሥርዓት እርምጃ ውሳኔ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ በ10 የትምህርት ቀናት ውስጥ የትምህርት ቤት አስተዳደር፣ ወላጅና ጉዳዩ የሚመለከታቸው የተማሪው/ዋ 'IEP' የሚባል የግል የትምህርት እቅድ ቡድን (በወላጅና በየትምህርት ቤት አስተዳደር በተወሰነው መሰረት) 'IEP' የሚባል የግል የትምህርት እቅድ፣ የማንኛውም አስተማሪ ምልከታዎች (አስተውሎቶች)፣ እንደዚሁም በወላጆች የቀረበ ማንኛውም ተገቢ መረጃ ጨምሮ፣ በተማሪው/ዋ ሰነድ ውስጥ ያሉትን ተገቢ መረጃዎች ሁሉ ማገናዘብ ያስፈልጋል።

ቡድኑ ቀጥሎ ያሉትን ጉዳዮች መወሰን አለበት፤ (1) የተማሪው/ዋ የምግባር ችግር ከአካለ ስንኩልነቱ/ቷ የመነጨ ወይም ከዚያ ጋር ቀጥታ ግኑኝነት እንዳለው፤ እንደዚሁም (2) የተማሪው/ዋ ምግባር ችግር ትምህርት ቤቱ 'IEP' የሚባል የተማሪው/ዋን የግል የትምህርት እቅድ ካለመፈጸም የተነሳ መሆኑን ነው። ከሁለቱ የአንዱ መልስ "አዎን" ከሆነ፣ የተማሪው/ዋ ምግባር የተማሪው/ዋ ምግባር የአካለ ስንኩልነቱ/ቷ መገለጫ ተደርጎ ይወሰዳል።

**የሥነ-ሥርዓት እርምጃና/ወይም አማራጭ የቦታ ድልደላ**

ቡድኑ የተማሪው/ዋ ባህሪ ከአካለ ስንኩልነቱ/ቷ የመነጨ መሆኑን ከወሰነ፣ ወደ አማራጭ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት መላክ ወይም ሌሎች የሥነ-ሥርዓት ማስያዣ የቦታ ለውጥ ሂደቶች ይቋረጣሉ። በአንጻሩ ደግሞ፣ ከታች እንደተገለጸው ተማሪው/ዋ ለ45 የትምህርት ቀናት በአማራጭ ቦታ እንዲሆን/እንዲትሆን ሊደረግ ይችላል፣ ወይም 'IEP' የሚባል የግል የትምህርት እቅድ ቡድን ወይም ህግ በሚፈቅደው መሰረት ለትምህርት ምክንያት የተማሪው/ዋ ድልደላ ሊለወጥ ይችላል።

የተማሪው/ዋ ምግባር ከአካለ ስንኩልነቱ ወይም ከሌላ ተማሳሳይ ጉዳይ የመነጨ መሆኑን ካረጋገጡ በኃላ፣ 'IEP' የሚባል የተማሪው/ዋን የግል የትምህርት እቅድ ቡድን በቶሎ የሚከተሉትን ነገሮች ይፈጽማል፤ (1) የተማሪው/ዋ ጠቃሚ ምግባር መገምገምና (2) የጥሩ ሥነ-ምግባር ድጋፍ ማድረግ ናቸው። ከዚህ በፊት የጥሩ ሥነ-ምግባር ድጋፍ ከተደረገ፣ ቡድኑ የምግባር ግምገማውን በመከለስ አስፈላጊውን ማሻሻል ያደርጋል።

**ለ45 የትምህርት ቀናት ተማሪን በአማራጭ ቦታ መመደብ**

በሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ የትምህርት ቤት አስተዳደር አካለ ስንኩላን ተማሪዎችን የምግባራቸ መገለጫ ባህሪን ሳያገናዝብ ለ45 የትምህርት ቀናት በአማራጭ ቦታ መመደብ ይችላል፤

1. ተማሪው/ዋ በትምህርት ቤትና በትምህርት ነክ ዝግጅቶች አከባቢ መሳሪያ ይዞ/ዛ ከተገኘ/ች፤
2. ተማሪው/ዋ በትምህርት ቤትና በትምህርት ነክ ዝግጅቶች አከባቢ መሳሪያን እንደ የግል ንብረት አድርጎ ይዞ/ዛ ከተገኘ/ች፤
3. ተማሪው/ዋ በትምህርት ቤትና በትምህርት ነክ ዝግጅቶች አከባቢ ሕገ-ወጥ እጾችን ሲ(ት)ይዝ ወይም ሲ(ት)ጠቀም ከተያዝ/ች፤
4. ተማሪው/ዋ ሕገ-ወጥ እጾችን ሲ(ት)ያመላልስ ወይም ሲ(ት)ሸጥ ከተያዘ፤
5. ተማሪው/ዋ በትምህርት ቤት ውስጥ ወይም በትምህርተ-ነክ ዝግጅቶች አካባቢ በሌላ ሰው ላይ አካላዊ ጉዳት ካደረሰ/ች፤
6. ተማሪው/ዋ በአማራጭ ቦታ እንዲ(ት)መደብ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ከተላለፈ ናቸው።

የተማሪው/ዋ ምግባር ከአካለ ስንኩልነቱ/ቷ የሚመነጭ ቢሆንም እንኳን፣ እንደዚህ ዓይነቱ ምደባ ይፈቀዳል። 'IEP' የሚባል የተማሪው/ዋ የግል የትምህርት እቅድ ቡድን ተማሪው/ዋ በተመደበበት (በተመደበችበት) ስፍራ ሊሰጠው/ሊሰጣት የሚገባውን ትምህርት ይወሰናል።

**አካለ ስንኩልነታቸው ያልተገለጸ ተማሪዎች**

የትምህርት ድስትሪክቱ የተማሪው/ዋ ስነ-ምግባር ችግር ከአካለ-ስንኩልነቱ/ቷ የመነጨ መሆኑን አስቀድሞ ከተረዳ፣ አካለ ስንኩልነታቸው ያልተገለጸ ተማሪዎች ጉዳይ አካለ-ስንኩል ካልሆኑ ተማሪዎች ሥነ-ምግባር ጉዳይ ጋር በተመሳሳይ መልኩ ይታያል።

በሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ ድስትሪክቱ የተማሪው/ዋን አካለ-ስንኩልነት እንደሚያውቅ ተደርጎ ይወሰዳል፤
1. የተማሪው/ዋ ወላጆች ለድስትሪክቱ አስተዳደር፣ ወይም ለተማሪው/ዋ አስተማሪ ተማሪው/ዋ የልዩ ትምህርት አገልግሎት እንደሚያስፈልገው/እንደሚያስፈልጋት በጽሁፍ ከገለጹ፤
2. የተማሪው/ዋ ወላጆች ለተማሪው/ዋ አስፈላጊው ግምገማ እንዲደረግ ከጠየቁ፤ ወይም
3. የተማሪው/ዋ አስተማሪ ወይም ሌሎች የድስትሪክቱ አስተዳዳሪዎች በግልጽ ለድስትሪክቱ የልዩ ትምህርት ኃላፊ ወይም ለሌሎች የድስትሪክቱ አስተዳዳሪዎች የተማሪው/ዋ ስነ-ምግባር ሁኔታ አሳሳቢ መሆኑን ካሳወቁ የተማሪው/ዋ አካለ-ስንኩልነት እንደሚታወቅ ይገመታል።

ግምገማው የተጠየቀው ተማሪው/ዋ ከአስቸጋሪ ስነ-ምግባሩ/ሯ የተነሳ የስነ-ሥርዓት ማስያዣ እርምጃ የተወሰደበ/ባት ጊዜ ከሆነ፣ ግምገማው በአስቸኳይ ይካሄዳል።ግምገማው እስከጠናቀቅ ድረስ፣ ተማሪው/ዋ በድስትሪክቱ ውስጥ በተወሰነለ/ላት ቦታ እንዲ(ት)ቆይ የሚ(ት)ቆይ ሲሆን፣ ይህም ጉዳይ ተማሪው/ዋን ለጊዜው ከመደበኛው ትምህርት ቤት መከልከል ወይም ወደ አማራጭ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት መውሰድን ሊያካትት ይችላል።

ወላጆች የተማሪው/ዋን ግምገማ ካልፈቀዱ፣ ወይም ከግምገማ በኃላ ተማሪው/ዋ የአካል ጉዳተኛ አላመሆኑ/ኗ ከተወሰነ፤ ወይም ተማሪው/ዋ የልዩ ትምህርትና ተመሳሳይ አገልግሎቶች እንዲያ(ታ)ገኝ ከተወሰነ በኃላ ወላጆች ያንን አገልግሎት ለልጆቻቸው ካልተቀበሉ ድስትሪክቱ የተማሪው/ዋን የአካል ጉዳተኝነት ወይም ተመሳሳይ ችግር እንደማያውቅ ተደርጎ ይወሰዳል።

የተሻሻለው፤ ሜይ 9፣ 2011
ሥራ ላይ የዋለው፤ ኖቬምበር 14፣ 2005

ሕጋዊ ዋቢዎች፤ C.R.S. 22-33-106 (1) (c)
C.R.S. 22-20-101 et seq. (የልዩ ተማሪዎች የትምህርት ሕግ) 20 U.S.C. Section 1401 et seq.
20 U.S.C. Section 1401 et seq. (የ2004 የስንኩላን ተማሪዎች ማሻሻያ ሕግ)
34 C.F.R. 300.530-300.537 (IDEIA regulations (መተዳደሪያ ደንቦች))
ጥምር ዋቢዎች፤ JIC፣ የተማሪ ምግባር፣ እና ንዑስ አንቀጾች
JK፣ የተማሪ ሥርዓት፣ እና ንዑስ አንቀጾች
JRC፣ የተማሪ ሰነዶች/የተማሪዎችን መረጃ ለሌላ መስጠት

## ከመደበኛ ትምህርት ቤት ለታገዱ ተማሪዎች የሚሰጡ አማራጭ የመማር ዕድሎች ፖሊሲ (JKD-4)

ተማሪ ወይም የተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ ሲጠይቅ፣ ከመደበኛ ትምህርት ቤት ለተከለከሉ ተማሪዎች ድስትሪክቱ ተገቢውንና አማራጭ የመማር ዕድሎችን ለማንኛውም ተማሪ ይሰጣል። የትምህርት ዕድሎቹ ተማሪው/ዋ ከመደበኛ ትምህርት ቤት ከመከልከሉ/ሏ በፊት ቀድሞ በተመዘገበበት/በተመዘገበችበት ትምህርት ቤት እንዲመለስ/እንዲትመለስ፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱ/ቷን እንዲያጠናቅቅ/እንዲታጠናቅቅ፣ ወይም የህዝብ ትምህርት ቤት ባልሆነ፣ ክፍት በሆነ ትምህርት ቤት ወይም በአማራጭ ትምህርት ቤት እንዲመዘገብ/እንዲትመዘገብ ማድረግ ነው።

በእነዚህ ብቻ ባይወሰኑም፣ የትምህርት እድሎቹ ተጨማሪ ገለጻ፣ አማራጭ የትምህርት ፕሮግራሞች፣ በክፍለ-ግዛት ህግ የጸደቁትን ፍት ለፊት ሳይሆን በኮምፒዩተር የታገዙ ትምህርቶች፣ ወይም የምንባብ፣ የጽሁፍ፣ የሂሳብ፣ የሳይንስና የማህበረሰብ ትምህርቶችን የሚያካትት የሙያ ትምህርት ናቸው። ከትምህርት ዕድሎች በተጨማሪ፣ ተማሪው/ዋ የተማርው/ዋ ወላጅ/አሳዳጊ ከክፍለ-ግዛት ተቋማትና ከማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር በመተባበር በድስትሪክቱ የሚሰጡትን ማንኛቸውንም የትምህርት ዕድሎች ለሚመለከተው ተማሪ መጠየቅ ይችላሉ።

የትምህርት ዕድሎቹ በቀጥታ በድስትሪክቱ ወይም ከክፍለ-ግዛት ተቋማትና ከማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር በመተባበር በክፍለ-ግዛቱ ህግ መሰረት ሊሰጡ ይችላሉ። አገልግሎቶቹ በትምህርት ድስትሪክት ቦታዎች መሰጠት የለባቸውም።

ለመመረቅ የሚያስችለውን የትምህርት ዕድል በተመለከተ ድስትሪክቱ ተማሪው/ዋ ማጠናቀቅ ያለበትን/ያለባትን የክረዲት/የነጥብ ብዛት ይወስናል።
በድስትሪክት የሚሰጡ አማራጭ የትምህርት እድሎች ለተማሪው/ዋ የትምህርት ክንውንና ስኬታማነት እንደ ሁለተኛ እድል መስጠት ተደርጎ መዘጋጀት አለበት። አማራጭ የትምህርት ዕድል ሲያገኝ/ሲታገኝ፣ ተማሪው/ዋ በድስትሪክቱ የተማሪ ሥርዓትና ምግባር ህገ-ደንብ መሰረት አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ሊባረር/ሊትባረር ይችላል/ትችላለች። የልዩ ትምህርት ተማሪዎችን በተመለከተ የፌዴራል ህግ የሚያዝ ካልሆነ በስተቀር፣ አማራጭ የትምህርት ዕድል እያገኘ/ች ሳለ/ች የተባረረ/ች ተማሪ በዚህ ፖሊሲ መሰረት የእገዳው የጊዜ ገደብ እስኪያልቅ ድረስ ሌላ ተጨማሪ አማራጭ የትምህርት ዕድል አያገኝም/አታገኝም"።

በሥነ-ሥርዓት ወይም በሥነ-ምግባር ጉድለት ምክንያት የሌሎች ተማሪዎችንና ሰራተኞች ደህንነት ለማረጋገጥ ሲባል ከመደበኛ ትምህርት የሚታገዱ ተማሪዎች በድስትሪክቱ ፈቃድ መሰረት በድስትሪክቱ ውስጥ ባሉትና ለእንደነዚህ ዓይነቶቹ ተማሪዎች በተዘጋጁት በሌሎች አማራጭ ትምህርት ቤቶች እንዲማሩ ይደረጋሉ።

ከመደበኛ ትምህርት ቤት የሚታገዱ ተማሪዎች በድስትሪክቱ የተማሪ ብዛት ውስጥ ይካተታሉ፣ ከጥቅምት ወር የተማሪ ቆጠራ በፊት የታገዱ ተማሪዎችም በቁጥሩ ይካተታሉ።

ተማሪ ለአመቱ በሙሉ ከታገደና በድስትሪክቱ የሚሰጠውን የትምህርት አገልግሎት የማያገኝ ከሆነ፣ ተማሪው/ዋ ዳግመኛ ወደ ትምህርት ቤት መመለስ እስክችል/እስኪትችል ድረስ የድስትሪክቱ ትምህርት ቤት የተማሪውን ወላጅ/አሳዳጊ በስልሳ ቀናት ውስጥ ቢያንስ አንድ ጊዜ በመደወል ተማሪው/ዋ ትምህርት እየተከታተለ/ች መሆኑን/መሆኗን ይጠይቃል። ነገር ግን፣ ተማሪው/ዋ በሌላ የትምህርት ድስትሪክት፣ በሌላ የግል ትምህርት ቤት ወይም በሌላ ገለልተኛ ትምህርት ቤት ከተመዘገበ/ች በኃላ፣ ወይም የተማሪው/ዋ ጉዳይ "Department of Human Services' የሚባል የዜጎች አገልግሎቶች ተቋም ከገባ፣ ወይም በልጆች ፍርድ ቤት ከተፈረደበ/ባት በኃላ የድስትሪክቱ ትምህርት ቤት ከተማሪው/ዋ ወላጅ ጋር መገናኘት የለበትም።
የቀረበው፤ ጥቅምት 10፣ 2000
ሥራ ላይ የዋለው፤ አገስት 13 2012 ተሻሻለ
ህጋዊ ዋቢዎች፤ C.R.S. 22-33-201.5 (የትምህርት አገልግሎቶች ትርጉም)

C.R.S. 22-33-203 (ከመደበኛ ትምህርት ቤት ለታገዱ ተማሪዎች የሚሰጡ አማራጭ የመማር ዕድሎች)
C.R.S. 22-33-204 (ለተጠቂ ተማሪዎች የሚሰጡ አገልግሎቶች)
C.R.S. 22-33-205 ((ከመደበኛ ትምህርት ቤት ለታገዱ ተማሪዎች የሚሰጡ የገንዘብ ድጎማ ፕሮግራሞች)

አባሪዎች፤ JIC, የተማሪ ምግባርና፣ ንዑሳን አንቀጾች
JK, የተማሪ ሥር ዓትና፣ ንዑሳን አንቀጾች

## ተማሪን በትምህርት ቤት ውስጥ ማገድ (JKG)

ተደጋጋሚ ሁኔታ የሚረብሹ ተማሪዎች በመደበኛ የመማሪያ ክፍል ውስጥ እንዲቆዩ አይፈቀድላቸውም፤ ነገር ግን እንደነዚህ ዓይነቶቹ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ሲታገዱ በተማሪዎች፣ በትምህርት ቤት እና በማኅበረሰቡ ላይ ሌላ ችግርን ይጨምራሉ። ስለዚህ፣ ቦርዱ የትምህርት ቤት ውስጥ እገዳ ጽንሰ ሀሳብን ይደግፋል።
የትምህርት ቤት ውስጥ እገዳ ዓላማ ከሥራት ወይም ከትምህርት ቤት ውጪ ተማሪን ከማገድ የተሻለ የተማሪ የቅጣት/የእርማት ዘዴ ለማቅረብ ነው። የትምህርት ቤት ውስጥ እገዳን በመጠቀም፣ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ሥራዎች ወደ ኃላ አይቀሩም። ነገር ግን፣ የከትምህርት ቤት ውጪ እገዳ አስፈላጊ የሚሆንበት አጋጣምም ሊኖር ይችላል።
የትምህርት ቤት ውስጥ እገዳዎች በሙሉ በተሰጠው ሂደት መሰረት መከናወን አለበት። የሚከተሉት መመሪያዎች መከተል አለባቸው፦

1. ተማሪዎች ሁል ጊዜ በቂ ቁጥጥር ሊደረግላቸው የሚቻልበት ልዩ በሆነ ቦታ መመደብ አለባቸው። የትምህርት ቤት ውስጥ እገዳ አስተማሪ እያንዳንዱ ተማሪ መጻህፍት እና የመማሪያ ክፍል ሥራዎችን ከመደበኛ አስተማሪዎቹ ማየት መቻል አለበት/አለባት።
2. ተማሪ በትምህርት ቤት ውስጥ እገዳ ከተደረገበት/ከተደረገባት ኃላፊ የተማሪው/ዋ ወላጅ ጉዳዩን በስልክ እንዲያዉቁ ይደረግ እና ስለሚደረገው ክትትል በጽሁፍ ይገለጽላቸዋል። የትምህርት ቤት ውስጥ እገዳ ምክንያት ይሰጣል፣ ተማሪው/ዋ ወደ መደበኛ መማሪያ ክፍል ከመመለሱ/ሷ በፊት ውይይት ይደረጋል።
3. በትምህርት ቤት ውስጥ እገዳ ላይ ሲሆኑ ተማሪዎች በተጓዳኝ ትምህርት ተግባራት ላይሳተፉ ይችላሉ፣ ነገር ግን በእገዳው ጊዜ ለሰሩት ሥራ ነጥብ ያገኛሉ። ሥራ ላይ የዋለው፦ መመሪያ ሥራ ላይ በዋለ ቀን

## የተማሪዎች የጤና አገልግሎቶችና አስፋላጊ ሁኔታዎች (JLCA)

የትምህርት ቤት የጤና መርሃ ግብር ዓላማ ከመደበኛው የጤና እንክብካቤ የሚገኙትን ጥቅሞች በተመለከተ የተማሪዎችን ግንዛቤ ለመጨመር የወላጆች/ አሳዳጊዎች ጥረቶችን እና አመራሮችን ለመደገፍ ነው።የትምህርት ቤት ጤና መርሆ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው:
- በተማሪዎች መካከል ጥሩ የጤንነት ልምዶችን ለማስፋፋት.
- በትምህርት ቤት ውስጥ ንጹህ፤ ጤናማ፤ጥንቃቄ የሞላበት አካባቢን ለማስፋፋት
- የሕክምና; የስነልቦና እና የአካላዊ የጤንነት ጉዳዮችን ለመለየትና ወደ ተገቢ የጤና እንክብካቤ ሰጪዎች ጋር ለመገናኘት

### የጤና መዛግብት

የጤና መዛግብት፤ የክትባት ማስረጃን ጨምሮ በትምህርት ቤቱ ምስጢራዊነቱን ለመጠበቅ ስርአት በለውና በተለየ ቦታ ይቀመጣል።
የተማሪዎችን የጤና ፋይሎች ማየት/ማግኘት የምችሉት መረጃው የተማሪውን/ዋን የትምህርት ክንውንን ለማሻሻል ወይም ደኅንነቱ የተጠበቀ እና ሥርዓት ያለው የትምህርት ሁኔታን ለማራመድ የምጠቅማቸው ትክክለኛና ህጋዊ እውቅና ያላቸው የትምህርት ቤት ሰራተኞች ብቻ ነው።
ኤች አይቪ / ኤድስ ያላቸው ተማሪዎች የሚመለከታቸው የሕክምና መረጃ በፖሊሲ JLCCA እና በ " JLCCA-R
ኤች አይ ቪ /ኤድስ ያለባቸው ተማሪዎች መሰረት ይጠበቃል።
በሕግ እና በዲስትሪክቱ ፖሊሲዎች JRC፤ JRC-R እና JRCA መሰረት የትምህርት ቤት ነርሶች መረጃዎችን የምሰጧቸዉን ሰዎች ስም ዝርዝር መቼና ምን አይነት ዝርዝር መረጃዎች እንደሰጡ መመዝገብ አለባቸው።

### አመታዊ የአይንና የጆሮ ምርምራ

በመዋዕለ ሕፃናት የአንደኛ ፤ሁለተኛ፤ ሶስተኛ፤ አምስተኛ፤ ዘጠነኛ ክፍል ያሉት ወይም በተመሳሳይ ዕድሜ ክልል ያሉ ተማሪዎች በትምህርት ዓመቱ ውስጥ በትምህርት ቤት ነርስ፤ አስተማሪ፤ ርእስ መምህር ወይም በህግ በተደነገገው መሠረት በዲስትሪክቱ በተወከለ ሌላ ብቁ አካል የአይንና የጆሮ ምርመራ ይደረግላቸዋል።ጉድለት ሲገኝ ለወላጆች ወይም ለአሳዳጊዎች ይነገራቸዋል።
ይህ ድንጋጌ ወላጆቻቸው ወይም አሳዳጊዎቻቸው በሃይማኖታዊ ወይም በግላዊ ምክንያቶች ምርመራው እንድደረግ የማይፈልጉ ተማሪዎችን አይመለከትም።

### ተላላፍ/ተዛማጅ በሽታዎች

እጅግ በጣም ከባድ የጤና ችግር፤እንደዝሁም ተላላፍናተዛመጅ ምልክቶችንና በሽታዎችን የምያሳዩ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤቱ ነርስ መላክ አለባቸው፡፤ ተገቢዉን እርምጃ ለመውሰድ የትምህርት ቤቱ ነርስ ተዛመጅ/ተላላፍ በሽታዎች ያለቸዉን ተማሪዎች ስም ዝርዝር ለዳይሬክተሩ ትሰጣለች/ይሰጣል፡፤ ለተጨማሪ አስፈላጊ እርምጃዎች እና የውሳኔ ሃሳቦች ርእስ መምህሩ ከድስትሪክቱ የጤና አገልግሎት ቢሮ ጋር መነጋገር ይኖርበታል።

### መድሃንቶችን ለተማሪዎች መስጠት

በትምህርት ቤት ዉስጥ መድሃንቶችን ለተማሪዎች መስጠት የምችሉት በህጋዊ መንገድ በትምህርት ቤቱ ነርሶች የመድሃንት አሰጣጥ ስልጠና የተሰጣቸው የትምህርት ቤቱ በልደረቦች ብቻ ነው።.ማንኛዉም በሃኪም ትህዛዝና ያለሃኪም ትህዛዝም የምሰጡ መድሃንቶች ሁሉ ከዝህ በታች ያሉት መስፈሮች ካልተሟሉ በስተቀር በትምህርት ቤት ነርስም ሆነ በማንኛዉም የትምህርት ቤት ሰራተኞች ልሰጡ አይችሉም።

1. ሁሉም መድሀኒቶች በአርጅናል ዕቃ መሆን አለበቸው፤ እንድሁም በዕቃው ላይ ትክክለኛው የመድሃንቱ ስም መለጠፍ አለበት።መድሃንቱ በሃኪም ትህዛዝ ብቻ የምሰጥ ከሆነ ደግሞ የተማርው/ዋ ስም /መድሃንቱን ያዘዘ ሃኪም ስም፤ የመድሃኒቱ ስም፤ የአወሰሰድ አኳሁን፤ሰአት ፤መጠን እና / ወይም ድግግሞሽ) እንድሁም ቀንም በላዩ ላይ መጻፍ ይኖርበታል።
2. በኮላራዶ ህግ መሰረት ትምህርት ቤቱ ለተማሪዎች መድሃንትን ለመስጠት ፈቃድ ካለው ከተማሪዎቹ የጤና ጥበቃ በለሙያዎች መድሃንቶችን የማዘዝ ስልጣን ከለው ግለሰብ የጽሑፍ ትዕዛዞች መቀበል አለበት።
3. መድሃኒቱን ለተማሪዎች ለመስጠት ትምህርት ቤቱ ከወላጅ/አሳዳጊዎች የጽሁፍ ፈቃድ ሊኖረው ይገባል።ወላጆች ይህንን ፍቃድ ለትምህርት ቤቱ ስሰጡ መድሃንቱ ከምያመጠው ያልተጠበቀ ጉዳትና ሌላም ተያያዥ ችግሮች ትምህርት ቤቱ ሃላፍነቱን እንደማይወስድ በፎርሙ ላይ መጠቀስ አለበት።
4. የመድሃንት አሰጣጥን በተመለከተ የድስትርክቱ የነርሶች ቡድን ከተማሪዎቹ የጤና ባለሙያ መድኃኒት አቅራቢ/አዛዥ ጋር እንድነጋገሩ ወላጆች መፍቀድ አለባቸው።

5. የልጆቻቸዉን መድሃንቶች ለትምህርት ቤት ማቅረብ ሙሉ ለሙሉ የወላጆች/የአሳዳጊዎች ሃላፍነት ነው።

## የተማሪዎች ጠቅላላ የጤና ምርመራ

ወላጆች ልጆቻቸው ትምህርት ቤት ከመግባታቸው በፍት እነ እንደዝሁም እንደገና አራተኛ ፣ ሰባተኛና አስረኛ ክፍል ከመግባታቸው በፍት ለጠቅላላ የጤና ምርመራ ወደ ሃኪም ቤት እንድወስዷቸው ይመከራሉ። የጥርስ ምርመራም እንዲደረግላቸው ይመከራል።
መምህራን የተማሪዎችን አጠቃላይ ደህንነት ለማረጋጋጥ በንቃት መከታተል አለባቸው እና ማንኛውንም አጠያያቂ ሁኔታዎችን ለትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር ወይም ተወካይ ማሳወቅ አለባቸው። ተማሪዎች በሰዉነት ማጎልመሻ(ስፖርት) ትምህርት የምኖረቸው ተሳትፎ ለጤንነታቸው ጎጂ ከሆነ ዕውቅና ከለው የጤና በለሙያ ይህን የምገልጽ ማስረጃ ከቀረቡ ከስፖርት ትምህርት እንቅስቃሴና ከትምህርት ስርአቱ መስፈርቶች ነጻ ልሆኑ ይችላሉ።

## የወላጅ ስምምነት

ከዝህ በላይ ያሉት ምርመራዎች ሁሉ በትምህርት ቤቱ የጤና በለሙያ ወይንም ትምህርት ቤቱ በወከለው ግለሰብ የምካሄድ ከሆነ የግድ የወላጅ ፍቃድ ያስፈልጋል። ይሁን እንጅ ምርመራው ከእርግዝና፤ከአባላዘር በሽታ ጋርና እንድሁም የመጠጥና የአሽሽ/ዕጽ ጋር የምያያዝ ከሆነ ግን ተማሪዎቹን ወደምያስፋልገው የጤና ክልንክ ለመላክ የግድ የወላጅ ፍቃድ አያስፈልግም። ተማሪዎች እንደዚህ ያሉ ሁኔታዎች ወይም ችግሮች ስንጥሟቸው ያለ/ወይንም በወላጅ ፍቃድ የጤና አግለግሎት ለማግኘት እንድጥሩ ድስትርክቱ ያበረታታል።
በህግ በተደነገገው መሰረት ትምህርት ቤቶች ለወላጆች/አሳዳጊዎች እና መስፈርቱን ለሚያሟሉ ( ዕድሜያቸው 18 አመት ለሆኑ ተማሪዎች) ስለ ምርመራው ማሳወቅ አለበት። እንደዝሁም ወላጆችም ሆኑ ተማሪዎች ከማንኛዉም ድንገተኛ ከልሆነ የጠቅላላ ምርመራ ለምሳሌ የአይንና የጆሮ ምርመራ የመታቀብ ዕድል አለቸው።ምርመራው ከዝህ በታች ያሉትን የምመለከት ከሆነ

1. በመደበኛነት ለመሳተፍ ብቻ ከሆን
2. በትምህርት ቤቱ አስቀድሞ ፕሮግራም ተይዞ በ ትምህርትቤት የምሰጥ ከሆነና
3. የግድ የተማሪውን ወይም የሌሎች ተማሪዎችን ጤንነት እና ደህንነት ለመጠበቅ አስፈላጊ ከልሆነ

ስራ ላይ የዋለው:ኦክቶበር 13, 2003
የተሻሻለው: ጁን 11፤ 2018
ህጋዊ ዋቢዎች፤C.R.§25-4 409(በልጆች የምከሰተዉን የአባላዛር በሽታን ለማካም የወላጆች ፍቃድ ያለማስፋለግ)
C.R.S. § 25-1.5-109 (CDPHE የተማሪዎችን የምግብ አሌርጂ የሚያስተዋውቁ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ለትምህርት ቤቶች መደበኛውን ቅጽ ለመያዝ)
C.R.S. § 24-10-101 (Colorado Governmental Immunity Act)
C.R.S. § 22-32-139 (የተማሪዎችን የምግብ አለሪጅና anaphylaxis አመራር በተመለከተ በተግባር ላይ ያለ ፖሊሲ )
C.R.S. § 13-22-102, 103 (ልጆች ለህክምናቸው ፍቃድ መስጠት ይችላሉ።)
1 CCR 301-68 (የምግብ አለርጅን፤የአስም በሽታንናanaphylaxis በተመለከተ ያሉ ደንቦች)
C.R.S.§ 12-38-132(የነርሶች አሰራር)
C.R.S.§22-1-1-199( በወላጆች የጹሁፍ ፍቃድ መሰረት የተሰጠ መድሃንት ለምያስከስተው ለልተጠበቀ የጎንዮሽ/ ጉዳቶች ኅላፍነት ያለመኖር )
C.R.S.§22-1-1-199.5 (የኮላራዶ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች የአስም፤የምግብ አለሪጅና የanaphylaxis የጤና አጠባበቅ health management act)
C.R.S.§22-32-109(i)(ee)የትምህርት ቤቶችን ሰራተኞችን የተወሰኑ መድሃንቶችን ለተማሪዎች እንዳያዙ ወይንም እንድወስዱ እንዳይመክሩና እንድሁም ያለ ወላጆች ፍቃድ የባህሪ ምርመራ እንዳያዙ የምከለክል ሃላፍነት )
C.R.S. §22-1-116 (የአይንና የጆሮ ምርመራ)
C.R.S. §22-2-135 (የኮላራዶ ትምህርት ቤት የተማሪዎች ፤የምግብ አለርጅና የAnaphylaxisአመራር ህግ)
C.R.S. §22-33-105 (እገዳ፤ማበረር፤ መከልከል)
C.R.S. §22-33-106 (2) ((የእገዳ፤የማበረር፤ የመከልከል ምክንያቶች)
C.R.S.§25-4-901(የትምህርት ቤት መግቢያ ክትባቶች)
C.R.S.§25-6-102(ስለ እርግዝና መከላከያ መረጃ ማሰራጨት)
20 U.S.C. §7906 (በትምህርት ቤቶች ዉስጥ የእርግዝና መከላካያን ፕሮግራምን ለማካሄድ የTitle I ድጎማ ገንዘብን ከመጠቀም መከልከል) 6 CCR 1010-6.13 (በትምህርት ቤቶች የጤና አገልግሎት መስፈርቶች)
ጥምር ዋቢዎች.: IMBB - አስፋላጊ ከሆኑ መመርያዎች ላይ ነጻ መሆን
JF - ምዝገባና ምዝገባን መከልከል
JLCD - የመጀመሪያ እርዳታ እና ድንገተኛ የህክምና እንክብካቤ
JLCCA-R - ኤች አይ ቪ / ኤድስ ያለባቸው ተማሪዎች JLCCA - ኤች አይ ቪ / ኤድስ ያለባቸው ተማሪዎች
JLCC - ተላላፍ/ተዛማጅ በሽታዎች
JLCB -የተማሪዎች ክትባት
JLCDB -የህክምና ማሩዋናን መስፈርቱን ለሚያሟሉት ተማሪዎች በድስትርክቱ ቅጥር ግቢ ዉስጥ መስጠት

## የልጆች ክትባት (JLCB)

ለጤንነት፣ ለሃይማኖት፣ ለግል ወይም ለሌሎች ሕጋዊ ምክንያቶች ተማሪው/ዋ ክትባት የማይወስድ ካልሆነ በስተቀር፣ ማንኛውም ተማሪ ለተለያዩ በሽታዎች አስፈላጊውን ሕጋዊ የክትባት መስፈርቶችን ሳያሟላ በዚህ ድስትሪክት ውስጥ ትምህርት ቤት ሊከታተል አይችልም/አትችልም።

የክትባት የምስክርት ወረቀትን የማያቀርቡ ወይም ለተለያዩ ምክንያቶች መከተብ አለመቻላቸውን የሚገልጽ መረጃ የማያቀርቡ ተማሪዎች መረጃውን እስኪያቀርቡ ድረስ ከትምህርት ቤት ይታገዱ እና/ወይም ወደ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት ይላካሉ።

ክትባት የሚያስፈልገው የተላላፊ በሽታ ወረርሽኝ አደጋ/ሥጋት ካለ፣ ከክትባቱ ነጻ የሚያደርግ ምንም ዓይነት ምክንያት/ሰበብ ተቀባይነት አይኖረውም። ያልተከተበ ተማሪ ወረርሽኙ እስኪጠፋ ድረስ ከተማሪዎች ይለያል።
ቦርዱ ሱፐርኢንቴንደንቱ ፣ ዋና የጤና ኦፊሰርን ወይም ተወካይን በየአመቱ ለተመዘገቡ ተማሪዎች ወላጆች እና አሳዳጊዎች ስለ መደበኛ ክትባቶች አስፈላጊ እና የሚመከሩ ክትባቶች ዝርዝር እና እያንዳንዱ ክትባት መሰጠት ያለበትን እድሜ(ቶች) ሰነዶችን በየዓመቱ እንዲያቀርቡ ይመራል። የዲስትሪክቱ ልዩ የክትባት እና የኩፍኝ፣ የኩፍኝ እና የኩፍኝ ክትባቶች ነፃ የመውለጃ ደረጃዎች ባለፈው የትምህርት ዘመን በዲስትሪክቱ የተመዘገቡ ተማሪዎች ቁጥር ከተከተቡት ህጻናት ደረጃ ጋር ሲነፃፀር እና ትምህርት ቤቱ መረጃውን መሰብሰብ እና ሪፖርት ማድረግ እንዳለበት የሚገልጽ መግለጫ፣ ነገር ግን ያ ዲስትሪክቱ የዲስትሪክቱን ልዩ የክትባት መጠን አይቆጣጠርም ወይም የተከተቡ ህፃናትን ደረጃ አያወጣም። ይህ ሰነድ በኤሌክትሮኒካዊ መንገድ በዲስትሪክቱ ድህረ ገጽ ላይ መቅረብ አለበት እና/ወይም ሃርድ ቅጂ ከትምህርት ቤት ነርስ ሊጠየቅ ይችላል።

በዲስትሪክቱ ለወላጆች እና ለአሳዳጊዎች የሚሰራጩ ሁሉም መረጃዎች በግዛት ህግ መሰረት ከክትባት መስፈርቶች ነፃ የመሆን መብታቸውን ያሳውቃቸዋል።

የተሻሻለው፤ ኖቬምበር 13፤2023
ሥራ ላይ የዋለው፤ ኦገስት 12፣ 1996

ሕጋዊ ዋቢዎች፤ C.R.S. 22-33-105 (ተማሪን ከትምህርት ቤት ማገድ፣ ወደ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት መላክ እና የትምህርት ቤት ምዝገባን መከልከል)
C.R.S. 22 33 106 (ተማሪን ከትምህርት ቤት ማገድ፣ ወደ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት መላክ እና የትምህርት ቤት ምዝገባን መከልከል ምክንያቶች)
C.R.S. 25 4 901 ተከታይ (የትምህርት ቤት መግቢያ ክትባቶች)
6 CCR 1009-2
ጥምር ዋቢዎች፤ JKD፣ ተማሪን ከትምህርት ቤት ማገድ/ወደ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት መላክ
JRC፣ የተማሪ ሰነዶች

## የተማሪ ክትባት (JLCB-R)

1. እንደአጠቃላይ፣ ማንኛውም ተማሪ የዘመነ የክትባት ሰርተፍኬት ወይም የተሟላ የመልቀቂያ ቅጽ ካላቀረበ በስተቀርበዲስትሪክቱ ውስጥ ትምህርት ቤት መከታተል አይችልም፣ ተማሪው ። ተማሪው ነፃ የሚሆነው የሚከተሉትን ሲሰጥ ብቻ ነው፡-
ሀ. የተማሪው አካላዊ ሁኔታ ክትባቱ የተማሪውን ህይወት ወይም ጤና አደጋ ላይ የሚጥል ወይም በሌላ የጤና ሁኔታ(ዎች) ምክንያት የተከለከለ መሆኑን ከፈቃድ ሀኪም፣ ብቃት ካለው ሀኪም ረዳት ወይም የላቀ ልምድ ነርስ የህክምና ነፃ የመውጣቱን የምስክር ወረቀት፤
ለ. በወላጅ ወይም በአሳዳጊ ወይም ነፃ በሆነ ተማሪ የተፈረመ ከህክምና ነፃ የመውጣቱን የምስክር ወረቀት ተማሪው ከአንዳንድ ወይም ከሁሉም ግዛቶች ትምህርቶቹ የሚቃወሙ ክትባቶች;
ሐ. ተማሪው ከአንዳንድ ወይም ከሁሉም ግዛቶች የሚፈለጉ ክትባቶችን የሚቃረን የግል እምነት እንዳለው በአንድ ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ነፃ በሆነ ተማሪ የተፈረመበት የተጠናቀቀ የምስክር ወረቀት፤ ወይም
መ. አሁን ባለው የግዛት ህግ በኮሎራዶ የህዝብ ጤና እና አካባቢ ዲፓርትመንት የሚተዳደረውን የመስመር ላይ ትምህርታዊ ሞጁል ያጠናቀቀ የምስክር ወረቀት።
ሠ. ዲስትሪክቱ ሲጠየቅ የኮሎራዶ የክትባት ሰርተፍኬት ቅጽ በግዛት እና በአካባቢው የጤና መምሪያዎች በሚፈለገው መሰረት ይሰጣል። የእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ነርስ እና/ወይም የዲስትሪክቱ የተማሪ ጤና ቢሮ አስፈላጊው መረጃ በተጠቀሰው ቅጽ ላይ መካተቱን የማየት ሃላፊነት አለበት።
ወረርሽኙን ጨምሮ ክትባቱ የሚያስፈልግበት በሽታ ሲከሰት ነፃ መሆን አይታወቅም እና እነዚያ ተማሪዎች በክልል እና በአካባቢው የጤና ዲፓርትመንት አስተያየቶች ከትምህርት ቤት ሊገለሉ ይችላሉ።
2. የክትባት መስፈርቶችን ማሟላት ካልተሳካ የሕንፃ አስተዳዳሪ እና/ወይም የትምህርት ቤቱ ነርስ ለወላጅ እና አሳዳጊ ወይም ነፃ ለወጣ ተማሪ በግል ያሳውቃሉ። እንደዚህ ዓይነቱ ማስታወቂያ በስልክ ፣ በኢሜል ወይም በአካል ይከናወናል ።
3. ያላሟላ ተማሪ በህንፃ ርእሰ መምህር እስከ አምስት (5) ቀናት ሊታገድ ይችላል እና የእገዳው ማስታወቂያ ለክልል ወይም ለአካባቢው የጤና መምሪያዎች ይላካል።

ወላጅ እና አሳዳጊ ወይም ነፃ የሆነ ተማሪ ስለሚከተሉት ነገሮች ይነገራቸዋል።
ሀ. በኮሎራዶ ህግ መሰረት አስፈላጊ ክትባቶች እንደሚያስፈልጉት እስከ አሁን ያለው ሁኔታ።
ለ. ማስታወቂያው በወጣ በአስራ አራት (14) ቀናት ውስጥ ወላጅ ወይም አሳዳጊ ወይም ነፃ የሆነ ተማሪ ከሚከተሉት አንዱን ማስገባት አለባቸው፡-

I የሕክምና ነፃ የተጠናቀቀ የምስክር ወረቀት;
iiከሕክምና ነፃ የሆነ የተጠናቀቀ የምስክር ወረቀት
iiiiii. በኮሎራዶ የህዝብ ጤና እና አካባቢ ዲፓርትመንት የሚተዳደረውን የመስመር ላይ ትምህርት ሞጁል የማጠናቀቂያ የምስክር ወረቀት; ወይም
iv. የሚቀጥለው አስፈላጊ ክትባት መሰጠቱን የሚያሳዩ ሰነዶች እና ሁሉንም አስፈላጊ ክትባቶች ለማጠናቀቅ የጽሁፍ እቅድ.
ሐ. አስፈላጊው ሰነድ ማስታወቂያ በወጣ በአስራ አራት (14) ቀናት ውስጥ ካልቀረበ ወይም ተማሪው ከጀመረ ነገር ግን የፅሁፍ እቅዱን ካልቀጠለ ወይም ካላጠናቀቀ፣ ተማሪው ከትምህርት ቤት ሊገለል፣ ሊታገድ ወይም ሊባረር ይችላል።
4. በእገዳው ጊዜ ምንም ዓይነት የክትባት የምስክር ወረቀት ካልደረሰ, የበላይ ተቆጣጣሪው ለመባረር ሂደቶችን ሊያዘጋጅ ይችላል.
5. በዚህ መመሪያ ስር ያለ ማንኛውም ማግለል፣ መታገድ ወይም መባረር ተገዢ ሲሆኑ በራስ-ሰር ይቋረጣሉ።
6. የማንኛውንም መታገድ ወይም መባረር መዝገብ በተማሪው ኤሌክትሮኒክ የጤና መዛግብት ውስጥ ከተገቢው ማብራሪያ ጋር ይቀመጣል።
7. የክትባት መስፈርቶችን ባለማክበር የተባረረ ማንኛውም ተማሪ የማቋረጥ መጠንን በማስላት ውስጥ አይካተትም ነገር ግን ለስቴት የትምህርት ቦርድ አመታዊ ሪፖርት ውስጥ ይካተታል።
8.ከቤት ውጭ ምደባዎች ውስጥ ያሉ ተማሪዎች

ዲስትሪክቱ ከቤት ውጭ በሆነ ምደባ ተማሪውን ለመከልከል ስልጣን ከሌለው በስተቀር፣ ዲስትሪክቱ የተማሪውን የክትባት መዝገቦች መቀበል አለመቀበሉን ከግምት ውስጥ ሳያስገባ ተማሪውን ማስመዝገብ አለበት። ተማሪውን ሲያስመዘግብ፣ ዲስትሪክቱ ተማሪው ከተመዘገበ በ14 ቀናት ውስጥ የተማሪውን የክትባት ሰርተፍኬት ወይም የክትባት መሰጠት የጽሁፍ ፈቃድ እስካላገኘ ድረስ፣ ዲስትሪክቱ ተማሪውን እስከዚህ ጊዜ ድረስ እንደሚያስወግድ ወይም እንደሚያግደው ዲስትሪክቱ ለተማሪው ህጋዊ አሳዳጊ ማሳወቅ አለበት። ዲስትሪክቱ የክትባት ወይም የፈቃድ የምስክር ወረቀት እንደተቀበለ

በመጀመሪያ የጸደቀው በሱፐርኢንቴንደንት ሞንቴ ሲ. ሞሰስ፣ ኦገስት 11፣ 2008 አሁን ያለው ክለሳ፡ ህዳር 13፣ 2023
ህጋዊ ማመሳከሪያ፡ C.R.S. § 22-32-138 (ከቤት ውጭ ያሉ ተማሪዎች)
ሲ.አር.ኤስ. § 25-4-902 (ትምህርት ከመቀጠልዎ በፊት የሚደረጉ ክትባቶች)
ሲ.አር.ኤስ. § 25-4-903 (ከክትባት ነፃ መሆን)
ሲ.አር.ኤስ. § 25-4-906 (የክትባት ቅጾች ማረጋገጫዎች)

## የመጀመሪያ እርዳታ እና የድንገተኛ ህክምና እንክብካቤ (JLCD)

## የመድሃኒት፤ የመጀመሪያ እርዳታ እና የድንገተኛ ህክምና እንክብካቤን መስጠት

### መድሃኒት መስጠት

በትምህርት ቤት ዉስጥ መድሃንቶችን ለተማሪዎች መስጠት የምችሉት በህጋዊ መንገድ በትምህርት ቤቱ ነርሶች የመድሃንት አሰጣጥ ስልጠና የተሰጣቸው የትምህርት ቤቱ በልደረቦች ብቻ ነው።.ማንኛዉም በሃከም ትህዛዝና ያለሃኪም ትህዛዝም የምሰጡ መድሃንቶች ሁሉ ከዝህ በታች ያሉት መስፈሮች ካልተሟሉ በስተቀር በትምህርት ቤት ነርስም ሆነ በማንኛዉም የትምህርት ቤት ሰራተኞች ልሰጡ አይችሉም።

1.ሁሉም መድሀኒቶች በአርጅናል ዕቃ መሆን አለበቸው፤ እንድሁም በዕቃው ላይ ትክክለኛው የመድሃንቱ ስም መለጠፍ አለበት።መድሃንቱ በሃኪም ትህዛዝ ብቻ የምሰጥ ከሆነ ደግሞ የተማርው/ዋ ስም /መድሃንቱን ያዘዘ ሃኪም ስም፤ የመድሃኒቱ ስም፤ የአወሰሰድ አኳሁን፤ሰአት ፤መጠን እና / ወይም ድግግሞሽ) እንድሁም ቀንም በላዩ ላይ መጻፍ ይኖርበታል።
2.በኮላራዶ ህግ መሰረት ትምህርት ቤቱ ለተማሪዎች መድሃንትን ለመስጠት ፈቃድ ካለው ከተማሪዎቹ የጤና ጥበቃ በለሙያዎች መድሃንቶችን የማዘዝ ስልጣን ከለው ግለሰብ የጽሑፍ ትዕዛዞች መቀበል አለበት።
3 ተማሪው አሥራ ስምንት ዓመት ካልሆነ ወይም ነፃ ካልወጣ በስተቀር .መድሃኒቱን ለተማሪዎች ለመስጠት ትምህርት ቤቱ ከወላጅ/አሳዳጊዎች የጽሁፍ ፈቃድ ሊኖረው ይገባል።
4.ተማሪው አሥራ ስምንት ዓመት ካልሆነ ወይም ነፃ ካልወጣ በስተቀር.የልጆቻቸዉን መድሃንቶች ለትምህርት ቤት ማቅረብ መሉ ለሙሉ የወላጆች/የአሳዳጊዎች ሃላፍነት ነው።

## የመጀመሪያ እርዳታ እና የድንገተኛ ህክምና እንክብካቤን ለተማሪዎች መስጠት

ከመጀመሪያ እርዳታ በስተቀር፣ በትምህርት ቤቶች ውስጥ ለቁስሎች ምንም ዓይነት ህክምና አይደረግም። የመጀመሪያ እርዳታ አደጋ ወይም ድንገተኛ ህመም ሲከሰት በትምህርት ቤት ውስጥ ባለው/ባሉችው አስፈላጊውን መስፈርቶች በሚያሟላ/በሚታሟላ ምርጥ ሙያተኛ አስቸኳይ እርዳታ መስጠት ነው። በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ቢያንስ አንድ ሰው በመጀመሪያ እርዳታ ልዩ ሥልጠና አለው/አላት። ዋና የመጀመሪያ እርዳታ እቃዎች እሽግ አግባብ ባለው ሁኔታ በተገቢው ቦታ ይደረጋል።

አንድ ተማሪ ከባድ ወይም ለሕይወት አስጊ የሆኑ ምልክቶች ከታየበት እና አፋጣኝ የሕክምና ዕርዳታ ካስፈለገው/ጋት ፣ የትምህርት ቤት ሠራተኞች 911 ጋር በመደወል አስቸኳይ እርዳታ ያገኛሉ። በCPR/AED የሰለጠኑ ሰራተኞች እና የመጀመሪያ እርዳታ ሰጪዎች ካሉ፣ የመጀመሪያ እርዳታ ሰጪዎች እስኪመጡ ድረስ አፋጣኝ እርምጃዎችን ሊወስዱ እና ተገቢውን ጣልቃገብነት ሊሰጡ ይችላሉ። የትምህርት ቤት ሰራተኞች የሕክምና ድንገተኛ ሁኔታን እና የተማሪውን ወቅታዊ ቦታ በተመለከተ ለተማሪው ወላጅ/አሳዳጊ ለማሳወቅ ይሞክራሉ። የመጀመሪያ እርዳታ ሰጪዎች ከመጡ በኋላ፣ ማንኛውም ጣልቃ ገብነት እና ለተማሪው የሚሰጠውን እንክብካቤ የሚወሰነው በመጀመሪያዎቹ እርዳታ ሰጪዎች ነው።

አደጋ ወይም ድንገተኛ ህመም ሲፈጠር በቅንነት ተጎጂውን ለመርዳት ብሎ/ላ ያለ ክፊያ የመጀመሪያ እርዳታ ያደረገ/ች ሰው ነገሩ በበጎነት ስለሚታይ እንደ ጥፋት አይቆጠርም። የክፍለ ግዛት ሕግም በቅንነት እና ያለ ክፊያ በውድድራዊ እስፖርቶች ጊዜ የድንገተኛ አደጋ ወይም ህመም የሚያጋጥማቸውን ሰዎች የሚረዱ የተወሰኑ የጤና እንክብካቤ ሰጪዎችን ከጥፋት/ከተጠያቂነት ነጻ ያደርጋቸዋል።

ማንኛውም የታመመ ወይም የተጎዳ የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪ ብቻውን ወደ ቤት መላክ የለበትም፣ ወይም ህመሙ ትንሽ ነው ተብሎ ካልተገመተ እና ወላጅ/አሳዳጊ አስቀድሞ በጽሁፍ ወይም በቃል ካልተስማማ በስተቀር የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ብቻውን ወደ ቤት መላክ የለበትም።

ተማሪው ከትምህርት ቤት ግቢ ውጭ እያለ፣ በዲስትሪክቱ መኪና ውስጥ ሳይሆን፣ እና በዲስትሪክቱ ስፖንሰር ባልተደረገባቸው ዝግጅቶች ወቅት የደረሰውን ጉዳት ማከም የት/ቤት ሰራተኞች ኃላፊነት አይደለም።

## III. በድንገተኛ ሁኔታዎች ውስጥ በክምቻታችን ዉስጥ ያለዉን የአክሲዮን ኤፒንፊን አውቶማቲክ መርፌዎችን መጠቀም

ድስትርክታችን አደገኛ ወይንም ለህይወት አስጊ የሆነ አለርጅ (anaphylaxis) በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ዉስጥ ብከሰት (epinephrine auto-injectors) የምባለዉን በመርፌ መልክ የምሰጥ መድሃንት ክምችት አለን።ማንኛዉም የድስትርክታችን በልደረባ ይህንን መድሃንት (epinephrine auto-injectors ) ለተማሪዎች ሰትሰጥ/ሰጥ የክፈለግዛቱን፤ እንደዝሁም የትምህርት ቦርዱን መመርያ መከተል አለባቸው።

የድስትርክታችን (epinephrine auto-injectors) የምበለዉ መድሃንት ክምችት በወላጆች የምቀርበዉን ተማሪዉ ለአለርጅዎች ወይንም ለህይወት አስጊ ለሆኑ ሁኔታዎች የምወስደዉን/ዉን መድሃንት ለመተካት የታቀደ አይደለም።

### IV በድንገተኛ ሁኔታዎች ውስጥ የሃሽሽ፤ድራግ አቨርዶዝን ማክሽፍያን መጠቀም

የስቴት የገንዘብ ድጋፍ እና አቅርቦቶች እስካሉ ድረስ፣ ዲስትሪክቱ ከopiate ከሚባል ጋር የተያያዘ መድሃኒት/ድራግን ከመጠን በላይ የመጠቀም ክስተት ሊያጋጥመው የሚችለውን ሰው ለመርዳት የድራግ/መድሃንት መመረዝን ማክሽፍያ ክምችት ሊኖረው ይገባል። ለዚህ ፖሊሲ ዓላማ፣ opiate antagonist ማለት ናሎክሶን ሃይድሮክሎራይድ ወይም ማንኛውም ተመሳሳይ ቁጥጥር ያልተደረገበት መድሀኒት እና በፌዴራል የምግብ እና የመድሀኒት አስተዳደር (ኤፍዲኤ) የተፈቀደ መድሃኒት ከመጠን በላይ መውሰድን ለማከም ነው።

የዲስትሪክቱ ሠረተኛ ይህን የድራግ ማክሽፍያን ለግለሰቡ በሚመለከተው የክልል ህግ መሰረት መስጠት አለበት።

### V. የተለያዩ/ተጨማሪ ነገሮች

በሚመለከተው የቦርድ ፖሊሲ መሰረት ከዚህ ፖሊሲ ጋር የማይጣጣም የተማሪ የመድሃኒት/ድራግ ይዞታ፣ አጠቃቀም፣ ማከፋፈል፣ መሸጥ ወይም በመድሃኒት ተጽእኖ ስር መሆን የተማሪዎችን የአደንዛዥ ዕፅ እና የአልኮል ተሳትፎ በተመለከተ የቦርድ ፖሊሲን እንደ መጣስ ይቆጠራል እና ተማሪውን ከትምህርት ማገድ እና/ወይም መባረርን ጨምሮ ለዲሲፕሊን መዘዝ ሊዳርግ ይችላል።

ሥራ ላይ የዋለው፤አክቶበር 15፣ 2007
ለመጨረሻ ጊዜ የተሻሻለው፡ ፌቡሪሪ 8፤2016
የቅርብ ጊዜ ክለሳ ኤፕሪል 10፤2023

ህግዊ ዋቢዎች፤ C .R.S. §12-38-132 (የነርስነት ስራ ስያሜ ድርሻ)

C.R.S. 12-38-132.3 (የትምህርት ቤት ነርሶች - የማስታጋሻ መድሃኒት አሰጣጥ ደንብ)

C.R.S. 13 21 108 (የድንገተኛ ጊዜ እርዳታ ለሚያደርጉ ሰዎች የህዝብ ድጋፍ/ይቅርታ)

C.R.S. 24 10 106.5 (የህዝብ የእንክብካቤ ሥራ/ድርሻ)

C.R.S. §22-1-119 (ድንገት ለምከሰተው የመድሃንት አለማስማማት ዋስትና አለመዉሰድ)

C.R.S .22-1-119.1 (የመድሃንት ማክሽፍያን መያዝ እና መስጠትን መፍቀድ)

C.R.S. 22-1-119.3 (የተማሪ የፕርስክሪፕሽን መድሃንት ይዞታ መዉሰድ)

( C.R.S. §22-1-119.5 (የኮላራዶ ተማርዎች የአስም፤ የምግብ አለርጅና የጤና አመራር)

C.R.S. 22-1-125 (አውቶማቲክ የሆነ የልብ/የደረት ችግርን ማስተካኪያ ‘defibrillator’ የሚባል ማሽን መስፈርቶች)

C.R.S. §22-2-135 (የኮላራዶ ተማርዎች የአስም፤ የምግብ አለርጅና የጤና አመራር)

C.R.S. §13-21-108.1 (አውቶማቲክ የሆነ የልብ/የደረት ችግርን ማስተካኪያ ‘defibrillator’ የሚባል ማሽን በመጠቀም እርዳታ ለምያደርጉት ሰዎች የተወሰነ ነጻነት መስጠት)

C.R.S. 13-21-108.5 (በእስፖርት ጊዜ በሚፈጠሩ አደጋዎች እርዳታ ሰጪዎች ያላቸው የህዝብ ድጋፍ)
C.R.S 24-10-101 እና ተከታዮቹ። (የኮሎራዶ ገቨርነር ያለመከሰስ ህግ)
1 CCR 301-68 (የኮሎራዶ የትምህርት ቦርድ የመድኃኒት አሰጣጥ ደንቦች)
6 CCR 1010-6፣ ደንብ 6.13 (በትምህርት ቤቶች ውስጥ ለጤና አገልግሎት የሚያስፈልጉ መስፈርቶች)

ጥምር ዋቢዎች፤ JICH፣ የተማሪዎች አልኮል እና ሌሎች እጾች መጠቀም
JLCDA፣ ሥር የሰደደ ወይም አጣዳፊ የጤና ሁኔታ ያለባቸው ተማሪዎች
JLCDB፣ በዲስትሪክት ግቢ ንብረት ላይ ብቁ ለሆኑ ተማሪዎች የህክምና ማሪዋናን መስጠት
JLIB፣ ተማሪን ከትምህርት ቤት የማሸኘት ቅድመ ጥንቃቄዎች
JLCA፣ የተማሪ የጤና አገልግሎቶች እና መስፈርቶች
KDE፣ አደጋን/ቀውስን መቆጣጠር

## የተማሪ ክፍያ፣ የገንዘብ መቀጮዎች እና ሌሎች ክፍያዎች (JQ)

መደበኛ በሆኑ የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ የመማሪያ ክፍል ወይም የትምህርት መገልገያ መሳሪያዎች ክፍያ አይኖርም። ለተሰጠው የክፍል ደረጃ የመማሪያ መጽሐፍት አስፈላጊ ከሆኑ፣ ያለ ክፍያ ይሰጣሉ። በመማሪያ ክፍል ውስጥ ለዋቢነት ለሚያገለግሉ መጽሐፍት ክራይ ወይም ሌላ ክፍያ አይጠየቅም። ለዋነኛ የትምህርት ዓይነት የመልመጃ ደብተር ፍጆታ ካለ፣ ትምህርት ቤቱ ለሁሉም ተማሪዎች የመልመጃ ደብተርን ያቀርባል።

ነገር ግን፣ ለጠፋባቸው፣ ለቀደዱት ወይም ላበላሹት መጽሐፍት (ከቤት መጽሐፍት ያወጡት መጽሐፍትን ጨምሮ)፣ ቁሳቁሶች ወይም የትምህርት መገልገያ መሳሪያዎች በገንዘብ መቀጮ ይቀጣሉ። የገንዘብ መቀጮው በጥፋቱ መጠን ይሆናል። የገንዘብ መቀጮው ሲሰላ፣ መጽሐፉ የተገዛበት ዋጋ 15% ባገለገለው ዓመት ብዛት ይቀነሳል።

ተማሪዎች ለአንድ ወይም ለተወሰነ የትምህርት ዓይነት ጠቅላላ ክፍያ አይጠይቁም፣ ነገር ግን፣ ተማሪው/ዋ የሚሰራው/የሚትሰራው ፕሮጀክት ተማሪው/ዋ ጋር የሚቆይ ከሆነ፣ ተማሪዎች ለፕሮጀክት መስሪያ የተጠቀሙት የትምህርት መገልገያ ቁሳቁሶች ወይም መሳሪያዎች ወጪ እንዲከፍሉ ይደረጋል።

የዘፈን ወይም የመዝሙር ባንድ/ጓድ ልብሶችን ለማሳጠብ የሚውል ክፍያ ተማሪዎች ሊጠየቁ ይችላሉ፤ በተጨማሪም ለትምህርት ቤት የሙዚቃ መሳሪያዎች ጥገና ወጪዎች እና ክራይ በቂ የሆነ ክፍያ ሊጠየቁ ይችላሉ።

የግዴታ ያልሆኑ፣ ነገር ግን ገንቢ በሆኑ በተለያዩ የትምህርት ቤት ተግባራት የሚሳተፉ ተማሪዎች የዝግጅቱን ወጪ እንዲሸፍኑ ሊጠየቁ ይችላሉ። እነዚህ ወጪዎች፣ በነዚህ ብቻ ባይወሰኑም፣ የመመዝገቢያ ክፍያ፣ የምግብ ወጪዎች፣ እና ለመስክ ትምህርት መጓጓዣ የሚውሉ ወጪዎችን ያካትታሉ። ነገር ግን፣ ተማሪዎች በገንዘብ ድጎማ እጥረት ምክንያት በመስክ ትምህርቶች ወይም በሌሎች ገንቢ ተግባራት ላይ የመሳተፍ መብት እንዳይከለከሉ ለማረጋገጥ አስተማሪ እና ኃላፊ አስፈላጊውን ጥረት ሁሉ ማድረግ አለባቸው።

የአትሌትክስ ክፍያ በድስትሪክት በተወሰነው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የሚካሄድ ሲሆን፣ ከሌሎች የትምህርተ-ነክ ክፍያዎች የተነጠለ እና የተለየ ነው። በኃላፊ እንዲቀር ካልተወሰነ በስተቀር፣ ክፍያው የግዴታ ነው።

ሁሉም ክፍያዎች፣ የገንዘብ መቀጮዎች፣ እና ሌሎች ክፍያዎች የሚከፍሉት ነገር/ገንዘብ ለሌላቸው ተማሪዎች መቅረት አለባቸው።

የተሻሻለው፤ ኤፕሪል 14፣ 2003
ሥራ ላይ የዋለው፤ ጁን 9፣ 2003

ህጋዊ ዋቢዎች፤ C.R.S. 22-32-117 (የተለያዩ ክፍያዎች)
C.R.S. 22-32-118 (የበጋ ትምህርት፣ የተከታታይ፣ እና የማታ እና የማኅበረሰብ ትምህርት መርሃ ግብሮች ክፍያዎች)
C.R.S. 22-45-104 (ክፍያዎች፣ የገንዘብ መቀጮዎች- ተጠባባቂ)

## የተማሪ ሰነዶችን/የተማሪዎችን መረጃዎች ለሌላ መስጠት (JRC)

ትርጉሞች
ለዚህ ፖሊሲ ዓላማ፣ የሚከተሉት ትርጉሞች ተሰጥተዋል፤

1. **ተማሪ** ፤ በቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤቶች ትምህርት ድስትርክት የሚከታተል ማንኛውም ግለሰብ።

2. **መስፈርት የሞላ ተማሪ**፤ 18 ዓመት የሞላው/የሞላት ወይም በአሁኑ ጊዜ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚከታተል ተማሪ ወይም የቀድሞ ተማሪ።

3. **ወላጅ**፤ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ መብታቸው ካልተከለከለ በስተቀር ወላጅ አባት እና እናት፣ አሳዳጊ፣ ወይም እንደ አባት/እናት የሆኑ ሰዎች ወይም የተማሪው/ዋ ወላጆች በለሉበት አሳዳጊ ወይም ከ18 ዓመት በታች የሆነ/ች የተማሪ አሳዳጊ።

4. **የትምህርት ሰነዶች**፤የተማሪ ትምህርት መዝገቦች በሁሉም ሚዲያዎች እና ቅርፀቶች በእጅ የተፃፉ ፣ የህትመት ፣ የፎቶግራፍ እና የኤሌክትሮኒክስ ሌሎች ሚዲያዎች ፣ በዲስትሪክቱ የሚጠበቁ እና በቀጥታ ከተማሪ ጋር የሚዛመዱ ፣እና በሌላ ዘዴ የተዘጋጀ እና፣ በነዚህ ብቻ ባይወሰንም፣ የሚከተሉትን መረጃ ያካተተ ነው: መረጃን መለየት፤ ያጠናቀቁት የትምህርት ተግባር፤ የክንውን ደረጃ (ነጥቦች፣ መደበኛ የሆኑ የመመዘኛ ፈተናዎች ነጥቦች)፤ የትምህርት ክትትል መረጃ፤ መደበኛ የሆኑ የአይምሮ፣ የተሰጥኦ/የችሎታ እና የሥነ ልቦና መመዘኛ ፈተናዎች፤ የፍላጎት መለያ ውጤቶች፤ የጤና መረጃ፤ የአእምሮ ጤና እና ሌሎች የሕክምና መረጃዎች የቤተሰብ ሁኔታ መረጃ፤ የአስተማሪ ወይም የአማካሪ/የምክር ሰጭ የደረጃ ትንተናዎች እና አስተውሎት/ምልከታ፣ (IEP) የሚባል የግል የትምህርት ፕሮግራም/መርሃ ግብር፣ አሳሳቢ ወይም ተደጋጋሚ የሆኑ የሥነ ምግባር ዘገባዎች፣ እና የተማሪ የሥርዓት መረጃ።

5.የሚከተሉት እንደ የትምህርት ሰነዶች አይቆጠሩም፤

ሀ. ለግል ማስታወሻ እንዲረዳ በትምህርት ቤት ሰራተኛ የተያዘ ሰነድ፣ የአዘጋጁ/ጇ ግለሰብ የሆነ ሰነድ፣ ለአዘጋጁ/ጇ ጊዜያዊ ተተኪ በስተቀር ለሌላ ሰው ጭራሽ ያልተሰጠ እና የማይሰጥ መረጃ የያዘ ሰነድ።

ለ. በትምህርት ድስትሪክቱ ከተማሪ ቅጥር ጋር ለተገናኘ ጉዳይ ብቻ የሚፈለግ የቅጥር ሰነድ። ለዚህ ዓላማ የሚሆን ቅጥር ተማሪ ማርከ/ነጥብ የሚያገኝበት የትምህርት ዓይነት ወይም የትምህርት ተግባራትን አያካትትም።

**6.ግላዊ መለያ**፤ የተማሪው/ዋን ስም፣ ወላጅ ወይም ሌላ የቤተሰብ አባል ስም፣ አድራሻ፣ የግል የምስጢር ቁጥር (Social Security Number)፣ የተማሪ ቁጥር፣ የግል ባህሪ ዝርዝር ፤ የኢሜይል አድራሻ፤ ወይም የተማሪው/ዋን ማንነት የሚገልጽ ሌላ ማንኛውም ዓይነት መረጃ።

**II የሙብቶች መግለጫና መብቶችን ማሳወቅ**

በየትምህርት ዘመን በየአመቱ ፣ ከዚህ በታች እንደተመለከተው ድስትሪክቱ ለወላጆች እና መስፈርት ለሚሞሉ ተማሪዎች መብታቸውን ያሳውቃል፤ ይህም የሚሆነው ለትምህርት ዘመኑ ተማሪው/ዋ ሲመዘገብ/ሲትመዘገብ ነው።

ማስታወቂያው የሚከተሉትን ያካትታል፤

1. ወላጆች እና መስፈርት የሚሞሉ ተማሪዎች የተማሪን የትምህርት ሰነድ የማስመርመር እና የመከለስ መብት።

2. ቅድሚያ ከወላጅ ወይም መስፈርት ከሚሞላ ተማሪ የጽሁፍ ፈቃድ ካላገኘ በስተቀር፣ በመመሪያ መሰረት ወይም በፌዴራል ሕግ በተፈቀደው መሰረት በተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ ከዚህ በታች እንደተገለጸው ድስትሪክቱ በተማሪ የትምህርት ሰነድ ውስጥ ያለውን መረጃ አግባብ በሌለው መንገድ መስጠትን የመገደብ ዓላማ/አቅድ።

3. ትክክል ያልሆነውን፣ አሳሳች ወይም የተማሪ ሙብቶችን የሚጥሱ ጉዳዮችን/መረጃዎችን ከተማሪው/ዋ የትምህርት ሰነድ ማስተካከል/ማረም ከፈለጉ የወላጅ ወይም መስፈርት የሚሞላ ተማሪ መብት።

4. የዩናይትድ ስቴትስ ትምህርት ቢሮ/ክፍል በአከባቢው በሚገኝ በዜጎች መብት ቢሮ የቤተሰብ መብቶች እና የግል ምስጢር መጠበቅ አዋጅ መሰረት የወላጅ ወይም መስፈርት የሚሞላ ተማሪ የመብት ጥሰትን በተመለከተ የማንኛውም ሰው አቤቱታ የማቅረብ መብት።

5. የዚህን ፖሊሲ ቅጂ/ግልባጭ ለማግኘት ወላጅ ወይም መስፈርት የሚሞላ ተማሪ መከተል ያለባቸው ሂደት እና ቅጂዎች/ግልባጮች የሚገኙበት ቦታዎች/ስፍራዎች።

በሕግ በሚጠይቀው መሰረት ፣የትምህርት ድስትሪክት የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪ ላልሆኑ ሰዎች ይህንን ማስታወቂያ በራሳቸው ቋንቋ ትርጉም ለማቅረብ ሁኔታዎችን ያመቻቻል።

**III.የሰነዶች ግልባጭ/ቅጂ ክፍያዎች**

ከዚህ በታች በተሰጡት የታተሙ ክፍያዎች ምክንያት ወላጆች ወይም መስፈርት የሚሞሉ ተማሪዎች የሰነዶችን ግልባጭ/ቅጂ የማግኘት መብት መከልከል የለባቸውም። መክፈል ካልቻሉ ድስትርክቱ ክፍያውን በከፍል ወይም በሙሉ ሊያስቀር/ሊታስቀር ይችላል/ትችላለች። ነገር ግን ድስትሪክቱ ለቀጣሪዎች ወይም ለኮሌጆች እና ለዩንቨርሲቲዎች ለቅጥር ወይም ለምዝገባ ዓላማ የሚልካቸውን የትራንስክርፕቶች ግልባጭ/ቅጂ ሒሳብ የማስከፈል መብት አለው። በተጨማሪም፣ ከወላጆች እና/ወይም ከተማሪዎች እና/ወይም ከተወካዮቻቸው የተጠየቁ መዝገቦችን ሚስጥራዊ መረጃን ለማሻሻል ወጪዎችን ለመሸፈን ፣ ወይም ሰፊ ዲጂታል ወይም ኤሌክትሮኒክስ መረጃን ወይም ትልቅ መጠን ያላቸውን ሰነዶችን ወይም ለተመሳሳይ የተባዛ ወረቀቶችን ወጪ ለመሸፈን የትላልቅ መዝገቦችን ጥያቄዎችን ከማሟላት ጋር የተያያዙ ክፍያዎች ሊኖሩ ይችላሉ።።

ድስትሪክቱ የሰነዶችን ግልባጭ/ቅጂ ማቅረብ ያለበት፤

1. ግልባጮችን/ቅጂዎችን አለመስጠት ወላጆችን ወይም መስፈርት የሚሞሉ ተማሪዎችን ሰነድ ማግኘትን መከልከል ሲሆን።

2. ቅድሚያ ከወላጅ ወይም መስፈርት ከሚሞላ ተማሪ ፈቃድ በማግኘት፣ ድስትሪክቱ በወላጅ ወይም መስፈርት በሚሞላ ተማሪ ጥያቄ መሰረት ሰነዶችን ለሦስተኛ ወገኖች ሲሰጥ።

3. በወላጅ ወይም መስፈርት በሚሞላ ተማሪ ጥያቄ መሰረት ድስትሪክቱ ሰነዶችን ተማሪው/ዋ መመዝገብ ወደ የሚፈልግበት/የሚትፈልግበት ትምህርት ቤት ሲልክ።

በዚህ ፖሊሲ መሰረት ለቀረቡት ቅጂዎች የሚከፈለው ክፍያ በኮሎራዶ ክፍት መዝገቦች ህግ፣ C.R.S 24-72-201 እና ተከታዮቹ ከሚፈቀደው ህጋዊ ክፍያ መብለጥ የለበትም።

**IV.ትምህርታዊ ያልሆኑ መዝገቦች/የመዛግብት ጥበቃ**

የትምህርት ሰነዶች በትምህርት ድስትሪክት የሕግ አስከባሪ ክፍል ቁጥጥር ሥር የሆነ እና ለሕግ ጉዳዮች ዓላማ የተዘጋጁ ሰነዶችን አያካትትም።

በዚህ ፖሊሲ ውስጥ አስተዳደሮችን፣ አስተማሪዎችን ወይም ሠራተኞችን፣ ከተማሪ የትምህርት ሰነዶች ሳይሆን፣ ከግል ዕውቀታቸው ወይም አስተውሎት/ምልከታ የመነጨን መረጃ ከመግለፅ የሚከለክላቸው ነገር የለም።

የተማሪን የትምህርት ሰነዶች ለመመርመር እና ለመከለስ የሚቀርቡ ጥያቄዎች በሙሉ እና የሰነዶቹ ግልባጭ/ቅጂ ጥያቄ ፣ በሕግ ካልተከለከለ በስተቀር፣ የግል መለያ መረጃዎችን ጨምሮ እንደ የእያንዳንዱ ተማሪ ሰነድ መታየት አለበት። የትምህርት ቤቱ ኃላፊ የተማሪ ሰነዶች ጠባቂ ባለ ሥልጣን ነው/ናት። የዲስትሪክት የምዝገባ ቢሮ እና የተማሪ መዛግብት የምሩቅ እና ለቀድሞ ተማሪዎች የተማሪ መዛግብት ኦፍሼላዊ ጠባቂ ነው።

**የትምህርት ሰነዶችን ማግኘት**

ወላጅ/አሳዳጊ ("ወላጅ") የልጆቻቸውን የትምህርት ፋይል የመመርመር እና የመከለስ መብት አላቸው። ነገር ግን፣ ተማሪ 18 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ/ች ("መስፈርት የሚሞላ የተማሪን ")፣ የትምህርት ሰነዶች የመመርመር እና የመከለስ፣ እንደዚሁም ሰነዶቹ እና በውስጡ ያሉትን የግል መለያ መረጃ እንዲገለፅ የመፍቀድ መብት አለው/አላት። መስፈርት የሚሞላ ተማሪ ለፌዴራል ታክስ ዓላማዎች ሲባል ጥገኛ ከሆነ/ች፣ ወላጆቹ/ቿ ከተማሪው/ዋ የጽሁፍ ፈቃድ ሳይፈልጉ የተማሪው/ዋን የትምህርት ሰነድ ማየት ይፈቀድላቸዋል።

የተማሪ ሰነድን ለማግኘት በሚጠየቅበት ጊዜ ሁሉ፣ በዚህ ፖሊሲ በተሰጠ ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር፣ ፋይሉን ለማየት ከወላጅ ወይም መስፈርት ከሚሞላ ተማሪ የጽሁፍ ፈቃድ መሰጠት አለበት። ኃላፊው/ዋ፣ በጽሁፍ ሲጠየቅ/ሲትጠየቅ፣ ሰነዶቹን ለመመርመር እና ለመከለስ እንዲቻል ያደርጋል/ታደርጋለች፤ ለምርመራው እና ለክለሳውም ቀን እና ሰዓት ይወስናል/ትወስናለች።

ወላጅ ወይም መስፈርት የሚሞላ ተማሪ የተማሪ ሰነዶችን የሚመረምሩት በኃላፊው/ዋ እና/ወይም በኃላፊው/ዋ በሚወከሉ በሌላ/በሌሎች ሰው/ሰዎች ፍትለፊት መሆን አለበት።

ሰነዱ ራሱ ከትምህርት ቤቱ መውጣት የለበትም። ነገር ግን፣ ከተጠየቀ ከ 45 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ከላይ በተገለጹት ሂደቶች መሰረት., ለወላጅ ወይም ብቁ ተማሪ የሰነዱ ግልባጭ/ቅጂ ለወላጅ ወይም መስፈርት ለሚሞላ ተማሪ አግባብ ባለው ጊዜ ውስጥ መሰጠት አለበት።

ሰነዱ ስለ ሌሎች ተማሪዎች መረጃ ሲኖረው፣ ወላጅ ወይም መስፈርት የሚሞላ ተማሪ ስለ የተወሰነ ተማሪ የሚመለከት መረጃ ብቻ ያገኛሉ።

**VI የትምህርት ሰነዶችን ለማማሻል/ለመቀየር/ለማስተካከል መጠየቅ**

ወላጅ ወይም መስፈርት የሚሞላ ተማሪ ትክክል አይደለም፣ አሳሳች ነው አለበለዚያም የተማሪው/ዋን የግል ምስጥር መጠበቅ ሙብት ይጥሳል ብለው የሚያምኑትን የተማሪ ሰነድ መሻሻል/መታረም ያለበትን የሰነዱ ክፍል በግልጽ በመለየት እንዲሻሻል/እንዲታረም በጽሁፍ ለትምህርት ቤቱ ኃላፊ ወይም አግባብ ላለው የትምህርት ቤት አስተዳደር ጥያቄያቸውን በማቅረብ ድስትሪክቱን መጠየቅ ይችላሉ። ጥያቄው የሚቀርበው ሰነዱ መጀመሪያ ከተመረመረ በኃላ ብዙ ሳይቆይ መሆን አለበት።
ምህርት ቤቱ
ኃላፊው/ዋ ከሚመለከተው ሰው ጋር በጉዳዩ ላይ ከተወያዩ በኃላ፣ በወላጅ ወይም መስፈርት በሚሞላ ተማሪ የቀረበው የሰነድ ጥያቄ እንዳይቀየር ከወሰነ፣ ውሳኔው ለወላጅ ወይም መስፈርት ለሚሞላ ተማሪ ይገለጽላቸዋል፤ በውሳኔው ላይ ቅሬታ ካላቸውም ለሚመለከትው ክፍል አቤቱታ የማቅረብ ሙብት እንዳላቸው ይመክራሉ።

በችሎት የአቤቱታ ማቅረብ ጥያቄ በጽሁፍ ለሱፐርንተንደንቱ ይቀርባል። ዲስትሪክቱ በተዋዋይ ወገኖች መካከል ስምምነት ካልተደረገ በስተቀር. የተጠየቀውን ችሎት ቀን በ 10 ቀናት ዉስጥ ቀጠሮ ይይዛል። ችሎቱ በሚከተለው መልኩ ይከናወናል።

ሀ. በተዋዋይ ወገኖች መካከል ስምምነት ካልተደረገ በስተቀር. ችሎቱ ጥያቄው ከቀረበ በኃላ በ15 የትምህርት ቀናት ውስጥ ይካሄዳል። የችሎቱ ቀን፣ ቦታ እና ሰዓት ለወላጅ ወይም መስፈርት ለሚሞላ ተማሪ በፖስታ ወይንም በኢሜይል ይሰጣል ።

ለ. ችሎቱ የሚካሄደው በትህምርት ቤቱ ኃላፊ ወይም በበላይ አለቃ በጽሁፍ በሚወከል/በሚትወከል በከፍተኛ የድስትርክቱ ደረጃ የአስተዳደር ባለ ሥልጣን ነው። ችሎቱን የሚመራ ባለ ሥልጣን የመጀመሪያ ውሳኔውን የሰጠ/ች ኃላፊ መሆን ወይንም ከዚያ የርእሰመምህር ትምህርት ቤት ሌላ አስተዳዳሪ መሆን የለበትም።

ሐ. ወላጆች ወይም መስፈርት የሚሞሉ ተማሪዎች ጉዳዩን አስመልክቶ ተገቢውን ማስረጃ እንዲሰጡ ፍትሃዊነት የተሞላው ዕድል ሊሰጣቸው ይገባል። በተጨማሪም በራሳቸው ወጪ ከሚፈልጉት ሰው ወይም ጠበቃ ምክር ሊያገኙ ይችላሉ።

መ. ባለ ሥልጣን/ኃላፊ ፤ ችሎቱ ከተጠቃለለ በኃላ በ10 የትምህርት ቀናት ውስጥበጉዳዩ ውሳኔ ይሰጣል/ትሰጣለች ውሳኔውን ለወላጅ ወይም መስፈርት ለሚሞላ ተማሪ በፖስታ ወይንም በኢሜይል ይላካል።

ሠ. የባለ ሥልጣኑ ውሳኔ በችሎቱ ላይ በቀረበው ማስረጃ ላይ የሞረኮዛል፤ ውሳኔው የማስረጃውን ማጠቃለያ ሀሳብ እና የውሳኔውን ምክንያት ማካተት አለበት።

ረ. ወላጅ ወይም መስፈርት የሚሞላ ተማሪ በሰነዱ ውስጥ ባለው መረጃ ላይ ያላቸውን አስተያየት ወይም ያልተስማሙበትን የሰነዱ ክፍል ከነምክንያቱ ጭምር በመግለጽ ሰነዱ ውስጥ የማስገባት ሙብት እንዳላቸው በውሳኔው ውስጥ መካተት አለበት። በሰነድ ውስጥ የተካተተ ማንኛውም ማብራሪያ በትምህርት ድስትሪክት መቆጣጠር አለበት። የተማሪ ሰነድ በትምህርት ቤቱ ለሌላ አካል ከተገለጸ፣ ማብራሪያውም አብሮ መገለጽ አለበት።

## VII.ከሌሎች የትምህርት ድስትሪክቶች ሰነዶችን መጠየቅ

ተማሪ ከሌላ የትምህርት ድስትሪክት ወደዚህኛው የትምህርት ድስትሪክት ሲዛወር/ሲትዛወር፣ የተማሪው/ዋ ሰነድ ወደዚህኛው ትምህርት ቤት ካልተላለፈ፣ ተቀባዩ ትምህርት ቤት የተማሪው/ዋ ሰነድ እንዲላክ የተማሪው/ዋን የቀድሞ ድስትሪክት ይጠይቃል።

***VIII.*ከክፍለ ግዛት ድርጅቶች/ተቋማት መረጃዎችን እና ሰነዶችን ጠይቆ ማግኘት**

በክፍለ ግዛት ሕግ ውስጥ፣ የትምህርት ድስትሪክት ሰራተኞች ሕጋዊ ሥራቸውን ለመፈጸም እና ኃላፊነታቸውን ለመወጣት፣ እንደዚሁም የህዝብን እና የተማሪው/ዋን ደኅንነት ለመጠበቅ፣ አስፈላጊውን የተማሪ መረጃ ጠይቆ የማግኘት ሙብት አላቸው። እንደዚህ ያለ መረጃ በኮሎራዶ የሕጻናት ሕግ ሥር የተለያዩ ጉዳዮችን ከሚፈጽም ከማንኛውም የክፍለ ግዛት ተቋም/ድርጅት ሕግ ክፍል ማግኘት ይቻላል።

እንደዚህ ዓይነቱን መረጃ የሚቀበል የትምህርት ድስትሪክት ሰራተኛ ለሕጋዊ ተግባራት ብቻ መጠቀም አለባቸው፤ አለባለዚያ ያገኙትን መረጃ/ሰነድ በምስጢር መያዝ አለባቸው።

**ሰነዶችን ወደ ሌሎች የትምህርት ድስትሪክቶች ማዘዋወር**

የተማሪ ሰነዶች፣ የተማሪ ሥርዓት ሰነዶችን ጨምሮ፣ ሰነዱን ከጠየቁ እና ተማሪው/ዋ መማር የሚፈልግበት/የሚያቅድበት ከሌላ የትምህርት መዋቅር ፣ ወይም ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ባለ ሥልጣናት ፈቃድ ሳይጠየቅ ሊዘዋወሩ ይችላሉ። ከተጠየቀ፣ ድስትሪክቱ የሰነዱን ግልባጭ/ቅጅ ለወላጅ ወይም መስፈርት ለሚሞላ ተማሪ ይሰጣል።

እንደዚህ ዓይነቱ መረጃ ተማሪው/ዋ ወደሚዛወርበት/ወደሚትዛወርበት ከሌላ የትምህርት ድስትሪክት ጋር ከተለዋወጠ፣ በፌዴራል ሕግ እና በ1974 በወጣው በፌዴራል የትምህርት ሙብት እና የግል ምስጢር የመጠበቅ አዋጅ (“FERPA”) መስፈርት መሰረት መከናወን አለበት።

**ያለ የጽሁፍ ፈቃድ መረጃን መስጠት**

የትምህርት ድስትሪክት ከወላጅ ወይም መስፈርት ከሚሞላ ተማሪ የጽሁፍ ፈቃድ ሳያገኝ የተማሪን የግል መለያ መረጃ ከተማሪ ሰነዶች ለሚከተሉት አካላት መስጠት ይችላል፡

1. ለህጋዊ የትምህርት ጉዳይ መረጃውን ለተማሪው/ዋ የትምህርት ክንውን መሻሻል ሥራ ወይም ደኅንነቱ የተጠበቀ እና ሥርዓት ያለው የመማሪያ አከባቢ ለመጠበቅ/ለመቆጣጠር ዓላማ ሲፈለግ በትምህርት መዋቅሩ ውስጥ ለሚሰሩ ለሌሎች የትምህርት ቤት ባለ ሥልጣናት። የሚሰጠው መረጃ ለተማሪው/ዋ ወይም ለሎች ሰላም እና ደኅንነት ተጽዕኖ ያለው ምግባር የሚመለከት የተማሪ ሥርዓት መረጃን ያካትታል። ለዚህ ፖሊሲ ዓላማዎች፣ “የትምህርት ቤት ባለ ሥልጣናት” የድስትሪክቱ ሰራተኛ የሆነ እና አስተዳደር፣ ኃላፊ/አለቃ፣ አስተማሪ ወይም ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች፣ ድስትሪክቱ ልዩ ሥራዎችን ለማሰራት የተኮናተረ ሰው ወይም ኩባኒያ (ምሳሌ፡ አቃቤ ሕግ፣ ኦዲተር፣ አማካሪዎች እና የጤና እንክብካቤ ሰጪዎች)፤ ያለ ክፍያ በመደበኛ ኮሚቴ ውስጥ የሚሰራ/የሚትሰራ ወይም ሌላ የትምህርት ቤት ኃላፊን በሥራው/ዋ የሚረዳ/የሚትረዳ ሰው (በጎ አድራጊ)። ለዚህ ፖሊሲ ዓላማ፣ የትምህርት ቤት ኃላፊዎች የሚከተሉትን ያጠቃልላል፣ በነዚህ ብቻ ግን አይወሰንም፡

   ሀ. የትምህርት ቦርድ አባል።

ለ. ለአስተዳደራዊ፣ ለኃላፊነት፣ ወይም ለአስተማሪነት ቦታ/ሙያ በክፍለ ግዛት የጸደቀ/ች እና በቦርዱ የተሰየመ/ች ወይም የተመደበ/ች ሰው።

ሐ. ለአስተዳደራዊ፣ ለኃላፊነት፣ ወይም ለአስተማሪነት ቦታ/ሙያ በክፍለ ግዛት የጸደቀ/ች እና እንደ የጊዜያዊ ተተኪ በቦርዱ የተመደበ/ች ወይም የተሰየመ/ች ሰው።

መ. የተለየ ሥራን ለመስራት በቦርዱ የተቀጠረ/ች ሰው፣ ለምሳሌ፡ ጸሀፊ፣ መዝገብ ክፍል፣ ኢቃቤ ሕግ ወይም ኦዲተር  የአውቶቡስ ሹፌር፣ የአትሌቲክስ አሰልጣኝ፣ የህክምና አማካሪ፣ ቴራፒስት እና የመስመር ላይ አገልግሎት አቅራቢዎች የትምህርት አገልግሎቶችን ለማቅረብ ያገለግላሉ።

ሠ. ተማሪው/ዋ በሚማርበት/በሚትማርበት ትምህርት ቤት ውስጥ የሚሰሩ አስተማሪዎችና ሌሎች ሠረተኞች  ሲሆን ውስን እና ሕጋዊ ለሆኑ የትምህርት ጉዳዮች መረጃው የተማሪው/ዋን የትምህርት ክንውን ለማሻሻል ወይም ደኅንነቱ የተጠበቀ እና ሥርዓት ያለው የመማሪያ ቦታ ለመፍጠርና ለመጠበቅ ካስፈለገ።

"ሕጋዊ የትምህርት ጉዳይ"የትምህርት ቤት ኃላፊዎች ለሚከተሉት ጉዳዮች ሲፈልጉ የሚል ትርጉም አለው፡

ሀ. በሥራ ድራሻው/ዋ ውስጥ በተሰጠው ለሥራ ተግባራት ወይም በውል ስምምነት አስፈላጊ ከሆነ፤

ለ. መረጃው ለድስትሪክት ኃላፊ የሥራ አውድ ውስጥ የሚያስፈልግ ከሆነ፤  ከኃላፊው/ዋ የሥራ ተጠያቂነት/ድርሻ ውጪ ለሆኑ ዓላማዎች አይደለም፤

ሐ. መረጃው የተወሰኑ ሥራዎችን ለማከናወን ተፈላጊ/ተገቢ ከሆነ ወይም ስለተማሪው/ዋ ውሳኔ ለመስጠት ካስፈለገ፤ እና

መ.የመረጃው ጥቅም መረጃው ካስፈለገበት ዓላማ ጋር በጽኑነት የሚሄድ ከሆነ።

2. ተማሪው/ዋ መማር የሚፈልግበት/የሚትፈልግበት ሌላ ትምህርት ቤት ወይም የትምህርት መዋቅር ወይም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ኃላፊዎች። በዚህ ሁኔታ ውስጥ፣ የተማሪ የሥርዓት መረጃ ሊካተት ይችላል። ወላጆች እና መስፈርት የሚሞሉ ተማሪዎች በዚህ መስፈርት የተዛወሩትን የሰነዶች ግልባጭ/ቅጂ ጠይቀው የማግኘት መብት አላቸው።

3. በየቤተሰብ የትምህርት መብቶች እና የግል ምስጥር የመጠበቅ አዋጅ እና ተያያዥ የፌዴራል ሕግና ደንቦች ውስጥ የተጠቀሱት ባለ ሥልጣናት። እነዚህም፡ የዩናይትድ ስቴትስ ተቆጣጣሪ ጀኔራል (የመንግሥት የተጠያቂነት ቢሮ)፣ የዩ.ኤስ የትምህርት ሚኒስቴር፣ ሀገር አቀፍ የትምህርት ተቋም (፣ የትምህርት ሚኒስቴር ረዳት ሚኒስቴር፣ የክፍለ ግዛት የትምህርት ባለ ሥልጣናት፣ እና ለተማሪዎች ጤና እና ደኅንነት የሚሰጡ የድንገተኛ አገልግሎቶችን የሚመረምሩ ወይም የሚያቀርቡ ባለ ሥልጣናት። የጤና እና የደኅንነት ድንገተኛ ጉዳይ ሲከሰት፣ መረጃ የሚሰጠው፡

ሀ. ለተማሪው/ዋ ወይም ለሌሎች ተማሪዎች ጤንነት እና ደኅንነት የአደጋው አሳሳቢነት መሰረታዊ/አስከፊ ከሆነ

ለ. ለድንገተኛ ክስተት ጊዜ አስፈላጊ ከሆነ

ሐ. መረጃው የሚሰጣቸው ሰዎች ብቁ እና የድንገተኛ ክስተቱን የመቆጣጠር ሥራ የሚሰሩ/የሚመለከታቸው ከሆነ

መ. በድንገተኛ ክስተት ውስጥ ጊዜ በጣም አስፈላጊ እና አጣዳፊ ጉዳይ ከሆነ

4. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከፍተኛ በፊት ተማሪው/ዋን የበለጠ ለመርዳት፣ በትምህርት ድስትሪክቱ የሚማርን/የሚትማርን  ወይም ሊማር/ሊትማር ያለውን/ያለችውን ተማሪ አስመልክቶ የወንጀል ጉዳይ/ሁኔታ ምርመራ ለሚያደርግ የወንጀለኛ ፍትሕ ድርጅት።እንደዚህ ዓይነቱ መረጃ የተማሪ ሥርዓት እና የትምህርት ክትትል መረጃ ብቻ ማካተት አለበት፤ ለተፈለገው ወይም ሕግ ከሚያዘው በስተቀር፣ ከተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ በቅድሚያ የጽሁፍ ፈቃድ ሳያገኙ መረጃው ለሌላ ለማንኛውም ሦስተኛ አካል/ወገን እንደማይገለጽ የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ሲያቀርብ ብቻ ለወንጀለኛ ፍትሕ ድርጅት መረጃው ይሰጣል።

5. የተማሪ  የገንዘብ ድጋፍ/እርዳታ ማመልከቻ ወይም ገንዘቡን ማግኘት ጋር ሲያያዝ።

6. ዕውቅና ሰጪ ተቋማት ሥራቸውን ለማከናወን ሲያስፈልግ።

7. ድስትሪክቱ አብሮ ለመስራት በጽሁፍ ስምምነት ያደረገ ወይም የውል ስምምነት የፈረመ የፌተና፣ እና የጥናት እና ምርምር ድርጅቶች ሲሆን፣ ድርጅቶቹ መረጃውን በምስጢር መያዝ እና ጉዳዩ ካለቀ በኃላ እና መረጃውን የማይፈልጉ ከሆነ በሥርዓቱ ማስወገድ አለባቸው።

8. በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የሚፈለግ ማንኘውም ሰው። ከፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ በፊት ትምህርት ቤቱ ወላጅን ወይም መስፈርት የሚሞላ ተማሪን ጉዳዩን ለማሳወቅ አስፈላጊውን ጥረት ሁሉ ያደርጋል። ድስትሪክቱ እንደዚህ ዓይነቱን የማሳወቅ ተግባር የማያደርገው የፍርድ ቤቱ ትዕዛዙ የተሰጠው በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሲሆን ወይም ለማንኛውም የሕግ ማስከበር ዓላማ ሆኖ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዙ/መጥሪያው እንዳይገለጽ ወይም የትዕዛዙ ይዘት እና መረጃዎቹ በምስጢር እንዲያዙ ካዘዘ ነው።

9. ለዩናይትድ ስቴትስ የጦር ኃይል ካድሬዎች/ተጠሪዎች ሆኖ ለምልመላ ዓላማ ብቻ። ወላጅ/አሳዳጊ ወይም መስፈርት የሚሞሉ ተማሪዎች መረጃው እንድ ካልጠየቁ በስተቀር፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ስም፣ አድራሻ እና የቤት የስልክ ቁጥሮች መረጃ ለውትድርና ምልመላ ባለ ሥልጣናት ጥያቄ ባቀረቡ በ90 ቀናት ውስጥ ይሰጣቸዋል።

10. ለፌዴራል የገቢ ታክስ ዓላማ ሲባል ከ18 ዓመት በላይ የሆኑትን ተማሪዎች በእነርሱ ሥር እንደሚተዳደሩ የሚገልጹ እና ይገባኛል ለሚሉ ወላጆች።

11. የተማሪውን የጉዳይ አስፈጻሚ  የማግኘት መብት ያለው የኤጀንሲ ኬዝ ሰራተኛ ወይም ሌላ የግዛት ወይም የአካባቢ የህጻናት ደህንነት ኤጀንሲ ወይም የጎሳ ድርጅት ተወካይ እንደዚህ አይነት ኤጀንሲ ወይም ድርጅት  በሚመለከተው የግዛት ወይም የጎሳ ህግ መሰረት ለተማሪው ጤና እና ለእንክብካቤ እና ጥበቃ በህጋዊ መንገድ ተጠያቂ ስለሆነ፣ .

ከወላጅ ወይም  መስፈርት ከሚሞላ ተማሪ የጽሁፍ ፈቃድ ሳያገኝ፣ የትምህርት ድስትሪክቱ ግለሰብ በተናጥል የማይገለጽበትን የቡድን/የጋራ የትምህርት የክንውን መረጃን መግለጽ ይችላል።

***XI በጽሁፍ ፈቃድ መረጃን መስጠት***

የተማሪን የግል መረጃ ከመግለጹ በፊት ድስትሪክቱ በሕግ ወይም በፖሊሲ መሰረት ከሚመለከተው ሰው የጽሁፍ ፈቃድ ማግኘት አስፈላጊ ሲሆን፣ ለወላጅ መስፈርት ለሚሞላ ተማሪ የሚቀርበው ማስታወቂያ የሚከተሉትን ነጥቦች ማካተት አለበት፡

1. የሚሰጠው የተወሰነ የመረጃ ክፍል
2. መረጃው የሚሰጥበት የተወሰኑ ምክንያቶች
3. መረጃውን የሚጠይቅ ሰው፣ ድርጅት ወይም ተቋም ማንነት እና መረጃው ለምን ሥራ/ተግባር እንደሚፈለግ
4. ሰነዶቹ የሚገለጹበት ዘዴ ወይም ስልት/አካሄድ
5. የሚሰጡትን የሰነዶች ግልባጭ ወይም ቅጅ የመከለስ ወይም የማግኘት መብት

የወላጅ ወይም መስፈርት የሚሞላ ተማሪ ፈቃድ ለተፈለገበት/ለተሰጠበት ለተወሰነ ጉዳይ ብቻ ይሰራል። ተማሪ በማንኛውም የትምህርት ዓይነት፣ የትምህርት ቤት ተግባራት፣ በልዩ ትምህርት መርሃ ግብር ወይም በሌላ በማንኛውም የትምህርት ቤት መርሃ ግብር እንዲሳተፍ/እንዲትሳተፍ ፈቃድ መስጠት አስፈላጊ የሆነውን የተወሰነ ፈቃድ አይተካም። የተፈረሙት የፈቃድ መስጫ ቅጾች በሙሉ በትምህርት ድስትሪክቱ መያዝ አለባቸው።

***XII የተማሪ የሥርዓት መረጃን ለትምህርት ቤት ሰራተኞች መስጠት***

በፌዴራል ሕግ መሰረት፣ ኃላፊ ወይም ተወካይ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ከተማሪዎች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ካላቸው አስተማሪዎች ወይንም ከሠረተኞች  እና  ከተማሪ ጋር ጋር የተማሪ ሥርዓት መረጃ ይለወወጣል። የዚህ ጉዳይ አስፈላጊነት ዓላማ የትምህርት ቤት ሰራተኞች ለሌሎች ሰላም እና ደኅንነት የሚያሰጉ ጉዳዮችን ለማሳወቅ ነው።

ለዚህ ፖሊሲ ዓላማ፣ ‘ ‘የተማሪ ሥርዓት መረጃ’’ ማለት በኃላፊ  የሚያዝ የተማሪ የግል መረጃ ሆኖ ተማሪው/ዋ የተማሪ ሥነ ምግባር ሕግ የጣሰ/ች እና/እንደዚያ እንደሆነ  ቀደም ሲል በነበረው የተማሪው/ዋ የሥርዓት አልበኝነት ሁኔታ ላይ በመመሰረት ተማሪው/ዋ ለተማሪዎች እና ለትምህርት ቤት ሰራተኞች ሰላም እና ደኅንነት የሚያስፈራ ሊሆን ይችላል።

የተማሪው/ዋ ምግባር ለሌሎች ተማሪዎች ወይም ለትምህርት ቤት ባለ ሥልጣናት ሰላም እና ደኅንነት የሚያስፈራ ከሆነ አስተማሪዎች የተማሪዎቻቸውን የሥርዓት መረጃ ከኃላፊ ወይም ከተወካይ ጥይቆ ማግኘት አግባብነት አለው።

የተማሪ የሥርዓት መረጃ የሚሰጠው/የሚሰጣት ማንኛውም/ማንኛዋም አስተማሪ መረጃውን በምስጢር መያዝ አለበት/አለባት፤ በዚህ ፖሊሲ ውስጥ በተሰጠው ልዩ ሁኔታ መሰረት ካልሆነ በስተቀር፣ መረጃው ለሌላ ሰው መስጠት የለበትም።

***XIII. ለውትድርና ምልመላ ባለ ሥልጣናት የተማሪ መረጃን መስጠት***

ወላጅ  መረጃው እንዳይሰጥ ካልጠየቁ በስተቀር፣ በውትድርና ምልመላ ባለ ሥልጣናት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ መረጃ ከተጠየቀበት ጊዜ ጀምሮ በ90 ቀናት ውስጥ የተማሪ ስም፣ አድራሻ እና የቤት የስልክ ቁጥሮች፣ እንደዚሁም የማውጫ መረጃ የሰጣል። ድስትሪክቱ ለሚሰጠው አገልግሎት አግባብ ያለው እና የደንበኝነት ክፍያ መረጃውን በጠየቀ ክፍል ይሸፈናል።

‘ XIV.**(ሜድኬድ) ለሚባል በመንግሥት ለሚደጎም የጤና እንክብካቤ የተማሪ መረጃን መስጠት**
ተማሪ በኮሎራዶ ‘Medicaid’ (ሜድኬድ) ፕሮግራም ሲመዘገብ/ሲትመዘገብ፣ ተማሪው/ዋ ለ ‘Medicaid’ ፕሮግራም መስፈር የሚሞላ/የሚትሞላ መሆኑ/ኗን ለማረጋገጥ እንዲቻል፣ ድስትሪክቱ የተማሪው/ዋን ስም፣ የትውልድ ቀን እና ጾታ የሚያካትት የተማሪው/ዋን መረጃ የኮሎራዶ  ‘Medicaid’ ድርጅት/ተቋም ለሆነው ለ ‘Health Care Policy and Financing’ ለሚባለው የጤና አጠባበቅ እና የገንዘብ ቁጥጥር ቢሮ ይሰጣል። የሕሳብ ደረሰኝን ለመላክ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ከመግለጹ በፊት፣ ድስትሪክቱ ከወላጅ  በየዓመቱ የጽሁፍ ፈቃድ ማግኘት አለበት።

XV **ለወንጀለኛ ፍትሕ ድርጅቶች/ተቋማት የተማሪ መረጃን መስጠት**

አስፍላጊ ሆኖ ሲገኝ ለወንጀል ነክ ጉዳዮች ከመፈተሹ/ሿ በፊት ተማሪው/ዋን የበለጠ ለመርዳት በትምህርት ድስትሪክቱ ውስጥ የተመዘገበን/የተመዘገበችን ወይም ወደፊት የሚመዘገብ/የሚትመዘገብ የተማሪ ሥርዓት  እና የትምህርት ክትትል መረጃ ለወንጀለኛ ፍትሕ ድርጅቶች/ተቋማት እንዲሰጡ በሕግ ይገደዳሉ። እንደዚህ ያለ መረጃ ለወንጀለኛ ፍትሕ ተቋማት/ድርጅቶች የሚሰጠው ድርጅቶቹ፣ በልዩ ሁኔታ ካልተገደዱ ወይም በሕግ ካልተፈለገ በስተቀር፣ አስቀድሞ ከወላጅ/አሳዳጊ የጽሁፍ ፈቃድ ሳያገኙ መረጃውን ለሌላ አካል/ክፍል እንደማይገልጹ በምስክር ወረቀት ሲያረጋግጡ ነው።

***XVI ለኮሎራዶ የከፍተኛ ትምህርት ኮሚሽን የተማሪ መረጃን መስጠት***

በየትምህርት ዘመኑ በተኅሣሥ 31 ወይም ከዚያ በፊት፣ በሕግ የሚፈለገውን ከመለስተኛ ደረጃ ትምህርት በኃላ ያሉትን የትምህርት ዕድሎች እና የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ተቋማት መግቢያ መስፈርቶች ለመስጠት እንዲቻል፣ የትምህርት ድስትሪክት ለኮሎራዶ የከፍተኛ ትምህርት ኮሚሽን በ8ኛ ክፍል የተመዘገቡትን የተማሪዎች ስም እና የፖስታ አድራሻ መስጠት አለበት።

***XVII .ለሌሎች ወገኖች የተማሪ መረጃን መስጠት***

በዚህ ፖሊሲ ውስጥ እንደተገለጸ በስተቀር፣ አስቀድሞ ከወላጅ ወይም መስፈርት ከሚሞላ ተማሪ የጽሁፍ ፈቃድ ሳይሰጥ የተማሪ ሰነድ ለሌሎች ሰዎች እና ወገኖች አይሰጥም።

የግል መረጃ ለሦስተኛ ወገን የሚሰጠው መረጃው በምስጢር ስለመያዙ ማረጋገጫ ከተገኘ ነው።

**በተማሪ የትምህርት ሰነድ ውስጥ ያሉትን መረጃዎች መግለጽ**

የትምህርት ድስትሪክት ከወላጅ ወይም መስፈርት ከሚሞላ ተማሪ የጽሁፍ ፈቃድ ሳይፈልግ በተማሪ የትምህርት ሰነድ ውስጥ ያሉትን መረጃዎች አግባብ ላለው ክፍል ሊሰጥ ይችላል። እንደዚህ ያሉ መረጃዎች ከተገለጹ ጎጂ ያልሆኑ እና የግል ምስጢር ማባከን ያልሆኑ ናቸው። ወላጅ ወይም መስፈርት የሚሞላ ተማሪ የማንኛውንም ወይም የሁሉንም መረጃ ሥያሜ በጽሁፍ ሊቃወሙ ይችላሉ- ይህ የሚቻለው ተቃውሞውን እስከ ሁለተኛ የትምህርት ሣምንት ድረስ ለተማሪው/ዋ የትምህርት ቤት ኃላፊ ቢሮ  በጽሁፍ ካስገቡ ነው። እንደዚህ ዓይነቱ መረጃ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፡ የተማሪው/ዋ ስም፣ የሚማረው/የሚትማረው ዋና የትምህርት ዓይነት፣  የክፍል ደረጃ፣ የክፍል ምደባ ፣ የስም ዝርዝሮች፣ተማሪው/ዋ

መደበኛ በሆኑ ተግባራት እና ስፖርቶች ያለውን/ያላትን ተሳትፎ፣ የአትሌቲክስ ቡድን አባላት ክብደት እና ቁመት፣ የትምህርት ክትትል ቀናት፤የምዝገባ ቀናት፣ ያገኙት ድግሪዎችን እና ሽልማቶች፣ ተማሪ በቅርብ ጊዜ የተከታተላቸው እና የቀድሞ የትምህርት ተቋም፣ አመታዊ መጽሃፍ፣ የተማሪውን በድራማ ፕሮዳክሽን ውስጥ ያለውን ሚና የሚያሳይ የመጫወቻ ቢል፣ የተማሪው ስም በምረቃ ፕሮግራም፣እና ሌሎች ተመሳሳይ መረጃዎች። በኮሎራዶ ሕግ መሰረት የተማሪ የስልክ ቁጥሮች እና የአሁን ተማሪዎች ኢሜል አድራሻዎችን ጨምሮ አድራሻ አይገለጽም።

### *XIX* መብትን አለመጠቀም

ወላጅ ወይም መስፈርት የሚሞላ ተማሪ በዚህ ፖሊሲ ውስጥ የተገለጹትን መብታቸውን በከፊል ወይም በሙሉ አለመጠቀም ይችላሉ። በጽሁፍ ሆኖ በወላጅ ወይም መስፈርት በሚሞላ ተማሪ ካልተፈረመበት መብትን ያለመጠቀም ጥያቄ ሕጋዊ አይሆንም። ድስትሪክቱ ይህንን ጉዳይ አያስገድድም፣ ነገር ግን ሊፈልግ ይችላል። በዚህ መስፈርት የሚሰጥ የመብት አለመጠቀም ጥያቄ በማንኛውም ጊዜ በጽሁፍ ሊነጠቅ/ሊቀየር ይችላል።

### XX የአስተዳደር ህግ

ዲስትሪክቱ የቤተሰብ የትምህርት መብቶች እና ግላዊነት ህግን እና ደንቦቹን እንዲሁም የተማሪ ትምህርት መዝገቦችን ምስጢራዊነት የሚያዘዉን የክልል ህግን ማክበር አለበት። ዲስትሪክቱ ሁሉንም እርምጃዎች የመውሰድ እና በህግ ያሉትን ሁሉንም አማራጮች የመጠቀም መብት አለው.

ይህ ፖሊሲ በሚመለከተው የግዛት ወይም የፌደራል ህግ ድንጋጌን የማይመለከት ከሆነ፣ ወይም ከሚመለከተው የክልል ወይም የፌደራል ህግ ጋር የማይጣጣም ወይም የሚጋጭ ከሆነ፣ የሚመለከታቸው የክልል ወይም የፌደራል ህጎች ድንጋጌዎች ሥራ ላይ ይዉላሉ።
ለመጨረሻ ጊዜ የተሻሻለው፤ ዴሰምበር 10፣ 2007
የአሁኑ ክለሳ ሰፕተምበር *2022*

ሕጋዊ ዋቢዎች፤
20 U.S.C. §1232g (የ 1974 የቤተሰብ የትምህርት መብቶች እና የግል ምስጢር መጠበቅ አዋጅ)
34 C.F.R. §99.1 ቀጣይ ( *FERPA* ሕገ-ደንቦች)
20 U.S.C. 7908 (የውትድርና ምልመላ መረጃ)
34 C.F.R § 300.610 እና ተከታታዮች. (የተማሪ መዝገቦችን ምስጢራዊነት በተመለከተ የIDEIA ደንቦች
C.R.S. 19-1-303 ሂ 304 (በ 'የኮሎራዶ ልጆች ሕግ' መሰረት ሰነዶችን እና መረጃዎችን መግለጽ)
C.R.S. 22-1-123 (ድስትሪክት 'FERPA' ለሚባል የቤተሰብ የትምህርት መብት እና የግል ምስጢር የመጠበቅ አዋጅ መታዘዝ አለበት)
C.R.S. 22-32-109 (1)(ff) (የ8ኛ ክፍል ተማሪዎችን ስም እና የፖስታ አድራሻዎች ለኮሎራዶ የከፍተኛ ትምህርት ኮሚሽን የመስጠት ፖሊሲን የማውጣት ኃላፊነት)
C.R.S. 22-32-109.1(6) (የትምህርት ቤቶችን ደኅንነት ከመጠበቅ ፍላጎት የተነሳ ከክፍለ ግዛት እና ከፌዴራል ሕግ ጋር የሚሄድን የመረጃ መስጠት ፖሊሲን የማውጣት ኃላፊነት)
C.R.S. 22-32-109.3(2) (ለወንጀለኛ ፍትሕ ተቋማት የተማሪ ሥርዓት እና የትምህርት ክትትል መረጃን የመስጠት ኃላፊነት)
C.R.S 22-32-126 (5) (የዲሲፕሊን መረጃን የማሳወቅ የርእሰ መምህሩ ግዴታ);
C.R.S. 22-33-106.5 (በሁከት እና በሕገ-ወጥ የወሲብ ምግባር ወንጀል ምክንያት በፍርድ ቤት በጥፋተኝነት መፈረድ)
C.R.S. 22-33-107.5 (ትምህርትን ያለመከታተል ጉዳይ አስመልክቶ የትምህርት ድስትሪክት ማሳሰቢያ)
C.R.S 24-10-106.3 (የክሌር ዴቪስ ትምህርት ቤት ደህንነት ህግ)
C.R.S 24-72-204(2)(ሠ) (በSafe2Tell ፕሮግራም የተቀበሏቸው፣ የተሰሩ ወይም የተያዙ ዕቃዎችን ምርመራ አለመቀበል)።
C.R.S. 24-72-204 (3)(a)(VI) (ትምህርት ቤቶች የተማሪን ስም እና አድራሻ ያለፈቃድ መግለጽ አይችሉም)
C.R.S. 24-72-204(3)(d) (የውትድርና ምልመላ ለሚያካሄዱ የሚሰጡ መረጃዎች)
C.R.S. 24-72-204 (3)(e)(I) (በኮሎራዶ ሕግ ውስጥ ተግባራዊ የሚደረጉ የተወሰኑ የ 'FERPA' መስፈርቶች)
C.R.S. 24-72-204 (3)(e)(II) (ሰራተኞች ከግል እውቀት እና ከአስተውሎት/ከምልከታ የተገኙትን መረጃ መግለጽ)
C.R.S. 24-72-205(5) (የህዝብ ሰነድ ግልባጭ/ቅጂ ክፍያ )
C.R.S 25.5-1-116 (የ HCPF መዝገቦች ምስጢራዊነት);

ጥምር ዋቢዎች:
JK፣ የተማሪ ሥርዓት፣
JLCA፣ የተማሪ የጤና አገልግሎቶች እና መስፈርቶች
JRCA፣ ለትምህርት ድስትሪክት እና ለክፍለ ግዛት ድርጅቶች/ተቋማት የተማሪ ሰነዶችን/መረጃዎችን መስጠት

## አድልዎ አለማድረግ/ለሰዎች ሁሉ እኩል ዕድል መስጠት/የሕዝብ ግንኙነት (AC)

በትምህርት ቤቱ ማኅበረሰብ መሃል መከባበር እና መተሳሰብ እንዲኖር እና ደህንነቱ የተጠበቀ የመማሪያ እና የሥራ ቦታ እንዲፈጠር ቦርዱ በትጋት ይሰራል።በድስትሪክቱ ውስጥ በዘር፣ በቀለም፣በቀድሞ ዝርያ/ጎሳ፣ በአመለካከት፣ በጾታ፣ የፆታ ማንነት, የፆታ መግለጫ በጾታዊ አመለካከት፣ በኃይማኖት፣ በሀገር/በብሔር ስረ ነገር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በስንኩልነት ወይም በልዩ ትምህርት እገዛ አስፈላጊነት ላይ የተመሰረተ መድልዎ ለመከልከል ያሉት ትምህርት ቤቶች ለሁሉም የፌዴራል እና የክፍለ ግዛት ሕጎች እና ለተሰጡት ሕገ-መንግሥቶች ይታዘዛሉ። በዚህ መሰረት፣ መስፈርት የሚሞላ ተማሪ፣ ሰራተኛ፣ ለሥራ የሚያመለክት ሰው ወይም የህዝብ አባል የሆነ ግለሰብ በዘር፣ በቀለም፣ በቀድሞ ዝርያ/በጎሳ፣ በጾታ፣ የፆታ ማንነት, የፆታ መግለጫ በጾታዊ አመለካከት፣ በኃይማኖት፣ በሀገር/በብሔር ስረ ነገር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በስንኩልነት ወይም በልዩ ትምህርት አገልግሎቶች አስፈላጊነት ምክንያት ከተሳትፎ መገለል፣ የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞችን መነፈግ፣ ወይም በድስትሪክቱ መርሃ ግብር/ፕሮግራም ወይም ተግባር/ድርጊት ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ መድልዎ ማድረግ ክልክል ነው። በዕድሜ ምክንያት በሰራተኞች እና በሥራ አመልካቾች ላይ የሚደረግ መድልዎ በክፍለ ግዛት እና በፌዴራል ሕግ መሰረት ክልክል ነው። ተማሪዎችን እና ሰራተኞችን በተመለከተ፣ የሚከተሉት የዚህ የትምህርት ድስትሪክት ግቦች ናቸው፡

1. በክፍለ ግዛት እና በፌዴራል ሕገ-መንግሥቶች ውስጥ በተቀመጠ መሰረት፣ የሁሉንም ሰዎች መብቶች እና ግዴታዎችን ለመጠበቅ፤ አግባብ ያላቸው የወጡ ሕጎች እና ሥራ ላይ የሚውሉ የሕግ ፍችዎች።
2. የተለያዩ ግላዊ/ተናጠላዊ እና ቤተሰባዊ ባህሪዎችን ያላቸውን ሰዎች ወይም ከተለያዩ ማህበረ ኢኮኖሚያዊ፣ የዘር እና የሀገረሰብ/የጎሳ ቡድኖች ለሆኑ ልጆች/ሕጻናት እና አዋቂዎች የጋራ የሆኑ የሰው ልጆች መልካም የሆኑ የህይወት ተሞክሮዎችን/ልምዶችን ማበረታት/ማነቃቃት።
3. በትምህርት ቤቶች ላይ ተጽዕኖ የሚያደርሱ ውሳኔዎች በሙሉ ሲወሰኑ፣ ውሳኔዎቹ ያላቸውን ጥቅሞች ወይም ማኅበረሰብን በሙሉ የሚመለከት የሰዎች ግንኙነቶች ላይ የሚያመጡትን ጉዳቶች በጥንቃቄ መገምገም።

4. የትምህርት ተሞክሮን/ልምድን ለመጠቀም በሚኖሩበት ማኅበረሰብ ውስጥ ተማሪዎች እንደ ማህበረሰብ አባላት በሙሉ አቅማቸው ትምህርትን እንዲያገኙ እና የወደፊት የስራ ምኞታቸውን እንዲያሳድጉ የሚያስፈልጓቸውን ክህሎቶች ማዳበር
5. የዚህን ፖሊሲ ዓላማዎች ለማሳካት የዲስትሪክቱን ሁሉንም ልምዶች እና ፖሊሲዎች ለመገምገም
6. የዲስትሪክቱን ፖሊሲ በመጣስ ህገ-ወጥ ትንኮሳ ወይም መድልዎ ቅሬታዎችን ለመመርመር እና በትክክል ለመፍታት
7. የቦርድ ፖሊሲን እና ህግን በመጣስ ህገ-ወጥ ትንኮሳ እና መድልዎ ተጠያቂ ሆነው የተገኙ ሰራተኞችን እና ተማሪዎችን ለመመርመር እና በአግባቡ ለመቅጣት።

**ዓመታዊ ማስታወቂያ**

ድስትሪክቱ የሚሰጣቸው የትምህርት መርሃ ግብሮች፣ ተግባራት/ድርጊቶች እና የቅጥር/የሥራ ማግኘት ዕድሎች በዘር፣ በቀለም፣ በቀድሞ ዝርያ/በጎሳ፣ በአመለካከት፣ በጾታ/የፆታ ማንነት, የፆታ መግለጫ ፣ በጾታዊ አመለካከት፣ በሀይማኖት፣ በሀገር/በብሔር ስረ ነገር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በስንኩልነት ወይም በልዩ ትምህርት አገልግሎቶች አስፈላጊነት ሁኔታ ላይ እንደማይመሰረት የቅጥር አሰራርን በሚመለከት፣ ዲስትሪክቱ በአድሜ፣ በዘረመል መረጃ ወይም ከአርግዝና እና ከወሊድ ጋር በተያያዙ ሁኔታዎች እንደማያዳላ የጽሁፍ ማስታወቂያ ይሰጣል። ተማሪዎችን፣ ወላጆ ማስታወቂያው 'Title IX፣ Section 504' እና 'ADA' ለሚባሉ አቀናባሪ / አቀናጅ ግለሰብ ስም/ማዕረግ፣ አድራሻ እና የስልክ ቁጥር ማካተት አለበት።

ማስታወቂያው በሚመለከተው መሠረት በእንግሊዝኛ ቋንቋ ውስን ችሎታ ላላቸው ሰዎች በራሳቸው ቋንቋ ይሰራጫል። እንዲሁም የማየት ወይም የመስማት ችግር ላለባቸው ሰዎች እንዲቀርብ ይደረጋል።

ማሳወቂያው የቅጥር ቁሳቁሶችን ፣ የማመልከቻ ቅጾችን ፣ ክፍት የሥራ ማስታወቂያዎችን ፣ የተማሪ የመጣቃሻ መጽሐፍን የትምህርት ቤት ህትመቶች፣ የዲስትሪክቱ ድህረ ገጽ ፣ ፣ የዲስትሪክቱ ጋዜጣዎችን ፤ ዓመታዊ ማሳወቂያዎችን ጨምሮ አጠቃላይ መረጃን ጨምሮ ለወላጆች በዲስትሪክቱ ሚዲያ ውስጥ ቀጣይነት ባለው መልኩ ይታያል።

**ተጠያቂነትን የሚወስድ የሥራ ባልደረባ መሰየም**
የትምህርት ቦርድ የትምህርት ድስትሪክት 'Rehabilitation Act' ለሚባለው መልሶ ማቋቋም አዋጅ ክፍል 504 እና የአስተዳደራዊ መተዳደሪያ ደንቦችን እና 'Title IX' ማስተደደር እና የአስተዳደራዊ መተዳደሪያ ደንቦቹ፣ እና 'ADA' ለሚባለው ተግባራት/ድርጊቶች መታዘዝ ተቆጣጣሪ ሰራተኛን/ሰራተኞችን ከኃላፊነት ጋር ይሰይማል።
የዲስትሪክቱ ባለስልጣን የእውቂያ መረጃ በትምህርት ኤግዚቢሽን AC-E-1 የቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤት ዲስትሪክት ቁጥር 5 የአድሎአዊነት/የእኩልነት ማስታወቂያ እና በዲስትሪክቱ ድርጣቢያ በcherrycreekschools.org ውስጥ ይገኛል።

**ወከባ ክልክል ነው**
በዘር፣ በቀለም፣ በቀድሞ ዝርያ/በጎሳ፣ በአመለካከት፣ በጾታ፣ የሥርዓተ-ፆታ ማንነት, የፆታ መግለጫ በጾታዊ አመለካከት፣ በሀይማኖት፣ በሀገር/በብሔር ስረ ነገር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በስንኩልነት ወይም በልዩ ትምህርት አገልግሎቶች አስፈላጊነት ምክንያት ሌላውን ግለሰብ ማዋከብ/ማስጨነቅ በክፍለ ግዛት እና በፌዴራል ሕግ መሰረት ክልክል የሆነው የመድልዎ ዓይነት መፈጸም ነው። በትምህርት ቤቶች ውስጥ እንደዚህ ያሉትን ወከባዎች መከልከል እና ማስተካከል መድልዎ የለለበት፣ ተማሪዎች ሊማሩበት የሚችሉ፣ ሰራተኞች ሊሰሩበት የሚችሉ፣ የሕዝብ አባላት የድስትሪክት ህንጻዎችን እና መርሃ ግብሮች/ፕሮግራሞች ጥቅማ ጥቅሞችን የሚያገኙበት ደኅንነቱ የተጠበቀ ቦታ እንዲሆን ለማረጋገጥ ወሳኝ ነው። የድስትሪክት ሰራተኞች፣ ተማሪዎች እና ሦስተኛ ወገኖች እንደዚህ ያሉትን ወከባዎች በሙሉ መፈጸም ፍጹም የተከለከለ ነው።

በማንኛውም የትምህርት ድስትሪክት፣ በማንኛውም የድስትሪክት ንብረት ላይ፣ በማንኛውም በድስትሪክት ወይም በትምህርት ቤት-እገዳ/እቀባ ሥር ያለ ተግባር/ድርጊት ወይም ክስተት፣ ወይም ማንኛውም የድስትሪክት ሥርዓተ-ትምህርት ወይም ተጓዳኝ ተግባር ወይም ክስተት ላይ ወከባ እንዳይኖር ለማረጋገጥ ሁሉም የድስትሪክት ሰራተኞች እና ተማሪዎች የጋራ ኃላፊነት አለባቸው።

ለዚህ ፖሊሲ ዓላማ ወከባ፣ በዘር፣ በቀለም፣ በቀድሞ ዝርያ/በጎሳ፣ በአመለካከት፣ በጾታ፣ በጾታዊ አመለካከት፣ በሀይማኖት፣ በሀገር/በብሔር ስረ ነገር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በስንኩልነት ወይም በልዩ ትምህርት አገልግሎቶች አስፈላጊነት ምክንያቶች፡ 1. አካላዊ፣ አእምሮአዊ ጥቃት የሚያደርስ፣ ወይም በንብረት ላይ ጉዳት የሚያደርስ፤ 2. በጣም አጣዳፊ፣ ሙጥኝ ያለ ወይም ተንሰራፊ እና የሚያስፈራ፣ ጠበኛ ወይም ዛቻ የሞላበት ቦታን የሚፈጥር፤ ወይም 3. ሥርዓት ባለው የትምህርት ቤት ሥራ ላይ መጠነ-ሰፊ ቀውስ/ረብሻ የሚያመጣ ማንኛውም ተቀባይነት የለለው፣ የቃላት ወይም የጽሁፍ ስድብ፣ አካላዊ የጠብ እና የጥቃት ምግባርን ማሳየት ነው።

**ወከባን ማሳወቅ**
በዚህ ፖሊሲ ውስጥ እና ተጓዳኝ ደንቦች በተወሰነው መሰረት ሕገ-ወጥ የሆነ መድልዎ እና የወከባ ጥቃት ደርሶብናል ወይም የጥቃቱ ሰለባ ሆነናል ብለው የሚያምኑ ማንኛውም ተማሪዎች ጉዳዩን በአስቸኳይ ለአስተዳደር፣ ለአማካሪ፣ ለአስተማሪ ወይም ለቅሬታ ሰሚ ቢሮ ማሳወቅ እና በዚህ ፖሊሲ ውስጥ እና ተጓዳኝ ደንቦች በተቀመጠው መመሪያ መሰረት መደበኛ የሆነ የአቤቱታ የክስ ፋይል መክፈት ያስፈልጋል።

ሕገ-ወጥ የሆነ መድልዎ እና የወከባ ጥቃት ደርሶብኛል ወይም የጥቃቱ ሰለባ ሆኛለሁ ብለው የሚያምኑ ማንኛውም ሠራተኞች ወይንም የሥራ አመልካቾች መዋከብ ክሶች በሙሉ ለሰራተኛው የቀጥታ የሥራ ኃላፊ ወይም የዲስትሪክቱ የሰራተኛ ጉዳይ ቢሮ ፣ወይም/እና ለድስትሪክት የቅሬታ ሰሚ ቢሮ መገለጽ አለበት።

ሕገ-ወጥ የሆነ መድልዎ እና የወከባ ጥቃት ደርሶብኛል ወይም የጥቃቱ ሰለባ ሆኛለሁ ብለው የሚያምኑ ማንኛውም የህዝብ አባል ለቅሬታ ሰሚ ቢሮ ቅሬታቸዉን ማቅረብ ይችላሉ።

**ጊዜያዊ የድስትርክቱ እርምጃ**
ተገቢ ሆኖ ሲገኝ ትንኮሳው የደረሰበት ሰዉን ከተጨማሪ ትንኮሳ ወይም ከበቀል ለመከላከል ዲስትሪክቱ በወንጀል ሪፖርት ምርመራው ወቅት ጊዜያዊ እርምጃዎችን ይወስዳል።

**የድስትሪክት ምርመራ/ እርምጃ**

የወከባ ክሶችን ለመመርመር፣ ያለውን ሕገ-ወጥ የሆነ ወከባ ለማስቆም፣ ሕገ-ወጥ የሆነ ወከባ እንዳይደገም ለማድረግ እና ጉዳዩን በሚያሳውቁ እና በዝህ የክስ ምርመራ ሂደት ውስጥ በሚሳተፉ ግለሰቦች ላይ የሚደረገውን የሀይል ምላሽ/መልሶ ማጥቃትን ለመከልከል፣ እንደዚሁም ለጉዳዩ ተጠቂ ለሆነ/ች ተማሪ ያመለጠውን/ያመለጣትን የትምህርት ዕድል ወይም ለተጠቂው/ዋ ሰራተኛ የቅጥር እድሉ/ሏን ለማካካስ ድስትሪክቱ አግባብ ያለውን እርምጃ ይወስዳል።

በተጨማሪም፣ ሌላ ተማሪን ወይም ሰራተኛን የማዋከብ ተግባር ላይ የሚሳተፍ/የሚትሳተፍ ማንኛው/ዋም ተማሪ ወይም ሰራተኛ በተገቢው የድስትሪክት ፖሊሲ መሰረት አግባብ ያለው ቅጣት ይሰጠዋል/ይሰጣታል። የወከባው ተጠቂ/ሰለባ እና በጉዳዩ መስካሪዎች ግለሰቦች ላይ እና የተጠረጠሩ ምላሽ ሰጪዎች የኃይል ምላሽ ወይም መልሶ ማጥቃት እንዳይደርስባቸው እና ያመለጡ የትምህርት እና የስራ እድሎችን በተቻለ መጠን ወደ ነበሩበት ለመመለስ አስፈላጊው እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው።በተጨማሪም፣ ሆን ብለው

በውሸት የወከባ ጥቃት እንደደረሰባቸው አድርገው ክስ በሚመሰርቱ ወይም  በወከባ የክስ ጉዳይ ሂደት አስመልክቶ የውሸት ምስክርነት በሚሰጡ ተማሪዎች ወይም ሰራተኞች ላይ ለተማሪዎች፣ ከትምህርት ቤት መታገድ/ወደ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት መወሰድ፣ እና ለሰራተኞች፣ ከሥራ መባረር የሚደርሱ የቅጣት እርምጃዎች ይወሰዳሉ።

በቦርድ ፖሊሲ JLF መሠረት ማንኛውም ተማሪ ወይም ሠራተኛ በደል ወይም ሌላ የወንጀል ድርጊት ተፈጽሞብኛል  ብሎ ለመጠራጠር  ምክንያት ሲኖረው ተገቢው የሕግ አስከባሪ ባለሥልጣናት እንዲያዉቁ ይደረጋል።

የሁከት ድርጊት በሚጠቁም በማንኛውም ተማሪ፣ ሰራተኛ፣ ወይም የህዝብ አባል  ግለሰብ ላይ  የበቀል ምላሽ / መሰንዘር የለበትም/። በተቻለ መጠን፣ የሁከት ጥቆማዎች በሙሉ በምስጢር ይያዛሉ።
ሁሉም የዲስትሪክቱ ሰራተኞች ህገወጥ አድልዎ ወይም ትንኮሳ የተመለከቱትን መድሎዎች ለማስወገድ የተረገጠዉን ድርጊት ለሠረተኛ ጉዳይ ቢሮ ወይንም  ለአስተዳዳሪው  ሪፖርት ማድረግን ጨምሮ   በንቃት እርምጃ መውሰድ አለባቸው

## VII. **የዲስትሪክት ማሻሻያ እርምጃዎች**

መድልዎ ወይም ትንኮሳ እንደተፈፀመ ሲታወቅ፣ ዲስትሪክቱ ችግሩን ለመፍታት እርምጃዎችን መተግበር አለበት፡፤

**ማስታወቂያ/ማስገነዘቢያ እና ስልጠና**
ሁከትን ለመቀነስ እና መከባበር የተሞላበት የትምህርት ቤት አካባቢን ለማረጋገጥ፣ ለሁለም ትምህርት ቤቶች ድስትሪክት እና የትምህርት ክፍሎች ይህንን ፖሊሲ ማሳወቅ የአስተዳደር ኃላፊነት ነው።

ፖሊሲው እና የአቤቱታ ሂደቱ ለሁሉም ተማሪዎች፣ ሰራተኞች፣ እና ለህዝብ ይህንን ፖሊሲ በዲስትሪክቱ ድረ-ገጽ ላይ መለጠፍ እና እንዲሁም በTitle IX ደንቦች ለመለጠፍ የሚያስፈልጉትን የስልጠና ቁሳቁሶችን ጨምሮ  በኮምፒዩተር ወይም  በወረቀት መልክ ተዘጋጅቶ መቅረብ አለበት።

ይህ ፖሊሲ እና ያለማዳላት ማስታወቂያ (AC-E-1) በተማሪ እና በሰራተኛ የመመሪያ መጽሐፍ ውስጥ መካተት አለበት ።

ተማሪዎች እና ሰራተኞች ሕገ-ወጥ የሁከት ተግባራትን የመለየት እና የመከልከል ሥልጠናዎችን በየጊዜው መውሰድ አለባቸው፤ በክፍለ ግዛት እና በፌዴራል ሕግ ሥር የተጠበቁትን ወገኖች፣ እና የሁከት ክስተቶችን መለየት እና መጠቆምን ጨምሮ አስፈላጊውን ክለሳ ማግኘት አለባቸው። ስልጠናዎቹ የምከተሉትን ጉዳዮች ያከትታሉ በዝህ ብቻ ግን አይወሰኑም።

- ማንኛውም ተማሪ ወይም ሰራተኛ በድስትሪክቱ የትምህርት ፕሮግራሞች/መርሃ ግብሮች ወይም ተግባራት/ድርጊቶች ውስጥ የሚከሰቱትን የመድልዎ ጉዳዮችን የሚፈቱበት ዝግጁ የሆነ ዘዴ መኖር አለበት።
- ወከባን እንዴት ማወቅና ምን አይነት ምላሽ መሰጠት እንደለበት
- በሙከራ የተረገገጡ ወከባን የመከላከያ መንገዶች

## IX **በግቢ ውስጥ ያለ አድልዎ**

ሽቀጦችን  እና አገልግሎቶችን ለዲስትሪክቱ ለማድረስ  ለሁሉም የውጭ ሻጮች እና ሥራ ተቋራጮች እኩል ዕድሎችን ለመስጠት ቦርዱ ቁርጠኛ ነው ;; በቦርዱ ፖሊሲ  DJ ውስጥ እንደተገለጸው የዲስትሪክቱ የግዥ ሂደቶች ጾታን ፣ ዘርን ፣ ጎሳን ፣ ሃይማኖትን ፣ ዕድሜን ፣ ጾታዊ ዝንባሌን ፣ ወይም አካል ጉዳተኝነትን ከግምት ውስጥ ሳያስገባ እኩል ዕድል እንደሚሰጡ ቦርዱ ይጠብቃል።በተለይ ይህ ቃል በኮሎራዶ ሕግ እና በአነስተኛ ንግዶች ስለሚገለጽ ፣ ይህ ቃል በ 13 C.F.R 121 ውስጥ ስለተገለጸ እና ከሃምሳ በመቶ በላይ የአክሲዮን ድርሻ ወይም ሌሎች ተመጣጣኝ ዋስትናዎች በአርበኞች እና/ወይም አካል ጉዳተኞች ግለሰቦች የተያዙ ስለሆኑ፣ የቦርድ ግዢዎችን እና የውል ሽልማቶችን  በታሪክ ጥቅም ላይ ያልዋሉ የንግድ ሥራዎችን ለማሳደግ በተለይ ቦርዱ ግዢዎችን ለማሳደግ በቅን ልቦና ለሚሳተፉ የዲስትሪክቱ ሠራተኞች ቁርጠኛ ነው።ይህ ዓላማ የሚከናወነው ከተጠቀሱት ነጋዴዎች ጨረታዎችን በማስተዋወቅ እና በማበረታታት ነው።
የአሁኑ ልምምድ የተቀናጀው በ1991
ስራ ላይ የዋለው - ጃንዋሪ  12/2009
ለመጨረሻ ጊዜ የተሻሻለው: ማርች  8፤ ቀን 2021
የቅርብ ጊዜ መሻሻል ፡ ኖቨምበር ቀን 2022

ሕጋዊ ዋቢዎች: 42 U.S.C. ክፍል 12101  ቀጣይ (ርዕስ II ስንኩላን የአሜሪካ ዜጎች አዋጅ)42 U.S.C. ክፍል 2000d
(በ 1972 በተሻሻለው መሰረት፣ የ 1964   ርዕስ VI  የዜጎች መብቶች )
20 U.S.C. ክፍል 1701-1758  (የ1972 እኩል የቅጥር ዕድል አዋጅ)
20 U.S.C. ክፍል 1681  ( ርዕስ VII , በ1972 የተደረጉ የትምህርት መሻሻሎች )
29 U.S.C. ክፍል 621  ቀጣይ (በቅጥር አዋጅ ውስጥ በዕድሜ ምክንያት መድልዎ ማድረስ)
29 U.S.C. ክፍል 701 ቀጣይ (ክፍል 504 የማገገሚያ/የመልሶ ማቋቋም አዋጅ)
42 U.S.C. 2000e  (የ1964 የዜጎች መብቶች አዋጅ  ርዕስ VII )
42 U.S.C. § 2000ff  (የጄኔቲክ መረጃ አድልዎ የሌለበት ሕግ የ2008 )
34 C.F.R. ክፍል 100 –በክፍል 110 (የሲቪል መብቶች ደንቦች)
C.R.S. § 2-4-401(3.4) (የሥርዓተ-ፆታ መግለጫ);
C.R.S. 2-4-401 3.5 (የጾታዊ አመለካከት ፍች)
C.R.S. § 24-34-402.3 (በእርግዝና ፣ በወሊድ ወይም በተዛማጅ ሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ መድልዎ)
C.R.S. 18-9-121 (አድሏዊ ዝንባሌ ያላቸው ወንጀሎች)
C.R.S. 22-32-109(1)(11) (አድሎን የሚከለክሉ ፖሊሲዎችን በጽሁፍ የማውጣት የቦርድ ተግባር)
C.R.S. § 22-32-110(1)(k)  (የዘር ወይም የጎሳ አመጣጥ ፍቺ);
C.R.S. § 24-34-301(3.3) (የሥርዓተ-ፆታ መግለጫ);
C.R.S. § 24-34-301 (3.5) (የጾታ ማንነት ፍቺ);
C.R.S§ 24-34-301 (7) (የጾታዊ  ዝንባሌ ፍቺ);
C.R.S. 24-34-301 ቀጣይ (የኮሎራዶ የዜጎች መብቶች ክፍል)
C.R.S. 24-34-401 ቀጣይ (አድሏዊ ወይም ፍትሃዊ ያልሆነ የቅጥር ሁኔታዎች)
C .R.S. 24-34-601 (በሕዝብ ቦታዎች ሕገ-ወጥ አድሎዎች)
C.R.S. 24-34-602 (ህጋዊ ለልሆነ መድልዎ ቅጠት)
C.R.S. § 24-49.5-105(4)( (በታሪክ ጥቅም ላይ ያልዋለ ንግድ ይገለጻል) 13 C.F.R. 121

ጥምር ወቢዎች፤  AC-R-1, በጾታ ላይ የተመሰረተ አድልዎ አለማድረግ ( Title IX)  AC-R-2-ጾታዊ አድልዎና ወካባ መከለከል
AC-R-7 ( አከለስንኩልነት ላይ  የተመሰረተ አድልዎ አለማድረግ የትምህርት እኩል
AC-E-1 -የኢ- አድሎአዊነት/የእኩልነት ማስታወቂያ
AC-R -  ኢ-አድልዎ/እኩል ዕድል (ቅሬታ እና ተገዢነት ሂደት)

AC-R-1 -በጾታ ላይ በመመሠረት መድልዎ አለማድረግ (ከTitle IX ጋር መጣጣም)
AC-R-2 -የጾታዊ መድልዎ እና ትንኮሳ
AC-R-3 -ጾታዊ ትንኮሳ (የቅሬታ ሀደት - የሰራተኞች አባላት)
AC-R-4 -የተማሪዎች ጾታዊ ትንኮሳ
AC-R-5 -የተማሪዎች ጾታዊ ትንኮሳ (የቅሬታ አቀራረብ)
AC-R-6 -በብሔር እና በዘር መሠረት ላይ አድልዎ አለማድረግ
AC-R-7 -በስንኩልነት /አካል ጉዳተኝነት መሠረት አድልኦ አለማድረግ (Section 504ን ማክበር)
ACB በጎሳ እና ዘር መሠረት አድልዎ አለማድረግ(የዘር ማስፈራራት/ትንኮሳ))
DJ፣ የግዥ/የግዥ ባለስልጣን
JB እኩል የትምህርት ዕድሎች

## አለማዳላት/እኩል ዕድል ማግኘት (A-C-E-1)

በ1964ቱ(42 U.S.C. § 2000d ና 42 U.S.C. § 2000e-2); የዜጎች መብቶች አዋጅ የሆኑት 'Titles VI' እና 'VII' ፣ በ1972ቱ(20 U.S.C. § 1681); 'Title IX' የሚባል የትምህርት ማሻሻያ አንቀጽ፤ በ1973ቱ (29 U.S.C. § 701 et seq.) የመልሶ ማቋቋም ክፍል 504፣ በእድሜ ምክንያት ማዳላትን የሚመለከት የ1967ቱ(29 U.S.C. § 621 et seq.) የቅጥር አዋጅ ፣ በአሜሪካ አካል ጉዳተኛ ዜጎች(42 U.S.C. § 1211 et seq.) አዋጅና በኮሎራዶ ክፍለ-ግዛት ህግ መሰረት የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት ቁ.5 ህገ-ወጥ በሆነ መንገድ በዘር፣ በቀለም፣በቀድሞ ዝርያ (አባት፣ እናት፣ ሌሎች የቀድሞ ሰዎች)፣ በእምነት፣ በጾታ፣ የሥርዓተ-ፆታ ማንነት ፣ የፆታ መግለጫ ፣ በጾታዊ አመለካከት፣ በሃይማኖት፣ በብሄር፣ በጋብቻ ሁኔታ የጄኔቲክ መረጃ, ከእርግዝና ወይም ከወሊድ ጋር የተያያዙ ሁኔታዎች,፣ በአካለ-ስንኩልነት ወይም በልዩ ትምህርት አገልግሎት ፍላጎት ላይ በመሞርኮዝ የተማሪዎችን ምዝገባ፣ የተማሪዎችን የትምህርት ፕሮግራሞች ማግኘት፣ በትምህርት ፕሮግራሞች ውስጥ መሳተፍ ወይም ተቀጥሮ መስራት ወይም በተለያዩ ተግባራት ውስጥ መሳተፍን አያዳላም።
በቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤት ዲስትሪክት ክፍል 504 መመሪያ መጽሐፍ ምዕራፍ IX አውራጃ ክፍል 504 የቅሬታ ሂደቶች በተጠቀሰው መሰረት የ'Title IX' እና ክፍል 504 የአቤቱታ ሂደቶች ለተማሪዎች፣ ለወላጆች፣ ለሰራተኞችና ለማህበረሰብ አባላት በሙሉ ተዘጋጅቷል። በትምህርት ድስትሪክታችን ይህንን የሚፈጽም ግለሰብ/ች ተሰይመዋል ፤

ሜገን ሎረንግን ( Megan Lonergan)
የድስትሪክቱ ለፍትሃዊነት መታዘዝ ተጠሪ
የሕግ ጉዳዮች ቢሮ
4700 S. Yosemite St.
Greenwood Village, CO 80111
720-554-4415

ስቴፍን ዴቭስ(Stephanie Davies)
የድስትርክቱ ለፍትሃዊነት መተዘዝ ተጠሪ
የሕግ ጉዳዮች ቢሮ
4700 S. Yosemite St.
Greenwood Village, CO 80111
720-554-4415

የሚከተሉት ሰው(ዎች) በተማሪዎች Section 504 ጉዳይ ላይ ይሰራሉ ፡-
Stephen White(እስቴፈን ዋይት)
Student Achievement Resource Center
14188 E. Briarwood Ave.
Centennial, CO 80112
720-554-4404
swhite7@cherrycreekschools.org

የሚከተለው ሰው የ ADA ወይንም ተጨማሪ ዕገዛዎችን ለሚፈልጉ ለ CCSD ሰራተኞች ዕገዛ ያደርጋል
Jennifer Squire
የሀዩማን ርሶርስ ዳይሬክተር
የትምህርት አገልግሎቶች ማዕከል
4700 S. Yosemite St.
Greenwood, CO 80111
720-554-4282
benefits@cherrycreekschools.org

የ'Titles VI' (በዘር፣ በቀለም፣በቀድሞ ዝርያ) ፤እንደዚሁም የ'Title IX'(በጾታ፣ በጾታዊ አመለካከት፣)አስመልክቶ አቤቱታዎች በአሜሪካ የትምህርት ቢሮ፣ ክልል 'VIII' የፌዴራል ቢሮ ህንጻ፣ በሚከተለው አድራሻ ለዜጎች መብቶች ቢሮ መቅረብ ይችላሉ፤ 1244 North Speer Boulevard, Suite 310, Denver, CO 80204 ነው።እንደዝሁም የ'Title'VII' በአካለ-ስንኩልነት፤በትምህርት ፕሮግራሞች ውስጥ መሳተፍ ወይም ተቀጥሮ መስራት ወይም በተለያዩ ተግባራት ውስጥ መሳተፍን ጥሰት አስመልክቶ አቤቱታዎች ለዜጎች የቅጥር እኩልነት መብት ተሚጋች በዝህ አድራሻ 303 E. 17th Ave., Suite 510, Denver, CO 80202, ወይም የኮሎራዶ የህዝቦች መብት ኮሚሽን፤1560 Broadway, Suite 1050, Denver, CO 80202 መቅረብ ይችላሉ።

በየበላይ አለቃ ሜሪ ቸስሊ፣ ጁን 25፣ 2009 ጸደቀ።
ማሻሻያ እና ማፅደቅ በሱፐርንተንደንት ዶር. ስካት A. Siegfried; በጃንዋሪ 11, 2021
የአሁኑ ማሻሻያ እና ማጽደቅ በሱፐርንተንደንት ክሪስቶፈር ስሚዝ፣ ኖቨምበር 14፣ 2022።

## የተማሪዎች የጾታ ሁከት/ጥቃት (AC-R-4)

የጾታ ሁከት የጾታ መድልዎ ዓይነት እና የጾታ መድልዎን የሚከለክል የሕግ ጥሰት ነው።

ከጾታዊ ጥቃት/ሁከት ነጻ የሆነ የመማሪያ አካባቢ መጠበቅ አለበት። በጾታዊ ባህሪ ወይም ግንኙነቶች ሰራተኛ ፤ተማሪን ወይም ተማሪ ሌላ ተማሪን ማጥቃት/ማዋከብ የፖሊሲ ጥሰት ይሆናል።
የሚከተሉት ፍችዎች እንደ ጾታዊ ጥቃት/ወከባ ይወሰዳሉ፡ ተቀባይነት የሌለው የወሲብ ፍላጎት፣ ለወሲባዊ ግንኙነት ውለታ/ወረታ መጠየቅ፣ ወይም ሌሎች የቃል ወይም አካላዊ የሆኑ የወሲባዊ ግንኙነት መግለጫ ባህሪያት/ምግባራት በሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ እንደ ወሲባዊ ጥቃት ይወሰዳሉ፡

1. ይህንን ጉዳይ መፈጸም በግልጽ ሆነ በስውር ከግለሰቡ የትምህርት እድገት ሁኔታ ጋር የሚያያዝ ሲሆን።

2. ይህንን ጉዳይ መቀበል ወይም አለመቀበል ግለሰቡን ሊጎዳ የሚችል ለትምህርት ነክ ጉዳዮች ውሳኔዎች መሰረት ሲሆን።

3. እንደዚህ ያለ ምግባር/ባህሪ በግለሰቡ የትምህርት ክንውን ላይ ጫና የሚፈጥር ዓላማ እና ውጤት ያለው ወይም አስፈሪ የሆነ፣ ፀብ/ጠብ የሚፈጥር ወይም ጥቃት ያለበት የትምህርት አካባቢን የሚፈጥር ሲሆን።

የጾታ ጥቃት/ሁከት ከላይ እንደተወሰነው የሚከተሉትን ሊያጠቃልል ይችላል፣ በነዚህ ብቻ ግን አይወሰንም፡
1. ጾታን የሚመለከቱ ቀልዶች ወይም ሁከት/ጥቃት በደል
2. ለጾታዊ ተግባራት/ድርጊቶች ማስጨነቅ
3. በተደጋጋሚ ሁኔታ ጾታዊ ወይም አንኳሳሽ መልዕክት ያላቸው ንግግሮች
4. ተቀባይነት የሌለው ንክኪ፣ለምሳሌ መዳሰስ፣ መቆንጠጥ ወይም በተከታታይ ከሌላ ሰው  ጋር መላፋት።
5. ለወሲብ ግንኙነት አስተያየት መስጠት ወይም መጠየቅ፣ ካልሆነ በግልጽ ስለ ግለሰቡ ማርክ/ነጥብ ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ግላዊ ደንታዎች/ጉዳዮች መዛት።

ተማሪዎች ለትምህርት ቤት አስተዳደር፣ ለትምህርት ቤት ቅሬታ ሰሚ ባለ ሥልጣን ወይም ለሌላ ለሚያምኑት አዋቂ ወሲባዊ ጥቃት/ሁከት ክስተቶች በሙሉ መጠቆም አለባቸው።
በተሰጠው የአቤቱታ ማቅረቢያ ሂደት መሰረት፣ ተማሪዎች በመደበኛም ሆነ መደበኛ ባልሆነ ሁኔታ ወሲባዊ ጥቃትን አስመልክቶ አቤቱታቸውን ማቅረብ ይችላሉ። ተጠርጣሪው/ዋ አጥቂ አቤቱታው የሚቀርብለት/የሚቀርብላት የትምህርት ቤቱ ኃላፊ ከሆነ/ች፣ ተማሪው/ዋ አቤቱታውን ለኃላፊው ተቆጣጣሪ ማቅረብ ይችላል/ትችላለች።
በተቻለ መጠን የወሲባዊ ጥቃት አቤቱታ ጉዳዮች በሙሉ በምስጥር ይያዛሉ።
አቤቱታን ማቅረብ ወይም ወሲባዊ ጥቃቶችን መጠቆም የግለሰቡን ሁኔታ  ወይም  ነጥብ/ማርክ አይጎዳም።
የዚህ ፖሊሲ ማስታወቂያ ለሁሉም የድስትሪክት ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ክፍሎች ይሰራጫል፤ በተማሪ መመሪያ መጽሐፍ ውስጥም ይካተታል።   የካቲት 8፣ 1999 ሥራ ላይ ዋለ።

## የተማሪዎች አቤቱታ ሂደት ወሲባዊ ጥቃት (AC-R-5)

1. ትርጓሜዎች

ሀ. ቅሬታ አቅራቢ . በTitle IX ስር ወሲባዊ ትንኮሳ ሊሆን ይችላል የሚል የጾታዊ ጥቃት ሰለባ ነው ተብሎ የሚታሰብ በዲስትሪክቱ የትምህርት ፕሮግራም ወይም እንቅስቃሴ ውስጥ የሚሳተፍ ወይም ለወደፊት ለመሳተፍ ዕቅድ ያለው ተማሪ።

ለ. ውሳኔ ሰጪ.. ተዛማጅ ማስረጃዎችን የሚገመግም ፣ ፓርቲ እና ምስክርነት ተአማኒነትን ጨምሮ ፣ እና ተጠሪጣሪው ለተፈጸመው የወሲባዊ ትንኮሳ ተጠያቂ መሆን አለመሆኑን ለመወሰን የማስረጃ ደረጃውን ቀዳሚነት የሚመለከት ግለሰብ።

ሐ አስቸኳይ አገዳ.. ትምህርት ቤቱ የግለሰባዊ ደህንነት እና የአደጋ ትንተና (የራስን ሕይወት የማጥፋት አደጋ ግምገማ ወይም የስጋት ግምገማ ጣልቃ -ገብነት ዕቅድ ጨምሮ) ፣ እና ከወሲባዊ ትንኮሳ(ከTitle IX) ክስ የተነሳ በማንኛውም ተማሪ ወይም ሌላ ግለሰብ አካላዊ ወይም ደኅንነት አስቸኳይ ሥጋት መሆኑን የሚወስን ከሆነ ትምህርት ቤት ተጠሪጣሪዉን ከትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት የትምህርት መርሃ ግብር ወይም እንቅስቃሴ በአስቸኳይ ሁኔታ ሊያስወግድ ይችላል።

መ. መደበኛ ቅሬታ.. በአቤቱታ አቅራቢ ወይም በ ጾታዊ ጥቃት (Title IX) አስተባባሪ በአካል ወይም በዲጂታል ፊርማ አማካይነት የተፈረመ ሰነድ ወይም በጾታዊ ጥቃት (TitleIX) አስተባባሪ በተጠያቂው ላይ ጾታዊ ትንኮሳ ክስ እና ትምህርት ቤቱ ስለ ወሲባዊ ትንኮሳ የቀረበውን ክስ እንዲመረምር በመጠየቅ።

ሠ. መርማሪ ሁሉንም የተገኙ ማስረጃዎችን ፣ የተቀናጀ እና የማይረባ ማስረጃን ጨምሮ የግለሰቦችን እና ምስክሮችን ተዓማኒነት በተጨባጭ ለመገምገም የሰለጠነ ግለሰብ ፣

ረ. ከሳሽ እና ተከሳሽ.. አቤቱታ አቅራቢው (ዎች) እና ተጠሪ (ዎች) በጋራ።

ሰ. ተጠሪጣሪ ወሲባዊ ትንኮሳን (Title IX )ሊያካትት የሚችል የስነምግባር ፈጻሚ ሆኖ ሪፖርት የተደረገ ግለሰብ

ሽ. የትምህርት ቤት ዲስትሪክት የትምህርት ፕሮግራም ወይም እንቅስቃሴ.. የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት በተጠሪም ሆነ የTitle IX(ወሲባዊ ትንኮሳ) በሚከሰትበት አውድ ላይ ከፍተኛ ቁጥጥር የሚያደርግባቸው አካባቢዎች ፣ ክስተቶች ወይም ሁኔታዎች።

ከ. ድጋፍ ሰጪ እርምጃዎች መደበኛ ቅሬታ ከማቅረቡ በፊት ወይም በኋላ ወይም መደበኛ ቅሬታ ባልተሰጠበት ቦታ አግባብነት ባለው መልኩ የሚገኝ እና ያለ ክፍያ ወይም ክፍያ ለቅሬታ አቅራቢው ወይም ለተጠሪ የተሰጠ ሥነ-ሥርዓት ያልሆነ ፣ የማይቀጣ የግለሰባዊ አገልግሎቶች።. እንደዚህ ዓይነቶቹ እርምጃዎች የሁሉንም ወገኖች ወይም የት / ቤቱን የትምህርት አከባቢን ደህንነት ለመጠበቅ ወይም የወሲብ ትንኮሳዎችን ለመከላከል የተነደፉ እርምጃዎችን ጨምሮ ለት / ቤቱ የትምህርት መርሃ ግብር ወይም እንቅስቃሴ እኩል መዳረሻን ለሌላኛው ወገን ሸክም ሳይሰጡ ለማቆየት ወይም ለመደገፍ የተነደፉ ናቸው። እነዝህም ምክክር ፣ የጊዜ ገደቦች ማራዘሚያ ወይም ሌላ ከኮርስ ጋር የተዛመዱ ማስተካከያዎች ፣ የሥራ ወይም የክፍል መርሃ ግብሮች ማሻሻያ ፣ የአጃቢ አገልግሎቶች ፣ በፓርቲዎች መካከል እርስ በእርስ መገናኘትን ፣ በይቅርታ የሚታለፉ ቀሪዎች ፣ በግቢው ውስጥ ባሉ አካባቢዎች ውስጥ ደህንነትን ወይም ቁጥጥርን እና ሌሎች ተመሳሳይ እርምጃዎችን ሊያካትት ይችላል።

ቀ. የጾታዊ ትንኮሳ(Title IX) አስተባባሪ. የድጋፍ እርምጃዎችን ውጤታማ አፈፃፀምን የማስተባበር ኃላፊነት ያለበት በት / ቤቱ የተሰየመ ግለሰብ. በማንኛውም ጊዜ የTitle IX አስተባባሪ ለማንኛውም ቅሬታ አካል አይሆንም(ገለልተኛ ) መሆን አለበት :: የTitle IX አስተባባሪ ለማንኛውም ችግሮች ውጤታማ አፈፃፀም ኃላፊነት አለበት።

በ. ወሲባዊ ትንኮሳ(Title IX): በጾታ ላይ በመመሥረት ከሚከተሉት ውስጥ አንዱን ወይም ከዚያ በላይ የሚያሟላዉን ማካሄድ

i. የትምህርት ቤት ዲስትሪክት ሠራተኛ አላግባብ በሆነ ጾታዊ ግንኙነት ተሳትፎ ምክንያት ለአንድ ግለሰብ የት / ቤቱን ዕርዳታ ፣ ጥቅም ወይም አገልግሎት መስጠት

ii. አንድ ሰው በትምህርት ቤቱ የትምህርት መርሃ ግብር ወይም እንቅስቃሴዎች ዉስጥ በእኩልነት ተደራሽነትን የሚከለክለው በጣም ከባድ ፣ የተስፋፋ እና ተጨባጭ አፀያፊ የማይፈለግ ተግባር ወይንም

iii. በ 20 U.S.C ውስጥ እንደተገለጸው ወሲባዊ ጥቃት ”። 34 1092 (f)(6)(A)(v), ፣ “የፍቅር ጓደኝነት ሁከት” በ 34 ዩ.ኤስ. 34 12291 (a) (10) ፣ “የቤት ውስጥ ጥቃት” በ 34 ዩ.ኤስ. 34 12221 (ሀ) (8) ፣ ወይም “መከታታል” በ 34 ዩ.ኤስ. 29 12291(a)(8), (30

2 .ሪፖርት ማድረግ

ሀ. ማንኛውም ሰው የወሲባዊ ትንኮሳ ሪፖርት ሊያቀርብ ይችላል (ሪፖርት የሚያደርገው ሰው የወሲባዊ ትንኮሳ ድርጊቱ ሰለባ ነው ተብሎ የተጠረጠረ ሰው ቢሆንም በይሆንም)።

ለ. ሪፖርቶች የTitle IX አስተባባሪ መረጃን በመጠቀም ለTitle IX አስተባባሪ ወይንም ለሌላ የትምህርት ቤት ዲስትሪክት ሠራተኛ በአካል ፣በፖስታ ፣በስልክ ወይም በኢሜይል በኩል ሊደረጉ ይችላሉ።

ሐ .ማንኛውም የትምህርት ቤት ዲስትሪክት ሠራተኛ የወሲብ ትንኮሳ ሪፖርቶች ወደ ትምህርት ቤቱ የየወሲብ ትንኮሳ(Title IX) አስተባባሪ ማተላለፍ አለባቸው. .የያንዳንዱ ትምህርት ቤት ህንጻ የወሲብ ትንኮሳ (Title IX) አስተባባሪዎች የስም ዝርዝር በዲስትሪክቱ ድረገጽ ላይ ይገኛል።

መ. ትንኮሳ አድራጊው የጾታዊ ትንኮሳ(Title IX) አስተባባሪ ከሆነ ሪፖርቱን ለመቅረፍ በድስትርክቱ ደረጃ ሌላ ተለዋጭ አስተዳዳሪ ይሰየማል።

3. የTitle IX አስተባባሪ ምላሽ

ሀ. ማንኛውም የት / ቤት ዲስትሪክት ሠራተኛ የ(Title IX) ወሲባዊ ትንኮሳ ሪፖርትን ስቀበል ለትምህርት ቤቱ የTitle IX አስተባባሪ ማሳወቅ አለበት።

i. የTitle IX አስተባባሪ ለግለሰቡ የሚገኙትን የድጋፍ እርምጃዎች ላይ ለመወያየት ወዲያውኑ ቅሬታ አቅራቢውን ያነጋግራል ፣

ii.የድጋፍ እርምጃዎችን በተመለከተ የአቤቱታ አቅራቢውን ምኞቶችን ማክበር

iii.መደበኛ ቅሬታ ከመቅረቡ በፍት ወይንም ቦሃላ ያሉትን የድጋፍ እርምጃዎች መኖሩን ያሳውቁ።

iv. መደበኛ ቅሬታ የማቅረብ ሂደቱን ያብራሩ እና

v.. ሚስጥራዊነትን መጠበቅ የት / ቤቱ የድጋፍ እርምጃዎችን የመስጠት አቅሙን የማይጎዳ ከሆነ ማንኛውም የድጋፍ እርምጃዎች በሚስጥር እንደሚያዙ ለቅሬታ አቅራቢው ያሳውቁ።

4.አቤቱታ ማቅረብ

ሀ. አቤቱታ አቅራቢ ፣ ወይም ወላጅ ወይም ሞግዚት አቤቱታ አቅራቢውን ለመወከል ሕጋዊ መብት ያለው ማንኛዉም ሰው ፣ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል። አቤቱታዎች በጽሑፍ መቅረብ እና በአቤቱታ አቅራቢው መፈረም አለባቸው። የተጠናቀቁ ቅሬታዎች ለትምህርት ቤቱ የጾታዊ ትንኮሳ ( Title IX ) አስተባባሪ መቅረብ አለባቸው. ከTitle IX አስተባባሪ ውጭ ለድስትሪክቱ ሠራተኛ የጽሑፍ ቅሬታ ከቀረበ ፣ የድስትሪክቱ ሠራተኛ ቅሬታውን ለTitle IX አስተባባሪ በፍጥነት ያስተላልፋል።.. ቅሬታው ከተፈጠረበት በ 180 ቀናት ውስጥ ወይም ቅሬታ አቅራቢው እንዲህ ዓይነቱን መከሰት ከተገነዘበበት ቀን ጀምሮ ቅሬታዎች መቅረብ አለባቸው። ቅሬታ አቅራቢው አቤቱታ በማቅረብ ህደቱ ላይ እንደ አስፈላጊነቱ እርዳታ ሊያገኝ ይችላል። Title IX አስተባባሪዎችም ቅሬታ ሊጀምሩ ይችላሉ።

5. የቅሬታ አቀራረብ ሂደት

ሀ. መደበኛ ቅሬታ በአቤቱታ አቅራቢው ከተፈረመ እና ከቀረበ ቦሃላ ፣ ወይም መደበኛ ቅሬታ በTitle IX አስተባባሪ ከተፈረመ ቦሃላ ፣ ከዚያ ትምህርት ቤቱ የቅሬታ ሂደቱን ይጀምራል።

i.: የTitle IX አስተባባሪ ወይም መርማሪ ለቅሬታ አቅራቢ እና ለተጠርጣሪው የጽሑፍ ማስታወቂያ ይሰጣል።

1.. መደበኛ ያልሆነ የመፍትሔ ሂደቱን ጨምሮ የ CCSD ቅሬታ ሂደት ማስታወቂያ።

2.: የTitle IX የወሲብ ትንኮሳ ሊያስከትሉ የሚችሉ ክሶች ማስታወቂያ ፣ የሚከተሉትንም ጨምሮ :-

ሀ. ከማንኛውም የመጀመሪያ ቃለ መጠይቅ በፊት መልስ ለማዘጋጀት ወቅታዊ እና በቂ ጊዜ እና በቂ ዝርዝር ማቅረብ ።

i. በቂ ዝርዝሮች ከዝህ በታች ያሉትን ያካትታሉ

1.በግጭቱ ውስጥ የተሳተፉ ወገኖች ማንነት ፣ የሚታወቅ ከሆነ።

2. Title IX (ወሲባዊ ትንኮሳን) ያካተተ ሥነ ምግባር

3. ትንኮሳው የተከሰበት ቀን እና ቦታ የሚታወቅ ከሆነ

3. ተጠሪጣሪው ለተከሰሰው ድርጊት ተጠያቂ አለመሆኑን የሚሚገት መሆኑን ፣ እና ኃላፊነትን መዉሰድን በተመለከተ የሚወሰነው በቅሬታ ሂደት መደምደሚያ ላይ መሆኑን ልብ ይበሉ።

4.አስተውሉ ኃላፊነትን የመዉሰድ ለመወሰን ጥቅም ላይ የሚውለው የማስረጃ መስፈርት የማስረጃ ደረጃው ቀዳሚነት መሆኑን ልብ ይበሉ

5. አቤቱታ አቅራቢው እና ተጠሪው የመረጡት አማካሪ ሊኖራቸው ይችላል ፣ ማንም ሊሆን ይችላል ፣ ግን ጠበቃ መሆን አይጠበቅበትም ፣ እና ማስረጃዎችን መመርመር እና መገምገም ይችላል

6..በCCSD የቦርድ ፖሊሲ JICDA መሠረት የውሸት መረጃን በቃልም ሆነ በጽሑፍ ለትምህርት ቤት ሠራተኛ በ CCSD የስነምግባር እና የዲሲፕሊን ሕግ መሠረት የቅጣት መዘዝ ሊያስከትል እንደሚችል ልብ ይበሉ።

7. መርማሪው መርምሮ በሚመርጣቸው ክሶች የመጀመሪያው የቅሬታ ማስታወቂያ ላይ ያልተካተቱ ተጨማሪ ክሶች ማስታወቂያ።

ለ.. መደበኛ ቅሬታዎችን ማወሃድ

i. ክሱ ብዙ ተጠሪጣሪዎችን ወይም ብዙ ቅሬታ አቅራቢዎችን ሲያካትት እና ከተመሳሳይ እውነታዎች ወይም ሁኔታዎች ሲነሱ መደበኛ ቅሬታዎች ሊወሃዱ ይችላሉ።

ሐ.መደበኛ ቅሬታን ማቆም

i. የTitle IX አስተባባሪ በሚከተሉት ምክንያቶች መደበኛ ቅሬታውን ማቆም አለበት

1. በመደበኛ አቤቱታ ውስጥ የተጠቀሰው ሥነ ምግባር የተረጋገጠ ቢሆንም የ Title IX ወሲባዊ ትንኮሳ አይሆንም።

2.. ድርጊቱ በዲስትሪክቱ የትምህርት ፕሮግራም ወይም እንቅስቃሴ ውስጥ አልተከሰተም።

3.. ድርጊቱ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ በሚኖር ሰው ላይ አልተከሰተም

ii. የTitle IX አስተባባሪ በሚከተሉት ምክንያቶች መደበኛ ቅሬታውን ማቆም ይችላል

1.. በምርመራው ወቅት በማንኛውም ጊዜ አቤቱታ አቅራቢው መደበኛ ቅሬታውን ወይም በውስጡ ያለውን ማንኛውንም ክስ ማንሳት እንደሚፈልግ ለTitle IX አስተባባሪ በጽሑፍ በኩል ስያስተዉቅ።

2. ተጠሪጣሪው ከአሁን በኋላ በትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ውስጥ አልተመዘገበም

3. የተወሰኑ ሁኔታዎች የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ስለ መደበኛ ቅሬታው ወይም በእሱ ላይ ውሣኔ ለመወሰን በቂ ማስረጃ እንዳይሰበስብ ይከለክላል

iii.. መደበኛ ቅሬታ ማቆም በ CCSD የተማሪዎች የስነምግባር እና የዲሲፕሊን ህግ መሰረት እርምጃን አይከለክልም።

iv.መደበኛ ቅሬታ ማቆም የድጋፍ እርምጃዎችን አማራጭ እና አቅርቦትን አይከለክልም።

v. መደበኛ ቅሬታ ሲቆም ፣ የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት ቅሬታው መቆሙን እና ምክንያት (ምክንያቶችን) ለቅሬታ አቅራቢው እና ለተጠሪጣሪው በአንድ ጊዜ የጽሑፍ ማስታወቂያ ይሰጣል።

መደበኛ ቅሬታዎች መደበኛ በልሆነ ሁኔታ ተፈቷል

i.. መደበኛ ያልሆነ አቤቱታ ከመቀጠሉ በፊት መደበኛ ቅሬታ መቅረብ አለበት

ii.. በትምህርት ቤት ዲስትሪክት ሰራተኛ ተማሪን ወሲባዊ ትንኮሳ ያካተቱ ክሶችን ለመፍታት መደበኛ ያልሆነ የመፍትሄ ሂደት ሊቀርብ አይችልም

iii.. ሀላፊነትን በሚመለከት ውሳኔ ላይ ከመድረሱ በፊት በማንኛውም ጊዜ ትምህርት ቤቱ መደበኛ ያልሆነ የመፍትሔ ሂደትን ሊያመቻች ይችላል።

iv.ሁለቱም ወገኖች  መደበኛ ባልሆነ የመፍትሔ ሂደት ላይ በፈቃደኝነት የጽሑፍ ስምምነት መስጠት አለባቸው።

v.መደበኛ ያልሆነ መፍትሄ የሚከተሉትን ማካተት አለበት

1. ለሁለቱም ወገኖች ውንጀላውን የሚገልጹ የጽሑፍ ማስታወቂያ

2. ከተመሳሳይ ውንጀላዎች የሚመነጭ መደበኛ ቅሬታ እንዳይጀመር የሚከለክልባቸውን ሁኔታዎች ጨምሮ የመደበኛ የመፍትሄ ሂደት መስፈርቶች።

3. በማንኛውም ውሳኔ ከመስማማቱ በፊት ማንኛውም አካል ከኢ-መደበኛው የመፍትሔ ሂደት የመውጣት እና የቅሬታ ሂደቱን ከመደበኛ ቅሬታ አንፃር የመቀጠል መብት ያለው መረጃ ፤ እና

4.. መደበኛ ባልሆነ የመፍትሔ ሂደት ውስጥ መሳተፍ የሚያስከትለው ማንኛውም ውጤት የሚጋራው ፣ መዝገቦቹ የሚጠበቁ ወይም የሚጋሩ ናቸው።

vi.. ሁለቱም ወገኖች በማንኛውም ሁኔታ መደበኛ ባልሆነ የመፍትሔ ሂደት ውስጥ ለመሳተፍ አይጠየቁም።

ሠ. የመደበኛ ቅሬታዎች ምርመራ

i..በትምህርት ቤቱ የተሰየመው የትምህርት ቤቱ የTitle IX አስተባባሪ ሊሆን የሚችል መርማሪ ፣ መደበኛ ቅሬታ ምርመራን ይጀምራል።

ii. መርማሪው በአጠቃላይ ለቅሬታ አቅራቢዎች ወይም ለተጠሪዎች ወይም ለግለሰብ ቅሬታ ወይም ተጠሪጣሪ የጥቅም ግጭት ወይም አድልዎ ሊኖረው አይገባም

iii. ጥፋተኝነትን በሚመለከት ውሳኔ ላይ ለመድረስ በቂ የማረጋገጫ ኃላፊነት እና ማስረጃ የመሰብሰብ ሸክም ያለው በመርመሪው ላ ነው እንጅ በተጠሪ ወይም በአቤቱታ አቅራቢ ላይ አይደለም

iv. መርማሪው በሐኪም ፣ በአእምሮ ሐኪም ፣ በስነ -ልቦና ባለሙያ ፣ ወይም በሌላ እውቅና ባለው ባለሙያ ወይም በባለሙያ ረዳት ወይንም እነርሱን በመወከል የሚሰሩትን ለፓርቲው ሕክምና ከመስጠት ጋር በተያያዘ የተሰሩ እና የተያዙ የአቤቱታ አቅራቢዉን ወይም የተጠሪውን  መዝገቦችን  ከፓርቲው የጽሑፍ ፈቃድ ውጭ ማየት ፤ ግምት ውስጥ ማስገባት ፣ ማሳወቅ ወይም በሌላ መንገድ መጠቀም አይችልም።

v.ሁለቱም ወገኖች ምስክሮችን እና ሌሎች የማይነጣጠሉ ወይም ገላጭ ማስረጃዎችን ለማቅረብ እኩል እድል ይሰጣቸዋል

vi. ሁለቱም ወገኖች በምርመራ ላይ ባሉት ክሶች ላይ ከመወያየት ወይም ተዛማጅ ማስረጃዎችን ከማሰባሰብ እና ከማቅረብ አይከለከሉም።

vii. ሁለቱም ወገኖች ለማንኛውም ተዛማጅ ስብሰባ ወይም ሂደት አማካሪያቸዉን ጨምሮ በሌሎች ግለሰቦች ሊታጀቡ ይችላሉ። የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክት አማካሪው (ዎች) በፍርድ ሂደቱ ውስጥ ሊሳተፉበት የሚችሉበትን መጠን በተመለከተ ገደቦችን የማቋቋም መብቱን ይጠብቃል። በአማካሪ (ዎች) ላይ የሚደረጉ ማናቸውም ገደቦች ለሁለቱም ወገኖች እኩል ተፈጻሚ ይሆናሉ።

viii..ተሳታፊዎቻቸው በተጋበዙበት ወይም በሚጠበቁበት ጊዜ እያንዳንዱ ወገን የቀኑን ፣ የሰዓቱን ፣ የቦታውን ፣ የተሳታፊዎችን ፣ የምርመራ ቃለ -መጠይቆችን ዓላማ እና ለእንደዚህ ዓይነት ቃለ -መጠይቆች የሚዘጋጅበትን በቂ ጊዜ በጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል።

ix .ምርመራው ከመጠናቀቁ በፊት እያንዳንዱ ወገን ማስረጃውን ትርጉም ባለው መልኩ እንድዘጋጅበት የትምህርት ቤቱ ዲስትሪክቱ ኀላፍነትን /ተጠያቂነትን ለመወሰን ዉሳኔ ላይ ለመድረስ የማይደገፍበትን  ማስረጃዎችን ጨምሮ በመደበኛ ቅሬታ ውስጥ ከተነሱት ክሶች ጋር በቀጥታ የተዛመደ ማንኛውንም ማስረጃ ለመመርመር እና ለመገምገም እያንዳንዱ ወገን እኩል ዕድል ይሰጠዋል።

x.. የምርመራ ሪፖርቱ ከመጠናቀቁ በፊት መርማሪው ለእያንዳንዱ ወገን በኤሌክትሮኒክ ቅርጸት ወይም በበጽሑፍ ቅጂ ምርመራ እና ግምገማ የተደረገባቸውን ማስረጃዎች መላክ አለበት።

1.የምርመራ ሪፖርቱ ከመጠናቀቁ በፊት መርማሪው ግምት ውስጥ እንዲያሰገባ ሁለቱም ወገኖች የጽሑፍ መልስ ለማቅረብ አሥር (10) የትምህርት ቀናት ይኖራቸዋል ።

xi. በሁለቱም ወገኖች  ምላሽ ከተሰጠ እና ከምርመራው በኋላ መርማሪው አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች በአጭሩ የሚያጠቃልል የምርመራ ዘገባ ያጠናቅቃል። መርማሪው የምርመራ ሪፖርቱን ለእያንዳንዱ ፓርቲ ይልካል እንደዝሁም ለዉሳኔ ሰጭው ለግምገማ እና ለፅሁፍ ምላሽ በኤሌክትሮኒክስ ቅርጸት ወይም በጹሁፍ ቅጂ ይልካል።

ሸ. ዉሳኔ

i.. መርማሪው ወይም የTitleIX አስተባባሪ ሊሆን የማይችል የውሳኔ ሰጭ ግለሰብ ፣ ቅሬታውን ለመቅረፍ በትምህርት ቤቱ ይሰየማል።

ii.. የውሳኔ ሰጭው በቅሬታ አቅራቢዎች ወይም በተጠሪዎች ላይ በዘር ወይም በግለሰብ ቅሬታ ወይም የጥቅም ግጭት ወይም አድልዎ ሊኖረው አይገባም።

iii. ውሳኔ ሰጪው ሀላፊነትን በሚመለከት ውሳኔ ከማድረጉ በፊት እያንዳንዱ ወገን ማንኛውንም ፓርቲ ወይንም ምስክርን መጠየቅ የሚፈልገውን አግባብነት ባላቸው ጥያቄዎች ምላሽ በጽሑፍ እንዲሰጥ እና ለእነዚያ ጥያቄዎች መልሶች ፣ እና ለተከታታይ ጥያቄዎች ዕድል ይሰጣል፣

1.. የውሳኔ ሰጭው ጥያቄውን አግባብነት የለውም ብሎ ለማግለል ማንኛውንም ውሳኔ ለሚመለከተው ወገን ማስረዳት አለበት።

iv. የውሳኔ ሰጭው ተጠያቂነትን በሚመለከት ከመወሰኑ በፊት የአቤቱታ ሂደቱን ለማጠቃለል ምክንያታዊ የሆነ ፈጣን የጊዜ ገደብ እና መደበኛ ያልሆነ የመፍትሔ ሂደትን በተመለከተ መረጃን እና ውስን የቅጥያ ሂደቱን የቅሬታ ሂደት ጊዜያዊ መዘግየት የሚፈቅድ ሂደት ይሰጣል። በመርማሪው ወይም በውሳኔ ሰጪው ተለይቶ ሊታወቅ ምክንያት የጊዜ ገደቦች እና፤ ድርጊቱ ፣ ለምን እንደዘገየ ወይም ስለ መራዘሙ ለቅሬታ አቅራቢው እና ለተጠርጣሪው  በጽሑፍ ማስታወቂያ ይሰጣል ።

ቀ. የውሳኔ ሰጭው ለፓርቲዎች ሃላፊነትን በተመለከተ በጽሑፍ ውሳኔ ይሰጣል. ይግባኝ ከቀረበ ሃላፍነትን ወይንም ተጠያቂነትን መወሰንን በተመለከተ የውሳኔ ሰጭው የይግባኙን ውጤት በጽሑፍ ውሳኔ የሰጠበት ቀን የመጨረሻ ዉሳኔ ይሆናል ይግባኝ ካልቀረበ ግን ፣ ይግባኝ ከአሁን በኋላ እንደ ወቅታዊ ተደርጎ የማይቆጠርበት ቀን የመጨረሻ ዉሳኔ ቀን ይሆናል ። የጽሑፍ ውሳኔው የሚከተሉትን ያጠቃልላል

i..የTitle IX ወሲባዊ ትንኮሳ ሊሆኑ የሚችሉትን ክሶች መለየት

ii መደበኛ ቅሬታ ከቀረበ እና እስከ ዉሳኔው ድረስ የተወሰዱ የአሠራር እርምጃዎች እነዝህም ፤ ለፓርቲዎች የተሰጠ ማንኛውንም ማሳወቂያ ፣ ከሁለቱም ወገኖች ጋር እና ከምስክሮች ጋር የሚደረግ ቃለ ምልልስ ፣ የጣቢያ ጉብኝቶች ፣ ሌሎች ማስረጃዎችን ለመሰብሰብ ያገለገሉ ዘዴዎች እና የተካሄዱ ችሎቶች ፣ማብራሪያ

iii. የሚተገበርበት የማስረጃ መስፈርቶች

iv. ውሳኔውን የሚደግፉ እውነታዎች ግኝቶች

v. የዲስትሪክቱ የተማሪ የስነ- ምግባር እና የስነ -ምግባር መመሪያን ወደ እውነታዎች መተግበርን በተመለከተ መደምደሚያዎች ፣

vi .የእያንዳንዱን ክስ ውጤት ፣ ሀላፊነትን በሚመለከት ውሳኔን ፣ ትምህርት ቤቱ በተጠሪጣሪ ላይ የሚያደርገውን ማንኛውንም የዲሲፕሊን ማዕቀብ ፣ እና ለቅሬታ አቅራቢው ትምህርት ቤቱ የትምህርት ፕሮግራሙን ወይም እንቅስቃሴውን እኩል ለማድረስ ወይም ለማቆየት የተነደፉ መፍትሄዎች /መላ ምቶች መግለጫ እና ምክንያታዊነት። and

vii.. ለቅሬታ አቅራቢው እና ለተጠሪጣሪው ይግባኝ ለማለት የዲስትሪክቱ ሂደቶች እና ፍቃዶች

viii..ሁለቱም ወገኖች የመጨረሻ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ይግባኝ ለዉሳኔ ሰጪው ወይንም ለየTitleIX (ጾታዊ ትንኮሳ)አስተባባሪ ለማቅረብ አሥር (10) የትምህርት ቀኖች እንዳሏቸው ማሳወቅ።

ix.. ይግባኝ ለማቅረብ ጊዜያዊ መዘግየት ወይም የውሳኔ ሰጭ ወይም የ Title IX አስተባባሪ ተለይቶ በተገለጸው መሠረት ለበጎ ምክንያት ጊዜያዊ መዘግየት የሚፈቅድ ሂደትን ያካትቱ ፣ ለቅሬታ አቅራቢው ለተጠሪጣሪው የመዘግየቱን እና የመራዛሙን ምክንያት በጽሑፍ ማስታወቂያ ያሳዉቁ።

ቀ. ይግባኞች

i: በሚከተሉት መሠረቶች ላይ ሁለቱም ወገኖች ኃላፊነትን ወይም የት / ቤትን መደበኛ ቅሬታን ዉድቅ ማድረጉን በተመለከተ ወይም በእሱ ውስጥ ያሉ ማናቸውንም ውንጀላዎች በተመለከተ ውሳኔን ይግባኝ ማለት ይችላሉ ።

1. በጉዳዩ ውጤት ላይ ተጽዕኖ ያሳደረ የአሠራር አለመመጣጠን;

2.ተጠያቂነት ወይም ጉዳዩ ዉድቅ እንዲሆን ስወሰን በጉዳዩ ውጤት ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል እና በወቅቱ ምክንያታዊ ያልሆነ አዲስ ማስረጃ ፤ እና/ወይም

3.የTitle IX አስተባባሪ ፣ መርማሪ ወይም የውሳኔ ሰጭ በተጠርጣሪ ወይም በአመልካቾች በአጠቃላይ ወይም በግለሰቡ ቅሬታ አቅራቢ ወይም ተጠሪጣሪዎች በጉዳዩ ውጤት ላይ ተጽዕኖ ያሳደረ የጥቅም ግጭት ወይም አድልዎ ነበረው

i. የይግባኝ ሂደቱ እገዳዎችን እና ማባረርን ጨምሮ በዲሲፕሊን ውጤቶች ላይ ብቻ በመመርኮዝ ግኝቶችን ለመቃወም ጥቅም ላይ ላይውል ይችላል ፣ እና ከላይ ከተዘረዘሩት መስፈርቶች አንዱን ማሟላት አለበት።

ii. ውሳኔውን ይግባኝ ለማለት ማንኛዉም ወገን በአሥር (10) የትምህርት ቀናት ውስጥ ለውሳኔ ሰጭው ወይም ለTitle IX አስተባባሪ የጽሑፍ ጥያቄ ማቅረብ አለበት።

iii.: ይግባኝ ከቀረበ

1. ይግባኝ ሲቀርብ ለሁለቱም ወገኖች በጽሑፍ ይነገራቸዋል እንደዝሁም የይግባኝ ሂደቶች በሁለቱም መካካል በእኩልነት ይተገበራሉ

2.የይግባኝ ውሳኔ ሰጭው ተጠያቂነትን ለመወሰን ወይንም ጉዳዩን ዉድቅ ለማድረግ በት / ቤቱ እንደ ይግባኝ ኦፊሰር ሆኖ ይሰየማል ። ይህ ሰው ተጠያቅነት የወሰነ ወይንም ጉዳዩን ዉድቅ ያደረገ ሰው መሆን አይችልም እንደዝሁም ፣ መርማሪው ፣ ወይም የTitle IX አስተባባሪውም ልሆን አይችልም ።

3. የይግባኙን ማሳወቂያ ከተቀበሉ በኋላ ፣ ሁለቱም ወገኖች ውጤቱን የሚደግፉ ወይም የሚቃወሙ የጽሑፍ መግለጫዎችን እንዲያቀርቡ እኩል የአሥር (10) የትምህርት ቀናት ዕድል ይሰጣቸዋል።

4. የይግባኝ አቤቱታው ኦፊሰር የይግባኙን ውጤት እና የውጤቱን ምክንያት የሚገልጽ ለሁለቱም ወገኖች በአንድ ጊዜ በጽሑፍ ውሳኔ ይሰጣል።

6 .የሰነድ አያያዝ

ሀ.: ዲስትሪክቱ ከሚከተሉት ጋር የተያያዙ መዝገቦችን ለሰባት (7) ዓመታት ማቆየት አለበት።

i, እያንዳንዱ የወሲባዊ ትንኮሳ ምርመራ እና ተጠያቂነትን የሚመለከት ማንኛውንም ውሳኔ ጨምሮ ፣ እንዲሁም ፣

1.በተጠሪጣሪ ላይ የተጣለ ማንኛውም የዲሲፕሊን ማዕቀብ

2. ለት / ቤቱ የትምህርት መርሃ ግብር ወይም እንቅስቃሴ እኩል ተጠቃሚነትን ለማሻሻል ወይም ለማቆየት የተነደፈ ማንኛውም ለቅሬታ አቅራቢ የቀረቡ የመፍትሄ ሃሳቦች ፤

3.ማንኛውም ይግባኝ እና ውጤት ፤

4. ማንኛውም መደበኛ ያልሆነ መፍትሄ እና ውጤቱ;

ii. የTitle IX አስተባባሪዎች ፣ መርማሪዎች ፣ የውሳኔ ሰጭ እና መደበኛ ያልሆነ የመፍትሔ ሂደትን የሚያመቻች ማንኛውንም ሰው ለማሰልጠን የሚያገለግሉ ሁሉም ቁሳቁሶች ፤ እና ፣

1. ዲስትሪክቱ እነዚህን የሥልጠና ቁሳቁሶች በድረ-ገጽ ላይ በይፋ እንዲገኝ ማድረግ አለበት።

iii. ለሪፖርቱ ወይም ለወሲባዊ ትንኮሳ አቤቱታ ምላሽ የተሰጡ የድጋፍ እርምጃዎችን ጨምሮ የማንኛውም እርምጃዎች መዛግብት።

1.ት / ቤቱ ምላሹ ሆን ብሎ ግድየለሽ እንዳልሆነ ለመደምደሚያው መሠረት መመስረት እና ለት / ቤቱ የትምህርት መርሃ ግብር ወይም እንቅስቃሴ እኩል ተደራሽነትን ለማድረስ ወይም ለማቆየት የተቀየሱ እርምጃዎችን እንደወሰደ በሰነድ መመዝገብ አለበት።

2.ትምህርት ቤቱ ለቅሬታ አቅራቢ የድጋፍ እርምጃዎችን ካልሰጠ ፣ ትምህርት ቤቱ እንደዚህ ዓይነት ምላሽ ለምን ከታወቁ ሁኔታዎች አንፃር ምክንያታዊ እንዳልሆነ በሰነድ መመዝገብ አለበት።

3. የአንዳንድ ተጨባጭ መሠረቶች ወይም እርምጃዎች ሰነዶች ወደፊት ዲስትሪክቱ ተጨማሪ ማብራሪያዎችን ወይም የተወሰዱ ተጨማሪ እርምጃዎችን በዝርዝር ከመስጠት አይገድበውም።

7. የበቀል እርምጃ

ሀ .በTitle IX ወይም በዚህ ክፍል የተረጋገጠ ማንኛውንም መብት ለማደናቀፍ ፣ ወይም ግለሰቡ ሪፖርት ወይም ቅሬታ ስላቀረበ ፣ ስለመሰከረ ፣ ስለረዳ ፣ወይም በዚህ የቦርድ ፖሊሲ መሠረት በምርመራ ወይም ሂደት ውስጥ ለመሳተፍ ወይም ለመሳተፍ ፈቃደኛ ካልሆነም ማንኛውም ትምህርት ቤት ወይም ሌላ ሰው፤ ማስፈራራት ፣ ማስገደድ ፣ ማሸማቀቅ፤ወይንም መግለል አይችልም።

ለ.. ማስፈራራት ፣ ማስገደድ ፣ ወይም መድልዎ ፣ የተማሪ የሥነ -ምግባር ጥሰቶችን ጨምሮ የጾታ መድልዎ ወይም ጾታዊ ትንኮሳ የማያካትት ፣ ነገር ግን እንደ ዘገባ ወይም እንደ ወሲባዊ አድልዎ ቅሬታ ፣ ወይም ከተመሳሳይ እውነታዎች ወይም ሁኔታዎች የሚነሱ በTitle IX ወይም በዚህ ፖሊሲ የተረጋገጠ ማንኛውንም መብት ወይም የማደናቀፍ ዓላማ የወሲብ ትንኮሳ ዘገባ ወይም መደበኛ ቅሬታ ፣ የበቀል እርምጃን ያመለክታል።

ሐ .በ 34 § 106.8(c). CFR መሠረት ልክ እንደ ጾታዊ አድልዎ የአቤቱታ ሂደቶች ሁሉ በቀልን የሚመለከቱ ቅሬታዎች ሊቀርቡ ይችላሉ

መ. በዩናይትድ ስቴትስ ሕገ መንግሥት የመጀመሪያ ማሻሻያ የተጠበቁ የሙብቶች አጠቃቀም የተከለከለ የበቀል እርምጃን አይወስድም።

ሠ.በቅሬታ ሂደቱ ወቅት የሐሰት መግለጫን በማድረጉ ተማሪዎች በተማሪዎች የሥነ ምግባር ሕግ መሠረት ተግሣጽ ሊሰጣቸው ይችላል ፣ እና እንዲህ ዓይነቱ ተግሣጽ ሀላፊነትን ብቻ መወሰን ብቻ በቂ ካልሆነ በቀልን አያካትትም። ማንኛውም ፓርቲ ሐሰት መግለጫ ሰጥቷል ብሎ ለመደምደም አይቻልም

ረ. ምስጢራዊነትን መጠበቅ

i. ማንኛውም ሪፖርት ያደረገን ወይም የወሲብ ትንኮሳ አቤቱታን ያቀረበ ማንኛውም ግለሰብ ፣ ማንኛውም ቅሬታ ፣ ሪፖርት የተደረገበት ግለሰብ ጨምሮ ፣የጾታ መድልዎ አድራጊ ፣ ማንኛውም ተጠሪጣሪ እና ማንኛውም ምስክር ስለ ጾታዊ በደል ሪፖርት ወይም ቅሬታ ያቀረበ ማንኛውም ግለሰብ ማንነት ትምህርት ቤቱ በሚስጥር መያዝ አለበት። በ FERPA 20 USC መሠረት ከተፈቀደው በስተቀር ወይንም የአፈፃፀም ደንቦቹ ፣ 34 CFR ክፍል 99 ፣ ወይም በሕግ በተደነገገው መሠረት። ፣

በመጀመሪያ በ ሱፐርንተንደንት Robert D. Tschirki,በፌብሯሪ 8፤ 1999 ጸደቀ . እንደገነ ኦገስት 14, 2020 ተሻሻለ

ሕጋዊ ወቢዎች አስተባባሪ መሰየም ፣ የፖሊሲ ስርጭት እና የቅሬታ አሰራሮችን መቀበል 20 U.S.C. § 1681 et. seq. ( የTitle IX የ1972 የትምህርት ማሻሻያዎች)

34 CFR § 106.30 (ትርጓሜዎች)

34 CFR §106.44 (ለወሲባዊ ትንኮሳ የተጠሪጣሪዎች ምላሽ)

34 CFR §106.45 (ለወሲባዊ ትንኮሳ መደበኛ ቅሬታዎች የቅሬታ ሂደት) 34 CFR §106.71 (Retaliation የበቀል እርምጃ)

## በኃሳ/በህገረሰብ እና በዘር ምክንያት መድልዎ አለማድረግ (AC-R-6)

በዘር፣ በቀለም፣ በቀድሞ ዝሪያ፣ በኃይማኖት ወይም በብሔር መረጃ ላይ ያልተመሰረተ ለሁሉም ሰራተኞች እና ተማሪዎች ከኅሳ ሁከት/ጥቃት እና ማስፈራራት ነጻ የሆነ የመማሪያ እና የሥራ ቦታ መኖር አለበት።

በዘር፣ በቀለም፣ በቀድሞ ዝሪያ፣ በኃይማኖት ወይም በብሔር ምክንያት ማንኛውም ሰራተኛ ወይም ተማሪ ሌላ ማንኛውንም የሥራ ባልደረባ ወይም ተማሪ ማወክ ወይም ማስፈራራት የቦርድ ፖሊሲ እና የክፍለ ግዛት ሕግ ጥሰት ይሆናል።

በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ፣ በትምህርት ቤቱ በተከለከሉ ተግባራት/ድርጊቶች ላይ፣ ወይም በድስትሪክቱ በሚሰራጩት ተሽከርካሪዎች ውስጥ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ቀጥሎ የተዘረዝሩትን ከፈጸሙ፣ የ ‘ACB’ ፖሊሲ ጥሰት ይሆናል፡

1. በዘር፣ በቀለም፣ በቀድሞ ዝሪያ፣ በኃይማኖት ወይም በብሔር ላይ በመመሰረት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሌላውን ሰው የሚያዋርድ አስተያየት መስጠት፣ (በጽሁፍም ሆነ በቃል)፣ የተለያዩ ስሞችን መስጠት፣ መሳደብ፣ አሽሙር፣ እና የዘር “ቀልዶች” በግለሰብ ወይም በቡድን ላይ መሰንዘር።

2. የአካላዊ ጥቃት ዛቻ ወይም በዘር፣ በቀለም፣ በቀድሞ ዝሪያ፣ በኃይማኖት ወይም በብሔር ላይ በመመሰረት ሰውን መጉዳት።

3. የግለሰብን ወይም የቡድንን ዘር፣ ቀለም፣ የቀድሞ ዝርያ፣ ኃይማኖት ወይም ብሄር ለማወረድ የጽሁፍ ወይም በዐይን የሚታይ ቁሳቁስ ማሳየት ወይም የትምህርት ቤት ንብረትን ማጥፋት።

4. በዘር፣ በቀለም፣ በቀድሞ ዝርያ፣ በኃይማኖት ወይም በብሔር ምክንያት የማንኛውንም ግለሰብ ንብረት መጉዳት፣ ማጥፋት፣ ወይም ማፍረስ።
5. የአንድን ሰው ትክክለኛ ወይም የታሰበ ዘር፣ ቀለም፣ የዘር ሀረግ ወይም ሌላ ሰው በከፊልም ሆነ በሙሉ ለማስፈራራት ወይም ለማዋከብ በማሰብ የኮሎራዶን የወንጀል ህግ የሚጥሱ ሌሎች የማዋከብ ወይም የማስፈራራት ድርጊቶችን መፈጸም ብሄራዊ አመጣጥ አንድ ግለሰብ በሚከተሉት ድርጊቶች ውስጥ መሳተፍ

   ሀ. ሆን ብሎ በሌላ ሰው ላይ አካላዊ ጉዳትን የማምጣት ምግባር።

   ለ. ሌላ ሰውን የሚያስፈራራ እና በግለሰቡ/ቧ እና በንብረቱ/ቷ ላይ የተሰነዘረ ሕገ-ወጥ የድርጊት ምግባር ወይም ንግግር በግለሰቡ ወይም በንብረቱ ላይ የሚደርሰውን ህገወጥ ድርጊት እያወቀ ሌላ ሰውን የሚያስፈራራ ድርጊት ወይም ቃላቶች በዚህ ሰው ላይ በሰውነት ላይ ጉዳት ሊያደርሱ ወይም በሰውየው ንብረት ላይ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ቃላቶች፤ ወይም።

   ሐ. በሌላ ሰው ላይ አካላዊ ጉዳትን የሚያመጣ ወይም የግለሰቡ/ቧን ንብረት ሊጎዳ የሚችል ምግባር ወይም ንግግር።

በኅሳ ምክንያት ማስፈራራት ወይም ወከባ ወይም አድልዎ ደርሶብኛል ብለው የሚያምኑ ተማሪዎች ወይም የሥራ ባልደረቦች ጉዳዩን/ክስተቱን በአስቸኳይ ለኃላፊው/ዋ ለምርመራ ፣ ወይም ለቅርብ አለቃ፣ ወይም ተወካይ ማሳወቅ አለባቸው። ሰራተኞቹም ለምርመራ ወደ ለሰባዊ መብት ጽሕፈት ቤት ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ። ምን ጊዜም፣ በተቻለ መጠን፣ ሁሉም ጥቆማዎች በምስጥር መያዝ አለባቸው። የኅሳ ማስፈራራት ጥቆማዎች ወይም ሁከት/ጥቃት ወይም አድልዎ በኃላፊው/ዋ ወይም በተወካይ በአስቸኳይ እና በጊዜ መመርመር አለበት።

አስፈላጊውን ምርመራ ለማካሄድ እና ለሕግ አስከባሪ ባለሥልጣናት የመጠቆም እና እንደዚህ ዓይነት ምግባር የሚታይበትን/የሚታይባትን ተማሪ ወደ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት የመውሰድ ተጨማሪ እርምጃዎች እንዲወሰዱ፣ ማንኛውም የኅሳ ማስፈራራት ክስተት በተቀላጠፈ ሁኔታ ለትምህርት ቤቱ ኃላፊ ወይም ተቆጣጣሪ መጠቆም አለበት።

ከላይ በተገለጹት ምግባራት በመሳተፍ የ‘ACB’ ፖሊሲ ጥሶ/ሳ የተገኘ/ች ተማሪ በትምህርት ቤት ከተማሪ የሚጠበቁ ሥርዓቶችን ግልጽ ለማድረግ ከወላጁ/ጇ ወይም ከአሳዳጊው/ዋ እና ከትምህርት ቤት ኃላፊ ወይም ተወካይ ጋር በሚደረገው ስብሰባ ላይ መገኘት አለበት/አለባት።

ከላይ በተገለጸው ምግባር በመሳተፍ እና/ወይም ከላይ እንደተገለጸው የሁከት/የጥቃት ድርጊቱን አይቶ አግባብ ላለው አካል ባለመጠቆም የ ‘ACB’ ፖሊሲን የሚጥስ ማንኛውም የሥራ ባልደረባ ላይ ተገቢው የሥርዓት እርምጃ ይወሰድባታል።

በየበላይ አለቃ ሞንተ ሙሴ (Monte C. Moses) ኖቨምበር 8 ,1999 ጸደቀ።

## በስንኩልነት ላይ የተመሰረተ መድልዎ አለማድረግ
## (AC-R-7)

የትምህርት ቦርድ ለተሃድሶ/ለመልሶ መቋቋም አዋጅ ክፍል 504ና ለ1973ቱ አዋጅ እና ለአስተዳደራዊ ሕግ እና ደንቦቹ ስራ ላይ መዋለቸው ለማረጋጋጥ ያለመተከት ይጥራል። ይህም ማንኛዉም ግለሰብ ከአከለጉዳተኝነቱ ብቻ የተነሳ ከማንኛዉም የድስትርከቱ የተለያዩ የትምህርት ዕድሎችን፤ ቅጥር፤ጥቅማጥቅሞችን ከመገኘት መከልከል የለበትም።

የትምህርት ቦርድም ሁኔታዎችን የሚያመቻች እና ለዚህ ጉዳይ ኃላፊነት የሚወስድ ከሰራተኞች ውስጥ አንድ ግለሰብን ይሰይማል።እበክዎትን የ(AC-E-1) ክፍል ይመልከቱ። ተወካዩ፣ የድስትሪክቱ ለክፍል 504 ተጠሪ፣ ፖሊሲዎቹ በዚህ መግለጫ ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችሉ ሂደቶችን ማውጣት እና ለክፍል 504 እና ለፖሊሲው ከመታዘዝ አንጻር የድስትሪክት የትምህርት ፕሮግራሞችን/መርሃ ግብሮችን እና ተግባራትን መቆጣጠር አለበት።

በተጨማሪም፣ በእያንዳንዱ የትምህርት ዘመን አንዴ የክፍል 504 ስም፣ ቢሮ፣ አድራሻ፣ እና የስልክ ቁጥር ለድስትሪክቱ ተማሪዎች እና ሰራተኞች በሙሉ ማሳወቅ አለበት(AC-R ና AC-E-1) ይመልከቱ።ማስታወቂያው ሁሉም ተማሪዎች እና ሰራተኞች በሚያዩበት ቦታ በመለጠፍ ወይም ሊደርሳቸው በሚችል በሌላ መንገድ መሆን አለበት። የትምህርት ቤቶች የበላይ አለቃ ለትምህርት አመልካቾች፣ ለተማሪዎች፣ ለአንደኛ እና ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወላጆች፣ ለዋቢዎች፣ ለሰራተኞች፣ እና ለሥራ አመልካቾች የሚያካሄዳቸውን የትምህርት ፕሮግራሞች/መርሃ ግብሮች እና ተግባራት በስንኩልነት ምክንያት እንደማያዳላ እና በክፍል 504 እና በአስተዳደራዊ መተዳደሪያ ደንቦቹ መሰረት መድልዎ እንደሌለ መግለጽ አለበት/አለባት። ማስታወቂያው በሕግ እና በመተዳደሪያ ደንብ በሚፈለገው አካሄድ መሆን አለበት።

በበላይ አለቃ Mary F. Chesley, ጃንዋሪ 12፤ 2009

ኖቨምበር 14, 2011 በበላይ አለቃ Mary F. Chesley ተሻሻለ

ሕጋዊ ዋቢ፤ 29 U.S.C.§U§U701 ቀጣይ (ክፍል 504) 34 C.F.R. 104 42 U.S.C.ክፍል 12101 ቀጣይ

በ1964 የዜጎች መብቶች አዋጅ ርዕስ VI እና VII፤ የ1972 የትምህርት ማሻሻል ርዕስ IX፤ የ1981 ወሲባዊ ጥቃት ፖሊሲ፤ የ1973 ክፍል 504 የተሃድሶ/መልሶ መቋቋም አዋጅ፤ የ1990 ስንኩላን የአሜሪካ ዜጎች አዋጅ፤ የ1988 የኮሎራዶ የኃሳ ማስፈራራት አዋጅ፤ እና የ1994 በትምህርት ተቋማት ውስጥ ተማሪዎች ላይ የሚደርሱ የፌዴራል የዘር ክስተቶች እና ወከባ/ጥቃት ፖሊሲ፤ የቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት በዘር፣ በቀለም፣ በብሔር/በሀገረሰብ፣ በቀድሞ ዝርያ፣ በጾታ፣ በሀይማኖት፣ በዕድሜ፣ በስንኩልነት ላይ በመመስረት ለሚያካሄዳቸው የትምህርት ፕሮግራሞች ምዝገባ፣ ቅጥር፣ የትምህርት ፕሮግራሞች ወይም ተግባራት ላይ አድልዎ አያደርግም።

ከላይ የተዘረዘሩት የዜጎች መብቶች ርዕሶች፣ አዋጆች፣ እና ፖሊሲዎች፣ እና የኮሎራዶ የኃሳ ማስፈራራት አዋጅ ጥሰት አስመልክቶ የአቤቱታ ማቅረቢያ ሂደት ለተማሪዎች፣ ለወላጆች፣ እና ለሠራተኞች ተዘጋጅቷል። አቤቱታው በተማሪ፣ በወላጅ፣ ወይም በሰራተኛ፣ ወይም በቡድን በተደራጁ ሰዎች፣ ወይም በተማሪዎቻቸው ፈንታ በወላጆች ሊቀርብ ይችላል። ድስትሪክቱ ለሚቀርቡት አቤቱታዎች በጣም አመቺ እና ተግባራዊ በሆነ መንገድ መፍትሔ ሊሰጥ ስለሚፈልግ፣ አቤቱታ አቅራቢዎች ቀጥሎ ባለው ገጽ ላይ የተነደፉትን /እርምጃዎችን ሂደቶች እንዲከተሉ ይበረታታሉ።

***የመጀመሪያ እርምጃ***

የፖሊሲዎች፣ የአዋጆች ወይም የሕጎች ጥሰት ጉዳዮች ሲከሰቱ ከትምህርት ቤት ወይም ከድስትሪክት የፍትህ ተጠሪ ወይም ከሚታምነው/ከሚታምኚው የትምህርት ድስትሪክቱ የሥራ ባልደረባ ጋር ተነጋገር/ሪ።

ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዘ ከሆነ፣ ተጠቂው/ዋ ግለሰብ ወይም ተጠቂ ግለሰቦች ክሳቸውን ለዜጎች መብቶች ሕጎች ወይም ለክፍለ ግዛት የኃሳ ማስፈራራት አዋጅ እና ከትምህርት ቤቱ የአቤቱታ ፍትሕ ተጠሪ ጋር፣ እና ከድስትሪክት ጋር የተያያዘ ከሆነ፣ ከድስትሪክቱ የአቤቱታ ፍትሕ ተጠሪ፣ ወይም አቤቱታ አቅራቢው/ዋ አቤቱታው/ዋን ከሌላ ከሚያምኑት የድስትሪክቱ የሥራ ባልደረባ ጋር ተገናኝተው በመወያየት የአቤቱታ ሂደቱን ሊጀምሩ ይችላሉ። አቤቱታ አቅራቢው በተሰጠው ምላሽ ከልረካ ወደምቀጥለው 2ተኛ ደረጃ መተላላፍ ይችላል። የትምህርት ቤቱም ኅላፍ የተከሰተዉን( VI እና VII፤) ጥሰት በመስረዳት ወደምቀጥለው ደረጃ ያሰተላልፋል።

***ሁለተኛ እርምጃ***

*አቤቱታን ለባለ ሥልጣናት ማቅረብ*

በድስትሪክቱ ውስጥ ላሉት ባለ ሥልጣናት የሚቀርበው የአቤቱታ ክስ በቃል ወይም በጽሁፍ መልክ ሆኖ፣ የመብት ጥሰት/ሕገ ወጥ ጉዳይ ከተከሰተ በኃላ በአስቸኳይ አቤቱታ አቅራቢው/ዋ ግለሰብ ወይም ግለሰቦች ጉዳዩን ለትምህርት ቤቱ ወይም ለድስትሪክቱ ለፍትህ ተጠሪ ለሆኑት ስተፍኒ ዳቬስ (**Stephanie Davies**) በዝህ አድራሻ 4700 S. Yosemite Street, Greenwood Village, CO 80111) 720-554-4471 ማሳወቅ አለባቸው ። የክሱ ጉዳይ በትምህርት ቤት ውስጥ የተከሰተ ከሆነ፣ ክሱ የሚቀርበው ለትምህርት ቤቱ የፍትህ ተጠሪ ይቀርባል፤ ጉዳዩ በድስትሪክት ደረጃ ከሆነ፣ ክሱ ለድስትሪክቱ የፍትህ ተጠሪ ይቀርባል።

አቤቱታ አቅራቢዎች ክሶችን በጊዜው እንዲያቀርቡ ይበረታታሉ። አብዛኛዎቹ የዜጎች መብቶች ሕጎች የሚፈልጉት አቤቱታ አቅራቢዎች የተባለው የሕገ ወጥ ድርጊት ከተፈጸመ በኃላ በ180 ቀናት ውስጥ በዚህ ሰነድ መጨረሻ ላይ ለተዘረዘሩት አግባብ ላላቸው ተቋማት/ድርጅቶች ክሳቸውን እንዲያቀርቡ ነው። ከመጠን በላይ መዘግየት ሙሉ እና ልክ የሆነን ምርመራ ለማድረግ ሊያስቸግር ይችላል። አቤቱታ አቅራቢዎች የክሱን ጉዳይ ሲገልጹ እንደሚከተለው ግልጽ መሆን አለባቸው፡

> በፌዴራል የዜጎች መብቶች ሕጎች ሥር፣ የተሰጡት አግባብ ያላቸው አዋጆች ወይም ፖሊሲዎች ወይም የክፍለ ግዛት የኃሳ ማስፈራራት አዋጅ ፣ ወይም የድስትሪክቱ ያለማዳላት ፖሊሲዎች፣ መተዳደሪያ ደንቦች እና/ወይም ልዩ የትምህርት ቤት ሂደቶች ተጥሰዋል፤ አቤቱታው ስሞችን፣ ቀኖችን፣ ቦታዎችን እና የተባለው ጥሰት ዝርዝር መግለጫዎችን ማካተት አለበት።
>
> ***ወይም***
>
> ከሳሹ ግለሰብ በፌዴራል የዜጎች መብቶች ሕጎች የተከለከሉ ተግባራት፣ የክፍለ ግዛት የኃሳ ማስፈራራት አዋጅ ተግባራት ወይም ፖሊሲዎች፣ ወይም የድስትሪክቱ ያለማዳላት ፖሊሲዎች፣ መተዳደሪያ ደንቦች ወይም ልዩ የትምህርት ቤት ሂደቶች የጥቃት ሰለባ ከሆነ/ች፣ ወይም በማንኛውም ተግባር/ጉዳይ ወይም ሁኔታ ከተቀመጠው የፍትህ ፖሊሲዎችን በሚጊጻረር መልኩ ፍትሃዊነት በጎደለው መንገድ ከታየ/ች፣ በተማሪዎች ወይም በሰራተኞች ላይ ተጽዕኖ የሚያደርስ የመተዳደሪያ ደንቦች ወይም ተግባራት። ክሱ ስሞችን፣ ቀኖችን፣ ቦታዎችን፣ እና የተጣሰው ጉዳይ ዝርዝር መግለጫ ማካተት አለበት።

***ሦስተኛ እርምጃ***

ትምህርት ቤት ወይም ድስትሪክት ጥልቅ ምርመራ ያደርጋል

> ትምህርት ቤቱ እና/ወይም የድስትሪክቱ የፍትህ ተጠሪ ፣ ከሁለቱ የሚመለከተው ክፍል፣ የጥቃቱ ሰለባ የሆነ/ች ግለሰብ ፣ ጥሰቱን የፈጸመ/ች ተጠርጣሪ፣ ወይም ምስክሮች የአፈጻጸም ሂደት መብት ሳይጥስ/ሳይጋፋ ጉዳዩን በሰፊው እና በጥልቅ ይመረምራል።
>
> የትምህርት ቤቱ ወይም የድስትሪክቱ የፍትህ ተጠሪ ክሱ ከቀረበበት ጊዜ አንስቶ በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ ለአቤቱታ አቅራቢው/ዋ ክሱ እንደደረሰው/እንደደረሳት በጽሁፍ በማረጋገጥ የምርመራውን ሂደት ለከሳሹ ማሳወቅ አለባት/አለበት። ድስትሪክቱ አቤቱታውን ከተቀበለ ጊዜ አንስቶ እስከ ምርመራ ሂደቱ ድረስ 45 የሥራ ቀናት አለው። ምርመራው ለምስክሮች ቃለ-መጠይቅ ማድረግ፣ ተገቢውን የድስትሪክት ፖሊሲዎች ሰነዶችን መመርመር፣ ሂደቶችና ሀገ-ደንቦችን ማየት፣ እንደዚሁም ጉዳዩ የሚመለካታቸው ወገኖች ያቀረቡትን መረጃ በሙሉ መመርመርን ያካትታል። ምርመራው ሲጠናቀቅ፣ ድስትሪክቱ ለአቤቱታ አቅራቢው/ዋ ግለሰብ ማንኛውም ማስተካኪያ ካለና አግባብ ያላቸውን ማስተካኪያዎች ሁሉ በጽሁፍ ያሳውቃል።

***አራተኛ እርምጃ***

የአቤቱታ አቅራቢ የይግባኝ ማለት መብት
የአቤቱታ አቅራቢም ሆነ የመብት ጥሰቱን/ጥቃቱን ያደረሰ ግለሰብ በትምህርት ቤት የፍትህ ተጠሪ የሚሰጠውን ውሳኔ፣ ለድስትሪክት ፍትሃዊነት ተጠሪ ይግባኝ የማለት፤ በድስትሪክት ፍትሃዊነት ተጠሪ የሚሰጠውን ውሳኔ፣ ለትምህርት ቤቶች የበላይ አለቃ ወይም ተወካይ ይግባኝ የማለት መብት አላቸው። የድስትሪክቱ የምርመራ ውጤት ከደረሰ ጊዜ ጀምሮ በ10 ቀናት ውስጥ ይግባኝ መቅረብ አለበት። የይግባኙ ሂደት ይግባኙ ከቀረበ ጊዜ ጀምሮ በ60 የሥራ ቀናት ውስጥ መጠናቀቅ አለበት። ይግባኙ ለማን መቅረብ እንዳለበት የሚገልጽ መረጃ ለሚመለከታቸው ወገኖች በጽሁፍ ይሰጣል። እንደዚሁም ከታች እንደተገለጸው አቤቱታ ለአሜሪካ የትምህርት ቢሮ፣ የዜጎች መብቶች ቢሮ ማቅረብ ይቻላል።

**የድስትሪክት የፍትሃዊነት ተጠሪ፤**
ስተፈኒ ዳቬስ(**Stephanie Davies**)
የድስትሪክት ለፍትሃዊነት መታዘዝ ተጠሪ
4700 South Yosemite Street
Greenwood Village,
720-554-4471

***የዜጎች መብቶች ድርጅቶች/ተቋማት የአቤቱታ ሂደት***

ሁሉም ሰዎች አቤቱታን ሲያቀርቡ ከላይ የተሰጡትን እርምጃዎች እንዲከተሉ የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት ቢያበረታታም፣ ሁሌም ይህ ሂደት መከተል የለበትም። ፍትህ ተዛብቷል ወይም የጎሳ ማስፈራራት፣ ወይም የወሲብ ወከባ/ጥቃት ደርሷል የሚሉ ወላጆች፣ ለልጆች እንደ የበላይ ተቆጣጣሪ በመሆን፣ ተማሪዎች፣ እና ሰራተኞች በቀጥታ ለፌዴራል ወይም ለክፍለ ግዛት የዜጎች መብቶች ድርጅቶች/ተቋማት ወይም ለጎሳ ማስፈራራት አቤቱታዎች ከታች በተሰጠው አድራሻ በአከባቢው ለሚገኙት የፖሊስ ክፍሎች በማሳወቅ ክስ መክፈት ይችላሉ።

ስለ ርዕስ VI፣ (ዘር፣ የብሄር/የሀገረሰብ ዝርያ)፣ ርዕስ IX፣ (ጾታ)፣ ክፍል 504፣ ADA፣ (ስንኩልነት)፣ የዘር ክስተቶች እና በትምህርት ተቋማት ፖሊሲ ተማሪዎችን መበደል(ዘር፣ ቀለም፣ ወይም የብሄር ዝርያ) የአቤቱታ ክስ በቀጥታ በሚቀጥለው አድራሻ፡ 'Office for Civil Rights, U.S. Department of Education, Region VIII, Federal Office Building, 1244 North Speer Blvd. Suite 310 Denver, CO 80204' ቢሮ ማቅረብ ይችላሉ። ቅሬታዎች በኢሜል ocr.denver@ed.gov ላይ ወይም በ OCR ኤሌክትሮኒክ በመጠቀም ሊቀርቡ ይችላሉበ OCR ድርጣቢያ ቅጽ:http://www.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.ጥያቄዎች በስልክ ቁጥር 303-844-5695 ወደ OCR ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡

የርዕስ VII ጥሰት አቤቱታዎች (ቅጥር) ቀጥሎ በተሰጠው አድራሻ በቀጥታ መቅረብ ይችላሉ፡ 'Federal Office of Equal Employment Oportunity Commission, 303 E. 17th Avenue, Suite 510, Denver, CO 80203' ወይም 'Colorado Civil Rights Commission, 1560 Broadway,Suite 1050, Denver, CO 80202፣ እና የኮሎራዶ የጎሳ ማስፈራራት አዋጅ (ዘር፣ ቀለም፣ የቀድሞ ዝርያ፣ የብሄር/የሀገረሰብ ዝርያ፣ ኃይማኖት፣ እና ዕድሜ) አቤቱታዎች በቀጥታ በአከባቢው በሚገኙት የፖሊስ ክፍሎች መቅረብ ይችላሉ።

የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት ለሁሉም ሰዎች በእኩልነት የሚያገለግል የትምህርት ተቋም ሲሆን፣ በዘር፣ በቀለም፣ በብሄር/በሀገረሰብ ዝርያ፣ በጾታ፤በሃይማኖት፣ በዕድሜና በአካለ-ስንኩልነት ላይ በመመሰረት የትምህርት ምዝገባ፣ የቅጥር፣ የትምህርት ፕሮግራሞች/መርሃ ግብሮች ወይም ተግባራት አስመልክቶ በህገ-ወጥ አድልዎ አያደርግም።

***የኮሎራዶ የትምህርት ቢሮ***
***ክፍል 504/ADA***
***የዜጎች መብቶች የአቤቱታ ሂደት ቢሮ***

ግለሰብ ወይም ተቋም አቤቱታን በአሜሪካ ትምህርት ቢሮ፣ ለዜጎች መብቶች ቢሮ ማቅረብ ይችላሉ። አቤቱታ ጉዳዩ ከተከሰተ ጊዜ ጀምሮ በ 180 ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ለዜጎች መብቶች ቢሮ መቅረብ አለበት።

ለዜጎች መብቶች ቢሮ አቤቱታ ማቅረብ የሚፈልግ ማንኛውም ግለሰብ የሚከተሉትን መረጃዎች በጽሁፍ በደብዳቤ መልክ ወይም በቢሮው በሚሰጠው የአድልዎ አቤቱታ ቅጽ በመሙላት ለቢሮው ማቅረብ አለበት።

- ስምና አድራሻ (የስልክ ቁጥር ይጠቅማል፣ ነገር ግን የግድ አስፈላጊ አይደለም)።
- የተጠቂው/ዋ ግለሰብ ወይም ቡድን መግለጫ (የተጠቂ ግለሰብ ስም አይገለጽም)።
- አድልዎውን የፈጸመ የተቋም ስምና ቦታ።
- ምን እንደተከሰተ፣ መቼና ዝርዝር ሃሳብ የሚገልጽ በቂ ማብራሪያ ለቢሮው መቅረብ አለበት።
- ከላይ የተዘረዘሩት መረጃዎች ቀጥሎ ባለው የአሜሪካ ትምህርት ቢሮ፣ የዜጎች መብቶች ቢሮ አድራሻ መላክ አለበት፤

U.S. Department of Educatio
Office for Civil Rights, Region VIII
Federal Office Buidling
1244 Speer Blvd., Suite #310
Denver, CO 80204-3582

ቅሬታዎች በኢሜል ocr@ed.gov ላይ በኢሜይል ወይም በኤሌክትሮንክስ የOCR's ድረ ጣቢያ በመጠቀም ሊቀርቡ ይችላሉ- http://www.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

አቤቱታውን የሚቀበል ግለሰብ አቤቱታ አቅራቢው/ዋን ግለሰብ መልሶ ላያጠቃ/ላታጠቃ ይችላል/ትችላለች።
የተሻሻለው : - ሴፕተምበር 2018

## የተገናኙ የኤለክትሮኒክስ የመረጃ መገልገያዎች
## (EHC)

በኮምፕዩተር የታገዘ ዓለም አቀፍ የመረጃ ልውውጥ የሆነው እንተርኔትን ጨምሮ የስልክ መስመሮችና ሌሎች አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች በማኅበረሰቡ ውስጥ የመረጃ ልውውጥን በማፋጠን ላይ እንደሚገኙ ቦርዱ ይረዳል። መመሪያዎችን ለመለወጥ እና የተማሪን የትምህርት ክንውን ለማማሻል የኤሌክትሮኒክ የመረጃ ልውውጥ ትልቅ ሚና አለው። በተጨማሪም፣ የኤሌክትሮኒክስ የጥናት እና ምርምር ችሎታዎች ለዜጎች እና ለወደፊት ሰራተኞች እንደ የመረጃ ልውውጥ ዘመን መሰረታዊ ዝግጅት የሆነ ይመስላል፤ እንደዚሁም ለማስተማር እና መረጃን ለመስጠት በትምህርት ቦታዎች ውስጥ እንደ ማስተማሪያ መጠቀም አለበት።

የስልክ መስመሮች፣ የኤሌክትሮኒክስ የመረጃ ልውውጦች፣ እና የተገናኙ የመረጃ መስመሮች የመማሪያ ክፍሎችን ወቅታዊውን የዓለም በተመለከተ ለመረጃ ክፍት በማድረግ የመማሪያ ቦታን እየለወጡ ነው። ተማሪዎች እና ሰራተኞች  ይህንን መረጃ እንዲያገኙ እና መረጃዎቹን ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችላቸውን ተገቢውን ችሎታዎች እንዲያገኙ ጭምር ቦርዱ ድጋፍ አስፈላጊውን ይሰጣል።

በድረ-ገጽ ውስጥ ያሉት የትምህርት ዕድሎች ብዙ ስለሆኑ የመረጃው ተጠቃሚዎች ከድስትሪክቱ የትምህርት ግቦች ጋር የማይገናኙ ብዙ መረጃዎችን ሊያገኙ እንደሚችሉ ቦርዱ ያምናል። ነገር ግን፣ እንተርኔት እና የኤሌክትሮኒክስ የመረጃ ልውውጦች ተጠቃሚዎች መረጃዎችን ከብዙ ምንጮች እንዲያገኙ የሚረዱ ናቸው። የሥራ ባልደረቦች፣ ተማሪዎች፣ እና ሌሎች ህጋዊ ተጠቃሚዎች፡ የነጻ አገልግሎት ሰጪዎች፣ የተለያዩ ምርቶች አቅራቢዎች እና ሌሎች የድስትሪክትን ኮምፒዩተሮች እና የኮምፒዩተር ሥርዓቶች ሲጠቀሙ፣ ከዚህ ፖሊሲ ጋር የሚንጻረር መረጃ እንዳይጠቀሙ ኃላፊነት ይወስዳሉ።

ቦርዱ ሰራተኞች ይህንን መረጃ በአግባቡ ከሥርዓተ-ትምህርት ጋር በሚሄድ መልኩ እንደሚጠቀሙ እና እነዚህን መረጃዎች በአግባቡ እንዲጠቀሙ ለተማሪዎች አስፈላጊውን መመሪያ እንደሚሰጧቸው ከሰራተኞች ይጠብቃል። አወዛጋቢ የሆኑ ጉዳዮችን ትምህርትን በተመለከተ ሰራተኞች የቦርድ ፖሊሲዎች የሆኑትን  'IMB/IMB R' ማማከር አለባቸው፤ በተጨማሪም የማስተማሪያ መረጃዎችን/መጽሐፍትን ለመምረጥ፣ በቦርድ ፖሊሲዎች ውስጥ የተቀመጡትን  የ 'IJ/IJK' መመሪያዎች መከተል አለባቸው፤ በውስጣቸው የተካተቱትን ግቦችንም ማክበር አለባቸው።

የኤሌክትሮኒክስ የመረጃ ምንጮችን ከድስትሪክት ሥርዓተ-ትምህርት ጋር በተቻለ መጠን ለማዛመድ፣ በተቻለ መጠን፣ የመረጃ/የመጽሐት ምርጫዎችን የሚመለከቱ በቦርድ ፖሊሲዎች  'IJ' እና 'IJK' ውስጥ የተዘረዘሩ የቦርድ መመሪያዎች አንጻር፣ መረጃዎቹ ለተማሪዎች ከመቅረባቸው በፊት የድስትሪክት ሰራተኞች መረጃዎቹን  መከለስ እና መገምገም ይኖርባቸዋል። የድስትሪክቱን የተገናኙ የኤሌክትሮኒክስ የመረጃ ምንጮችን የሚያገኙ ተጠቃሚ ተማሪዎች ተከልሶ እና ተገምግሞ የቀረበላቸውን ነው የሚጠቀሙት። ምናልባት ተማሪዎች ተከልሶ እና ተገምግሞ ከቀረበላቸው መረጃ ሌላ ያልተገመገሙ እና ያልተፈቀደላቸው መረጃ  ማግኘት ቢችሉም እንኳን፣ መረጃን በተገቢው መንገድ መምረጥ እና መጠቀም እንዲችሉ መመሪያ ሊሰታቸው ይገባል። በዚህ መንገድ፣ ሰራተኞች ተማሪዎች ከድስትሪክቱ ሥርዓተ-ትምህርት ጋር የተገናኙ ጥናት እና ምርምር እና ሌሎች ጥናቶችን ለማካሄድ፣ ቴሌኮሚኒከሽን እና የኤሌክትሮኒክስ የመረጃ ምንጮችን ለመጠቀም እንዲችሉ ግልጽ የሆነ መመሪያ ይሰጧቸዋል።

ተማሪዎች የድስትሪክቱን ኮምፒዩተሮች እና የተገናኙ የኤሌክትሮኒክስ የመረጃ ምንጮች መጠቀም የሚችሉት የቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት የመረጃ ምንጮች የአጠቃቀም ሥርዓት ስምምነት ከተቀበሉ እና ከፈረሙ በኃላ ነው። ስምምነቱ፣ የሥነ-ምግባር እና የመገናኛ መመዘኛዎች ንድፍ የሆነ የአጠቃቀም ፖሊሲዎች ያካተተ ሲሆን፣ ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች ለሆኑ ልጆች የተገናኙ የኤሌክትሮኒክስ የመረጃ ምንጮችን እንዲጠቀሙ የወላጆች ፈቃድ ያስፈልጋል። ተማሪዎች በኤሌክትሮኒክስ የታገዘ ጥናት እና ምርምር በራሳቸው ያለ የሥራ ባልደረባ ቁጥጥር ማካሄድ የሚችሉት ከወላጅ እንደዚያ እንዲሆን ፈቃድ ከተሰጠ ብቻ ነው።

ተማሪዎች፣ የሥራ ባልደረቦች እና የተፈቀደላቸው ተጠቃሚዎች የድስትሪክቱን ኮምፒዩተሮች እና የተገናኙ የኤሌክትሮኒክስ የመገናኛ መስመሮች ምንጮች አጠቃቀም አስመልክቶ ተገቢው ስልጠና እና መመሪያ ይሰጣቸዋል። ይህም የተገናኙ የኤሌክትሮኒክስ የመገናኛ መስመሮች ምንጮች ለመጠቀም የሚያስችል የሙያዊ ችሎታ ሥልጠና እና የየተገናኙ የኤሌክትሮኒክስ የመገናኛ መስመሮች ምንጮች አጠቃቀም የስነ-ምግባር ትምህርት ያካትታል፣ በዚህ ብቻ ግን አይወሰንም።

የድስትሪክት ኮምፒዩተሮችን እና የቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት ድረ-ገጽ አጠቃቀም ከየቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት የትምህርት ግብ ጋር አብሮ መሄድ አለበት። ከዚህ ጋር በሚጻረር መልኩ የፌዴራል ወይም የክፍለ ግዛት ሕግ ወይም መተዳደሪያ ደንብ በመጣስ መረጃዎችን ማሰራጨት ክልክል ነው።

የሚከተሉት መመሪያዎች ለሁሉም የድስትሪክቱ ኮምፒዩተሮች እና የተገናኙ የኤሌክትሮኒክስ የመገናኛ መስመሮች ምንጮች ድረ-ገጽ ይሰራሉ፡

**መጥፎ፣ ወሲብ ነክ፣ ጎጂ የሆኑ መረጃዎችን መዘጋት ወይም ማጣራት**
ተማሪዎችን መጥፎ፣ ወሲብ ነክ እና ጎጂ ከሆኑ መረጃዎች ለመጠበቅ፣ አለበለዚያም ልጆችን ከሚጎዱ ነገሮች ለመጠበቅ፣ በቦርዱ እንደተወሰነው፣ እንደነዚህ ያሉትን መጥፎ እና ጎጂ ነገሮችን እና መረጃዎችን የሚዘጉ ወይም የሚያጣሩ ሶፍትወር  የሚባል የኮምፒዩተር ፕሮግራሞች ኢቴርኔት ወይም የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ምንጭ ባላቸው በሁሉም የድስትሪክት ኮምፒዩተሮች ላይ ተገጥመዋል። ነገር ግን፣ ፕሮግራሞቹ ፍጹም ያልሆኑ እና የኮምፒዩተር ተጠቃሚዎችን ከእነዚህ ዓይነቶቹ ጎጂ የሆኑ መረጃዎች ለመከልከል አስተማማኝ ላይሆኑ ይችላሉ።

የቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት የእንተርኔት ይዘትን ወይም አጠቃቀሙን አይቆጣጠርም፣ ሊቆጣጠርም አይችልም። ስለዚህ ተጠቃሚዎች ከእንቴርኔት ለሚያገኙት ጎጂ የሆኑ መረጃዎች ኃላፊነት አይወስድም፤ መረጃው በተጠቃሚው/ዋ ላይ ለሚያመጣው ጎጂ የሆነ ተጽዕኖም ተጠያቂ አይሆንም። ተጠቃሚዎች ከድስትሪክት ኮምፕዩተሮች ወይም ከቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት ድረ-ገጽ ለሚያገኙ ማንኛቸውም መረጃዎች ኃላፊነት ይወስዳሉ።

የቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት ከድስትሪክቱ ኮምፒዩተሮች ወይም ከቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት ድረ-ገጽ ለሚገኙ መረጃዎች ትክክለኛነት እና ጥራት ኃላፊነት አይወስድም፤ በተጨማሪም በመረጃ ሥርዓቱ ውስጥ ያሉትን የመረጃ ይዘቶችን አይቆጣጠርም። ከትምህርት ድስትሪክት ሥራዎች ጋር የማይገናኙ የግል ዕቃዎች እና አገልግሎቶች በመረጃ ሥርዓቱ በመጠቀም መግዛት/መገልገል የለበትም።

በሕገ-ወጥነት የድስትሪክቱን የመረጃ ሥርዓት በመጠቀም የግል ዕቃዎችን በመግዛት የሚከሰቱ ማንኛቸውም ከገንዘብ ክፍያ ጋር የተገናኙ ክስተቶች የተጠቃሚው/ዋ ኃላፊነት ይሆናል። በድስትሪክት ድረ-ገጽ ላይ፣ በኢ-ሜል ውስጥ የተከማቹ ፋይሎች/ሰነዶች እና የድስትሪክት ኮምፒዩተሮችን እና የቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት ድረ-ገጽ ለግል ጥቅም የሚውሉ አይደሉም፣ እናም ላይመረመሩ እና/ወይም ላይቆጣጠሩ ይችላሉ።

**የግል ምስጢር አይጠበቅም**

የድስትሪክት ኮምፒዩተሮች እና የቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት ድረ-ገጽ የድስትሪክቱ የሆኑ እና ሁል ጊዜ ለትምህርት ዓላማዎች እና ለድስትሪክቱ ሥራ የሚውሉ ናቸው። ሰራተኞች፣ ተማሪዎች እና ሌሎች ሊጠቀሙ የሚችሉ ኢንቴርኔቱን ወይም የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎችን ሲጠቀሙ በዚያ ውስጥ የግል ምስጥር እንደማይጠበቅ ማወቅ አለባቸው። ድስትሪክቱ ሁሉንም የኢንቴርኔት እና የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎችን እና የሚላኩትን እና የሚቀበሉትን መረጃዎች ጨምሮ፣ በማንኛውም ጊዜ እና አስቀድሞ ሳያስፈቅድ ሁሉንም የድስትሪክት ኮምፒዩተሮች እና የቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት ድረ-ገጽ የኮምፒዩተር ሥርዓቶችን የመቆጣጠር፣ የመፈተሽ፣ የመገልበጥ/የመቅዳት፣ የመከለስ እና የማከማቸት መብት አለው።

በድስትሪክት ኮምፒዩተሮች እና በቼሪ ክሪክ የትምህረት ድስትሪክት ድረ-ገጽ የኮምፒዩተር የመረጃ ሥርዓቶች የሚገኙ ሁሉም መረጃዎች የትምህርት ድስትሪክት ንብረቶች ናቸው። የመረጃው ተጠቃሚዎች በድስትሪክት ድረ-ገጾች ላይ ወይም በድስትሪክት ኮምፒዩተሮች ላይ፣ ወይም በቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት ድረ-ገጽ አማካይነት የሚገኙ መረጃዎች፣ ኢ-ሜልን ጨምሮ የግል እንዳልሆኑ ማወቅ ይገባቸዋል።

**የህዝብ ሰነዶች**

በድስትሪክት ሰራተኞች የሚላኩ እና የሚቀበሉ የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎች ለህዝብ ሊገለጹ የሚችሉ የህዝብ ሰነዶች የሆኑ ወይም በኮሎራዶ ክፍት/ግልጽ የሆኑ ሰነዶች አዋጅ መሰረት ሊፈተሹ የሚችሉ ሰነዶች ሊሆኑ ይችላሉ። የህዝብ የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ሰነዶች በሙሉ ሕጋዊ በሆነ መንገድ እና ፖሊሲ በሚያዘው መሰረት መወሰዳቸውን፣ መለቀቃቸውን፣ በማጎደር መያዛቸውን እና መወገዳቸውን ለማረጋገጥ፣ የሁሉም ሰራተኞች የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎች ከተገቢው የክፍለ ግዛት እና ከፌዴራል ሕጎች አንጻር፣ እና ከሚመለከተው የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ መሰረት መቆጣጠር አለበት።

**ያልተፈቀዱና ተቀባይነት የሌላቸው አጠቃቀሞች**

ሰራተኞች፣ ተማሪዎች እና ሌሎች የተፈቀደላቸው ተጠቃሚዎች የድስትሪክት ኮምፒዩተሮችን እና የኮምፒዩተር የመረጃ ሥርዓቶችን ኃላፊነት በተሞላበት፣ በብቃት፣ በጥሩ ስነ-ምግባር እና ሕጋዊ በሆነ መንገድ መጠቀም አለባቸው።

ቴክኖሎጂ እና የቴክኖሎጂ አጠቃቀም በተከታታይነት እየተሻሻሉ ስለሆነ፣ ሁሉም ተቀባይነት የሌላቸው የድስትሪክት ኮምፒዩተሮች እና የቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት ድረ-ገጽ አጠቃቀሞች በተለየ ሁኔታ ተወስነው በዚህ ፖሊሲ ውስጥ ሊገለጹ አይችሉም። ስለዚህም፣ ተቀባይነት የለላቸው አጠቃቀሞች ምሳሌዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፣ በነዚህ ብቻ ግን አይወሰኑም፡፡

ለማንኛውም የድስትሪክቱ ሰራተኛ፣ ለተማሪ ወይም ለሌሎች ህጋዊ ተጠቃሚዎች ቀጥሎ ለተዘረዘሩት ጉዳዮች የድስትሪክቱን የኮምፒዩተር መረጃዎች ወይም ፕሮግራሞች መጠቀም፣ ማሰራጨት፣ ፋይል መክፈት ወይም መላክ አይቻልም፡

- ሁከትን የሚፈጥር ወይም የንብረት ማውደም ዓላማን የሚያራምድ ጉዳይ፣ ይህም የአጥፊ መሳሪያዎች አምራች ወይም ሽያጭ መረጃን ማግኘት/መስጠት ሊሆን ይችላል፣ በዚህ ብቻ ግን አይወሰንም።
- ከድስትሪክት የትምህርት ዓላማዎች/ግቦች ጋር የማይገናኙ ጉዳዮች።
- ወሲብ-ነክ፣ መጥፎ ወይም ሌሎች ለወሲብ ፍላጎት የሚያነሳሱ ወይም መላ ሰውነትን ለወሲብ የሚሰቡ እርቃን/ራቁት የሚያሳዩ እና ስለ ወሲብ ጉዳዮችን ያተኮሩ/የያዙ የሥዕል ወይም የጽሁፍ መረጃዎች።
- በዘር፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በኃይማኖት፣ በብሄር/በሀገረሰብ ዝርያ፣ በዕድሜ፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በስንኩልነት ምክንያት ሌላ ሰውን ወይም ቡድንን የሚያስፈራራ፣ የሚያንኳስስ፣ ወይም ሁከትን ወይም ጥላቻን የሚያነሳሳ።
- ለግል ጥቅም፣ ገንዘብን ለማግኘት፣ ለማስታወቂያ፣ ለንግድ ልውውጥ ወይም ለፖለቲካ ዓላማዎች።
- የሌላውን ሰው ሥራ ያለ ህጋዊ ፈቃድ እንደ የራስ አድርጎ መውሰድ/መጠቀም።
- በትምህርት ቤት ማኅበረሰብ ውስጥ በለሌሎች  ላይ ጥቃት ሊያደርስ የሚችል የባለጌ ወይም አግባብ የሌለው ንግግርን መጠቀም።
- የሌላውን ሰው ስም ለማበላሸት/ለማጥፋት ዓላማ ሆን ተብሎ የተፈጠረ ውሸት።
- ማንኛውንም የፌዴራል ወይም የክፍለ ግዛት ህግ የሚንጻረር፣ የባለቤትነት መብቱ የተጠበቀ ጽሁፍ እና በንግድ ምልክት የተጠበቀ ጽሁፍ ሊያካትት ይችላል፣ በዚህ ብቻ ግን አይወሰንም።
- ስለ ራሳቸው ወይም ስለ ሌሎች ሰዎች የግል መረጃ የያዘ እና በሕግ የግል ምስጥር አያያዝ የተጠበቀ።
- ከህጋዊ የሥራ ድርሻ ወይም ከትምህርታዊ ዓላማ ጋር የሚገናኝ መልዕክትን አስተዳደርን አስቀድሞ ሳያስፈቅዱ በግል መያዝ ወይም ማሰራጨት።
- አስቀድሞ ከኮምፒዩተር የመረጃ ሥርዓት/ፕሮግራም ተቆጣጣሪ ፈቃድ ካልተገኘ እና ከህጋዊ የሥራ ድርሻ ወይም ከትምህርታዊ ጉዳዮች ጋር ካልተገናኘ በስተቀር፣ ወደብን ማሰስ፣ የተገናኙ መስመሮችን ማሰስ፣ የተገናኙ መስመሮችን መቆጣጠር፣ ወይም  የቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት ድረ-ገጽ ወይም ከቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት ድረ-ገጽ ማንኛውንም የማሰሻ መሣሪያ ወይም ፕሮግራም መጠቀም።
- ተከፍቶ የሚገባ፣ ፓስዎርድን የሚከፍቱ ፕሮግራሞች፣ እና የኮምፒዩተር ፕሮግራም የሆኑ ሶፍትወሮችን በሕገ-ወጥነት መጠቀም፣ ወይም እንደዚህ ዓይነቱ ድርጊት ህጋዊ የሆነ የሥራ ድርሻ አካል ወይም ለትምህርታዊ ዓላማዎች ካልሆነ በስተቀር፣ ማንኛውንም ፋይል ለሌላ ሰው መስጠት። ለዚህ ፖሊሲ ዓላማዎች ሲባል፣ 'ሶፍትወሮችን በሕገ-ወጥነት' መጠቀም ማለት " ኮምፒዩተርን በመክፈት የኮምፒዩተር ፋይል/ሰነድ፣ ሕገ-ወጥ በሆነ መንገድ ወይም ያለ ፈቃድ ፤ ለማየት፣ ለመቀየር/ለማሻሻል፣ ለመስረቅ፣ ለማጥፋት ዓላማ መጠቀም ወይም ያለ ፈቃድ የኮምፒዩተርን መረጃ ማጥፋት።
- ከመረጃ ሥርዓት ቁጥጥርና ጥበቃ አስተዳዳሪ ፈቃድ ሳያገኙ መገልገልና መረጃን ማየት።

የድስትሪክት የኮምፒዩተር የመረጃ ሥርዓት በጥብቅ መጠበቅ ከፍተኛ ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ነው። ኢንቴርኔትን፣ የቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት ድረ-ገጽ ወይም ሌሎች የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎችን የሚጠቀሙ ሰራተኞች፣ ተማሪዎች ወይም ሌሎች ሕጋዊ ተጠቃሚዎች እየተጠቀሙ እያሉ የሚከሰተውን የድረ-ገጽ/የኮምፒዩተር የደኅንነት ችግር ለትምህርት ቤቱ አስተዳደር፣ ወይም ተወካይ በአስቸኳይ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል። ሰራተኞች እና ተማሪዎች ችግሩን ለሌሎች ተጠቃሚዎች መግለጽ የለባቸውም። እንደ የመረጃ ሥርዓት አስተዳዳሪ ሆኖ በኢንተርኔት ድረ-ገጽ ላይ ወይም የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎች ላይ መግባት ክልክል ነው።

ሰራተኞች እና ተማሪዎች፡

- በድስትሪክቱ በተወሰነው መሰረት፣ ተገቢውን ፈቃድ ሳያገኙ የሌላን ሰው ፓስወርድ ወይም ማንኛውንም ሌላ መለያ መጠቀም ወይም ለመጠቀም መሞከር የለባቸውም።
- በሕገ-ወጥ መንገድ የድስትሪክት ኮምፒዩተሮችን ወይም የኮምፒዩተር የመረጃ ሥርዓቶችን፣ የኮምፒዩተር የመረጃ ፋይሎችን ማግኘት ወይም ለማግኘት መሞከር።
- ያለ ፈቃድ ወይም በድስትሪክቱ በተወሰነው መሰረት አግባብ ባልሆነ መንገድ የሌሎች የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ የመረጃ ሥርዓቶችን ተጠቃሚዎች መረጃ ማንበብ፣ መቀየር/መለወጥ፣ ማጥፋት ወይም መገልበጥ ወይም እንደዚያ ለማድረግ መሞከር።

ለኮምፒዩተር ድረ-ገጽ እና ለመረጃ ሥርዓቱ ደኅንነት አስጊ የሆኑ፣ ወይም በሌላ የኮምፒዩተር የመረጃ ሥርዓቶች ችግር ያለባቸው እና ከዚህ የተነሳ መጥፎ ታሪክ ያላቸው ማንኛቸውም የሥራ ባልደረቦች፣ ተማሪዎች ወይም ሌሎች ህጋዊ ተጠቃሚዎች ኢንቴርኔት እና የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ሥርዓቶችን እንዳይጠቀሙ ሊከለከሉ ይችላሉ።

**ለህዝብ  በኤሌክትሮኒክስ (እንቴርነት ወይም ስልክ) የሚተላለፍ መልዕክቶች**

የድስትሪክት  የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ለትምህርታዊ እና ለትምህርት ሥራ ብቻ ነው። ለድስትሪክቱ የትምህርታዊ ዓላማ ወይም ለድስትሪክቱ ትምህርት ቤቶች ሥራ ሳይሆን የግል ድረ-ገጽ መክፈት እና መጠቀም፣ 'Wiki' የሚባል ድረ-ገጽ መክፈት እና መጠቀም ፣ ሌሎች የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎች ወይም በኮምፒዩተር መስመር በመገናኘት ውይይቶችን ማካሄድ በድስትሪክቱ ኮምፒዩተር መገናኛ ሥርዓት መሆን የለበትም።

ለህዝብ የሚተላለፍ የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎች እና በኮምፒዩተር መገናኛ መስመሮች መወያየት ፣ ነገር ግን በድረ-ገጾች፣ በ'Wiki'፣ በቡለትን ቦርድ፣ በኢ-ሜል፣ ወይም በሌሎች የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ መስመሮች ብቻ ያልተወሰኑ ሁሉም የድስትሪክቱ የኮምፒዩተር የመረጃ ሥርዓቶች በትምህርት ቦርድ ፖሊሲዎች እና መተዳደሪያ ደንቦች መሰረት የትምህርት ድስትሪክት ሥራዎችን ወይም ፕሮግራሞችን/መርሃ ግብሮችን ለማፋጠን የሚረዱ እና የመማሪያ ክፍል እና/ወይም የድስትሪክት ሥራዎችን ማስኬጃ መሳሪያዎች ናቸው።

ከላይ የተጠቀሰውን የመረጃ መገልገያ መሳሪያዎችን በመማሪያ ክፍሎች ውስጥ የሚጠቀም/የሚትጠቀም የሥራ ባልደረባ ከታች በተዘረዘሩት መሰረት መሆን አለበት፡

1. ዓለም አቀፍ ድረ-ገጽ የሆነውን የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ መስመሮችን ለመጠቀም ለእያንዳንዱ ተማሪ የወላጅ/የአሳዳጊ ፈቃድ መሰጠቱን ማረጋገጥ።
2. የደህንነት ጉዳዮችን እና አግባብ ያለው እንዲሁ ዓይነቱን የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ መስመሮችን አጠቃቀም በተመለከተ ለተማሪዎች መመሪያ መስጠት።
3. ተገቢው የትምህርት ቦርድ ፖሊሲዎች እየተገበሩ መሆኑን ለማረጋገጥ የኤሌክትሮኒክስ የመገናኛ መስመሮቹን ይዘት በየጊዜው መቆጣጠር እና መከለስ።

**ቁጥጥር**

ኢንተርኔትን የሚጠቀሙ ሁሉንም ሰራተኞች እና ተማሪዎች መቆጣጠር እንደማይቻል ይታወቃል፤ ነገር ግን፣ በቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት መሰረት በድስትሪክቱ ኮምፒዩተር ማንኛውም ዓይነት ሕገ-ወጥ ተግባር መፈጸም ፍጹም ክልክል የሆነ እና ኮምፒዩተሩን እንዳይጠቀሙ መከልከል እና/ወይም የቅጣት እርምጃን ሊያስከትል ይችላል። ለተማሪዎች የሚሰጠው የቅጣት እርምጃ በተሰጠው የስነ-ምግባር ፖሊሲዎች የሚፈጸም ሲሆን፣ ለጊዜው ከትምህርት ቤት መታገድ እና/ወይም ወደ ሌላ አማራጭ የጸባይ ማረሚያ ትምህርት ቤት መወሰድ ሊያካትት ይችላል። ተጠቃሚው በሕገ-ወጥ ተግባር የሚጠረጠር ከሆነ አግባብ ያላቸው የሕግ ባለ ሥልጣናት ጉዳዩ ይገለጻል። ተጠቃሚዎች በድስትሪክቱ ኮምፒዩተሮች ተገቢ ያልሆኑትን ጉዳዮች እንዳያስገቡ፣ እንዳያሳትሙ ወይም በኮምፒዩተሩ ላይ እንዳያሳዩ ወይም በቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት ድረ-ገጽ በመጠቀም ሰውን የሚያዋርድ፣ ትክክል ያልሆነ፣ የግፍ እርምጃ ያለበት፣ መጥፎ፣ ወሲብ-ነክ ጉዳዮችን፣ ዛቻን፣ የዘር ጥቃት፣ ወይም ሕገ-ወጥ ጽሁፎችን ማስገባት እንደሌለባቸው መስማማት አለባቸው። በተጨማሪም፣ ተጠቃሚዎች የድስትሪክቱን ኮምፒዩተር  እና/ወይም የቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት ድረ-ገጽ ለመጠቀም በሁሉም የባለበትነት መብቶች ሕጎች መስማማት አለባቸው። የባለበትነት መብቶች የተጠበቀላቸውን ጽሁፎች መገልበጥ/መቅዳት፣ እንደ የራስ አድርጎ ማስቀመጥ ወይም ማሰራጨት ክልክል ነው፤ በግልጽ ካልተገለጸ በስተቀር፣ የኮምፒዩተር ተጠቃሚዎች ጽሁፎቹ በየባለበትነት መብት የተጠበቁ እንደሆኑ ማሰብ አለባቸው።

**በምስጢር የሚያዝ ሰነድ**

የድስትሪክት ኮምፒዩተሮች እና የቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት ድረ-ገጽ ተጠቃሚዎች በተገቢው የክፍለ ግዛት እና የፌዴራል የግል ምስጥር መያዝ ሕጎች እና የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ መሰረት የተማሪ፣ የወላጅ/የአሳዳጊ ወይም የድስትሪክቱ ሰራተኛ የግል ምስጥር መረጃ ማግኘት፣ መቀበል፣ ማስተላለፍ ወይም እንደገና ማሰራጨት አለባቸው። መረጃ በሕግ ያልተጠበቀ ከሆነ፣ ነገር ግን የግል ምስጥር ወይም በጣም አስፈላጊ ከሆነ፣ መረጃውን ማግኘት ያለባቸው አግባብ ያላቸው ሰዎች ብቻ መሆኑን በማረጋገጥ ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግለት ይገባል።

በኢ-ሜል ወይም በሌሎች የቴሌኮሚኒከሽን የመረጃ ለውውጥ ሥርዓቶች የሚደረጉ ጨምሮ፣ የግል ምስጥር የሆኑ የተማሪ ሰነዶችን መግለጽ በየቤተሰብ የትምህርት መብቶች እና የግል ምስጥር መጠበቅ አዋጅ መቆጣጠር አለበት። ስለዚህም፣ መረጃው የሚገለጸው በልዩ ሁኔታ በትምህርት ቦርድ ፖሊሲ 'JRC' ውስጥ በተወሰነው መሰረት፣ የተማሪ ሰነዶች/የተማሪ ሰነዶችን መስጠት እና ተያያዥ መተዳደሪያ ደንብ 'JRC-R' መሰረት፣ በየቤተሰብ የትምህርት መብቶች እና የግል ምስጥር መጠበቅ አዋጅ አማካይነት ካልሆነ በስተቀር፣  አስቀድሞ ከተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ የጽሁፍ ፈቃድ ሳያገኙ የተማሪ ሰነዶችን ወይም ሌሎች የግል መረጃዎችን ከትምህርት ድስትሪክት ውጪ ለሆኑ ሰዎች ወይም ድርጅቶች/ተቋማት በኢ-ሜል መስጠት ክልክል ነው። የተማሪ ሰነዶች እና ሌሎች የተማሪ የግል ምስጥር መረጃዎች  ለሌሎች የድስትሪክት ሰራተኞች በኢ-ሜል የሚሰጠው መረጃው የሚሰጠው የሥራ ባልደረባ ሕጋዊ ለሆነ ለትምህርት ጉዳይ የሚፈልግ/የሚትፈልግ ከሆነ ነው።

በድስትሪክት ተክኖሎጂ የሚያዙ ማንኛውም የተማሪ ሰነዶች፣ የተማሪ ሰነዶችን የያዙ ኢ-ሜልን ወይም ማንኛውም ሌሎች የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎችን ጨምሮ፣ የተማሪ ሰነዶች ናቸው፤ ለወላጅ/ለአሳዳጊ ክለሳም የሚፈቀዱ እና በየቤተሰብ የትምህርት መብቶች እና የግል ምስጥር መጠበቅ አዋጅ መስፈርቶች መሰረት መያዝ አለባቸው። የተማሪ ሰነዶች እና የግል ምስጥሮች መረጃ ወደ ሌላ አላስፈላጊ ቦታ እንዳይላክ/እንዳይተላለፍ፣ በኤሌክትሮኒክስ የመገናኛ መስመሮች የተማሪ ሰነድን/የግል ምስጥር መረጃን የሚለዋወጡ ሰራተኞች ስለቴክኖሎጂው በቂ ዕውቀት እና መረዳት ሊኖራቸው አለባቸው። የቤተሰብ የትምህርት መብቶች እና የግል ምስጥር መጠበቅ አዋጅ በሚንጻረር መሰረት በኢ-ሜል የተማሪ ሰነዶችን ወይም ሌሎች የግል ምስጥር መረጃዎችን በሚገልጹ ሰራተኞች ላይ የቅጣት እርምጃ ይወሰድባቸዋል።

**ሆን ብሎ የመገናኛ መስመሮቹን ማውደም/ማጥፋት**

የመገናኛ መስመርችን/የኮምፒዩተር መረጃዎችን ማውደም የኮምፒዩተር መጠቀም መብትን መከልከል ወይም ወደ የቅጣት እርምጃ ሊያመራ ይችላል።ማውደም/ማጥፋት ማለት በትምህርት ድስትሪክት ውስጥ ወይም ማንኛውም ከኢንቴርኔት ጋር የተገናኘ መስመር እና በውስጡ ያለውን መረጃ፣ ማንኛውንም ዓይነት የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ፣ የሌላን ሰው መረጃ፣ የሌላን ሰው የኮምፒዩተር አጠቃቀም፣ ወይም የድስትሪክቱን የኮምፒዩተር ሶፍትዌር ወይም ሀርድዌር ሆን ብሎ መጉዳት፣ ማጥፋት፣ መለወጥ/ማሻሻል፣ የግፍ ተግባር መፈጸም፣ ወይም ሥራውን ማሰናከል ነው። ይህም የኮምፒዩተር ቫይረሶችን መቅዳት ወይም መፍጠር እና የሶፍትዌር መረጃን ወደ ሌላ ምስጥራዊ ወደ ሆነ ነገር መለወጥ እና መጠቀም ቢያካትትም፣ በዚህ ብቻ ግን አይወሰንም። ድስትሪክቱ የመረጃ ሥርዓቱን በሙሉ የመቆጣጠር መብት አለው።

**ህጋዊ ያልሆነ ሶፍትዌር (በኮምፕዩተር ቋንቋ የተሰራ ክትብ ቁስ)**

ለሰራተኞች እና ለተማሪዎች የተቀዳን ሶፍትዌር ወይም አለበለዚያም የሌላን ሰው ሶፍትዌር ያለ ተገቢው ፈቃድ ወይም ለባለበቱ አስፈላጊውን ክፊያ ሳይሰጡ መጠቀም ወይም ባለበት መሆን ክልክል ነው። ሰራተኞችተማሪዎች ወይም ሌሎች ተጠቃሚዎች የትምህርት ድስትሪክቱ ያልሆነውን ወይም ለመጠቀም ያልተፈቀደውን ሶፍትዌር በድስትሪክት ኮምፒዩተር ላይ መጫን አይችሉም።

**የመጠቀም መብት**

የሠራተኞች እና የተማሪዎች የድስትሪክቱን እና የቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት ድረ-ገጽ ኮምፒዩተሮች መጠቀም፣ ኢንቴርኔትን መጠቀም እና በኢ-ሜል መገናኘት የግለሰብ ኃላፊነት እና ተቀባይነት ያላቸውን እና የሌላቸውን ጉዳዮች ማወቅ ያስፈልጋል። የሰራተኞች እና የተማሪ ኢንቴርኔት እና የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎችን መጠቀም ከመብት ያለፈ ነው። በዚህ ፖሊሲ ውስጥ የተገለጸውን የአጠቃቀም ሂደት አለመከተል ይህንን መብት ማጣት እና የቅጣት እርምጃ እና/ወይም ሕጋዊ እርምጃን ሊያስከትል ይችላል። የትምህርት ድስትሪክቱ በድስትሪክት ቴክኖሎጂ መጠቀምን ሊከለክል፣ መብትን ሊገፍ ወይም ለጊዜው ማገድ ወይም በማንኛውም ጊዜ አካውንቱን/ፋይሉን ሊዘጋ ይችላል።

ከሰራተኞችና ከተማሪዎች ጋር ያደረጉ ሁሉም ዓይነት የመገናኛ መንገዶች አግባብ ያላቸውና በክፍለ-ግዛቱ ህግ መሰረት መሆን እንዳለባቸው የትምህርት ቦርድ ያዛል። እነዚህን ቁሳቁሶች በመጠቀም የሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ከተማሪ ጋር ትምህርተ-ነክ የሆኑ ጉዳዮችና በወላጆች ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ጉዳዮች ሲሆኑ፣ ሁሉም የመረጃ ቅብብሎሾች በአግባብ መሆን አለባቸው።

የሰራተኞችና የተማሪዎች ስምና ሥራ አግባብ በለላቸው የመረጃ ቅብብሎሾች ምክንያት እንደተጎዱ ቦርዱ ይገነዘባል። ስለዚህም፣ ተማሪዎችና ሰራተኞች በሙሉ እንደሚጠበቅባቸውና አግባብ ባለው መንገድ የመረጃ ማሰራጫ መስመሮችን መጠቀም እንዳለባቸው ቦርዱ ያዛል። ይህ ደግሞ የተማሪዎችና የሰራተኞችን የመረጃ ምንጭ የመጠቀም መብት ለመገደብ ሳይሆን አግባብ እንዲኖረው ነው።

ሠራተኞች ከተማሪዎች ጋር በሚያደርጉት ግንኙነቶች በሙሉ ውስጥ በቦርዱና በአስተዳዳሪ የተሰጡትን ሁሉንም ፖሊሲዎች፣ ሂደቶችና ተግባራት እንዲጠብቁ ይጠበቅባቸዋል፤ ይህንን መተላለፍ ከሥራ መባረር ጨምሮ አስፈላጊውን ቅጣት ሁሉ ያስከትላል። የባሰ እንድሆነም እንደ ሆን ተብሎ የሚደረግ የሥራ ቸልተኝነት ሊቆጠር ይችላል። ይህንን ህግ መጣስ የፌዴራል ህግ መጣስ ስለሆነ፣ የድስትሪክቱ የበላይ አለቃ ወይም ተወካይ ጉዳዩን ለሚመለከታቸው ክፍሎች ያስታውቃል/ታስታውቃለች።

**የትምህርት ድስትሪክት ምንም ዋስትና አይወስድም**

ኢንተርኔት መጠቀም እና የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎች አገልግሎቶች፣ ወይም እንደዚህ ዓይነቶቹ አገልግሎቶች ማግኘት ስህተት ወይም ችግር የሌለበት ማድረግን ጨምሮ፣ የድስትሪክቱን ኮምፒዩተሮች እና የኮምፒዩተር የመረጃ ሥርዓቶችን መጠቀም በተመለከተ፣ የቼሪ ክሪክ የትምህርት ድስትሪክት፣ በግልጽም ሆነ በውስጥ ታዋቂነት፣ ማንኛውንም ዓይነት ዋስትና አይወስድም። ድስትሪክቱ እነዚህን አገልግሎቶች ሲሰጥ የመረጃውን ይዘት ይደግፋል ወይም የሚገኘውን መረጃ ትክክለኛነት ወይም ጥራት ያረጋግጣል ማለት አይደለም። የድስትሪክት ኮምፒዩተሮችን፣ ወይም ኢንቴርኔት እና የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎችን ሲጠቀሙ ወይም በሥርዓቱ መጠቀም ካለመቻል የተነሳ ለሚፈጠሩ ጉዳቶች ወይም ችግሮች ለሚያስፈልጉ ወጪዎች፣ የትምህርት ድስትሪክቱ ኃላፊነት አይወስድም። ይህም የመረጃ መጥፋት እና የአገልግሎት መስተጓጎልን ያካትታል። በኢንተርኔት እና በኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎች የሚገኙትን መረጃዎች መጠቀም የተጠቃሚው ኃላፊነት እና ተጠያቂነት ነው።

የቀረበው፤ ጁን 9፣ 1997
ሥራ ላይ የዋለው፤ ኦገስት 11፣ 1997
የተሻሻለው፤ ጃንዋሪ 9፣ 2012

ህጋዊ ዋቢዎች፤ 47 U.S.C. 254(h) (የ2000 የልጆች የኢንተርኔት ጥበቃ አዋጅ)
47 U.S.C. 231 (የ1998 የልጆች የመገናኛ መስመር ጥበቃ አዋጅ )
20 U.S.C. 6801 ቀጣይ (የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቶች አዋጅ)
C.R.S. 22-87-101፣ ቀጣይ (የልጆች ከእንተርኔት ጥበቃ አዋጅ)
C.R.S. 24-72-204.5 (የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎች ቁጥጥር)

ጥምር ዋቢዎች፤ EGA፣ ኢ-ሜል
EGAD፣ የባለበትነት መብት/
EHCA፣ የድረ-ገጽ እና የኢንተርኔት ህትመት
JS ፣ የተማሪ ኢንቴርኔት እና የኤሌክትሮኒክስ መጠቀም
JRC ፣ የተማሪ ሰነዶች/የተማሪዎችን መረጃ መስጠት

ኢንተርኔት፣ የዓለም አቀፍ በኮምፒዩተር የተገናኙ መስመሮች የሆነ እና ዓለም አቀፍ የመረጃ ድር የሚባል፣ እና የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎች (በእነዚህ ብቻ ባይወሰኑም፣ ኢ-ሜል፣ የመገናኛ መስመሮች፣ ፋይሎችን መስጠት እና ሌሎች የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ መልኮች ጨምሮ) ሥርዓተ ትምህርት እና ተማሪዎችን በትምህርታቸው ለማገዝ እምቅ ኃይል አለው። እነዚህ የመረጃ ምንጮች በትምህርት ቤቶች ውስጥ እንደ የማስተማሪያ የመረጃ ምንጮች ለማስተማር እና ለማሳወቅ/መረጃን ለመስጠት ማገልገል እንዳለበት የትምህርት ቦርድ ያምናል።

ኢንተርኔትና የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎችን መጠቀም የተማሪዎች የማሰብ/የማሰላሰል፣ መረጃን የመተንተን፣ የጽሁፍ ችሎታን የማዳበር፣ ችግሮችን የመፍታት ብቃትና ችሎታዎች፣ እና የሥራ ቀጣሪዎች የሚፈልጉ የኮምፒዩተር እንደዚሁም የጥናትና የምርምር ችሎታዎችን ይፈልጋል። እነዚህን ነገሮች መጠቀም የእድሜ ልክ በቀጣይነት መማር ባህሪን ያበረታታል፤ በተጨማሪም ለተማሪዎች በርቀት ትምህርት ተግባራት የመሳተፍ፣ ጥያቄዎችን የመጠየቅ እና ከአዋቂዎች ጋር የመማከር፣ ከሌሎች ተማሪዎች እና ግለሰቦች ጋር የመገናኘት፣ እና የትምህርት እና የግል የመረጃ ጥማት የማርካት ዕድል ይሰጣል።

የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ከድስትሪክቱ የትምህርት ዓላማ ጋር የማይሄዱትን አንዳንድ መረጃዎችን ሊያገኙ ቢችሉም፣ ከእነዚህ የመረጃ ምንጮች አገልግሎቶች የሚያገኙት የትምህርት ዕድሎች ብዙ እንደሆኑ ቦርዱ ያምናል። ነገር ግን፣ ኢንቴርኔት እና የኤሌክትሮኒክስ የመረጃ ምንጮች ተማሪዎች ብዙ ጽሁፎችን እና መረጃዎችን፣ ጎጂ ሊሆኑ የሚችሉ የተወሰኑ መረጃዎችን ጨምሮ፣ የሚያገኙበት ነው። ተማሪዎች የድስትሪክቱን ኮምፒዩተሮች እና የመረጃ ምንጮቹን የአጠቃቀም ሥርዓቱን በመጠበቅ የመጠቀም ኃላፊነት አለባቸው። ተማሪዎች ምን ዓይነት መረጃዎችን ከኮምፒዩተር ውስጥ ሊያገኙ እንደሚችሉ በእርግጠኝነት መገመት ባይቻልም፣ መጥፎ፣ ወሲብ ነክ ጽሁፎችን ወይም አለበለዚያም በቦርዱ በተወሰኑ መሰረት ለልጆች ጎጂ ከሆኑትን ጽሁፎችና መረጃዎች ተማሪዎችን ለመጠበቅ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎች መወሰድ እንዳለባቸው ቦርዱ ያምናል። እነዚህን ጉዳዮች በተመለከተ ተማሪዎች የድስትሪክት ኮምፒዩተርና የኮምፒዩተር የመረጃ ሥርዓት ሲጠቀሙ ለሚያደርጉት ሁሉ ኃላፊነት አለባቸው።

**መጥፎ፣ ወሲብ ነክ ጽሁፎችንና ጎጂ የሆኑትን መረጃዎች መከልከል ወይም ማጣራት**

በቦርድ ውሳኔ መሰረት መጥፎ፣ ወሲብ ነክ ጽሁፎችን አለበለዚያም በቦርዱ በተወሰነው መሰረት ለልጆች ጎጂ የሆኑትን ጽሁፎች እና መረጃዎችን የሚዘጋ ወይም የሚያጣራ ሶፍትዌር የሚባል የኮምፒዩተር ቋንቋ ኢንተርኔትና የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎች ባላቸው በሁሉም የድስትሪክቱ ኮምፒዩተሮች ላይ መገጠም አለበት። የድስትሪክት ኮምፒዩተሮችን ወይም ድረ-ገጹን የሚጠቀሙ ተማሪዎች የድስትሪክቱን የመረጃ ማጣሪያ ማለፍ ወይም ለማለፍ መሞከር የለባቸውም። እንደዚሁም፣ በድስትሪክቱ ማጣሪያ በኩል የማያልፉትን ኢንቴርኔት የማግኘት ተግባራት መፈጸም የለባቸውም። ይህንን ፖሊሲ የሚጥስ ማንኛውንም ግለሰብ ካዩ ተማሪዎች ለአለቃ ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል። እንደዚሁም፣ በሌላ ይህ ድርጊት በሌላ ተማሪ ሲፈጸም ያየ/ች ተማሪ ጉዳዩን ለአለቃ ማሳወቅ አለበት/አለባት።

**የግል ምስጢር የመጠበቅ ልዩ መብት አይኖርም**

የድስትሪክት ኮምፒዩተሮችና የኮምፒዩተር የመረጃ ሥርዓቶች የድስትሪክቱ የሆኑና ሁል ጊዜ ለድስትሪክቱ የትምህርት ዓላማዎች ብቻ የሚውሉ ናቸው። ኢንቴርኔትን ወይም የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎችን ሲጠቀሙ፣ ተማሪዎች የግል ምስጢር እንደሚጠበቅ መገመት የለባቸውም። ድስትሪክቱ ሁሉንም የድስትሪክቱን ኮምፒዩተሮችና የኮምፒዩተር ሥርዓቶች አጠቃቀም፣ ሁሉንም ኢንተርኔትና የኤሌክትሮኒክስ የመረጃ መገናኛዎች ማግኘትና ማስተላለፍ/መቀበል ጨምሮ፣ (በማንኛውም ጊዜ አስቀድሞ ሳያስፈቅድ) የመቆጣጠር፣ የመፈተሽ፣ የመገልበጥ/የመቅዳት፣ የመከለስና የማከማቸት መብት አለው። በድስትሪክት ኮምፒዩተሮች የኮምፒዩተር ሥርዓቶች  የሚገኙት ጽሁፎች እና መረጃዎች በሙሉ የትምህርት ድስትሪክቱ ንብረቶች ናቸው።

**ክልክል የሆኑና ተቀባይነት የሌላቸው አጠቃቀሞች**

ተማሪዎች የድስትሪክትን ኮምፒዩተሮች እና የኮምፒዩተር የመረጃ ሥርዓቶችን በኃላፊነት፣ በብቃት፣ በሥርዓትና ሕጋዊ በሆነ ሁኔታ መጠቀም አለባቸው።

ቴክኖሎጂና የቴክኖሎጂ አጠቃቀሞች በየጊዜው እየተሻሻሉና እያደጉ ስለሚሄዱ፣ እያንዳንዳቸው ተቀባይነት የሌላቸው የድስትሪክት ኮምፒዩተሮች እና የኮምፒዩተር የመረጃ ሥርዓቶች አጠቃቀሞችን በመወሰን በዚህ ፖሊሲ ውስጥ  መግለጽ አይቻልም። ስለዚህም፣ ተቀባይነት የሌላቸው አጠቃቀሞች ምሳሌዎች ከታች ተዘርዝረዋል፣ በእነዚህ ብቻ ግን አይወሰኑም፤

ማንኛውም ተማሪ ቀጥሎ ያሉትን መረጃዎች ወይም ሶፍትዌር የሚባል የኮምፒዩተር ቋንቋ ማግኘት፣ መፍጠር፣ ለሌላ ሰው መላክ፣ የተላከውን ለሌላ ሰው ማስተላለፍ አይቻልም፤

- ከድስትሪክቱ የትምህርት ዓላማዎች ጋር ያልተገናኙ
- ሁከትን የሚፈጥር ወይም ንብረትን ለማጥፋት የሚቀሰቅስ፣ ስለ ፋብሪካ ወይም አጥፊ መሳሪያዎችን የመግዛት መረጃ ሊሆን ይችላል፣ በእነዚህ ብቻ ግን አይወሰኑም
- የወሲብ ነክ ጽሁፎችን፣ መጥፎ ወይም ወሲብ ላይ የሚያተኩሩ ጽሁፎች፣ በሥዕል መልክም ሆነ በጽሁፍ ሊሆን ይችላል፣ ወሲባዊ ስሜቶችን የሚቀሰቅሱ ወይም እርቃንን የሚያሳዩ እና ለወሲብ የሚቀሰቅሱ መረጃዎች
- ሰውን የሚያስፈራራ፣ ዛቻን የሚፈጥር፣ የሚያዋርድ፣ ወይም ሁከትን የሚፈጥር ወይም በሌላ ሰው ወይም ቡድን ላይ ጥላቻን የሚፈጥር እና ከድስትሪክቱ ያለማዳላት ፖሊሲዎች ጋር የሚንጻረር
- ለግል ጥቅም፣ ገንዘብን ለማግኘት፣ ለማስታወቂያ፣ ለንግድ ወይም ለፖለቲካ ዓላማዎች
- ያለ ህጋዊ ፈቃድ የሌላን ሰው ሥራ እንደ የራስ አድርጎ መውሰድ/መጠቀም
- ሌሎችን ለማስቆጣት በትምህርት ቤት ውስጥ አግባብ የሌላቸውን ወይም መጥፎ ቃላትን መጠቀም
- ሆን ብሎ ውሸት መናገር ወይም የሌላን ሰው ስም ማጥፋት
- ከፌዴራል ወይም ከክፍለ ግዛት ሕግ ጋር የሚንጻረር፣ የቅጅ መብት ያላቸው ጽሁፎች እና በንግድ ምልክት የተጠበቁ ጽሁፎች

- ሌላ ሰው በመምሰል የሚደረግ የመረጃ ልውውጥ
- ከመረጃ ሥርዓት አስተዳዳሪ ፈቃድ ሳይገኝ የአገልግሎቶችን ክፊያ ማግኘት
- ከሚመለከተው ግለሰብ የጽሑፍ ፈቃድ ሳይገኝ የሌላ ሰው ኢንተርኔት ወይም የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎች አካውንት/ፋይል መጠቀም
- የተገናኙ መስመሮችን የሚያስስ፣ የተገናኙ መስመሮችን የሚቆጣጠር፣ ፓስዎርድን ጥሶ የሚያልፍ ፕሮግራም፣ ያልተፈቀዱ ፋይሎችን ለሌላ ሰው መስጠት። ኮምፒዩተር፣ የኮምፒዩተር ፋይሎችን፣ ወይም የኮምፒዩተር የተገናኙ መስመሮችን ሕገ-ወጥ በሆኑ መንገዶች ወይም ያለ ፈቃድ መጠቀም፤ ወይም ለማየት፣ መረጃን ለመለወጥ፣ ለመስረቅ፣ ለመጉዳት ወይም ያለ ፈቃድ የኮምፒዩተር መረጃን ለማጥፋት

**ደህንነት/ጥንቃቄ**

የድስትሪክት ኮምፒዩተር ሥርዓት ደህንነት ቀዳሚነት ያለው ተግባር ነው፡፡ ኢንተርኔትን ወይም የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎችን ሲጠቀሙ የደህንነት ጉድለት ያሳዩ ተማሪዎች ወዲያው ጉዳዩን ለኮምፒዩተር የመረጃ ሥርዓት አስተዳዳሪ ማሳወቅ አለባቸው። ተማሪዎች ችግሩን ለሌሎች ተጠቃሚዎች ማሳወቅ/ማሳየት የለባቸውም። እንደ የኮምፒዩተር የመረጃ ሥርዓት አስተዳዳሪ ሆኖ ኢንተርኔት ወይም የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎችን መጠቀም ክልክል ነው። ተማሪዎች፤

- የሌላ ሰውን ፓስዎርድ ወይም መለያ መጠቀም የለባቸውም
- ያልተፈቀዱ የድስትሪክት ኮምፒዩተሮችን ወይም የኮምፒዩተር የመረጃ ሥርዓቶችን ማግኘት ወይም ለማግኘት መሞከር የለባቸውም
- የሌሎች የመረጃ ሥርዓቶች ተጠቃሚዎችን የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎች መረጃን ማንበብ፣ መለወጥ፣ ማጥፋት ወይም መገልበጥ/መቅዳት ወይም እንደዚህ ያሉትን ድርጊቶች ለመፈጸም መሞከር የለባቸውም።

የደኅንነት/የጥንቃቄ ጉድለት የሚታይበት/የሚታይባት ተጠቃሚ፣ ወይም በሌሎች ኮምፒዩተሮች እና የመረጃ ሥርዓቶቹ እንደዚህ ዓይነቱ ችግር ታሪክ ያለባቸው ተጠቃሚዎች ኢንተርኔቱን ወይም የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎቹን እንዳይጠቀሙ ሊከለከሉ ይችላሉ።

**የግል ኮምፒዩተሮችን መጠቀም**

ለትምህርት ዓላማ ተማሪዎች የግል ኮምፒዩተሮቻቸውንና ወይም የኤሌክትሮኒክ ቁሳቁሶችን ከቼሪ ክሪክ ትምህርት ድስትሪክት የመረጃ ሥርዓት ጋር አግባብ ባለው መንገድ በማገናኘት ሊጠቀሙ ይችላሉ።

ተማሪዎች የግል ኮምፒዩተሮቻቸውን ከድስትሪክቱ በኤሌክትሮኒክስ የተገናኙ መስመሮች ጋር ካገናኙ በኃላ፣ የግል ምስጥር መጠበቅን ተስፋ ማድረግ የለባቸውም።

የተማሪ የግል ኮምፒዩተር ከድስትሪክቱ በኤሌክትሮኒክስ የተገናኙ መስመሮች ጋር ተገናኝቶ ሳለ፣ በግል ኮምፒዩተሩ ላይ ለሚፈጠረው ጥፋት ወይም ጉዳት፣ በሃርድዌር አለመስራት ምክንያት ለሚፈጠር ጉዳት፣ የመረጃ መጥፋት ወይም ለቫይረስ መጋለጥ/መዳረግ ችግሮች፣ የትምህርት ድስትሪክቱ ኃላፊነት አይወስድም።

**የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎችን ለሕዝብ ግንኙነት መጠቀም**

የድስትሪክት ኮምፒዩተሮች ጥቅም ለትምህርት እና ለትምህርት ቤት ሥራ ብቻ የሚውል ነው። ከትምህርት ቤት ወይም ከድስትሪክት የትምህርት ሥራዎች ወይም የትምህርት ፕሮግራሞች ጋር የማይገናኙ የግል ድረ-ገጾች፣ ዊኪዎች፣ ወይም ሌሎች የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎች ወይም በኮምፒዩተር የሚደረጉ ውይይቶች በድስትሪክት ኮምፒዩተሮች ወይም የድስትሪክቱ በኤሌክትሮኒክስ የተገናኙ የመረጃ መስመሮች መሆን የለበትም።

ድረ-ገጾች፣ ዊኪዎች፣ ቡሌቲን ቦርዶች፣ የመወያያ ድረ-ገጾች፣ ወይም ሌሎች ኢ-ሜሎች እና የመሳሰሉት ለድስትሪክት የትምህርት መርሃ ግብር/ፕሮግራም ለሕዝብ ግንኙነት የሚውሉ የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎች እና ማንኛውም ዓይነት በኮምፒዩተር የሚደረጉ ውይይቶች የመማሪያ ክፍል ወይም የትምህርት ፕሮግራም ማስፋፊያ መገልገያዎች ስለሆኑ የሚተገበሩት አግባብ ባላቸው የትምህርት ቦርድ ፖሊሲዎች እና መተዳደሪያ ደንቦች መሰረት ነው።

ተማሪዎች በድስትሪክቱ በኤሌክትሮኒክስ የተገናኙ የመረጃ ምንጮች አማካይነት የሚገኙትን እና ከትምህርት ወይም ከመማሪያ ክፍል ጋር የተገናኙ ድረ-ገጾች፣ ዊኪዎች፣ ወይም ሌሎች የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎች ወይም በኮምፒዩተር የሚደረጉ ትምህርታዊ ውይይቶች ላይ ለመሳተፍ እና ለመጠቀም በድስትሪክት የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎች እና የመረጃ ምንጮች ዓለም አቀፍ ድረ-ገጽ መጠቀም የሚችሉት ከወላጅ/ከአሳዳጊ የጽሁፍ ፈቃድ ካገኙ ብቻ ነው።

**ጥንቃቄ**
ኢንተርኔትን ወይም የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎችን ሲጠቀሙ፣ ተማሪዎች እንደ የቤት አድራሻ ወይም የስልክ ቁጥር ያሉትን የግል መረጃዎችን ማሳየት የለባቸውም። የሥራ ባልደረባ የሆነ የኃላፊን ፈቃድ ሳያገኙ፣ ተማሪዎች ሌሎች ሰዎች እንዲያገኟቸው የሚረዱ መረጃዎችን የሚሰጡ የአያት ስም ወይም ማንኛውንም ሌላ ዓይነት መረጃ መጠቀም የለባቸውም። ተማሪዎች በኢንቴርኔት ወይም በኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎች አማካይነት ካገኙት ሰው ጋር ፊት ለፊት ለመገናኘት መቀጣጠር የለባቸውም።

**እያወቁ ንብረትን ማውደም/ማበላሸት**

የድስትሪክቱን ኮምፒዩተር ወይም የኮምፒዩተር መረጃን ሆን ብሎ ማጥፋት፣ ማውደም፣ የግፍ ተግባር፣ ወይም በትምህርት ድስትሪክት ውስጥ ያሉትን የተገናኙ የመረጃ መስመሮች ወይም ማንኛቸውንም ከኢንቴርኔት ጋር የተገናኙትን መስመሮች ማበላሸት፣ ማንኛቸውንም የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎች፣ በማንኛቸውም የመገናኛ መስመሮች ላይ የሚገኙትን መረጃዎች ወይም የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎች፣ የሌላ ተጠቃሚን/ሰውን መረጃ፣ የሌላ ተጠቃሚን/ሰውን የመረጃ አጠቃቀም፣ ወይም የድስትሪክት ሶፍትዌር ወይም ሀርድዌር መረበሽ እና ማበላሸት የድስትሪክቱን የኮምፒዩተር መጠቀም ልዩ መብትን የማሰረዝ እና ማንኛውንም የትምህርት ቤት የቅጣት እርምጃ እና/ወይም ሕጋዊ እርምጃን ሊያስከትል ይችላል። ይህም የኮምፒዩተር ቫይረስን ኮምፒዩተር ላይ መጫን እና በኮምፒዩተር ውስጥ ያሉትን ጽሁፎች ወደ ኮድ/ልዩ ቋንቋ የሚለውጥ ሶፍትዌርን መጠቀም ያካትታል፣ በእነዚህ ብቻ ግን አይወሰንም።

**ያልተፈቀደ ሶፍትዌር**
ተማሪዎች ማንኛውንም የተቀዳ፣ አለበለዚያም የሌላን ሰው ሶፍትዌር ያለተገቢው ፈቃድ ወይም ለበለቤቱ ያለተገቢው ክፊያ ማንኛውንም ሶፍትዌር መጠቀም ወይም እንደ የግላቸው ማድረግ ክልክል ነው።

**ለተማሪዎች ፕሮጀክቶችን/የትምህርት ሥራዎችን መስጠት እና የተማሪዎችን አጠቃቀም መቆጣጠር**

ኢንተርኔት እና የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎች አግባብ ባለው እና ኃላፊነት በተሞላው መልኩ በተማሪዎች መጠቃማቸውን ለማረጋገጥ ድስትሪክቱ አስፈላጊውን እርምጃ ሁሉ ይወስዳል። አስተዳደሮች፣ አስተማሪዎች እና ሰራተኞች አብረው በመስራት እና የተማሪዎችን የኢንተርኔት እና የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎችን ለመቆጣጠር፣ ተማሪዎች ምሁራዊ በሆነ መንገድ የመረጃ ምንጮችን መለየት እንዲችሉ፣ ከዕድሜያቸው እና ከእድገታቸው መጠን ጋር የሚመጣጠኑትን መረጃዎች መለየት እንዲችሉ፣ እና የትምህርታቸው ግቦች ለማሳካት የሚረዱ መረጃዎች ለመጠቀም እንዲችሉ የመርዳት ሙያዊ ኃላፊነት አለባቸው። በኢንተርኔት እና በኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎች ጽሁፎችን እና መረጃዎችን ከማግኘታቸው በፊት፣ ተማሪዎች ግልጽ የሆኑ ዓላማዎች እና የመረጃ አሰሳ ስልቶች ሊኖራቸው ይገባል።

**የተማሪ ኮምፒዩተርን / የመረጃ ምንጭን የመጠቀም ልዩ መብት**

ኢንተርኔትን እና የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎችን መጠቀም የግል ኃላፊነትን እና ተቀባይነት ያላቸውን እና የሌላቸውን አጠቃቀሞች መረዳት ይፈለጋል። የተማሪዎች ኢንተርኔትን እና የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎችን መጠቀም መብት ሳይሆን ልዩ ዕድል ነው። በዚህ ፖሊሲ ውስጥ የተቀመጡትን የአጠቃቀም ሂደቶችን መጣስ ይህንን ልዩ ዕድል ያሳጣል፣ በተጨማሪም የትምህርት ቤት የቅጣት እርምጃ እና/ወይም ሕጋዊ ቅጣትንም ሊያስከትል ይችላል።

ኢንተርኔት እና የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎች አካውንቶች/ፋይሎች ለተማሪዎች ከመሰጠታቸው ወይም እንዲጠቀሙ ከመፈቀዱ በፊት፣ተማሪዎች እና ወላጆች/አሳዳጊዎች የድስትሪክቱን ኮምፒዩተር እና የመረጃ ሥርዓት የአጠቃቀም ስምምነት በየዓመቱ መፈረም አለባቸው።

**የትምህርት ቤት ድስትሪክት ዋስትና አይወስድም**

የድስትሪክት ኮምፒዩተሮች እና የኮምፒዩተር የመረጃ ሥርዓቶችን መጠቀምን በተመለከተ፣ ኢንቴርኔት እና የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎች አገልግሎቶችን ጨምሮ፣ የትምህርት ድስትሪክት ለማንኛውም ነገር፣ በግልጽም ሆነ በተዘዋዋሪ፣ ምንም ዓይነት ዋስትና አይወድስም። ድስትሪክቱ እነዚህን አገልግሎቶች ለተማሪዎች በማቅረቡ፣ የሚቀርቡትን የመረጃ ይዘቶች ይደግፋል ማለት አይደለም፣ እንደዚሁም ድስትሪክቱ ተማሪዎች ለሚያገኙትን መረጃዎች ትክክለኛነት እና ጥራት ዋስትና አይወስድም። ተማሪዎች ኢንቴርኔት እና የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎችን ሲጠቀሙ ለሚከሰቱ ማንኛቸውም ጉዳቶች፣ ጥፋቶች ወይም ወጪዎቹ የትምህርት ድስትሪክት ኃላፊነት አይወስድም። ይህ የመረጃዎች /የውሁቦችመጥፋት እና የአገልግሎቶች መስተጓጎልን ያካትታል። በኢንቴርኔት እና በኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎች የሚገኙ ማንኛቸውም መረጃዎች አጠቃቀም የተማሪው/ዋ ኃላፊነት ይሆናል።

የተሻሻለው፤ ዲሰምበር 12፣ 2012
ሥራ ላይ የዋለው፤ ጃንዋሪ 9 ፤ 2012

ሕጋዊ ዋቢዎች፤ 447 U.S.C. 254(h) (የ2000 ልጆችን ከኢንቴርኔት ጥበቃ አዋጅ)
47 C.F.R. Part 54, Subpart F (ለትምህርት ቤትና ለቤተ-መጽሀፍት የሚደረግ ሁሉ-አቀፍ ድጋፍ)
20 U.S.C. 6751 et seq. (የ2000 የቴክኖሎጂ/ሥነ-መላ አዋጅ በመጠቀም ትምህርትን ማሳደግ)
C.R.S. 22-87-101 et seq. (ልጆችን ከእንቴርነት የመጠበቅ አዋጅ)

ጥምር ዋቢዎች፤ AC፣ አለማዳላት/እኩል ዕድል
EGA፣ ኢ-ሜል
EGAD፣ መገልበጥ (መቅዳት)/ማሳተም
EHC፣ በተገናኙ መስመሮች የኤሌክትሮኒክስ የመረጃ ምንጮች
EHCA፣ የድረ-ገጽ እና የኢንቴርኔት ህትመት
JB፣ እኩል የትምህርት ዕድሎች
JICDA፣ የስነ-ምግባር እና የስነ-ሥርዓት ህግ

# የድስትርክት ተቋማት ጎብኚዎች
# (KI)

የትምህርት ቦርዱ ህብረተሰባችንን በት / ቤቶቻችን ውስጥ መሳተፍ አስፈላጊ መሆኑን እና የት / ቤት እና የማህበረሰብ ትብብር አስፈላጊነት ይገነዘባል እንዲሁም ስለተማሪዎች ጤና እና ደህንነት ስለምኖሩት ስጋቶችንም ይገነዘባል። ስለዚህ ዲስትሪክቱ በአጠቃላይ በዲስትሪክቱ ትምህርት ቤት ህንፃዎች ፣ ጎብኝዎችን ለሚከተለው ይገድባል-

1 የመደበኛ ተማሪዎች ወላጆች / አሳዳጊዎች
2በተማሪ ወላጅ / አሳዳጊ የፀደቁ የመደበኛ ተማሪዎች የቤተሰብ አባላት
3. የቦርድ አባላት; እና
4.በዲስትሪክቱ ወይም በት / ቤቱ አስተዳዳሪ ፣ በዋና ተቆጣጣሪው ወይም በእሱ / የእሱ ተወካይ ወይም ለትምህርት ወይም ለልዩ ስራዎች ዓላማዎች በቦርድ አባል የተጋበዙ ሌሎች ሰዎች

ሆን ብለው የከፋት ዓላማን ለመፈጸም ትምህርት ቤቶች ውስጥ መግባት የሚፈልጉ ሰዎችን ለመከልከል፣ ሁሉም የትምህርት ቤት ጎብኚዎች ትምህርት ቤት ሲመጡ ለትምህርት ቤቱ ቢሮ ራሳቸውን ማሳወቅ አለባቸው፣ ተገቢውን መታወቂያ ማሳየት አለባቸው፣ ሁሉም የተፈቀደላቸው ጎብኝዎች በቦርዱ ደንብ KI-R የተዘረዘሩትን የተወሰኑ መመሪያዎችን መከተል አለባቸው ።የተማሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች ወደ የመማሪያ ክፍል ወይም ለስብሰባ ሲጠሩ ወይንም ለአትሌትክስ ዉድድር፤ ባክቱ ስኩል ፤እና ብዙ ታዳሚዎች ወደሉበት ተጋብዘው ስመጡ እነዚህ ሂደቶች ተፈፃሚነት ላይኖራቸው ይችላል።

ጎብኝዎች ለአንዳንድ ወይም ለሁሉ ጉብኝት ከዲስትሪክቱ ሰራተኛ ጋር አብረው ሊሄዱ ይችላሉ ፣ እናም ጎብኝዎች ሁሉንም የተማሪዎችን የግለኝነት መብቶች ማክበር አለባቸው

ዲስትሪክቱ በት / ቤቶች ውስጥ የቤተሰብ እና እማህበረሰቡን ተሳትፎን የሚያደንቅ ቢሆንም ፣ የዲስትሪክቱ ትምህርት ቤት ህንፃዎችን ፣ እና መገልገያዎችን መጎብኘት ልዩ መብት ሳይሆን የድስትርክቱ በጎ ፍቃድ ነው ስለሆነም ከወረርሽኝ መከሰት ጋር የተዛመዱ፤ የተማሪ እና / ወይም የሰራተኞችን ደህንነት እና ጤናን ከግምት ውስጥ በማስገባት ፣ ተገቢ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የትምህርት አካባቢ ጥገና ፣ ወይም ይህን ፖሊሲ ማክበር አለመቻል ጨምሮ በዲስትሪክቱ ወይም በት / ቤቱ አስተዳዳሪ ወይም ተወካይ ሊከለከል ፣ ሊገደብ ወይም ሊሽረው የሚችል መብት ነው። ። ትክክለኛ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የትምህርት አከባቢን ለመጠበቅ የዲስትሪክቱ ትምህርት ቤቶች ህንፃዎች ፣ እና መገልገያዎች ጎብኝዎችን የሚመለከቱ ተጨማሪ አካሄዶችን ሊያፀድቁ ይችላሉ።

በቦርዱ ፖሊሲ JLCDB ከሚፈቀደው በስተቀር በድስትርክቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚገቡትን ሰዎች አጠቃላይ ጤንነት፣ ሰላም እና ደኅንነት ለመጠበቅ እና ለማሻሻል፣ እና በክፍለ ግዛት ሕግ መሰረት፣ በሁሉም በድስትርክቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ እና ንብረት አከባቢ ለሰራተኞች፣ ለተማሪዎች፣ ወይም ለጎብኚዎች ወይም ማንኛውም የትምባሆ ምርቶችን መጠቀም ክልክል ነው።

በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ፣ ተማሪዎችን በሚያጓጓዝ የትምህርት ቤት አውቶብሶች ውስጥ ወይም በ1000 ጫማ የትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ክልል ውስጥ ክልክል የሆኑትን እጾች በመጠቀም፣ በመሸጥ ወይም በማደል የወንጀል ህጉን የሚጥሱ ሰዎች በሁሉም የሕግ ቅጣት ይቀጣሉ።
በትምህርት ቤት አካባቢም መዉደልደል ፣ በ C.R.S በተገለጸው መሠረት § 18-9-112 ፣ እንዲሁም ክልክል ነው ፡፡
ሥራ ላይ የዋለው፤ አክቶበር 10፣ 2000
ለመጨረሻ ጊዜ የተሻሻለው-ሰፕተምቤር 11 ቀን 2000
ወቅታዊ ክለሳ-ጁላይ 20 ቀን 2020
ሕጋዊ ዋቢዎች፤

C.R.S. § 18-9-109 (በት / ቤት ሰራተኞች ወይም በተማሪዎች ላይ ጣልቃ መግባት)
C.R.S. § 18-9-117 (በትምህርት ቤት ንብረት ላይ ህገወጥ ተግባር)
C.R.S. § 18-9-112 (ማዉደልደል)
C.R.S. 18-9-112፣105.5 (በትምህርት ቤት ንብረቶች ላይ ህገ-ወጥ የጦር መሳሪያን ይዞ መገኘት)

C.R.S. § 18-18-407 (2) (በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ቁጥጥር የሚደረግበት ንጥረ ነገር መገኘት)

C.R.S. 22-32-109.1(7) (ግልጽ የሆነ የትምህርት ቤት ፖሊሲ አስፈላጊ የሆነ የትምህርት ቤት የደኅንነት እቅድ አካል ነው)

C.R.S. § 18-9-110 (መተላለፍ ፣ በሕዝባዊ ሕንፃዎች ውስጥ ወይም ጣልቃገብነት)

ጥምር ዋቢዎች፤
ADC፣ ከትምባሆ ነጻ የሆኑ ትምህርት ቤቶች
ECAጥበቃ/ትምህርት ቤቶች ውስጥ መግባት
KFA፣ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ እና በንብረቶቹ አከባቢ የሚፈለገው የሕዝብ ምግባር
JLCDB - በዲስትሪክቱ ንብረት ላይ ብቁ ለሆኑ ተማሪዎች የሕክምና ማሪዋናን መስጠት

## የድስትርክት ተቋማት ጎብኝዎች (KI-R)

የሁሉም ትምህርት ቤቶች ዋና ተግባር ምቹ የትምህርት ቦታን መፍጠር/ማቅረብ እና መጠበቅ ነው። ስለዚህም ሥርዓት ለማስያዝ፣ የተማሪዎችን ጤንነት፣ ሰላም እና ደኅንነት ለመጠበቅ፣ እና በትምህርት ሂደት እና በትምህርት ቤቶች ተግባር ውስጥ የሚከሰቱትን ረብሻዎች እንዲቀንሱ ለማረጋገጥ የተወሰኑ ገደቦች፣ እገዳዎች እና መመሪያዎች ተሰጥተዋል።

እነዚህ መተዳደሪያ ደንቦች መደበኛ ወይም በየጊዜው የሚደረጉ የወላጅ-መምህር ህብረት ስብሰባዎች ጊዜ፣ የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች መክፈቻዎች/ውይይቶች ጊዜ፣ ወይም ሌሎች ተመሳሳይ የወላጅ/የመምህር/የትምህርት ቤት ድርጊቶች/ተግባራት ጊዜ አይተገበሩም።
በትምህርት ሂደት ውስጥ የሚከሰቱትን ረብሻዎች ለመቀነስ እና ከፍተኛውን እና ምርጥ የሆነን የወላጅ-መምህር ግንኙነቶችን ለማረጋገጥ ማንኛዉም ጎብኚ የዲስትሪክቱ የትምህርት ቤት ህንፃዎች ፣ መገልገያዎች ፣ ወይም ቅጥር ግቢ ለመጎብኘት ሲመጡ የሚከተሉት ሂደቶች ይተገበራሉ፡

1. ጎብኚው/ዋ ግለሰብ ራሱ/ሷን ለቢሮ በመግለጽ በድስትርክቱ ትምህርት ቤት ህንፃ ፣ መገልገያ ወይም ግቢ የመጣበትን/የመጣችበትን ምክንያት ማሳወቅ አለበት/አለባት። የጎብኝዎች መግቢያ ምዝገባዎች በትምህርት ቤቱ ውስጥ ለአንድ ዓመት ያህል እንዲቆዩ ይደረጋል ተብሎ ይጠበቃል ፡፡

2. ጎብኝው በተገቢው መታወቂያ (የመንጃ ፈቃድ ፣ በስቴት የተሰጠው መታወቂያ ፣ ፓስፖርት ወይም ቆንስላ ካርድ) በዲስትሪክቱ የጎብኝ መለያ (ራፕቶር) በኩል ለመፈተሽ ያቀርባል ፡ጎብኝው ትክክለኛ መታወቂያ ከሌለው ፣ የዲስትሪክቱ ሰራተኞች የጎብኝዎችን የመጀመሪያ እና የመጨረሻ ስም እና የትውልድ ቀንን በስርዓት ውስጥ ያስገቡት

3. በዲስትሪክቱ ት / ቤቶች ህንፃዎች ፣ መገልገያዎች ፣ ወይም ግቢ ውስጥ በማንኛውም ጊዜ ጎብኝው በማንኛውም ጊዜ መልበስ ያለበት የጎብኝ ባጅ ይሰጠዋል

4. ከዲስትሪክቱ ት / ቤት ህንፃ ፣ መገልገያ ፣ ወይም ከህንፃው ከወጡ በኋላ ጎብኝው መለያውን (ባጅ) መመለስ አለበት እንደዝሁም ሳይን አዉት ማድረግ አለበት
5. ማንኛውም የት / ቤት ሰራተኛ አባል ያለ ጎብኝ ባጅ ያጋጠመውን ጎብኝውን ለምዝገባ ወደ ዋና ቢሮው ድረስ መምጣት አለበት ፡፡

6. አንድ የታወቀ ጎብኝ ቀደም ሲል የጎብኝዎችን የመለያ ስርዓት ለመቃኘት የራሱን ወይም የእሷን መታወቂያ ካቀረበ መታወቂያውን እንደገና እስካን ማድረግ አስፈላጊ ላይሆን ይችላል ፡፡እንደዚህ ባሉ ሁኔታዎች ውስጥ ቀለል በላ ሁኔታ የአባቱን ስም በመናገር ፣ ጎብኝው ባጅ ይሰጠዋል ፡፡

ጉብኝቱን ለማሳካት አስፈላጊው ጥረት ሁሉ ይደረጋል።ነገር ግን፣ የጉብኝቱ ሰዓት እና ቀን ከፈተናዎች፣ ከመስክ ጉብኝቶች፣ ከልዩ ፕሮጀክቶች ወይም ከሌሎች የትምህርት ቤት ተግባራት ጋር የሚጋጭ ከሆነ፣ ለጊዜው ጉብኝቱን በመከልከል ሌላ ቀጠሮ ሊሰጥ ይችላል።

በዲስትሪክቱ እና በት / ቤት አስተዳዳሪዎች ዉሳኔ መሰረት በልዩ ሁኔታ፣ ባልተለመደ ወይም በድንገተኛ ሁኔታዎች ምክንያት ካልተራዘመ በስተቀር፣ ለመማሪያ ክፍል የሚደረገው ጉብኝት በተለምዶ ከአራት ሰዓት በላይ መሆን የለበትም።በተጨማሪም፣ በልዩ ሁኔታ፣በዲስትሪክቱ እና በት / ቤት አስተዳዳሪዎች ዉሳኔ መሰረት። ባልተለመደ ወይም በድንገተኛ አስገዳጅ ሁኔታዎች ምክንያት ካልተፈቀደ በስተቀር፣ የተከታታይ ቀናት የመማሪያ ክፍል ጉብኝት ሊከለከል ይችላል።

ከባለፈው የጉብኝት ልምድ የተነሳ የወደፊት ጉብኝት ረብሻን የሚፈጥር፣ ተቃውሞን ወይም ዘግይታን የሚያስከትል ከሆነ፣ አለበለዚያም የትምህርት ሂደት ላይ አሉታዊ ተጸዕኖን የሚያመጣ ከሆነ ለጉብኝት የሚቀርብ ጥያቄ ውድቅ ሊደረግ ይችላል።

በትምህርት ቤት ወይም በመማሪያ ክፍል የሚደረግ ጉብኝት በማንኛውም ጊዜ ረብሻን የሚፈጥር፣ የትምህርት ሂደትን የሚያስተጓጎል፣ በተማሪዎች ወይም በሰራተኞች ጤና ፣ እና ደህንነት ላይ ዛቻን ወይም አደጋን የሚፈጥር ከሆነ፣ አለበለዚያም የተማሪዎች ወይም የአስተማሪዎች በሙሉ ትኩረት በትምህርት ሂደት መሳተፍን የሚያደናቅፍ መሆኑ በዲስትሪክቱ ወይም በትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪ ወይም የእነሱ ተወካይ ኃላፊው/ዋ ጉብኚቱ እንዲያበቃ እና ጎብኚው/ዋ ግለሰብ የትምህርት ቤት ቅጥር ግቢውን እንዲለቅ/እንዲትለቅ ሊጠየቅ/ሊትጠይቅ ይችላል/ትችላለች።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ጎብኚው/ዋ ግለሰብ የትምህርት ቤቱን ቅጥር ግቢ በተጠየቀው መሰረት ለቆ/ቃ የማይሄድ/የማትሄድ ከሆነ/ች፣ዲስትሪክት ወይም የትምህርት ቤት አስተዳዳሪ ወይም ተወካይ ከማዕከላዊ የአስተዳደር ብሮ ፣ከድስትርክቱ ሴኩሪቲ ፣ እና / ወይም ከአካባቢው ህግ አስካባሪዎች እርዳታን የመጠየቅ መብት አለው/አላት።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ በዲስትሪክት ወይም የትምህርት ቤት አስተዳዳሪ ውሳኔ መሰረት አግባብ ባለው መንገድ በዲስትሪክት ወይም የትምህርት ቤት አስተዳዳሪ ወይም በተወካይ፣ አስተማሪ፣ ወላጅ ወይም ከማዕከላዊ የአስተዳደር ቢሮ ሊሆን ይችላል፣ አማካይነት የማንኛውንም ግለሰብ የትምህርት ቤት ወይም የመማሪያ ክፍል ጉብኝት ሊቆጣጠሩ ይችላሉ።

መጀመሪያ የፀደቀው ጁላይ 1987
ወቅታዊ ክለሳ-ጁላይ 20 ቀን 2020

## I. ለተማሪ የትምህርት ክንውን የሚደረግ የማስተማሪያ ፕሮግራሞች ግምገማ

ለተማሪ የትምህርት ክንውን መሻሻል እና የድስትሪክቱ ተልዕኮ ለሆኑት፡ ሁሉንም ተማሪዎች እንዲያስቡ፣ እንዲማሩ፣ እንዲከናወንላቸው እና ለሌሎች እንዲያስቡ ለመቀስቀስ/ለማነሳሳት የሚሉትን ተልዕኮዎች ለማሳካት ተከታታይ የማስተማሪያ ፕሮግራሞች ግምገማ አስፈላጊ ነው።

### ሀ. የድስትሪክት ፕሮግራሞች

የድስትሪክት የትምህርት ፕሮግራሞች ግምገማዎችን ለማካሄድ፣ የትምህርት ቤቶች ተባባሪ የትምህርት ጥራት መሻሻል አለቃ ለድስትሪክት ትምህርት ቤቶች ፕሮግራሞች ግምገማ ኃላፊነት የሚወስዱትን የአስተዳደር ሰራተኞች ይሰይማል/ትሰይማለች። አስተዳደሩም:

1. የድስትሪክቱን የቡድን ሚዘና እና የቴስቶች ፕሮግራሞችን ይጀምራል፣ ያደራጃል/ያስፋፋል፣ ይጠብቃልም።
2. በአከባቢው፣ በክፍለ ግዛት፣ ወይም በሀገር አቀፍ የዜጎች ወይም ሙያዊ ተቋማት፣ ወይም እውቅና ሰጪ ማህበራት በሚካሄዱት ወይም በሚደገፉት ጥናቶች ውስጥ መተባበር እና ጥናቶቹን መደገፍ/መርዳት።
3. ከትምህርት ቤቶች ኃላፊዎች፣ አስተማሪዎች፣ የመማር ማስተማር ኃላፊዎች፣ እና ከሥርዓተ-ትምህርት ኮሚቴዎች ጋር በመተባበር የድስትሪክት የትምህርት ፕሮግራሞችን መገምገም።

የትምህርት ቤቶች የትምህርት ጥራት መሻሻል ተባባሪ የበላይ አለቃው/ዋ፣ በሚዘና እና በግምገማ ቢሮ በኩል፣ የተማሪ የትምህርት ክንውንን በተመለከተ የትምህርት ጥራት እና መሻሻል መረጃን የማግኘት ኃላፊነት አለበት/አለባት። እንደዚህ ዓይነቱ መረጃ አጠቃላይ የትምህርት ፕሮግራም ውጤታማነትን ለመገምገም መረጃን ይሰጣል።

ከድስትሪክቱ ሚዘናዎች የሚገኙ መረጃዎች በትምህርት ቤቶች ኃላፊዎች፣ በአስተማሪዎች፣ በአማካሪዎች፣ በሥርዓተ-ትምህርት ኮሚቴዎች፣ እና ከተማሪዎች ፍላጎት እና የተማሪን የትምህርት ክንውን ከማሻሻል አንጻር ሥርዓተ-ትምህርት እና የትምህርት ፕሮግራሞችን በሚያዘጋጁ ባለሙያዎች መጠቀም አለባቸው። በተጨማሪም፣ ወላጆችን ስለልጆቻቸው የትምህርት መሻሻል ለመምከር መሰረት መሆን አለበት። የድስትሪክት የሚዘና ሂደቶች የተለያየ እና በትምህርት ቤቱ የተዘጋጁ ቴስቶችን፣ የዳሰሳ ጥናቶችን፣ ቃለ-መጠይቆችን፣ ሀገር አቀፍ መደበኛ ቴስቶች፣ ምልከታዎች/አስተውሎቶች፣ እና ክንዋኔ ላይ የተመሰረቱ ሚዘናዎችን ማካተት አለበት፣ በእነዚህ ብቻ ግን አይወሰንም።

ከድስትሪክት የሚገኙ መረጃዎች (ለምሳሌ፣ የተማሪ የትምህርት ክትትል፣ ነጥቦች/ማርኮች፣ የትምህርት ዓይነቶች፣ የመሳሰሉት) ከሚዘና መረጃ ጋር መያያዝ አለባቸው፤ ይህም የተማሪን የሚዘና እና የግምገማ ውጤቶችን ለመተንተን እና የወደፊት የትምህርት፣ የበጀት፣ ወይም የተማሪ ክንዋኔን ለማሻሻል የተደረጉ የፕሮግራም ለውጦችን ለማቀድ ይረዳል።

የድስትሪክት የሚዘና እና የግምገማ ፕሮግራም በአስተዳደሩ፣ በሚዘና እና ግምገማ ቢሮ፣ እና በአስተማሪዎች በየጊዜው መከለስ አለበት። የሚዘና እና የግምገማ እቅድ ለሦስት እስከ አምስት ዓመት መውጣት አለበት፤ እንደዚሁም በቀጣይ የትምህርት ዘመናት አግባብ ያለው የሚዘና ፕሮግራም በየዓመቱ በቦርዱ እየተከለሰ መዘጋጀት አለበት።

በየዓመቱ ጽኑ የሆነን መረጃ በትምህርት ድስትሪክት ውስጥ ለማወዳደር ዓላማዎች እና የክፍለ ግዛት ቦርድ ህግ በሚያዘው መሰረት መረጃውን ከሌሎች የትምህርት ድስትሪክቶች ጋር ለማወዳደር እንዲቻል የድስትሪክት የትምህርት ጥራት እና የተማሪ የትምህርት ክንውን ጠቋሚዎች መዘጋጀት አለባቸው። የድስትሪክት የሚዘና እና የግምገማ ፕሮግራም ውጤቶች በየዓመቱ ታትሞ በቦርዱ መከለስ አለበት።

### ለ. የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች

የትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪዎች እና ሰራተኞች ለትምህርት ቤት መሻሻል ፕሮግራሞች ግምገማ እና ለማሻሻል ተጠያቂነትን የመውሰድ ኃላፊነት አለባቸው። እያንዳንዱ የትምህርት ቤት አስተዳደር ከትምህርት ቤት ተጠያቂነት እና የማሻሻል ግቦች ጋር የሚሄድ እና ፕሮግራሞቹ በሥር ዓቱ መገምገሙን ለማረጋገጥ የግምገማ እቅድ ማዘጋጀት አለባቸው። የፕሮግራሙን ውጤታማነት ለማስተዋል አዲስ ፕሮግራም በጊዜ መገምገም አለበት።

የትምህርት ቤቶች የበላይ አለቃው/ዋ ለድስትሪክት ምክር እና እንደ አስፈላጊነቱ ለፕሮግራም ግምገማው ውጤታማ ሥራን ለማከናወን የሚረዳ ለትምህርት ቤት አስተዳደሮች የተለያዩ አገልግሎቶችን ይሰጣል/ትሰጣለች።

### ሐ. የማስተማሪያ ፕሮግራሞች መገምገሚያ መመሪያ ወነች

ሁሉም የፕሮግራም ግምገማ ተግባራት የተማሪን የትምህርት ሥራ እና ተለውጦ/ግስጋሴ ማሻሻልን ማተኮር አለባቸው። የተማሪን የትምህርት ክንውን ለማሻሻል፣ ግለሰቦች ውሳኔን ለመስጠት መረጃን በማስተዋል መጠቀም አለባቸው። የሚከተሉት ወነች የማስተማሪያ ፕሮግራሞች ግምገማን እና ውጤቶቹን የመጠቀም አካሄድ መምራት አለባቸው:

1. የትምህርት ጥራትን ሙሉ በሙሉ ለመረዳት ብዙ ዓይነት ጠቋሚዎች ያስፈልጋሉ።
2. ውጤታማ የሆነ ሥርዓተ-ትምህርት እና ማስተማር ተከታታይ ግምገማን/ሚዘናን ይፈልጋል።
3. የትምህርት ጥራት ጠቋሚዎች ግልጽ/የሚስተዋሉ እና ሥራ ላይ የሚውሉ መሆን አለባቸው።
4. ሚዘና እና ግምገማ ከማስተማር ጋር የተዋሃዱ ናቸው።
5. በየደረጃዎቹ (በድስትሪክት፣ በትምህርት ቤት፣ በመማሪያ ክፍል) የሚሰበሰቡ የመማር-ማስተማር መረጃዎች የትምህርት ጥራትን ሙሉ በሙሉ ለመረዳት ያስፈልጋሉ።

## የትምህርት ሥራ ክንዋኔን ለማሻሻል የሚደረግ የተማሪ ሚዘና እና ግምገማ

ቦርዱ፣ የትምህርት ቤቶች የበላይ አለቃ፣ የመማር-ማስተማር ኃላፊዎች፣ የትምህርት ቤት ኃላፊዎች፣ እና አስተማሪዎች ለድስትሪክቱ ተልዕኮ አስፈላጊ የሆኑትን እያንዳንዱ ተማሪ እንዲያስብ፣ እንዲማር፣ እንዲከናወንለት፣ ለሌላው እንዲያስብ የሚሉትን መሪህ ሃሳቦችን ለማሳካት የተማሪ የትምህርት ክንዋኔ ሚዘና እና ግምገማን በተመለከተ ተግተው ይሰራሉ። የሚዘና እና የግምገማ ዋና ዓላማ በቦርድ በተሰጡ የብቃት ደረጃዎች እና በትምህርት ሥራ የክንዋኔ መመዘናዎች፣ እና በሥርዓተ-ትምህርት ግቦች መሰረት ቀጣዩን ከፍተኛ የትምህርት ክንዋኔ ደረጃ ለመድረስ የሚረዱ የተከታታይ ተለውጦ/ግስጋሴ መረጃዎችን ለተማሪዎች እና ለወላጆቻቸው ለመስጠት ነው። በተጨማሪም፣ ከሚዘና/ከግምገማ የሚገኙ መረጃዎች አስተማሪዎች፣ የመማር-ማስተማር ኃላፊዎች፣ የትምህርት ቦርድ፣ እና ማኅበረሰቡ ከተማሪ የትምህርት ዕድገት እና ክንዋኔ አንጻር የቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ጥራትን እንዲረዱ ያግዛሉ።

### ሀ. የክፈለግዛቱ የምዘና /ግምገማ ሥርዓት

የቼር ክሪክ ትምህርት ቤቶች በፌዴራልና በክፍለግዛቱ ህግ መሰረት ተማርዎች በተለያየ የትምህርት አይነቶች መቀበል የምገባቸዉን ምዘናዎች ይሰጣል።

**1..በወረቀትና እርሳስ ዘዴ የፈተና አሰጣጥ አማራጭ**

በክፍለግዛቱ ደረጃ የምሰጡትን ምዘናዎች በኮምፕዩተር ላይ እንደሰጡ የድስትርክቱ አለማ ብሆንም እንኳን አንዳንድ ሁኔታዎች ግን በኮምፕዩተር ከምሰጡት ምዘናዎች ገምሶቹ በወረቀትና በእርሳስ ዘዴ ብሰጡ አስፈላጊ / መሆኑን ድስትርክቱ ያስባል። አከለጉደተኛ ለሆኑ ተማርዎች ምዘናዉን በኮምፕዩተር ላይ ከመዉሰድ በወረቀትና እርሳስ ዘዴ ለመወሰን የተማርዉ የግል የትምህርት ዕቅድ ቡድን በክፈለግዛቱ ህግ መሰረት መወሰን አለባቸው፡፤

ምዘናዉን ከኮምፕዩተር ወደ ወረቀትና እርሳስ ዘዴ ለመቀየር እንዝህ ሁኔታዎች ብቁ ልያደርጉ ይችላሉ

- የያንዳንዱ ትምህርት ቤቶች የተክኖሎጅያዊ ይዘትና መጠን/ብዛት
- የተማርዎች በኮምፕዩተርና በጽሁፍ ምዘናዎች ላይ የነበረው የቀድሞ ተሞክሮ
- የያንዳንዱ ትምህርት ቤቶች የትምህርት አሰጣጡ ከኮምፕዩተርና ወይንም ከጽሁፍ ምዘናዎች ጋር የምጣጣም መሆን /አለመሆኑ
- በዝያ ትምህርት ቤት ምዘናዎችን በተለየ ዘዴ መስጠት ያለዉን ተግባራት

ይህንን ዉሳኔ ይህም የወረቀትና የእርሳስ ዘዴ አማራጭ ከመዉሰድ በፍት የትምህርት ቤቶች የበላይ አለቃ ወይንም ተወካዩ ጉዳዩ ከምመለከተው ትምህርት ቤቶች ደይረክቶሮች፤ እንድሁም ልጆቻቸው በድስትርክታችን ዉስጥ ከተመዘገቡት ወላጆች ጋር መወያየት መመካካር ያስፈልጋቸዋል።

**2. ወላጆች/አሰዳጊዎች ልጆቻቸዉን ከምዘና ማገድ**

ልጆቻቸዉ ማንኛዉንም በክፈለግዝቱ ደረጃ የምሰጠዉን መመዘኛ እንደይቀበሉ የምፈልጉ ወላጆች /አሳዳጊዎች ይህንን ማመልከቻቸዉን በክፍለግዛቱ ህግ መሰረት ህጋዊ በሆነ መልኩ መቅረብ ይችላሉ።

ወላጆች ልጆቻቸዉን ከምዘናው ከማገደቸው የተነሳ ድስትርክታችን በወላጆችም ሆነ በልጆች ላይ ምንም አይነት አሉታዊ ተጽህኖ አያደርግም ወይንም ምንም ቅጣት የለም፡

ይህ ተማርዎችን ከምዘና የማገድ ፖሊስ የምሰረው በክፈለ ግዛቱ ደረጃ የምሰጡትን ምዘናዎችን ብቻ እንጅ በክፍል ዉስጥና በድስትርክቱ የምሰጡትን አያጠቃልልም።

**3. የተማርዎችን የክፈለግዛቱን ምዘናዎች ዉጤት ለወላጆች ማሳወቅ**

የኮላራዶ የትምህርት ቢሮ የተማሪዎችን የትምህርት ዕድገት መረጃና የበለፈዉን አመት የምዘና ዉጤቶችን በድስትርክቱ ዉስጥ ለተመዘገቡት ለያንዳንዱ ተማርዎችና ለያንዳንዱ በድስትርክቱ ዉስጥ ላሉት ትምህርት ቤቶች ማሳወቅ ይጠብቅበታል።ይህ መረጃ መመስረት ያለበት በበለፈው ትምህርት ዘመን የምዘና ዉጤት ላይ መሆን አለበት።እነዝህ መረጃዎችም በያንዳንዱ ተማሪዎች ፍይል ዉስጥ ተቀማጭ ይሆናል።ጉዳዩ የምመለከተቸው የተማሪን ፈይል መመልከት የምችሉ የትምህርት ቤቶች በልደረቦች የምዘነዉን ዉጤት መመልከት ይችላሉ እንደዝሁም ለወላጆች/ለአሰዳጊዎች ያሰዉቃሉ/ያስረዳሉ።

በዝህ ፖሊሲ በክፈለግዛቱ ህግ መሰረት ድስትርክታችን የምዘናዎችን ሰሌዳና ተዘማጅ መረጃዎችን ይህም ምዘናዎች የምሰጡበትን ቀናቶች የምገልጽ ዕቅዶቹን ለወላጆች/ለአሳዳጊዎች በየአመቱ ያሰረጫል።

**ለ.የድስትሪክት በሞላ የሚዘና/የግምገማ ሥርዓት**

የድስትሪክት በሞላ የሚዘና/የግምገማ ሥርዓት የድስትሪክቱ ተልዕኮ ምን ያህል እየተሳካ እንደሆነ ለመቆጣጠር የሚረዳ መረጃን መስጠት አለበት። ከድስትሪክት ሚዘና/ግምገማ የሚገኝ መረጃ የተማሪን የትምህርት ተለውጥ/ግስጋሴ ግምገማ እና ቁጥጥር በተመለከተ የአስተማሪ ዳኝነትን የሚተካ ሳይሆን የሚረዳ እና የሚደግፍ መሆን አለበት። የአስተማሪ ዳኝነት ትክክለኛነት በትምህርት ቤት እና በድስትሪክት ሚዘናዎች/ግምገማዎች፣ እንደዚሁም በክፍለ ግዛት እና በሀገር አቀፍ በተዘጋጁ ቴስቶች አማካይነት መጎልበት/መጠንከር እና መረጋገጥ አለበት። የድስትሪክት በሞላ የሚዘና/የግምገማ ሥርዓት የድስትሪክት ኃላፊዎች በትምህርት ቤቶች ውስጥ እና በትምህርት ቤቶች መሃል የሚደረጉትን የአስተማሪ ዳኝነት ጽኑነት እና ትክክለኛነትን ለመመርመር ያስችላቸዋል።

የድስትሪክት በሞላ የሚዘና/የግምገማ ሥርዓት ሰፊ የሆነ የጋራ የተጠያቂነት ሥርዓት ሆኖ፣ ለተማሪ የትምህርት ዕድገት እና ክንዋኔ ኃላፊነት እና ተጠያቂነት ያለባቸውን ተማሪዎችን፣ አስተማሪዎችን፣ ወላጆችን፣ የትምህርት ቤት አስተዳደሮችን፣ እና ቦርዱን ያካትታል።

በዝህ ፖሊሲ በክፈለግዛቱ ህግ መሰረት ድስትርክታችን የምዘናዎችን ሰሌዳና ተዘማጅ መረጃዎችንይህም ምዘናዎች የምሰጡበትን ቀናቶች የምገልጽ ዕቅዶቹን ለወላጆች/ለአሳዳጊዎች በየአመቱ ያሰረጫል።

**1.በመማሪያ ክፍል እና በትምህርት ቤት ደረጃ የሚሰጡ ማርኮች/ነጥቦች እና የሚደረጉ የሚዘና/የግምገማ ሥርዓቶች**

የትምህርት ክንዋኔ ዓላማውን/ግቡን ግልጽ፣ የሚታወስ፣ እና ለተማሪዎች የሚቻል ለማድረግ፣ ድስትሪክቱ የማስተማር ፕሮግራሙን በተመለከተ በትጋት ይሰራል። ድስትሪክቱ፣ በተማሪ የሥራ ክንዋኔ ግምገማ ሂደቱ ውስጥ፣ ምሁራዊ ክንዋኔን ማተኮር አለበት።

አስተዳደሩ እና ባለሙያ ሰራተኞቹ፣ የተማሪ የትምህርት ግቦች እና የድስትሪክት የብቃት መመዘኛዎችን በተመለከተ፣ ለተማሪ የትምህርት ተለውጥ/ግስጋሴ የሚረዱ የማርክ/የነጥብ አሰጣጥ እና የሚዘና/የግምገማ ሥርዓቶችን ማውጣት አለባቸው። የእያንዳንዱ/ዷ ተማሪ መዝገቦች እና ነጥቦች በሥርዓቱ ተይዞ፣ እንደአስፈላጊነቱ ለወላጆች እና ለተማሪዎች ለሥራ ክንዋኔ ማሻሻል ግምገማ፣ እንደዚሁም ለአስተማሪዎች ይገለጻል።

የመማሪያ ክፍል እና የትምህርት ቤት የግምገማ ሥርዓቶች የተለያዩ የሚዘና/የግምገማ ስልቶችን በመጠቀም ተማሪዎች እውቀታቸውን እና ችሎታቸውን የሚያሳዩበት ብዙ ዓይነት ዕድሎችን መስጠት አለባቸው።

ማንኛውም የማርክ/የነጥብ አሰጣጥ እና/ወይም የሚዘና/የግምገማ ሥርዓት በተለምዶ በዳኝነት ላይ እንደሚመሰረት ቦርዱ ቢያውቅም እንኳን፣ የሰውን ስህተት ወይም የተማሪ የሥራ ክንዋኔ ግምገማ ውስጥ የሚፈጠሩትን አለመግባባቶችን ለመቀነስ፣ ፖሊሲ እና ውስን የሆኑ ዘዴዎችን/ስልቶችን የሚጠቀም የጥራት ጥበቃ ሥርዓት መኖር አለበት።

**2. ለተማሪ ሚዘና/ግምገማ እና የትምህርት ሥራ ማሻሻል መረጃ መለዋወጥ የሚረዱ የመመሪያ ወጎች**

ሁሉም የተማሪ ሚዘና/ግምገማ ተግባራት የተማሪ የትምህርት ዕድገት እና ክንዋኔን ማሻሻል ላይ ማተኮር አለባቸው። የሚከተሉት ወጎች የተማሪ የሚዘና ፈተናዎችን ማዘጋጀት እና መስጠት፣ እና ውጤቶቹን መጠቀም መምራት አለባቸው፡

ሀ. የተማሪ የሥራ ክንዋኔ እና የትምህርት ተለውጥ/ግስጋሴ ሚዘና/ግምገማ በተመለከተ አስተማሪዎች ዋናውን ድርሻ ሊኖራቸው ይገባል። የተማሪ ሥራ ክንዋኔ እና የትምህርት ተለውጥ/ግስጋሴ በተመለከተ አስተማሪ የሚሰጠው ዳኝነት ትክክል እና ጽኑ የሚሆነው፣ ዳኝነቱ ተማሪ በመማሪያ ክፍል ውስጥ በሚያደርገው የሥራ ክንዋኔ፣ ነጥቦች/ማርኮች፣ የቤት ሥራ፣ ሚዘናዎች/ግምገማዎች፣ የመሳሰሉት ላይ ሲመሰረት ነው።

ለ. ውጤታማ የሆነ የመማር-ማስተማር ለውጥ ለማምጣት እና የተማሪ የሥራ ክንዋኔን ለማሻሻል፣ ሚዘና/ግምገማ የተዋሃደ ሥርዓት መሆን አለበት (ሥርዓተ-ትምህርት፣ ማስተማር፣ ሚዘና/ግምገማ፣ የሠራተኞች ዕድገት/መሻሻል)።

ሐ. በሁሉም ደረጃዎች የሚደረጉ ሚዘናዎች/ግምገማዎች (በመማሪያ ክፍል፣ በትምህርት ቤት፣ በድስትሪክት) ተገቢውን የጽኑነት እና የትክክለኛነት፣ እና በአጠቃላይ ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ስልታዊ መመዘኛዎች ማሟላት አለባቸው፤ እንደዚሁም ለትምህርት ዕድገት አግባብ ያለው እና ለሁሉም ተማሪዎች፣ መመዘኛው ሳይቀነስ፣ እኩል መሆን/ፍትሃዊ መሆን አለበት።

መ. በድስትሪክት እና በትምህርት ቤት ደረጃዎች የሚደረጉ ሚዘናዎች/ግምገማዎች የአስተማሪዎችን ተከታታይ የሚዘናዎች እና የግምገማዎች ተግባራትን መደገፍ አለበት።

ሠ. ሚዘናዎች ፣ ዋና ክፍሎቹ ላይ በማተኮር፣ ምርጥ የሆኑ የማስተማር ሥራዎችን እና ሥርዓተ-ትምህርት ማሳየት አለባቸው።

ረ. ተማሪዎች የሥራ ክንዋኔያቸውን በተለያዩ የሚዘና/የግምገማ መልኮች ለማሳየት የተለያዩ ዕድሎች ሊሰጣቸው ይገባል። የብቃት የክንዋኔ ደረጃን ወይም የሥርዓተ-ትምህርት ግቦችን በተመለከተ አስፈላጊውን መረጃ ለማግኘት ነጠላ የሆነ ሚዘና በቂ አይደለም።

ሰ. የሚዘና ሥርዓቱ የተማሪን የትምህርት ክንዋኔን ፍትሃዊ በሆነ እና ማወዳደር በሚቻል መንገድ በመደገፍ ረገድ የትምህርት ቤትን እና የአስተማሪ ጽኑነትን ማሻሻል አለበት።

III. **ትርጉሞች**

ሚዘና/ግምገማ

ስለ ተማሪዎች ወይም ስለ ፕሮግራሞች መረጃን መሰብሰብ፤ የተለያዩ ሚዘናዎች ውጤቶች በግምገማ ውስጥ ሊጣመሩ/ሊቀናበሩ ይችላሉ።

ግምገማ

ከሚዘና መረጃ የተገኘውን ዳኝነትን ሥራ ላይ ማዋል፣ የትምህርት ክንዋኔን ከታሰቡ/ከታቀዱ ውጤቶች ጋር ማወዳደር።

ሥራ ላይ የዋለው፤ ዴሰምበር 12፣ 2011

**ጥምር ዋቢዎች፤** JLDAC፣ ማጣሪያዎች/የተማሪዎች ቴስቶች

LC፣ ከትምህርት ጥናት እና ምርምር ድርጅቶች/ተቋማት ጋር ያሉ ግንኙነቶች

በመጀመርያ የተሻሻለው ጃንዋሪ 9፤2012 ጸደቀ
ፌብሩራሪ 8፤2016 ተሻሻለ

ጥምር ወቢዎች C.R.S. § 22-7-1006.3(1) (የክፈለግዛት ምዘናዎች ስራ ላይ መወያ ሰሌዳ)

C.R.S. § 22-7-1006.3(1)(መ) (ድስትርክቱ ምዘነዉን በወረቀትና በእርሳስ ዘዴ የተሰጣቸዉን ተማሪዎች ቁጥር ለኮላራዶ የትምህርት ቢሮ ርፖርት መቅረብ አለበት)

C.R.S. § 22-7-1006.3(7)(መ) ( በተቻለ መጠን የተማሪዎች የክፈለግዛቱ ምዘና ዉጤት በተማሪዎቹ መደበኛ የዉጤት መግለጫ ካርድ ላይ መካተት አለበት)

C.R.S. § 22-7-1006.3(8)(ሀ) (የተማሪዎችን የክፈለግዛቱን ዉጤት ገለጻ የምፈልግ ፖሊሲ)

C.R.S. § 22-7-1013(1) (የድስትርክት የትምህርት መመዘኛ ደረጃ)

C.R.S. § 22-7-1013(6) በ(በክፈለግዛቱ መመዘኛ ላይ የወረቀትና የእርሳስ ዘዴ መጠቀም የምገልጽ ፖሊሲ )

C.R.S. § 22-7-1013(7) (የምዘና የጊዜ ሰሌዳን ለወላጆች ማሰረጨት አስመልክቶ የምያስፈልጉ ህደቶች)

C.R.S. § 22-7-1013(8)( ወላጆች ልጆቻቸዉን ከምዘና ለማገድ የምያስፈልጉ ፖሊሲዎችና ህደቶች)

C.R.S. § 22-11-101 (.የ2009 የትምህርት ተጠያቅነት ህግ)

C.R.S. § 22-11-203(2)(ሀ) (የትምህርት ቤቶች ረዕሰ መምህራን የተማርዎችን ዉጤት እንደደረሰቸው መምህራኖች እንድመለከቱ ፍቃድ መስጠት)

C.R.S. § 22-22-504(3) የተማርዎችን የክፈለግዛቱን የምዘና ዉጤቶችን ገለጻ ለማረገገጥ የምያስፍልግ ፖሊሲ )

ጥምር ወቢዎች .: JLDAC፤ምዘናዎችን ለተማሪዎች መስጠት

LC, ጥምረት ከትምህርት ምርምር ድርጅቶች ጋር

JRC፤የተማሪ መረጃን መልቀቅ

ብዙ ተማሪዎች ለህይወት አስጊ የሆኑ እንደ የምግብ አለርጅ (አለመስማማት)፤የንብ/በራሪ ነፍሳት ንክሻ፤ ወይንም አንዳንድ አካባቢያዊ ቁሳዊ አካል ሁኔታዎች እነዝህን አለርጅዎች ልቀሰቅሱ እንደምችሉ ቦርዱ ያዉቃል። የተማሪዎችን የምግብ አለርጅና መቆጣጣርን በተመለከተ ፤ለጉዳዩ ትኩረት ለመስጠትና የክፍለግዛት ህግ መስፈርቶችን ለማሟላት ቦርዱ የምከተሉትን መስፈርቶችን ሰጥቷል።

**የጤና እንክብካቤ እቅድ**(IHP)

የትምህርት ቤት ነርስ ፤ወይንም የትምህርት ቤት አስተዳዳር ከትምህርት ቤት ነርስ ጋር በመመካካር ፤ከፍተኛ ለህይወት አስጊ የሆነ አሌርጅ ላላባቸው ተማሪዎች የጤና እንክብካቤ እቅድ በማዘጋጀት ይተግብራሉ።እቅዱ የድንገተኛ ጊዜ ህክምናን ጨምሮ ፤የትምህርት ቤትና የድንገተኛ ጊዜ የህክምና አገልግሎቶችን ግኑኝነትና የመረጃ

ልዉዉጥና ትግባራን ይመለከታል።
በፌዴራል ህግ መሰረት ተማሪ ስንኩልነቱ/ቷ ከተገለጸ፣ የተማሪው/ዋ ክፍል 504 እቅድ፣ የግል የትምህርት ፕሮግራም (IEP)፣ እና/ወይም በፌዴራል ህግ መሰረት የሚወጡ ሌሎች ፕሮግራሞች ይህንን መስፈርት ማሟላት አለባቸው።
በጣም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘና እንድሁም ከትምህርት ቤቱ ነርስ ወይንም ከትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ጋር ምክክር ከተደረገ ቦሃላ አንድ ሙያዊ የመማር ማስተማር የምስክር ወረቀት ያለው ሰው ለተወሰኑ ልጆች ወይንም ሁኔታዎች እንደ ነርስ ለማገልገል ይሰየማል። በነዝህ ሁኔታዎች ዉስጥ የጤና እንክብካቤ እቅድ (IHP) የዝህን ሰው መሰየም በህጉ መሰረት በእቅዱ ዉስጥ ያሳያል።

### አሳማኝ ልዩ ሁኔታ

ልዩ ሁኔታ የተፈለገው በትምህርት ቤት ውስጥ የተማሪዎች ላልተፈለገ የምግብ አሌርጂ የመጋለጥ ሁኔታን ለመቀነስ ነው። በፌዴራል ህግ መሰረት ተማሪ ስንኩልነቱ/ቷ ከተወሰነ፣ የተማሪ ክፍል 504 እቅድ፣ የግል የትምህርት ፕሮግራም (IEP)፣ እና/ወይም አግባብ ባለው የፌዴራል ህግ መሰረት የሚወጣ ሌላ እቅድ ይህንን መስፈርት ማሟላት አለበት።

### ድንገተኛ ህክምናን /መድሃንቶችን ማግኘት

የምግብ አሌርጂ ያለባቸውን ተማሪዎች ለማከም እንዲያመች የድንገተኛ ህክምና መድሃኒቶች ጥብቅ የሆነና ለትምህርት ቤት ሰራተኞች ግልጽ የሆነ ቦታ ተማርዎች ግን ልደርሱበት የማይችሉበት ቦታ መሆን አለበት። በሚቻልበት ጊዜ ሁሉና በጊዜ፣ በቦርድ ፖሊሲ JLCA፣ የተማሪ የጤና አገልግሎቶችና መስፈርቶች መሰረት፣ ተማሪ የምግብ አሌርጂ መድሃኒት ይዞ/ዛ የማይሄድ/የማትሄድ ከሆነ/ች፣ የተማሪው/ዋ ወላጅ/ህጋዊ አሳዳጊ አስፈላጊውን መድሃኒት ለትምህርት ቤቱ ማቅረብ አለባቸው።

### የሠራተኞች ሥልጠና

የትምህርት ቤት ኃላፊ ወይም አቻ የትምህርት ቤት አስተዳዳሪ፣ ከትምህርት ቤት ነርስ ጋር በመመካከር፣ ታዋቂ የምግብ አሌርጂ ወይንም ለህይወት አስጊ የሆነ ሥር የሰደደ ወይም ከባድ የጤና ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች በትምህርት ቤት የሚረዱ የሰራተኞችን ዝርዝር የሚያካትት የድንገተኛ የምግብ አሌርጂ ህክምና (እርዳታ ሰጪ) ሥልጠና መውሰድ የሚገባቸውን ሰዎች መወሰን አለባቸው። ቢያንስ፣ ሥልጠናው ለሰራተኞቹ የምግብ አሌርጂ መሰረታዊ መረዳትንና መንስዔውን የመቅረፍ አስፈላጊነት፣ እንደዚሁም ጉዳዩ ሲከሰት ምልክቶቹን የማወቅ ብቃት እንዲኖራቸውና እንዴት ተማሪው/ዋን መርዳት እንደሚችሉ ግንዛቤ መስጠት አለበት። በተጨማሪም ሥልጠናው በራስ የሚከተቡ (የሚወጉ) 'epi-nephrine' የሚባል መዲሃኒት (መርፌ) አሰጣጥ የሚመለከት መመሪያ ማካተት አለበት።

ሥራ ላይ የዋለው፤ 14፣ 2010
የተሻሻለው፤ ፌብሯሪ 8፤2016

**የሕግ ዋቢዎች፤** 20 U.S.C. 1400 ቀጣይ (የ2007 የአካለ ስንኩላን ተማሪዎች የትምህርት መሻሻል አዋጅ)
29 U.S.C. 701 ቀጣይ (የ1973 የማገገሚያ አዋጅ ክፍል 504)
42 U.S.C. 12101 ቀጣይ (በአሜሪካ የአካለ ስንኩላን ዜጎች አዋጅ) C.R.S. §12-38-132 (ለነርስነት ስራ ስያሜ)
C.R.S. 22-2-135 (የኮሎራዶ ትምህርት ቤት ልጆች የምግብ አሌርጂ ቁጥጥር አዋጅ)
C.R.S. 22-32-139 (ለተማሪዎች የምግብ አሌርጂ ቁጥጥር የሚያስፈልግ ፖሊሲ)
C.R.S. 25-1.5-109 (የኮሎራዶ የማኅበረሰብ ጤናና የአከባቢ ጥበቃ ክፍል የተማሪዎችን የምግብ አሌርጂ በተመለከተ አስፈላጊውን መረጃ ለማሰባሰብ የሚረዳ መደበኛ ፎርም(ቅጽ) ለትምህርት ድስትሪክቶች ያዘጋጃል፥ እንድዚሁም ይቆጣጠራል ፎርሙንም በቀላሉ እንዲገኙ ያደርጋል።
1 CCR 301-68 (የክፍለ ግዛት የትምህርት ቦርድ የኮሎራዶ ትምህርት ቤት ልጆች አስማና የምግብ አለርጂና ቁጥጥር አዋጅን ይቆጣጠራል)

**ተዛማጅ ዋቢ፤** JLCA፣ የተማሪ የጤና አገልግሎቶችና መስፈርቶች

**የግርጌ ማስታወሻ**

የግርጌ ማስታወሻ